፲፱፤ ያም ፡ ቀን ፡ እርሱም ፡ ከሳምንቱ ፡ ፊተኛው ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ተሰብስበው ፡ በነበሩበት ፡ አይሁድን ፡ ስለ ፡ ፈሩ ፡ ደጆቹ ፡ ተዘግተው ፡ ሳሉ ፡ ኢየሱስ ፡ መጣ ፤ በመካከላቸውም ፡ ቆሞ ፡— ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ይሁን ፡ አላቸው ። ፳፤ ይህንም ፡ ብሎ ፡ እጆቹንም ፡ ጎኑንም ፡ አሳያቸው ። ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ጌታን ፡ በዩ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አላቸው ። ኢየሱስም ፡ ዳግመኛ ፡— ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ይሁን ፤ አብ ፡ እንደ ፡ ላከኝ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ እልካችኋለሁ ፡ አላቸው ። ፳፪ ይህንም ፡ ብሎ ፡ እፍ ፡ አለባቸውና ፡— መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀበሉ ። ፳፫ ኃጢአታቸውን ፡ ይቅር ፡ ያላችኋቸው ፡ ሁሉ ፡ ይቀርላቸዋል ፤ የያዛችሁባቸው ፡ ተይዘባቸዋል ፡ አላቸው ።

፳፬፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከአሥራ ፡ ሁለቱ ፡ አንዱ ፡ ዳዲሞስ ፡ የሚሉት ፡ ቶማስ ፡ ኢየሱስ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ አልነበረም ። ፳፭ ሌሎቹም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡— ጌታን ፡ አይተነዋል ፡ አሉት ። እርሱ ፡ ግን ፡— የችንካሩን ፡ ምልክት ፡ በእጆቹ ፡ ካላየሁ ፡ ጣቴንም ፡ በችንካሩ ፡ ምልክት ፡ ካላገባሁ ፡ እጄንም ፡ በጎኑ ፡ ካላገባሁ ፡ አላምንም ፡ አላቸው ።

፳፮፤ ከስምንት ፡ ቀን ፡ በኋላም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ደግመው ፡ በውስጥ ፡ ነበሩ ፡ ቶማስም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ነበረ ። ደጆች ፡ ተዘግተው ፡ ሳሉ ፡ ኢየሱስ ፡ መጣ ፤ በመካከላቸውም ፡ ቆሞ ፡— ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ይሁን ፡ አላቸው ። ፳፯ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ቶማስን ፡— ጣትህን ፡ ወደዚህ ፡ አምጣና ፡ እጆቼን ፡ እይ ፤ እጅህንም ፡ አምጣና ፡ በጎኔ ፡ አግባው ፤ ያመንህ ፡ እንጂ ፡ ያላመንህ ፡ አትሁን ፡ አለው ። ቶማስም ፡ — ጌቻዬ ፡ አምላኬም ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ፳፰ ኢየሱስም ፡— ስለ ፡ አየኸኝ ፡ አምነሃል ፤ ሳያዩ ፡ የሚያምኑ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ አለው ።

፴፤ ኢየሱስም ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ያልተጻፈ ፡ ሌላ ፡ ብዙ ፡ ምልክት ፡ በደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ፊት ፡ ፴፩ አደረገ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ኢየሱስ ፡ እርሱ ፡ ክርስቶስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ታምኑ ፡ ዘንድ ፡ አምናችሁም ፡ በስሙ ፡ ሕይወት ፡ ይሆንላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ተጽፎአል ።

ምዕራፍ ፡ ፳፩ ።

፩፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስ ፡ በጥብርያዶስ ፡ ባሕር ፡ አጠገብ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተገ ፪፤ ለጥላቸው ፡ እንዲህ ፡ ተገለጠ ። ስምዖን ፡ ጴጥሮስና ፡ ዲዲሞስ ፡ የሚባለው ፡ ቶማስ ፡ ከገሊላ ፡ ቃና ፡ የሆነ ፡ ናትናኤልም ፡ የዘብዴዎስም ፡ ልጆች ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ሌሎች ፡ ሁለት ፡ ፫ በአንድነት ፡ ነበሩ ። ስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፡— ዓሣ ፡ ላጠምድ ፡ እሄዳለሁ ፡ አላቸው ። እነርሱም ፡— እኛም ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ እንመጣለን ፡ አሉት ። ወጥተውም ፡ ወደ ፡ ታንኳይቱ ፡ ገቡ ፡ በዚያችም ፡ ሌሊት ፡ ምንም ፡ አላጠመዱም ።

፬፤ በነጋም ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ ቆመ ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ግን ፡ ኢየሱስ ፡ መሆኑን ፭፤ አላወቁም ። ኢየሱስም ፡— ልጆች ፡ ሆይ ፡ አንዳች ፡ የሚበላ ፡ አላችሁን ? አላቸው ። ፮ የለንም ፡ ብለው ፡ መለሱለት ፡ እርሱም ፡ መረቡን ፡ በታንኳ ፡ ይቱ ፡ በስተቀኝ ፡ ጣሉት ፡ ታገኙማላችሁ ፡ አላቸው ፡ ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ ደክመን ፡ ምንም ፡ ያገኘነው ፡ የለም ፡ በትእዛዝህ ፡ ግን ፡ እንጥላለን ፤ ስለዚህ ፡ ጣሉት ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከዓሣው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ሊጎትቱት ፡ አቃታቸው ። ፯ ኢየሱስ ፡ ይወደው ፡ የነበረው ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ጴጥሮስን ፡ ጌታ ፡ እኮ ፡ ነው ፡ አለው ። ስለዚህ ፡ ስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፡ ጌታ ፡ መሆኑን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ዕራቍቱን ፡ ነበርና ፡ ልብሱን ፡ ታጥቆ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ራሱን ፡ ጣለ ። ፰ ሌሎቹ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ግን ፡ ከምድር ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ያህል ፡ እንጂ ፡ እጅግ ፡ አልራቁምና ፡ በጀልባ ፡ መጡ ።

፱፤ ወደ ፡ ምድርም ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ፍምና ፡ ዓሣ ፡ በላዩ ፡ ተቀምጦ ፡ እንጀራም ፡ አዩ ። ፲ ኢየሱስም ፡— አሁን ፡ ከጠመዳችሁት ፡ ዓሣ ፡ አምጡ ፡ አላቸው ። ስምዖን ፡ ጴጥሮስም ፡ ወደ ፡ ጀልባ ፲፩፤ ይቱ ፡ ገብቶ ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ሦስት ፡ ታላላቅ ፡ ዓሦች ፡ ሞልቶ ፡ የነበረውን ፡ መረብ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ጐተተ ፤ ይህንም ፡ ያህል ፡ ብዙ ፡ ሲሆን ፡ መረቡ ፡ አልተቀደደም ። ፲፪ ኢየሱስም ፡— ኑ ፤ ምሳ ፡ ብሉ ፡ አላቸው ። ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡— አንተ ፡ ማን ፡ ነህ ? ብሎ ፡ ሊመረምረው ፡ የደፈረ ፡ አልነበረም ፤ ጌታ ፡ መሆኑን ፡ አውቀው ፡ ነበርና ። ፲፫ ኢየሱስም ፡ መጣና ፡ እንጀራ ፡ አንሥቶ ፡ ሰጣቸው ፡ እንዲሁም ፡ ዓሣውን ። ፲፬ ኢየሱስ ፡ ከሙታን ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሲገለጥላቸው ፡ ይህ ፡ ሦስተኛው ፡ ጊዜ ፡ ነበረ ።

፲፭፤ ምሳ ፡ ከበሉ ፡ በኋላም ፡ ኢየሱስ ፡ ስምዖን ፡ ጴጥሮስን ፡— የዮና ፡ ልጅ ፡ ስምዖን ፡ ሆይ ፡ ከእነዚህ ፡ ይልቅ ፡ ትወደኛለህን ? አለው ። አዎን ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፤ እንደ ወድህ ፡ አንተ ፡ ታውቃለህ ፡ አለው ። ግልገሎቼን ፡ አሰማራ ፡ አለው ። ፲፮ ደግሞ ፡ ሁለተኛ ፡— የዮና ፡ ልጅ ፡ ስምዖን ፡ ሆይ ፡ ትወደኛለህን ? አለው ። አዎን ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፤ እንደ ወድህ ፡ አንተ ፡ ታውቃለህ ፡ አለው ። ጠቦቶቼን ፡ ጠብቅ ፡ አለው ። ፲፯ ሦስተኛ ፡ ጊዜ ፡— የዮና ፡ ልጅ ፡ ስምዖን ፡ ሆይ ፡ ትወደኛለህን ? አለው ። ጴጥሮስ ፡ አዘነና ፡— ጌታ ፡ ሆይ ፡ አንተ ፡ ሁሉን ፡ ታውቃለህ ፡ እንደ ወድህ ፡ አንተ ፡ ታውቃለህ ፡ አለው ። ኢየሱስም ፡— በጎቼን ፡ አሰማራ ፡ ይሆናል ? አለው ። ኢየሱስም ፡— እስክመጣ ፡ ድረስ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ብወድስ ፡ ምን ፡ አግዶህ ? አንተ ፡ ተከተለኝ ፡ አለው ። ፳፪ ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ አይሞትም ፡ የሚለው ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ወንድሞች ፡ ወጣ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ኢየሱስ ፡— እስክመጣ ፡ ድረስ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ብወድስ ፡ ምን ፡ አግዶህ ? አለው ፡ እንጂ ፡ አይሞትም ፡ አላለውም ።

፳፬፤ ስለ ፡ እነዚህም ፡ የመሰከረ ፡ ይህንንም ፡ ጽፎ ፡ ያለ ፡ ይህ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ነው ፡ ምስክሩም ፡ እውነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እናውቃለን ።

፳፭፤ ኢየሱስም ፡ ያደረገው ፡ ብዙ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ደግሞ ፡ አለ ፤ ሁሉ ፡ በእያንዳንዱ ፡ ቢጻፍ ፡ ለተጻፉት ፡ መጻሕፍት ፡ ዓለም ፡ ራሱ ፡ ባልበቃቸውም ፡ ይመስለኛል ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩፤ ቴዎፍሎስ ፡ ሆይ ፡ ኢየሱስ ፡ የመረጣቸውን ፡ ሐዋርያትን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከዘዘቸው ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ዐረገበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ያደርገውና ፡ ያስተምረው ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ጀመረው ፡ ፪፤ ሁሉ ፡ መጀመሪያውን ፡ ነገር ፡ ጻፍሁ ፤ ደግሞ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ እየታያቸው ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ነገር ፡ እየነገራቸው ፡ በብዙ ፡ ማስረጃ ፡ ከሕማማቱ ፡ በኋላ ፡ ሕያው ፡ ሆኖ ፡ ለእነርሱ ፡ ራሱን ፡ አሳያቸው ። ፫ ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ሳለ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ እንዳይወጡ ፡ አዘዛቸው ፡ ነገር ፡ ግን ፡— ከእኔ ፡ የሰማችሁትን ፡ ፬፤ አብ ፡ የሰጠውን ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ጠብቁ ፤ ዮሐንስ ፡ በውኃ ፡ አጥምቆ ፡ ነበርና ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ትጠመቃላችሁ ፡ አለ ።

፮፤ እነርሱም ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡— ጌታ ፡ ሆይ ፡ በዚህ ፡ ወራት ፡ ለእስራኤል ፡ መንግሥትን ፡ ትመልሳለህን ? ብለው ፡ ጠየቁት ። ፯ እርሱም ፡— አብ ፡ በገዛ ፡ ሥልጣኑ ፡ ያደረገውን ፡ ወራትንና ፡ ዘመናትን ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ ለእናንተ ፡ አልተሰጣችሁም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ በወረደ ፡ ጊዜ ፡ ኃይልን ፡ ትቀበላላችሁ ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ በይሁዳም ፡ ሁሉ ፡ በሰማርያም ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ዳርም ፡ ድረስ ፡ ምስክሮቼ ፡ ትሆናላችሁ ፡ አለ ። ፱ ይህንም ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ እነርሱ ፡ እያዩት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ፤ ደመናም ፡ ከዓይናቸው ፡ ሰውሬ ፡ ተቀበለችው ። ፲ እርሱም ፡ ሲሄድ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ትኵር ፡ ብለው ፡ ሲመለከቱ ፡ ሳሉ ፡ እነሆ ፡ ነጫጭ ፡ ልብስ ፡ የለበሱ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ በአጠገባቸው ፡ ቆሙ ፤ ፲፩፤ ደግሞም ፡— የገሊላ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ እየተመለከታችሁ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ቆማችኋል ? ይህ ፡ ከእናንተ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ የወጣው ፡ ኢየሱስ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሲሄድ ፡ እንዳያችሁት ፡ እንዲሁ ፡ ይመጣል ፡ አሉአቸው ።

፲፪፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ከሚባለው ፡ ተራራ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተመለሱ ፡ እርሱም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ የሰንበት ፡ መንገድ ፡ ያህል ፡ የራቀ ፡ ነው ። ፲፫ በገቡም ፡ ጊዜ ፡ ወደሚኖሩበት ፡ ሰገነት ፡ ወጡ ፡ ጴጥሮስና ፡ ዮሐንስም ፡ ያዕቆብም ፡ እንድርያስም ፡ ፊልጶስም ፡ ቶማስም ፡ በርተሎሜዎስም ፡ ማቴዎስም ፡ የአልፍዮስ ፡ ልጅ ፡ ያዕቆብም ፡ ቀናተኛ ፡ የሚባለው ፡ ስምዖንም ፡ የያዕቆብ ፡ ልጅ ፡ ይሁዳም ። ፲፬ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ከሴቶችና ፡ ከኢየሱስ ፡ እናት ፡ ከማርያም ፡ ከወንድሞቹም ፡ ጋር ፡ በአንድ ፡ ልብ ፡ ሆነው ፡ ለጸሎት ፡ ይተጉ ፡ ነበር ።

፲፭፤ በዚህም ፡ ወራት ፡ ጴጥሮስ ፡ መቶ ፡ ሀያ ፡ በሚያህል ፡ በሰዎች ፡ ማኅበር ፡ አብረው ፡ በነበሩ ፡ ፲፮፤ በወንድሞቹ ፡ መካከል ፡ ተነሥቶ ፡ አለ ፡— ወንድሞች ፡ ሆይ ፡ ኢየሱስን ፡ ለያዙት ፡ መሪ ፡ ስለ ፡ ሆናቸው ፡ ስለ ፡ ይሁዳ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አስቀድሞ ፡ በዳዊት ፡ አፍ ፡ የተናገረው ፡ የመጽሐፍ ፡ ቃል ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ይገባ ፡ ነበር ፤ ፲፯ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ተቈጥሮ ፡ ነበርና ፡ ለዚህም ፡ አገልግሎት ፡ ታድሱ ፡ ነበርና ። ይህም ፡ ሰው ፡ በዓመፅ ፡ ዋጋ ፡

ያዩ፡ ፩ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ ፪ ፡ ፫ ፡ ፫ ፡ ፬ ፡ ፬ ፡ ፭ ፡ ፭ ፡ ፮ ፡ ፮ ፡ ፯ ፡ ፯ ፡ ፰ ፡ ፰ ፡ ፱ ፡ ፱ ፡ ፲ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ፡ ፲፭ ፡ ፲፮ ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ፡ ፳ ፡ ፳፩ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ፡ ፳፫ ፡ ፳፬ ፡ ፳፬ ፡ ፳፭ ፡ ፳፭ ፡ ፳፮ ፡ ፳፮ ፡ ፳፯ ፡ ፳፯ ፡ ፳፰ ፡ ፳፰ ፡ ፳፱ ፡ ፳፱ ፡ ፴ ፡ ፴ ፡ ፴፩ ፡ ፴፩ ፡ ፴፪ ፡ ፴፪ ፡ ፴፫ ፡ ፴፫ ፡ ፴፬ ፡ ፴፬ ፡ ፴፭ ፡ ፴፭ ፡ ፴፮ ፡ ፴፮ ፡ ፴፯ ፡ ፴፯ ፡ ፴፰ ፡ ፴፰ ፡ ፴፱ ፡ ፴፱ ፡ ፵ ፡ ፵ ፡ ፵፩ ፡ ፵፩ ፡ ፵፪ ፡ ፵፪ ፡ ፵፫ ፡ ፵፫ ፡ ፵፬ ፡ ፵፬ ፡ ፵፭ ፡ ፵፭ ፡ ፵፮ ፡ ፵፮ ፡ ፵፯ ፡ ፵፯ ፡ ፵፰ ፡ ፵፰ ፡ ፵፱ ፡ ፵፱ ፡ ፶ ፡ ፶ ፡ ፶፩ ፡ ፶፩ ፡ ፶፪ ፡ ፶፪ ፡ ፶፫ ፡ ፶፫ ፡ ፶፬ ፡ ፶፬ ፡ ፶፭ ፡ ፶፭ ፡ ፶፮ ፡ ፶፮ ፡ ፶፯ ፡ ፶፯ ፡ ፶፰ ፡ ፶፰ ፡ ፶፱ ፡ ፶፱ ፡ ፷ ፡ ፷ ፡ ፷፩ ፡ ፷፩ ፡ ፷፪ ፡ ፷፪ ፡ ፷፫ ፡ ፷፫ ፡ ፷፬ ፡ ፷፬ ፡ ፷፭ ፡ ፷፭ ፡ ፷፮ ፡ ፷፮ ፡ ፷፯ ፡ ፷፯ ፡ ፷፰ ፡ ፷፰ ፡ ፷፱ ፡ ፷፱ ፡ ፸ ፡ ፸ ፡ ፸፩ ፡ ፸፩ ፡ ፸፪ ፡ ፸፪ ፡ ፸፫ ፡ ፸፫ ፡ ፸፬ ፡ ፸፬ ፡ ፸፭ ፡ ፸፭ ፡ ፸፮ ፡ ፸፮ ፡ ፸፯ ፡ ፸፯ ፡ ፸፰ ፡ ፸፰ ፡ ፸፱ ፡ ፸፱ ፡ ፹ ፡ ፹ ፡ ፹፩ ፡ ፹፩ ፡ ፹፪ ፡ ፹፪ ፡ ፹፫ ፡ ፹፫ ፡ ፹፬ ፡ ፹፬ ፡ ፹፭ ፡ ፹፭ ፡ ፹፮ ፡ ፹፮ ፡ ፹፯ ፡ ፹፯ ፡ ፹፰ ፡ ፹፰ ፡ ፹፱ ፡ ፹፱ ፡ ፺ ፡ ፺ ፡ ፺፩ ፡ ፺፩ ፡ ፺፪ ፡ ፺፪ ፡ ፺፫ ፡ ፺፫ ፡ ፺፬ ፡ ፺፬ ፡ ፺፭ ፡ ፺፭ ፡ ፺፮ ፡ ፺፮ ፡ ፺፯ ፡ ፺፯ ፡ ፺፰ ፡ ፺፰ ፡ ፺፱ ፡ ፺፱ ፡ ፻ ፡ ፻ ፡ ፻፩ ፡ ፻፩ ፡ ፻፪ ፡ ፻፪ ፡ ፻፫ ፡ ፻፫ ፡ ፻፬ ፡ ፻፬ ፡ ፻፭ ፡ ፻፭ ፡ ፻፮ ፡ ፻፮ ፡ ፻፯ ፡ ፻፯ ፡ ፻፰ ፡ ፻፰ ፡ ፻፱ ፡ ፻፱ ፡ ፻፲ ፡ ፻፲ ፡ ፻፲፩ ፡ ፻፲፩ ፡ ፻፲፪ ፡ ፻፲፪ ፡ ፻፲፫ ፡ ፻፲፫ ፡ ፻፲፬ ፡ ፻፲፬ ፡ ፻፲፭ ፡ ፻፲፭ ፡ ፻፲፮ ፡ ፻፲፮ ፡ ፻፲፯ ፡ ፻፲፯ ፡ ፻፲፰ ፡ ፻፲፰ ፡ ፻፲፱ ፡ ፻፲፱ ፡ ፻፳ ፡ ፻፳ ፡ ፻፳፩ ፡ ፻፳፩ ፡ ፻፳፪ ፡ ፻፳፪ ፡ ፻፳፫ ፡ ፻፳፫ ፡ ፻፳፬ ፡ ፻፳፬ ፡ ፻፳፭ ፡ ፻፳፭ ፡ ፻፳፮ ፡ ፻፳፮ ፡ ፻፳፯ ፡ ፻፳፯ ፡ ፻፳፰ ፡ ፻፳፰ ፡ ፻፳፱ ፡ ፻፳፱ ፡ ፻፴ ፡ ፻፴ ፡ ፻፴፩ ፡ ፻፴፩ ፡ ፻፴፪ ፡ ፻፴፪ ፡ ፻፴፫ ፡ ፻፴፫ ፡ ፻፴፬ ፡ ፻፴፬ ፡ ፻፴፭ ፡ ፻፴፭ ፡ ፻፴፮ ፡ ፻፴፮ ፡ ፻፴፯ ፡ ፻፴፯ ፡ ፻፴፰ ፡ ፻፴፰ ፡ ፻፴፱ ፡ ፻፴፱ ፡ ፻፵ ፡ ፻፵ ፡ ፻፵፩ ፡ ፻፵፩ ፡ ፻፵፪ ፡ ፻፵፪ ፡ ፻፵፫ ፡ ፻፵፫ ፡ ፻፵፬ ፡ ፻፵፬ ፡ ፻፵፭ ፡ ፻፵፭ ፡ ፻፵፮ ፡ ፻፵፮ ፡ ፻፵፯ ፡ ፻፵፯ ፡ ፻፵፰ ፡ ፻፵፰ ፡ ፻፵፱ ፡ ፻፵፱ ፡ ፻፶ ፡ ፻፶ ፡ ፻፶፩ ፡ ፻፶፩ ፡ ፻፶፪ ፡ ፻፶፪ ፡ ፻፶፫ ፡ ፻፶፫ ፡ ፻፶፬ ፡ ፻፶፬ ፡ ፻፶፭ ፡ ፻፶፭ ፡ ፻፶፮ ፡ ፻፶፮ ፡ ፻፶፯ ፡ ፻፶፯ ፡ ፻፶፰ ፡ ፻፶፰ ፡ ፻፶፱ ፡ ፻፶፱ ፡ ፻፷ ፡ ፻፷ ፡ ፻፷፩ ፡ ፻፷፩ ፡ ፻፷፪ ፡ ፻፷፪ ፡ ፻፷፫ ፡ ፻፷፫ ፡ ፻፷፬ ፡ ፻፷፬ ፡ ፻፷፭ ፡ ፻፷፭ ፡ ፻፷፮ ፡ ፻፷፮ ፡ ፻፷፯ ፡ ፻፷፯ ፡ ፻፷፰ ፡ ፻፷፰ ፡ ፻፷፱ ፡ ፻፷፱ ፡ ፻፸ ፡ ፻፸ ፡ ፻፸፩ ፡ ፻፸፩ ፡ ፻፸፪ ፡ ፻፸፪ ፡ ፻፸፫ ፡ ፻፸፫ ፡ ፻፸፬ ፡ ፻፸፬ ፡ ፻፸፭ ፡ ፻፸፭ ፡ ፻፸፮ ፡ ፻፸፮ ፡ ፻፸፯ ፡ ፻፸፯ ፡ ፻፸፰ ፡ ፻፸፰ ፡ ፻፸፱ ፡ ፻፸፱ ፡ ፻፹ ፡ ፻፹ ፡ ፻፹፩ ፡ ፻፹፩ ፡ ፻፹፪ ፡ ፻፹፪ ፡ ፻፹፫ ፡ ፻፹፫ ፡ ፻፹፬ ፡ ፻፹፬ ፡ ፻፹፭ ፡ ፻፹፭ ፡ ፻፹፮ ፡ ፻፹፮ ፡ ፻፹፯ ፡ ፻፹፯ ፡ ፻፹፰ ፡ ፻፹፰ ፡ ፻፹፱ ፡ ፻፹፱ ፡ ፻፺ ፡ ፻፺ ፡ ፻፺፩ ፡ ፻፺፩ ፡ ፻፺፪ ፡ ፻፺፪ ፡ ፻፺፫ ፡ ፻፺፫ ፡ ፻፺፬ ፡ ፻፺፬ ፡ ፻፺፭ ፡ ፻፺፭ ፡ ፻፺፮ ፡ ፻፺፮ ፡ ፻፺፯ ፡ ፻፺፯ ፡ ፻፺፰ ፡ ፻፺፰ ፡ ፻፺፱ ፡ ፻፺፱ ፡ ፪፻ ፡ ፪፻ ፡ ፪፻፩ ፡ ፪፻፩ ፡ ፪፻፪ ፡ ፪፻፪ ፡ ፪፻፫ ፡ ፪፻፫ ፡ ፪፻፬ ፡ ፪፻፬ ፡ ፪፻፭ ፡ ፪፻፭ ፡ ፪፻፮ ፡ ፪፻፮ ፡ ፪፻፯ ፡ ፪፻፯ ፡ ፪፻፰ ፡ ፪፻፰

ያዩ፡ ፩ «ሉሊቱን ፡ ሁሉ ፡ ደክምን ፡ ምንም ፡ ያገኘነው ፡ የለም ፡ በትእዛዝህ ፡ ግን ፡ እንጥላለን» ፡ የሚሉ ፡ ንግግር ፡ በግሪኩ ፡ እይነኝም ፡ ይህ ፡ የተወሰደው ፡ ከሉቃ ፡ ፭ ፡ ፭ ፡ ነው ።

• በግዕዝ ፡ « በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ታመጠምቃላችሁ » ይላል ።

መሬት፡ገዛ፡በግንባሩም፡ተደፍቶ፡ከመካከሉ፡
፲፱፤ ተሰነጠቀ ፡ አንጀቱም፡ሁሉ፡ተዘረገፈ ፤ በኢ
የሩሳሌምም፡ለሚኖሩ፡ሁሉ፡ታወቀ ፤ ስለዚ
ህም ፡ ያ ፡ መሬት ፡ በቋንቋቸው ፡ አኬልዳማ ፡
ተብሎ ፡ ተጠራ ፥ እርሱም ፡ የደም ፡ መሬት ፡
፳፤ ማለት፡ነው ። በመዝሙር፡መጽሐፍ ፡— መኖ
ሪያው ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ትሁን ፡ የሚኖርበትም ፡
አይኑር ፤ ደግሞም ፡— ሹመቱን ፡ ሌላ ፡ ይውሰ
፳፩፡፳፪፤ ዳት ፡ ተብሎ ፡ ተጽፎአልና ። ስለዚህ ፡ ከዮሐ
ንስ ፡ ጥምቀት ፡ ጀምሮ ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ እስከረ
ገበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፥ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ በእኛ ፡ መካ
ከል ፡ በገባበትና ፡ በወጣበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡
ከእኛ ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ ከነበሩት ፡ ሰዎች ፥ ከእ
ነዚህ ፡ አንዱ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ የትንሣኤው ፡ ምስ
፳፫፤ ክር ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ። ኢዮስጦስም ፡
የሚሉትን ፡ በርስያን ፡ የተባለውን ፡ ዮሴፍንና ፡
፳፬፡፳፭፤ ማትያስን ፡ ሁለቱን ፡ አቆሙ ። ሲጸልዩም ፡—
የሁሉን ፡ ልብ ፡ የምታውቅ ፡ አንተ ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፥
ይሁዳ ፡ ወደ ፡ ገዛ ፡ ራሱ ፡ ስፍራ ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡
በተዋት ፡ በዚህች ፡ አገልግሎትና ፡ ሐዋርያነት ፡
ስፍራን ፡ እንዲቀበል ፡ የመረጥኸውን ፡ ከእነ
፳፮፤ ዚህ ፡ ከሁለቱ ፡ አንዱን ፡ ሹመው ፡ አሉ ። ዕጣም ፡
ተጣጣሉላቸው ፥ ዕጣውም ፡ ለማትያስ ፡ ወደ
ቀና ፡ ከአሥራ ፡ አንዱ ፡ ሐዋርያት ፡ ጋር ፡ ተቈ
ጠረ ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩፤ በዓለ ፡ ኀምሳም ፡ የተባለው ፡ ቀን ፡ በደረሰ ፡
ጊዜ ፥ ሁሉም ፡ በአንድ ፡ ልብ ፡ ሆነው ፡ አብረው ፡
፪፤ ሳሉ ፥ ድንገት ፡ እንደሚነጥቅ ፡ ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡
ከሰማይ ፡ ድምፅ ፡ መጣ ፥ ተቀምጠው ፡ የነበሩ
፫፤ በትንም ፡ ቤት ፡ ሁሉ ፡ ሞላው ። እንደ ፡ እሳ
ትም ፡ የተከፋፈሉ ፡ ልሳኖች ፡ ታዩአቸው ፤ በያ
፬፤ ንዳንዳቸውም ፡ ላይ ፡ ተቀመጡባቸው ። በሁ
ሉም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሞላባቸው ፥ መንፈ
ስም ፡ ይናገሩ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሰጣቸው ፡ በሌላ ፡
ልሳኖች ፡ ይናገሩ ፡ ጀመር ።
፭፤ ከሰማይም ፡ በታች ፡ ካሉ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ በጸ
ሎት ፡ የተጉ ፡ አይሁድ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ይኖሩ ፡
፮፤ ነበር ፤ ይህም ፡ ድምፅ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝብ ፡
ሁሉ ፡ ተሰበሰቡ ፥ እያንዳንዱም ፡ በገዛ ፡ ቋን
ቋው ፡ ሲናገሩ ፡ ይሰማ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ የሚሉትን ፡
፯፤ አጡ ። ተገርመውም ፡ ተደንቀውም ፡ እንዲህ ፡
አሉ ፡— እነሆ ፥ እነዚህ ፡ የሚናገሩት ፡ ሁሉ ፡
፰፤ የገሊላ ፡ ሰዎች ፡ አይደሉምን ? እኛም ፡ እያን
ዳንዳችን ፡ የተወለድንበትን ፡ የገዛ ፡ ቋንቋችንን ፡
፱፤ እንዴት ፡ እንሰማለን ? የጳርቴና ፡ የሜድ ፡ የኢ
ላሜጤም ፡ ሰዎች ፥ በሁለት ፡ ወንዝም ፡ መካ
ከል ፡ በይሁዳም ፡ በቀጰዶቅያም ፡ በጳንጦስም ፡
፲፤ በእስያም ፥ በፍርግያም ፡ በጵንፍልያም ፡ በግብ
ፅም ፡ በቀሬናም ፡ በኩል ፡ ባሉት ፡ በሊቢያ ፡ ወረ
ዳዎች ፡ የምንኖር ፥ በሮሜም ፡ የምንቀመጥ ፥
አይሁድም ፡ ወደ ፡ ይሁዲነትም ፡ የገባን ፥ የቀር ፲፩፤
ጤስና ፡ የአረብ ፡ ሰዎች ፥ የእግዚአብሔርን ፡
ታላቅ ፡ ሥራ ፡ በልሳኖቻችን ፡ ሲናገሩ ፡ እንሰማ
ቸዋለን ። ሁሉም ፡ ተገረሙና ፡ አመንትተው ፡ ፲፪፤
እርስ ፡ በርሳቸው ፡— እንጃ ፡ ይህ ፡ ምን ፡ ይሆን ?
አሉ ። ሌሎች ፡ ግን ፡ እያፌዙባቸው ፡— ጕሽ ፡ ፲፫፤
የወይን ፡ ጠጅ ፡ ጠግበዋል ፡ አሉ ።
ነገር ፡ ግን ፡ ጴጥሮስ ፡ ከአሥራ ፡ አንዱ ፡ ጋር ፡ ፲፬፤
ቆመ ፥ ድምፁንም ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ እንዲህ ፡
ሲል ፡ ተናገራቸው ፡— አይሁድ ፡ በኢየሩሳሌ
ምም ፡ የምትኖሩ ፡ ሁላችሁ ፥ ይህ ፡ በእናንተ ፡
ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ይሁን ፥ ቃሎቼንም ፡ አድ
ምጡ ። ለእናንተ ፡ እንደ ፡ መሰላችሁ ፡ እነዚህ ፡ ፲፭፤
የሰከሩ ፡ አይደሉም ፥ ከቀኑ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰዓት ፡
ነውና ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ በነቢዩ ፡ በኢዩኤል ፡ ፲፮፤
የተባለው ፡ ነው ፡—
እግዚአብሔር ፡ ይላል ፡— በመጨረሻው ፡ ፲፯፤
ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይሆናል ፤ ሥጋ ፡ በለበሰ ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ ከመንፈሴ ፡ አፈስሳለሁ ፤ ወን
ዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችሁም ፡ ትንቢት ፡
ይናገራሉ ፥ ጎበዞቻችሁም ፡ ራእይ ፡ ያያሉ ፥
ሽማግሌዎቻችሁም ፡ ሕልም ፡ ያልማሉ ፤
ደግሞም ፡ በዚያች ፡ ወራት ፡ በወንዶችና ፡ ፲፰፤
በሴቶች ፡ ባሪያዎቼ ፡ ላይ ፡ ከመንፈሴ ፡ አፈ
ስሳለሁ ፡ ትንቢትም ፡ ይናገራሉ ። ድንቆ ፲፱፤
ችን ፡ በላይ ፡ በሰማይ ፥ ምልክቶችንም ፡
በታች ፡ በምድር ፡ እሰጣለሁ ፤ ደምም ፡ እሳ
ትም ፡ የጢስ ፡ ጭጋግም ፡ ይሆናል ፤ ታላቅ ፡ ፳፤
የሆነ ፡ የተሰማም ፡ የጌታ ፡ ቀን ፡ ሳይመጣ ፡
ፀሐይ ፡ ወደ ፡ ጨለማ ፡ ጨረቃም ፡ ወደ ፡
ደም ፡ ይለወጣሉ ። የጌታን ፡ ስም ፡ የሚ ፳፩፤
ጠራም ፡ ሁሉ ፡ ይድናል ።
የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ቃል ፡ ፳፪፤
ስሙ ፤ ራሳችሁ ፡ እንደምታውቁ ፥ የናዝሬቱ ፡
ኢየሱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመካከላችሁ ፡ በእ
ርሱ ፡ በኩል ፡ ባደረገው ፡ ተአምራትና ፡ በድን
ቆች ፡ በምልክቶችም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡
ለእናንተ ፡ የተገለጠ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ እርሱንም ፡ ፳፫፤
በእግዚአብሔር ፡ በተወሰነው ፡ አሳቡና ፡ በቀደ
መው ፡ እውቀቱ ፡ ተሰጥቶ ፡ በዓመፀኞች ፡ እጅ ፡
ሰቅላችሁ ፡ ገደላችሁት ። እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ፳፬፤
የሞትን ፡ ጣር ፡ አጥፍቶ ፡ አስነሣው ፥ ሞት ፡
ይይዘው ፡ ዘንድ ፡ አልቻለምና ። ዳዊት ፡ ስለ ፡ ፳፭፤
እርሱ ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፡—
ጌታን ፡ ሁልጊዜ ፡ በፊቴ ፡ አየሁት ፥ እንዳ
ልታወክ ፡ በቀኜ ፡ ነውና ። ስለዚህ ፡ ልቤን ፡ ፳፮፤
ደስ ፡ አለው ፥ ልሳኔም ፡ ሐሤት ፡ አደረገ ፥
ደግሞም ፡ ሥጋዬ ፡ በተስፋ ፡ ያድራል ፤
ነፍሴን ፡ በሲኦል ፡ አትተዋትምና ፥ ቅዱስ ፳፯፤
ህንም ፡ መበስበስን ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ አትሰ

፩። ፳ ፤ መዝ. ፷፰ ፥ ፳፭ ፤ ፻፰ ፥ ፰ ። ፳፩ ፤ ዮሐ. ፲፭ ፥ ፳፯ ። ፳፬ ፤ ፩ ዜና ፳፰ ፥ ፱ ። ፳፮ ፤ ምሳ. ፲፮ ፥ ፴፫ ።
፪። ፩ ፤ ዘሌዋ. ፳፫ ፥ ፲፭ ፡ ፲፮ ። ፫ ፤ ማቴ. ፫ ፥ ፲፩ ። ፲፯—፳፩ ፤ ኢዩ. ፪ ፥ ፳፰—፴፪ ። ፳፪ ፤ ዮሐ. ፫ ፥ ፪ ። ፳፫ ፤ ሉቃ. ፳፪ ፥ ፳፪ ። ፳፭—፳፰ ፤ መዝ. ፲፮ ፥ ፰—፲፩ ።

፳፰፤ ጠውም ። የሕይወትን ፡ መንገድ ፡ አስታ
ወቅኸኝ ፤ ከፊትህ ፡ ጋር ፡ ደስታን ፡ ትሞ
ላብኛለህ ።
፳፱፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ አባቶች ፡ አለቃ ፡
ስለ ፡ ዳዊት ፡ እንደ ፡ ሞተም ፡ እንደ ፡ ተቀበረም ፡
ለእናንተ ፡ በግልጥ ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ ፍቀዱልኝ ፤
መቃብሩም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።
፴፤ ነቢይ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፥ ከወገቡም ፡ ፍሬ ፡ በዙፋኑ ፡
ያስቀምጥ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሐላ ፡
፴፩፤ እንደ ፡ ማለለት ፡ ስለ ፡ አወቀ ፥ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡
ትንሣኤ ፡ አስቀድሞ ፡ አይቶ ፥ ነፍሱ ፡ በሲኦል ፡
እንዳልቀረች ፡ ሥጋውም ፡ መበስበስን ፡ እንዳ
፴፪፤ ላየ ፡ ተናገረ ። ይህን ፡ ኢየሱስን ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ አስነሣው ፡ ለዚህም ፡ ነገር ፡ እኛ ፡ ሁላ
፴፫፤ ችን ፡ ምስክሮች ፡ ነን ፤ ስለዚህ ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ቀኝ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሎና ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱ
ስን ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ከአብ ፡ ተቀብሎ ፡ ይህን ፡
እናንተ ፡ አሁን ፡ የምታዩትንና ፡ የምትሰሙትን ፡
፴፬፡፴፭፤ አፈሰሰው ። ዳዊት ፡ ወደ ፡ ሰማያት ፡ አልወጣ
ምና ፥ ነገር ፡ ግን ፡ እርሱ ፡—
ጌታ ፡ ጌታዬን ፡— ጠላቶችህን ፡ የእግርህ ፡
መረገጫ ፡ እስከደርግልህ ፡ ድረስ ፡ በቀኜ ፡
ተቀመጥ ፡ አለው ፡
፴፮፤ አለ ። እንግዲህ ፡ ይህን ፡ እናንተ ፡ የሰቀላችሁ
ትን ፡ ኢየሱስን ፡ እግዚአብሔር ፡ ጌታም ፡ ክር
ስቶስም ፡ እንዳደረገው ፡ የእስራኤል ፡ ወገን ፡
ሁሉ ፡ በእርግጥ ፡ ይወቅ ።
፴፯፤ ይህንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ልባቸው ፡ ተነካ ፥
ጴጥሮስንና ፡ ሌሎችንም ፡ ሐዋርያት ፡— ወንድ
ሞች ፡ ሆይ ፥ ምን ፡ እናድርግ ? አሉአቸው ።
፴፰፤ ጴጥሮስም ፡— ንስሐ ፡ ግቡ ፥ ኃጢአታችሁም ፡
ይሰረይ ፡ ዘንድ ፡ እያንዳንዳችሁ ፡ በኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ተጠመቁ ፤ የመንፈስ ፡ ቅዱስ
፴፱፤ ንም ፡ ስጦታ ፡ ትቀበላላችሁ ። የተስፋው ፡ ቃል ፡
ለእናንተና ፡ ለልጆቻችሁ ፡ ጌታ ፡ አምላካችንም ፡
ወደ ፡ እርሱ ፡ ለሚጠራቸው ፡ በሩቅ ፡ ላሉ ፡ ሁሉ ፡
፵፤ ነውና ፡ አላቸው ። በብዙ ፡ ሌላ ፡ ቃልም ፡ መሰ
ከረና ፡— ከዚህ ፡ ጠማማ ፡ ትውልድ ፡ ዳኑ ፡ ብሎ ፡
፵፩፤ መከራቸው ። ቃሉንም ፡ የተቀበሉ ፡ ተጠመቁ ፥
በዚያም ፡ ቀን ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡ የሚያህል ፡ ነፍስ ፡
፵፪፤ ተጨመሩ ፤ በሐዋርያትም ፡ ትምህርትና ፡ በኅ
ብረት ፡ እንጀራውንም ፡ በመቍረስ ፡ በየጸሎ
ቱም ፡ ይተጉ ፡ ነበር ።
፵፫፤ ነገር ፡ ግን ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ፍርሃት ፡ ሆነ ፤
በሐዋርያትም ፡ እጅ ፡ ብዙ ፡ ድንቅና ፡ ምልክት ፡
፵፬፤ ተደረገ ። ያመኑትም ፡ ሁሉ ፡ አብረው ፡ ነበሩ ፤
፵፭፤ ያላቸውንም ፡ ሁሉ ፡ አንድነት ፡ አደረጉ ። መሬ
ታቸውንና ፡ ጥሪታቸውንም ፡ እየሸጡ ፥ ማን
ኛውም ፡ እንደሚፈልግ ፡ ለሁሉ ፡ ያካፍሉት ፡
፵፮፤ ነበር ። በየቀኑም ፡ በአንድ ፡ ልብ ፡ ሆነው ፡ በመ
ቅደስ ፡ እየተጉ ፡ በቤታቸውም ፡ እንጀራ ፡ እየ
ቈረሱ ፥ በደስታና ፡ በጥሩ ፡ ልብ ፡ ምግባቸውን ፡
ይመገቡ ፡ ነበር ፤ እግዚአብሔርንም ፡ እያመሰ ፵፯፤
ገኑ ፡ በሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ ሞገስ ፡ ነበራቸው ።
ጌታም ፡ የሚድኑትን ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ በእነርሱ ፡
ላይ ፡ ይጨምር ፡ ነበር ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ጴጥሮስና ፡ ዮሐንስም ፡ በጸሎት ፡ ጊዜ ፡ በዘ ፩፤
ጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ይወጡ ፡ ነበር ።
ወደ ፡ መቅደስም ፡ ከሚገቡት ፡ ምጽዋት ፡ ይለ ፪፤
ምን ፡ ዘንድ ፥ ሰዎች ፡ ተሸከመው ፡ መልካም ፡
በሚሉአት ፡ በመቅደስ ፡ ደጅ ፡ በየቀኑ ፡ ያስቀም
ጡት ፡ የነበሩ ፡ ከእናቱ ፡ ማኅፀን ፡ ጀምሮ ፡ አንካሳ ፡
የሆነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ። እርሱም ፡ ጴጥሮስና ፡ ፫፤
ዮሐንስ ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ሊገቡ ፡ እንዳላቸው ፡
ባየ ፡ ጊዜ ፥ ምጽዋትን ፡ ለመናቸው ። ጴጥ ፬፤
ሮስም ፡ ከዮሐንስ ፡ ጋር ፡ ትኵር ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡
እርሱ ፡ ተመልክቶ ፡— ወደ ፡ እኛ ፡ ተመልከት ፡
አለው ። እርሱም ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ከእነርሱ ፡ ፭፤
እንዲቀበል ፡ ሲጠብቅ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ተመለ
ከተ ። ጴጥሮስ ፡ ግን ፡— ብርና ፡ ወርቅ ፡ የለኝም ፤ ፮፤
ይህን ፡ ያለኝን ፡ ግን ፡ እሰጥሃለሁ ፤ በናዝሬቱ ፡
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ተነሥና ፡ ተመ
ላለስ ፡ አለው ። በቀኝ ፡ እጁም ፡ ይዞ ፡ አስነ ፯፤
ሣው ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ እግሩና ፡ ቍርጭም
ጭምቱ ፡ ጸና ፥ ወደ ፡ ላይ ፡ ዘሎም ፡ ቆመ ፥ ፰፤
ይመላለስም ፡ ጀመር ፤ እየተመላለሰም ፡ እየዘለ
ለም ፡ እግዚአብሔርንም ፡ እያመሰገነ ፡ ከእነርሱ ፡
ጋር ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ገባ ። ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ፱፤
እግዚአብሔርን ፡ እያመሰገነ ፡ ሲመላለስ ፡ አዩት ፤
መልካምም ፡ በሚሉአት ፡ በመቅደስ ፡ ደጅ ፡ ስለ ፡ ፲፤
ምጽዋት ፡ ተቀምጦ ፡ የነበረው ፡ እርሱ ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ አወቁት ፤ በእርሱም ፡ ከሆነው ፡ የተነሣ ፡
መደነቅና ፡ መገረም ፡ ሞላባቸው ።
እርሱም ፡ ጴጥሮስንና ፡ ዮሐንስን ፡ ይዞ ፡ ሳለ ፥ ፲፩፤
ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ እየተደነቁ ፡ የሰሎሞን ፡ ደጅ ፡
መመላለሻ ፡ በሚባለው ፡ አብረው ፡ ወደ ፡ እነ
ርሱ ፡ ሮጡ ። ጴጥሮስም ፡ አይቶ ፡ ለሕዝቡ ፡ ፲፪፤
እንዲህ ፡ ሲል ፡ መለሰ ፡— የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡
ሆይ ፥ በዚህ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትደነቃላችሁ ? ወይስ ፡
በገዛ ፡ ኃይላችን ፡ ወይስ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመ
ፍራታችን ፡ ይህ ፡ ይመላለስ ፡ ዘንድ ፡ እንዳደረ
ግነው ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትኵር ፡ ብላችሁ ፡ ታዩና
ላችሁ ? የአብርሃምና ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብም ፡ ፲፫፤
አምላክ ፥ የአባቶቻችን ፡ አምላክ ፥ እናንተ ፡ አሳ
ልፋችሁ ፡ የሰጣችሁትንና ፡ ሊፈታው ፡ ቈርጦ ፡
ሳለ ፡ በጲላጦስ ፡ ፊት ፡ የካዳችሁትን ፡ ብላቴና
ውን ፡ ኢየሱስን ፡ አከበረው ። እናንተ ፡ ግን ፡ ፲፬፤
ቅዱሱን ፡ ጻድቁንም ፡ ክዳችሁ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩን ፡

፪። ፳፱ ፤ ፩ ነገሥ. ፪ ፥ ፲ ፤ ነህ. ፫ ፥ ፲፮ ። ፴ ፤ መዝ. ፻፴፪ ፥ ፲፩ ። ፴፬ ፡ ፴፭ ፤ መዝ. ፻፲ ፥ ፩ ። ፴፰ ፤ ማቴ. ፳፰ ፥ ፲፱ ፤
ሉቃ. ፳፬ ፥ ፵፯ ፤ ዮሐ. ፯ ፥ ፴፱ ። ፵ ፤ ማቴ. ፲፯ ፥ ፲፯ ። ፵፪ ፤ ሉቃ. ፳፬ ፥ ፲፱ ። ፵፬ ፤ ም. ፬ ፥ ፴፪ ። ፵፯ ፤ ቆሎ. ፵፪ ።
፫። ፰ ፤ ኢሳ. ፴፭ ፥ ፮ ። ፲፩ ፤ ዮሐ. ፲ ፥ ፳፫ ። ፲፫—፲፭ ፤ ም. ፪ ፥ ፳፪—፳፬ ። ፲፫ ፤ ዘፀአ. ፫ ፥ ፮ ፤ ሉቃ. ፳፫ ፥ ፲፱ ፡ ፲፯ ።
፲፬ ፤ ሉቃ. ፳፫ ፥ ፲፰ ።

፲፭ ሰው ፡ ይሰጣችሁ ፡ ዘንድ ፡ ለመናችሁ ÷ የሕይ
ወትንም ፡ ራስ ፡ ገደላችሁት ፤ እርሱን ፡ ግን ፡
እግዚአብሔር ፡ ከሙታን ፡ አስነሣው ÷ ለዚህም ፡
፲፮ ነገር ፡ እኛ ፡ ምስክሮች ፡ ነን ። በስሙም ፡ በማ
መን ፡ ይህን ፡ የምታዩትንና ፡ የምታውቁትን ፡
የእርሱ ፡ ስም ፡ አጸናው ÷ በእርሱም ፡ በኩል ፡
የሆነው ፡ እምነት ፡ በሁላችሁ ፡ ፊት ፡ ይህን ፡
ፍጹም ፡ ጤና ፡ ሰጠው ።
፲፯ አሁንም ÷ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ÷ እናንተ ፡ እንደ ፡
አለቆቻችሁ ፡ ደግሞ ፡ ባለማወቅ ፡ እንዳደረጋ
፲፰ ችሁት ፡ አውቄአለሁ ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡
ክርስቶስ ፡ መከራ ፡ እንዲቀበል ፡ አስቀድሞ ፡ በነ
ቢያት ፡ ሁሉ ፡ አፍ ፡ የተናገረውን ፡ እንዲሁ ፡ ፈጸ
፲፱፡፳ መው ። እንግዲህ ፡ ከጌታ ፡ ፊት ፡ የመጽናናት ፡
ዘመን ፡ እንድትመጣላችሁ ፡ አስቀድሞም ፡ ለእ
ናንተ ፡ የመረጠውን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ እን
ዲልክላችሁ ÷ ኃጢአታችሁ ፡ ይደመሰስ ፡ ዘንድ ፡
፳፩ ንሕሉ ፡ ግቡ ፡ ተመለሱም ። እግዚአብሔር ፡
ከዋኃት ፡ ጀምሮ ፡ በቅዱሳን ፡ ነቢያቱ ፡ አፍ ፡ የተ
ናገረው ÷ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እስከሚታደስበት ፡ ዘመን ፡
ድረስ ፡ ሰማይ ፡ ይቀበለው ፡ ዘንድ ፡ ይገባልና ።
፳፪ ሙሴም ፡ ለአባቶች ፡— ጌታ ፡ አምላክ ፡ እኔን ፡
እንዳስነሣኝ ፡ ነቢይን ፡ ከወንድሞቻችሁ ፡ ያስነ
ሣላችኋል ፤ በሚነግራችሁ ፡ ሁሉ ፡ እርሱን ፡
፳፫ ስሙት ። ያንም ፡ ነቢይ ፡ የማትሰማው ፡ ነፍስ ፡
ሁሉ ፡ ከሕዝብ ፡ ተለይታ ፡ ትጠፋለች ፡ አለ ።
፳፬ ሁለተኛም ፡ ከሳሙኤል ፡ ጀምሮ ፡ ከእርሱም ፡
በኋላ ፡ የተናገሩት ፡ ነቢያት ፡ ሁሉ ፡ ደግሞ ፡ ስለ
፳፭ ዚህ ፡ ወራት ፡ ተናገሩ ። እናንተ ፡ የነቢያት ፡
ልጆችና ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአብርሃም ፡— በዘ
ርህ ፡ የምድር ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ ይባረካሉ ፡ ብሎ ÷
ከአባቶቻችን ፡ ጋር ፡ ያደረገው ፡ የኪዳን ፡ ልጆች ፡
፳፮ ናችሁ ። ለእናንተ ፡ አስቀድሞ ፡ እግዚአብሔር ፡
ብላቴናውን ፡ አስነሥቶ ÷ እያንዳንዳችሁን ፡ ከክ
ፋታችሁ ፡ እየመለሰ ፡ ይበርክችሁ ፡ ዘንድ ÷ ሰደ
ደው ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

፩ ለሕዝቡም ፡ ሲናገሩ ፡ የክህናት ፡ አለቆችና ፡
፪ የመቅደስ ፡ አዛዣ ፡ ሰዱቃውያንም ÷ ሕዝቡን ፡
ስለ ፡ አስተማሩና ፡ በኢየሱስ ፡ የሙታንን ፡ ትን
ሣኤ ፡ ስለ ፡ ሰበኩ ፡ ተቸግረው ÷ ወደ ፡ እነርሱ ፡
፫ ቀረቡ ÷ እጃቸውንም ፡ ጭነውባቸው ፡ አሁን ፡
መሽቶ ፡ ነበርና ፡ እስከ ፡ ማግሥቱ ፡ ድረስ ፡ በወ
፬ ኅኒ ፡ አኖሩአቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ቃሉን ፡ ከሰ
ሙት ፡ ብዙዎች ፡ አመኑ ÷ የወንዶችም ፡ ቍጥር ፡
አምስት ፡ ሺህ ፡ ያህል ፡ ሆነ ።
፭፡፮ በነገውም ፡ አለቆቻቸውና ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጻፎ
ችም ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ሐናም ፡ ቀያፋም ፡ ዮሐን

ስም ፡ እስክንጽሮስም ፡ የሊቀ ፡ ካህናቱም ፡ ዘመ
ዶች ፡ የነበሩት ፡ ሁሉ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተሰበ
፯ ሰቡ ፤ እነርሱንም ፡ በመካከል ፡ አቁመው ፡— ኀ
በምን ፡ ኃይል ፡ ወይስ ፡ በማን ፡ ስም ፡ እናንተ ፡
ይህን ፡ አደረጋችሁ ? ብለው ፡ ጠየቁአቸው ።
፰ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጴጥሮስ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተሞ ፍ፡ ፰
ልቶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡— እናንተ ፡ የሕዝብ ፡
አለቆችና ፡ ሽማግሌዎች ፡ እኛ ፡ ዛሬ ፡ ለድውዩ ፡ ፱
ሰው ፡ ስለ ፡ ተደረገው ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ ይህ ፡
በምን ፡ እንደ ፡ ዳነ ፡ ብንመረመር ÷ እናንተ ፡ በሰ ፲
ቀላችሁት ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከሙታን ፡ ባስነ
ሣው ፡ በናዝሬቱ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡
ይህ ፡ ደኅና ፡ ሆኖ ፡ በፊታችሁ ፡ እንደ ፡ ቆመ ÷
ለእናንተ ፡ ለሁላችሁ ፡ ለእስራኤልም ፡ ሕዝብ ፡
፲፩ ሁሉ ፡ የታወቀ ፡ ይሁን ። እናንተ ፡ ግንበኞች ፡
የናቃችሁት ÷ የማዕዘን ፡ ራስ ፡ የሆነው ፡ ይህ ፡
፲፪ ድንጋይ ፡ ነው ። መዳንም ፡ በሌላ ፡ በማንም ፡
የለም ፤ እንድንበት ፡ ዘንድ ፡ የሚገባን ፡ ለሰዎች ፡
የተሰጠ ፡ ስም ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ሌላ ፡ የለምና ።
፲፫ ጴጥሮስና ፡ ዮሐንስም ፡ በግልጥ ፡ እንደ ፡ ተና
ገሩ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ÷ መጽሐፍን ፡ የማያውቁና ፡ ያል
ተማሩ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ አስተውለው ፡
አደነቁ ÷ ከኢየሱስም ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ አወ
፲፬ ቁአቸው ። የተፈወሰውንም ፡ ሰው ፡ ከእነርሱ ፡
ጋር ፡ ቆሞ ፡ ሲያዩ ፡ የሚመልሱትን ፡ አጡ ።
፲፭ ከሸንጎም ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይወጡ ፡ ዘንድ ፡ አዝ
፲፮ ዘው ፡— በእነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ምን ፡ እንሥራ ? የታ
ወቀ ፡ ምልክት ፡ በእነርሱ ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ተደ
ረገ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ተገልጦአ
ልና ÷ እንሸሽገውም ፡ ዘንድ ፡ አንችልም ። ነገር ፡
፲፯ ግን ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ እብዝቶ ፡ እንዳይስፋፋ ÷
ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ለማንም ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡
ስም ፡ እንዳይናገሩ ፡ እየዛትን ፡ እንዘዛቸው ፡
ብለው ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተማከሩ ። ጠርተ
፲፰ ውም ፡ በኢየሱስ ፡ ስም ፡ ፈጽመው ፡ እንዳይና
ገሩና ፡ እንዳያስተምሩ ፡ አዘዙአቸው ። ጴጥሮ
፲፱ ስና ፡ ዮሐንስ ፡ ግን ፡ መልሰው ፡— እግዚአብሔ
ርን ፡ ከመስማት ፡ ይልቅ ፡ እናንተን ፡ እንሰማ ፡
ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የሚገባ ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ ቊረጡ ፤ እኛስ ፡ ያየነውንና ፡ የሰማነውን ፡
፳ ከመናገር ፡ ዝም ፡ ማለት ፡ እንችልም ፡ አሉአ
፳፩ ቸው ። እነርሱም ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እንደሚቀጡ ፡
ምክንያት ፡ ስላላገኙባቸው ÷ እንደ ፡ ገና ፡ ዝተው ፡
ከሕዝቡ ፡ የተነሣ ፡ ፈቱአቸው ። ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
ስለ ፡ ሆነው ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያከብሩ ፡
፳፪ ነበርና ። ይህ ፡ የመፈወስ ፡ ምልክት ፡ የተደረገ
ለት ፡ ሰው ፡ ከአርባ ፡ ዓመት ፡ ይበልጠው ፡ ነበርና ።
፳፫ ተፈትተውም ፡ ወደ ፡ ወገኖቻቸው ፡ መጡና ፡
የክህናት ፡ አለቆችና ፡ ሽማግሌዎች ፡ ያሉአቸውን ፡

፫ ፲፭ ዮሐ ፭ ÷ ፱ ። ፲፮ ። ማቴ ፱ ÷ ፳፬ ። ፲፯ ። ሉቃ ፳፫ ÷ ፴፬ ። ፲፰ ። ሉቃ ፳፬ ÷ ፳፭—፳፯ ። ፲፱ ። ም
፪ ÷ ፻፵፮ ። ሕዝ ፴፮ ÷ ፳፫—፳፯ ። ፳፪፡፳፫ ። ዘዳግ ፲፰ ÷ ፲፭ ፡ ፲፰ ። ፳፭ ። ዘፍጥ ፳፪ ÷ ፲፰ ።

፬ ፩ ፡ ፪ ። ማቴ ፳፪ ÷ ፳፫ ። ፫ ። ዮሐ ፲፰ ÷ ፲፫ ። ፮ ። ማቴ ፳፭ ÷ ፳፫ ። ፯ ። ማቴ ፲ ÷ ፳ ።
፲ ። ም ፪ ÷ ፯ ። ፲፩ ። መዝ ፻፲፰ ÷ ፳፪ ። ማቴ ፳፭ ÷ ፵፪ ። ፲፪ ። ማቴ ፭ ÷ ፳፭ ። ፲፫ ። ማር ፫ ÷ ፲፱ ። ፲፬ ። ማቴ
፲ ÷ ፳፰ ።

፳፬ ሁሉ ፡ ነገሩአቸው ። እነርሱም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡
በአንድ ፡ ልብ ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ድምፃቸውን ፡ ከፍ ፡ አደረጉ ፡ እንዲህም ፡ አሉ ፡—
ጌታ ፡ ሆይ ÷ አንተ ፡ ሰማይንና ፡ ምድሩን ፡ ባሕ
ሩንም ፡ በእነርሱም ፡ የሚኖረውን ፡ ሁሉ ፡ የፈ
፳፭ ጠርህ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በብላቴናህ ፡ በአ
ባታችን ፡ በዳዊት ፡ አፍ ፡— አሕዝብ ፡ ለምን ፡ አኮ
ረመረሙ ? ሕዝቡስ ፡ ከንቱን ፡ ነገር ፡ ለምን ፡
፳፮ አሰቡ ? የምድር ፡ ነገሥታት ፡ ተነሡ ፡ አለቆ
ችም ፡ በጌታና ፡ በተቀባው ፡ ላይ ፡ አብረው ፡
ተከማቹ ፡ ብለህ ፡ የተናገርህ ፡ አምላክ ፡ ነህ ።
፳፯፡፳፰ በቀባኸው ፡ በቅዱሱ ፡ ብላቴናህ ፡ በኢየሱስ ፡
ላይ ፡ ሄሮድስና ፡ ጴንጤናዊው ፡ ጲላጦስ ፡ ከአሕ
ዛብና ፡ ከእስራኤል ፡ ሕዝብ ፡ ጋር ÷ እጅህና ፡ አሳ
ብህ ፡ እንዲሆን ፡ አስቀድመው ፡ የወሰኑትን ፡
ሁሉ ፡ ሊፈጽሙ ÷ በዚች ፡ ከተማ ፡ በእውነት ፡
፳፱፡፴ ተሰበሰቡ ። አሁንም ÷ ጌታ ፡ ሆይ ÷ ወደ ፡ ዛቻ
ቸው ፡ ተመልከት ፤ ለመፈወስም ፡ እጅህን ፡ ስት
ዘረጋ ፡ በቅዱስ ፡ ብላቴናህም ፡ በኢየሱስ ፡ ስም ፡
ምልክትና ፡ ድንቅ ፡ ሲደረግ ፤ ባሪያዎችህ ፡ በፍ
፴፩ ጹም ፡ ግልጥነት ፡ ቃልህን ፡ እንዲናገሩ ፡ ስጣ
ቸው ። ከጸለዩም ፡ በኋላ ፡ ተሰብስበው ፡ የነበሩ
በት ፡ ስፍራ ፡ ተናወጠ ÷ በሁሉም ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ ሞላባቸው ÷ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡
በግልጥ ፡ ተናገሩ ።
፴፪ ያመኑትም ፡ ሕዝብ ፡ አንድ ፡ ልብ ፡ አንዲትም ፡
ነፍስ ፡ ነበሩአቸው ÷ ገንዘባቸውም ፡ ሁሉ ፡ በአን
ድነት ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ካለው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ስንኳ ፡
የራሱ ፡ አንደ ፡ ሆነ ፡ ማንም ፡ አልተናገረም ።
፴፫ ሐዋርያትም ፡ የጌታን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶ
ስን ፡ ትንሣኤ ፡ በታላቅ ፡ ኃይል ፡ ይመሰክሩ ፡
ነበር ፤ በሁሉም ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ጸጋ ፡ ነበረባ
፴፬ ቸው ። በመካከላቸው ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ ችግረኛ ፡
አልነበረምና ፤ መሬት ፡ ወይም ፡ ቤት ፡ ያላቸው ፡
ሁሉ ፡ እየሸጡ ፡ የተሸጠውን ፡ ዋጋ ፡ ያመጡ ፡
፴፭ ነበርና ÷ በሐዋርያትም ፡ እግር ፡ አጠገብ ፡ ያኖሩ ፡
ነበር ፤ ማናቸውም ፡ እንደሚፈልግ ፡ መጠን ፡
፴፮ ለእያንዳንዱ ፡ ያከፍሉት ፡ ነበር ። ትውልዱም ፡
የቆጵሮስ ፡ ሰው ፡ የነበረ ፡ አንድ ፡ ሌዋዊ ፡ ዮሴፍ ፡
የሚሉት ፡ ነበረ ÷ እርሱም ፡ በሐዋርያት ፡ በርና
ባስ ፡ ተባለ ፡ ትርጓሜውም ፡ የመጽናናት ፡ ልጅ ፡
፴፯ ነው ፤ እርሻም ፡ ነበረውና ፡ ሸጦ ፡ ገንዘቡን ፡ አም
ጥቶ ፡ ከሐዋርያት ፡ እግር ፡ አጠገብ ፡ አኖረው ።

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

፩ ሐናንያም ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሰጲራ ፡
፪ ከተባለች ፡ ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ መሬት ፡ ሸጠ ÷ ሚስ
ቱም ፡ ደግሞ ፡ ስታውቅ ፡ ከሸያጩ ፡ አስቀረና ፡
እኩሌታውን ፡ አምጥቶ ፡ በሐዋርያት ፡ እግር ፡
፫ አጠገብ ፡ አኖረው ። ጴጥሮስም ፡— ሐናንያ ፡
ሆይ ÷ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ታታልልና ፡ ከመሬቱ ፡
ሸያጭ ፡ ታስቀር ፡ ዘንድ ፡ ሰይጣን ፡ በልብህ ፡
ስለ ፡ ምን ፡ ሞላ ? ሳትሸጠው ፡ የአንተ ፡ አልነ ፬
በረምን ? ከሸጥኸውስ ፡ በኋላ ፡ በሥልጣንህ ፡
አልነበረምን ? ይህን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ምን ፡ በል
ብህ ፡ አሰብህ ? እግዚአብሔርን ፡ እንጂ ፡ ሰውን ፡
፭ አልዋሸህም ፡ አለው ። ሐናንያም ፡ ይህን ፡ ፭
ቃል ፡ ሰምቶ ፡ ወደቀ ፡ ሞተም ። በሰሙትም ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ፍርሃት ፡ ሆነ ። ጕበዞችም ፡ ፮
ተነሥተው ፡ ከፈኑት ፡ አውጥተውም ፡ ቀበሩት ።
፯ ከሦስት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ በኋላም ፡ ሚስቱ ፡
የሆነውን ፡ ሳታውቅ ፡ ገባች ። ጴጥሮስም ፡ ፰
መልሶ ፡— እስቲ ፡ ንገሪኝ ÷ መሬታችሁን ፡
ይህን ፡ ለሚያህል ፡ ሸጣችሁትን ? አላት ። እር
ስዋም ፡— አዎን ÷ ይህን ፡ ለሚያህል ፡ ነው ፡
አለች ። ጴጥሮስም ፡— የጌታን ፡ መንፈስ ፡ ትፈ ፱
ታተኑ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተስማማችሁ ?
እነሆ ፡ ባልሽን ፡ የቀበሩት ፡ ሰዎች ፡ እግር ፡
በደጅ ፡ ነው ፡ አንቺንም ፡ ያወጡሻል ፡ አላት ።
፲ ያን ፡ ጊዜም ፡ በእግሩ ፡ አጠገብ ፡ ወደቀች ፡ ሞተ ፲
ችም ። ጕበዞችም ፡ ሲገቡ ፡ ሞታ ፡ አገኙአት ፡
አውጥተውም ፡ በባልዋ ፡ አጠገብ ፡ ቀበሩአት ።
፲፩ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉና ፡ ይህንም ፡ በሰሙ ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ፍርሃት ፡ ሆነ ።
፲፪ በሐዋርያትም ፡ እጅ ፡ ብዙ ፡ ምልክትና ፡
ድንቅ ፡ በሕዝብ ፡ መካከል ፡ ይደረግ ፡ ነበር ፤
ሁሉም ፡ በአንድ ፡ ልብ ፡ ሆነው ፡ በሰሎሞን ፡
፲፫ ደጅ ፡ መመላለሻ ፡ ነበሩ ። ከሌሎችም ፡ አንድ ፡
ስንኳ ፡ ሊተባበራቸው ፡ የሚደፍር ፡ አልነበረም ÷
ሕዝቡ ፡ ግን ፡ ያከብሩአቸው ፡ ነበር ። ፲፬ የሚያም
ኑትም ፡ ከፊት ፡ ይልቅ ፡ ለጌታ ፡ ይጨመሩለት ፡
ነበር ፤ ወንዶችና ፡ ሴቶችም ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ።
፲፭ ስለዚህም ፡ ጴጥሮስ ፡ ሲያልፍ ፡ ጥላውም ፡ ፲፮
ቢሆን ፡ ከእነርሱ ፡ አንዱን ፡ ይጋርድ ፡ ዘንድ ፡
ድውያንን ፡ ወደ ፡ አደባባይ ፡ አውጥተው ፡ በአ
ልጋና ፡ በወለከ ፡ ያኖሩአቸው ፡ ነበር ። ደግ ፲፯
ሞም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ዙሪያ ፡ ካለችው ፡ ከተማ ፡
ድውያንንና ፡ በርኩሳን ፡ መናፍስት ፡ የተሣቀ
ዩትን ፡ እያመጡ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ይሰበሰቡ ፡
ነበር ፤ ሁሉም ፡ ይፈወሱ ፡ ነበር ።
፲፰ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ግን ፡ የሰዱቃውያን ፡ ወገን ፡
ሆነውም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የነበሩት ፡ ሁሉ ፡ ተነሡ ፡
፲፱ ቀንዓትም ፡ ሞላባቸው ። በሐዋርያትም ፡ ላይ ፡
እጃቸውን ፡ ጭነው ፡ በሕዝቡ ፡ ወኅኒ ፡ ውስጥ ፡
አኖሩአቸው ። የጌታ ፡ መልአክ ፡ ግን ፡ በሌሊት ፡
የወኅኒውን ፡ ደጅ ፡ ከፍቶ ፡ አወጣቸውና ፡—
፳ ሂዱና ፡ ቆማችሁ ፡ የዚህን ፡ ሕይወት ፡ ቃል ፡
ሁሉ ፡ ለሕዝብ ፡ በመቅደስ ፡ ንገሩ ፡ አላቸው ።
፳፩ በሰሙም ፡ ጊዜ ፡ ማልደው ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡
ገብተው ፡ አስተማሩ ።
ግን ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱና ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የነበ
ሩት ፡ መጥተው ፡ ሸንጎውንና ፡ የእስራኤልን ፡

፭ ፩ ፡ ፪ ። ፪ ። ፫ ። ፬ ። ፭ ። ፮ ። ፰ ። ፱ ። ፲ ። ፲፩ ። ፲፪ ። ፲፫ ። ፲፬ ። ፲፭ ። ፲፮ ። ፲፯ ። ፲፰ ። ፲፱ ። ፳ ። ፳፩ ።

ልጆች ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሁሉ ፡ በአንድነት ፡ ጠሩ ፥
ያመጡአቸውም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ወኅኒ ፡ ላኩ ።
፳፪፡፳፫፤ ሎሌዎችም ፡ መጥተው ፡ በወኅኒው ፡ አላገኙአ
ቸውም ፤ ተመልሰውም ፡— ወኅኒው ፡ በጣም ፡
በጥንቃቄ ፡ ተዘግቶ ፡ ጠባቂዎችም ፡ በደጁ ፡
ፊት ፡ ቆመው ፡ አገኘን ፥ በከፈትን ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡
በውስጡ ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ አላገኘንም ፡ አሉአ
፳፬፤ ቸው ። የመቅደስ ፡ አዛዥና ፡ የካህናት ፡ አለቆ
ችም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡— እንጃ ፡
ይህ ፡ ምን ፡ ይሆን ? እያሉ ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ አመ
፳፭፤ ነቱ ። አንድ ፡ ሰውም ፡ መጥቶ ፡— እነሆ ፥ በወ
ኅኒ ፡ ያኖራችኋቸው ፡ ሰዎች ፡ እየቆሙ ፡ ሕዝ
ቡንም ፡ እያስተማሩ ፡ በመቅደስ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡
፳፮፤ አወራላቸው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አዛዡ ፡ ከሎ
ሌዎች ፡ ጋር ፡ ሄዶ ፡ አመጣቸው ፥ በኃይል ፡
ግን ፡ አይደለም ፤ ሕዝቡ ፡ እንዳይወግሩአቸው ፡
ይፈሩ ፡ ነበርና ።
፳፯፤ አምጥተውም ፡ በሸንጎ ፡ አቆሙአቸው ።
፳፰፤ ሊቀ ፡ ካህናቱም ፡— በዚህ ፡ ስም ፡ እንዳታስ
ተምሩ ፡ አጥብቀን ፡ አላዘዝናችሁምን ? እነ
ሆም ፥ ኢየሩሳሌምን ፡ በትምህርታችሁ ፡ ሞል
ታችኋል ፤ የዚያንም ፡ ሰው ፡ ደም ፡ በእኛ ፡ ታመ
ጡብን ፡ ዘንድ ፡ ታስባላችሁ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ።
፳፱፤ ጴጥሮስና ፡ ሐዋርያትም ፡ መልሰው ፡ አሉ ፡—
ከሰው ፡ ይልቅ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልንታዘዝ ፡
፴፤ ይገባል ። እናንተ ፡ በእንጨት ፡ ላይ ፡ ሰቅላችሁ ፡
የገደላችሁትን ፡ ኢየሱስን ፡ የአባቶቻችን ፡ አም
፴፩፤ ላክ ፡ አስነሣው ፤ ይህን ፡ እግዚአብሔር ፥ ለእስራ
ኤል ፡ ንስሐን ፡ የኃጢአትንም ፡ስርየት ፡ ይሰጥ ፡
ዘንድ ፥ ራስም ፡ መድኃኒትም ፡ አድርጎ ፡ በቀኙ ፡
፴፪፤ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገው ። እኛም ፡ ለዚህ ፡ ነገር ፡
ምስክሮች ፡ ነን ፥ ደግሞም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሚ
ታዘዙት ፡ የሰጠው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ምስክር ፡
ነው ።
፴፫፤ እነርሱም ፡ ሲሰሙ ፡ በጣም ፡ ተቈጡ ፡ ሊገድ
፴፬፤ ሉአቸውም ፡ አሰቡ ። ነገር ፡ ግን ፡ በሕዝብ ፡
ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የከበረ ፡ የሕግ ፡ መምህር ፡ ገማል
ያል ፡ የሚሉት ፡ አንድ ፡ ፈሪሳዊ ፡ በሸንጎ ፡ ተነ
ሥቶ ፡ ሐዋርያትን ፡ ጥቂት ፡ ፈቀቅ ፡ እንዲያደ
፴፭፤ ርጉአቸው ፡ አዘዘ ፥ እንዲህም ፡ አላቸው ፡—
የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡
ምን ፡ እንደምታደርጉ ፡ ለራሳችሁ ፡ ተጠንቀቁ ።
፴፮፤ ከዚህ ፡ ወራት ፡ አስቀድሞ ፡ ቴዎዳስ ፡— እኔ ፡
ታላቅ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ተነሥቶ ፡ ነበርና ፥ አራት ፡
መቶ ፡ የሚያህሉ ፡ ሰዎችም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡
ተባበሩ ፤ እርሱም ፡ ጠፋ ፡ የሰሙትም ፡ ሁሉ ፡
፴፯፤ ተበተኑ ፡ እንደ ፡ ምናምንም ፡ ሆኑ ። ከዚህ ፡
በኋላ ፡ ሰዎች ፡ በተጻፉበት ፡ ዘመን ፡ የገሊላው ፡
ይሁዳ ፡ ተነሣ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችንም ፡ አሸፍቶ ፡ አስ
ከተለ ፤ እርሱም ፡ ጠፋ ፡ የሰሙትም ፡ ሁሉ ፡ ተበ
፴፰፤ ታተኑ ። አሁንም ፡ እላችኋለሁ ፡— ከእነዚህ ፡
ሰዎች ፡ ተለዩ ፡ ተዉአቸውም ፤ ይህ ፡ አሳብ ፡
ወይም ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ ከሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይጠ
ፋልና ፤ ከእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ፴፱፤
ታጠፉአቸው ፡ ዘንድ ፡ አይቻላችሁም ፥ በእር
ግጥ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ ስትጣሉ ፡ ምናል
ባት ፡ እንዳትገኙ ።
ሰሙትም ፥ ሐዋርያትንም ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ፵፤
ጠርተው ፡ ገረፉአቸው ፥ በኢየሱስም ፡ ስም ፡
እንዳይናገሩ ፡ አዝዘው ፡ ፈቱአቸው ። እነር ፵፩፤
ሱም ፡ ስለ ፡ ስሙ ፡ ይናቁ ፡ ዘንድ ፡ የተገባቸው ፡
ሆነው ፡ ስለ ፡ ተቈጠሩ ፡ ከሸንጎው ፡ ፊት ፡ ደስ ፡
እያላቸው ፡ ወጡ ፤ ዕለት ፡ ዕለትም ፡ በመቅደ ፵፪፤
ስና ፡ በቤታቸው ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ እርሱ ፡ ክር
ስቶስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማስተማርንና ፡ መስበክን ፡
አይተዉም ፡ ነበር ።

ምዕራፍ ፡ ፮ ።

በዚህም ፡ ወራት ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ እየ ፩፤
በዙ ፡ ሲሄዱ ፡ ከግሪክ ፡ አገር ፡ መጥተው ፡ የነበ
ሩት ፡ አይሁድ ፡ በይሁዳ ፡ ኖረው ፡ በነበሩት ፡
አይሁድ ፡ አንጐራጐሩባቸው ፥ በየቀኑ ፡ በተሠ
ራው ፡ አገልግሎት ፡ መበለቶቻቸውን ፡ ችላ ፡
ይሉባቸው ፡ ነበርና ። አሥራ ፡ ሁለቱም ፡ ደቀ ፡ ፪፤
መዛሙርት ፡ ሁሉን ፡ ጠርተው ፡ እንዲህ ፡ አሉ
አቸው ፡— የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ትተን ፡
ማዕድን ፡ እናገለግል ፡ ዘንድ ፡ የሚገባ ፡ ነገር ፡
አይደለም ። ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ በመልካም ፡ ፫፤
የተመሰከረላቸውን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስና ፡ ጥበ
ብም ፡ የሞላባቸውን ፡ ሰባት ፡ ሰዎች ፡ ከእናንተ ፡
ምረጡ ፥ ለዚህም ፡ ጉዳይ ፡ እንሾማቸዋለን ፤
እኛ ፡ ግን ፡ ለጸሎትና ፡ ቃሉን ፡ ለማገልገል ፡ እን ፬፤
ተጋለን ። ይህም ፡ ቃል ፡ ሕዝብን ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ፭፤
አሰኛቸው ፤ እምነትና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ የሞ
ላበትን ፡ ሰው ፡ እስጢፋኖስን ፡ ፊልጶስንም ፡ ጵሮ
ኮሮስንም ፡ ኒቃሮናንም ፡ ጢሞናንም ፡ ጳርሜና
ንም ፡ ወደ ፡ ይሁዲነት ፡ ገብቶ ፡ የነበረውን ፡ የአ
ንጾኪያውን ፡ ኒቆላዎስንም ፡ መረጡ ። በሐዋር ፮፤
ያትም ፡ ፊት ፡ አቆሙአቸው ፥ ከጸለዩም ፡ በኋላ ፡
እጃቸውን ፡ ጫኑባቸው ።
የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ እየሰፋ ፡ ሄደ ፥ ፯፤
በኢየሩሳሌምም ፡ የደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ቍጥር ፡
እጅግ ፡ እየበዛ ፡ ሄደ ፤ ከካህናትም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡
ለሃይማኖት ፡ የታዘዙ ፡ ሆኑ ።
እስጢፋኖስም ፡ ጸጋንና ፡ ኃይልን ፡ ተሞልቶ ፡ ፰፤
በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ድንቅንና ፡ ታላቅ ፡ ምል
ክትን ፡ ያደርግ ፡ ነበር ። የነጻ ፡ ወጪዎች ፡ ከተ ፱፤
ባለችው ፡ ምኵራብም ፡ ከቀሬናና ፡ ከእስክንድር
ያም ፡ ሰዎች ፡ ከኪልቅያና ፡ ከእስያም ፡ ከነበሩት ፡
አንዳንዶቹ ፡ ተነሥተው ፡ እስጢፋኖስን ፡ ይከራ
ከሩት ፡ ነበር ፤ ይናገርበት ፡ የነበረውንም ፡ ጥበ ፲፤
ብና ፡ መንፈስ ፡ ይቃወሙ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ።

፭። ፳፯፤ ምዕ ፬ ፥ ፳፭። ፳፰፤ ምዕ ፬ ፥ ፲፰፤ ማቴ ፳፯ ፥ ፳፭። ፳፱፤ ዳን ፮ ፥ ፱—፲። ፴—፴፪፤ ምዕ ፪ ፥ ፴፪ ፡ ፴፫ ፡ ፴፮።
፴፰፤ ማቴ ፲፭ ፥ ፲፫። ፴፱፤ ምሳ ፳፩ ፥ ፴። ፵፤ ምዕ ፬ ፥ ፲፰፤ ማቴ ፲ ፥ ፲፯። ፵፩፤ ማቴ ፭ ፥ ፲፩ ፡ ፲፪።
፮። ፩፤ ምዕ ፬ ፥ ፴፭። ፮፤ ምዕ ፲፫ ፥ ፫። ፲፤ ሉቃ ፳፩ ፥ ፲፭።

፲፩፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡— በሙሴ ፡ ላይ ፡ በእግዚአብሔ
ርም ፡ ላይ ፡ የስድብን ፡ ነገር ፡ ሲናገር ፡ ሰምተነ
፲፪፤ ዋል ፡ የሚሉ ፡ ሰዎችን ፡ አስነሡ ። ሕዝቡንና ፡
ሽማግሌዎችንም ፡ ጻፎችንም ፡ አናደዱ ፥ ቀርበ
ውም ፡ ያዙት ፡ ወደ ፡ ሸንጎም ፡ አመጡትና ፡—
፲፫፤ ይህ ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ በተቀደሰው ፡ ስፍራ ፡ በሕ
ግም ፡ ላይ ፡ የስድብን ፡ ነገር ፡ ለመናገር ፡ አይ
፲፬፤ ተውም ፤ ይህ ፡ የናዝሬቱ ፡ ኢየሱስ ፡ ይህን ፡
ስፍራ ፡ ያፈርሰዋል ፡ ሙሴም ፡ ያስተላለፈልንን ፡
ሥርዓት ፡ ይለውጣል ፡ ሲል ፡ ሰምተነዋልና ፡
፲፭፤ የሚሉ ፡ የሐሰት ፡ ምስክሮችን ፡ አቆሙ ። በሸ
ንጎም ፡ የተቀመጡት ፡ ሁሉ ፡ ትኵር ፡ ብለው ፡
ሲመለከቱት ፡ እንደ ፡ መልአክ ፡ ፊት ፡ ሆኖ ፡
ፊቱን ፡ አዩት ።

ምዕራፍ ፡ ፯ ።

፩፤ ሊቀ ፡ ካህናቱም ፡— ይህ ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡
፪፤ ነውን ? አለው ፤ እርሱም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡—
ወንድሞችና ፡ አባቶች ፡ ሆይ ፥ ስሙ ። የክ
ብር ፡ አምላክ ፡ ለአባታችን ፡ ለአብርሃም ፡ በካራን ፡
ሳይቀመጥ ፡ ገና ፡ በሁለት ፡ ወንዝ ፡ መካከል ፡ሳለ ፡
፫፤ ታየና ፡— ከአገርህና ፡ ከዘመዶችህም ፡ ወጥተህ ፡
ወደማሳይህ ፡ ወደ ፡ ማንኛውም ፡ ምድር ፡ ና ፡
፬፤ አለው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከከለዳውያን ፡ አገር ፡
ወጥቶ ፡ በካራን ፡ ተቀመጠ ። ከዚያም ፡ አባቱ ፡
ከሞተ ፡ በኋላ ፡ እናንተ ፡ ዛሬ ፡ ወደምትኖሩበት ፡
፭፤ ወደዚች ፡ አገር ፡ አወጣው ። በዚችም ፡ የእግር ፡
ጫማ ፡ ስንኳ ፡ የሚያህል ፡ ርስት ፡ አልሰጠውም ፤
ነገር ፡ ግን ፡ ልጅ ፡ ሳይኖረው ፡ ለእርሱ ፡ ከእር
ሱም ፡ በኋላ ፡ ለዘሩ ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ ይሰጠው ፡
፮፤ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡ ሰጠው ። እግዚአብሔርም ፡ ዘሩ ፡
በሌላ ፡ አገር ፡ መጻተኞች ፡ እንዲሆኑ ፡ አራት ፡
መቶ ፡ ዓመትም ፡ ባሪያዎች ፡ እንዲያደርጉአ
ቸው ፡ እንዲያስጨንቁአቸውም ፡ እንዲህ ፡ ተና
፯፤ ገረ ፤ ደግሞም ፡ እግዚአብሔር ፡— እንደ ፡ ባሪ
ያዎች ፡ በሚገዙአቸው ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ እኔ ፡
እፈርድባቸዋለሁ ፥ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ይወጣሉ ፡
፰፤ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ ያመልኩኛል ፡ አለ ። የመገ
ረዝንም ፡ ኪዳን ፡ ሰጠው ፤ እንዲሁም ፡ ይስሐ
ቅን ፡ ወለደ ፡ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ገረዘው ፡
ይስሐቅም ፡ ያዕቆብን ፡ ያዕቆብም ፡ አሥራ ፡ ሁለ
ቱን ፡ የአባቶችን ፡ አለቆች ።
፱፤ የአባቶችም ፡ አለቆች ፡ በዮሴፍ ፡ ቀንተው ፡
ወደ ፡ ግብፅ ፡ ሸጡት ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከእ
፲፤ ርሱ ፡ ጋር ፡ ነበረ ፥ ከመከራውም ፡ ሁሉ ፡ አወ
ጣው ፥ በግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ በፈርዖንም ፡ ፊት ፡ ሞገ
ስንና ፡ ጥበብን ፡ ሰጠው ፥ በግብፅና ፡ በቤቱ ፡
ሁሉ ፡ ላይም ፡ ቢትወደድ ፡ አድርጎ ፡ ሾመው ።
፲፩፤ በግብፅና ፡ በከነዓንም ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ራብና ፡
ብዙ ፡ ጭንቅ ፡ መጣ ፥ አባቶቻችንም ፡ ምግብን ፡
አላገኙም ። ያዕቆብም ፡ በግብፅ ፡ እህል ፡ መኖ ፲፪፤
ሩን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በመጀመሪያ ፡ አባቶቻችንን ፡
ሰደዳቸው ፤ በሁለተኛውም ፡ ዮሴፍ ፡ ለወንድ ፲፫፤
ሞቹ ፡ ታወቀ ፥ የዮሴፍም ፡ ትውልድ ፡ በፈር
ዖን ፡ ዘንድ ፡ ተገለጠ ። ዮሴፍም ፡ አባቱን ፡ ያዕ ፲፬፤
ቆብንና ፡ ሰባ ፡ አምስት ፡ ነፍስ ፡ የነበረውን ፡ ቤተ ፡
ዘመድ ፡ ሁሉ ፡ ልኮ ፡ አስጠራ ። ያዕቆብም ፡ ፲፭፤
ወደ ፡ ግብፅ ፡ ወረደ ፡ እርሱም ፡ ሞተ ፡ አባቶቻ
ችንም ፤ ወደ ፡ ሴኬምም ፡ አፍልሰው ፡ አብር ፲፮፤
ሃም ፡ ከሴኬም ፡ አባት ፡ ከኤሞር ፡ ልጆች ፡ በብር ፡
በገዛው ፡ መቃብር ፡ ቀበሩአቸው ።
እግዚአብሔርም ፡ ለአብርሃም ፡ የማለለት ፡ የተ ፲፯፡፲፰፤
ስፋው ፡ ዘመን ፡ ሲቀርብ ፥ ዮሴፍን ፡ የማያው
ቀው ፡ ሌላ ፡ ንጉሥ ፡ በግብፅ ፡ ላይ ፡ እስኪነሣ ፡
ድረስ ፥ ሕዝቡ ፡ እየተጨመሩ ፡ በግብፅ ፡ በዙ ።
እርሱም ፡ ወገናችንን ፡ ተተንኰሎ ፡ ሕፃናትን ፡ ፲፱፤
በሕይወት ፡ እንዳይጠብቁ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይጥሉ ፡
ዘንድ ፡ አድርጎ ፡ አባቶቻችንን ፡ አስጨነቀ ።
በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሙሴ ፡ ተወለደ ፡ በእግዚአብሔ ፳፤
ርም ፡ ፊት ፡ ያማረ ፡ ነበር ፤ በአባቱ ፡ ቤትም ፡
ሦስት ፡ ወር ፡ አደገ ፤ በተጣለም ፡ ጊዜ ፡ የፈር ፳፩፤
ዖን ፡ ልጅ ፡ አንሥታው ፡ ልጅም ፡ ይሆናት ፡ ዘንድ ፡
አሳደገችው ። ሙሴም ፡ የግብፃችን ፡ ጥበብ ፡ ፳፪፤
ሁሉ ፡ ተማረ ፥ በቃሉና ፡ በሥራውም ፡ የበረታ ፡
ሆነ ።
ነገር ፡ ግን ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ሲሞላው ፡ ወንድ ፳፫፤
ሞቹን ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ይጐበኝ ፡ ዘንድ ፡
በልቡ ፡ አሰበ ። አንዱም ፡ ሲበደል ፡ አይቶ ፡ ፳፬፤
ረዳው ፥ የግብፁን ፡ ሰውም ፡ መትቶ ፡ ለተገፋው ፡
ተበቀለ ። ወንድሞቹም ፡ እግዚአብሔር ፡ በእጁ ፡ ፳፭፤
መዳንን ፡ እንዲሰጣቸው ፡ የሚያስተውሉ ፡ ይመ
ስለው ፡ ነበር ፥ እነርሱ ፡ ግን ፡ አላስተዋሉም ።
በማግሥቱም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲጣሉ ፡ አገ ፳፮፤
ኛቸው ፥ ሊያስታርቃቸውም ፡ ወዶ ፡— ሰዎች ፡
ሆይ ፥ እናንተስ ፡ ወንድማማች ፡ ናችሁ ፤ ስለ ፡
ምን ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ትበዳደላላችሁ ? አላ
ቸው ። ያም ፡ ባልንጀራውን ፡ የሚበድል ፡ ግን ፡— ፳፯፤
አንተን ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ ሹምና ፡ ፈራጅ ፡ እንድት
ሆን ፡ የሾመህ ፡ ማን ፡ ነው ? ወይስ ፡ ትናንትና ፡ ፳፰፤
የግብፁን ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ገደልኸው ፡ ልትገድ
ለኝ ፡ ትወዳለህን ? ብሎ ፡ ገፋው ። ሙሴም ፡ ፳፱፤
ከዚህ ፡ ነገር ፡ የተነሣ ፡ ሸሸቶ ፡ በምድያም ፡ አገር ፡
መጻተኛ ፡ ሆኖ ፡ ኖረ ፤ በዚያም ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡
ወለደ ።
አርባ ፡ ዓመትም ፡ ሲሞላ ፡ የጌታ ፡ መልአክ ፡ ፴፤
በሲና ፡ ተራራ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በቍጥቋጦ ፡ መካ
ከል ፡ በእሳት ፡ ነበልባል ፡ ታየው ። ሙሴም ፡ ፴፩፡፴፪፤
አይቶ ፡ ባየው ፡ ተደነቀ ፤ ሊመለከትም ፡ ሲቀ

፮። ፲፩፤ ፩ ነገሥ ፳ ፥ ፲ ፡ ፲፫። ፲፫ ፡ ፲፬፤ ማቴ ፳፮ ፥ ፶፱—፷፩።
፯። ፪፤ ዘፍጥ ፲፩ ፥ ፯ ፤ ፲፩ ፥ ፴፩። ፫ ፡ ፬፤ ዘፍጥ ፲፪ ፥ ፩ ፡ ፬። ፭፤ ዘፍጥ ፲፫ ፥ ፲፬ ፡ ፲፭። ፮ ፡ ፯፤ ዘፍጥ ፲፭ ፥ ፲፫ ፡
፲፬። ፰፤ ዘፍጥ ፲፯ ፥ ፱—፲፩ ፤ ፳፩ ፥ ፪—፬ ፤ ፳፭ ፥ ፳፮ ፤ ፴፭ ፥ ፳፫—፳፮። ፱፤ ዘፍጥ ፴፯ ፥ ፲፩—፳፰። ፲—፲፯፤
ዘፍጥ ምዕ ፴፱—፵። ፲፯—፳፱፤ ዘፀአ ፩ ፥ ፯—፪ ፥ ፲። ፳፫—፳፱፤ ዘፀአ ፪ ፥ ፲፩—፳፪ ፤ ፲፰ ፥ ፫ ፡ ፬። ፴—፴፬፤ ዘፀአ
፫ ፥ ፩—፲።

ርብ፡ የጌታ፡ ቃል፡— እኔ፡ የአባቶችህ፡ አምላክ፡ የአብርሃም፡ አምላክ፡ የይስሐቅም፡ አምላክ፡ የያዕቆብም፡ አምላክ፡ ነኝ፡ ብሎ፡ ወደ፡ እርሱ፡ መጣ ። ሙሴም፡ ተንቀጥቅጦ፡ ሊመለከት፡ አልደፈረም ። ፲፮ ጌታም፡— የቆምህበት፡ ስፍራ፡ የተቀደሰች፡ ምድር፡ ናትና፡ የእግርህን፡ ጫማ፡ አውልቅ ። ፲፯ በግብፅ፡ ያሉትን፡ የሕዝቤን፡ መከራ፡ ፈጽሜ፡ አይቼ፡ መቃተታቸውንም፡ ሰምቼ፡ ላድናቸው፡ ወረድሁ ፤ አሁንም፡ ና ÷ ወደ፡ ግብፅ፡ እልክሃለሁ፡ አለው ። ፲፰ ሹምና፡ ፈራጅ፡ እንድትሆን፡ የሾመህ፡ ማን፡ ነው ? ብለው፡ የካዱትን ÷ ይህን፡ ሙሴን፡ በቀኑ፡ ጥቂቶው፡ በታየው፡ በመልአኩ፡ እጅ፡ እግዚአብሔር፡ ሹምና፡ ቤዛ፡ አድርጎ፡ ላከው ። ፲፱ ይህ፡ ሰው፡ በግብፅ፡ ምድርና፡ በኤርትራ፡ ባሕር፡ በምድረ፡ በዳም፡ አርባ፡ ዓመት፡ ድንቅና፡ ምልክት፡ እያደረገ፡ አወጣቸው ። ፳ ይህ፡ ሰው፡ ለእስራኤል፡ ልጆች፡— እግዚአብሔር፡ ከወንድሞቻችሁ፡ እንደ፡ እኔ፡ ያለ፡ ነቢይ፡ ያስነሣላች ኋል ፤ እርሱን፡ ስሙት፡ ያላቸው፡ ሙሴ፡ ነው ። ፳፩ ይህ፡ ሰው፡ በሲና፡ ተራራ፡ ከተናገረው፡ መልአክና፡ ከአባቶቻችን፡ ጋር፡ በምድረ፡ በዳ፡ በማኅበሩ፡ ውስጥ፡ የነበረው፡ ነው ፤ ይሰጠንም፡ ዘንድ፡ ሕይወት፡ ያላቸውን፡ ቃላት፡ ተቀበለ፤ ፳፪ ለእርሱም፡ አባቶቻችን፡ ሊታዘዙት፡ አልወደዱም ፤ ነገር፡ ግን፡ ገሉት፡ በልባቸውም፡ ወደ፡ ግብፅ፡ ተመለሱ ፤ አሮንንም፡— በፊታችን፡ የሚሄዱ፡ አማልክት፡ ሥራልን ፤ ይህ፡ ከግብፅ፡ ምድር፡ ያወጣን፡ ሙሴ፡ ምን፡ እንደ፡ ሆነ፡ አናውቅምና፡ አሉት ። ፳፫ በዚያም፡ ወራት፡ ጥጃ፡ አደረጉ፡ ለጣዖቱም፡ መሥዋዕት፡ አቀረቡ ÷ በእጃቸውም፡ ሥራ፡ ደስ፡ አላቸው ። ፳፬ እግዚአብሔር፡ ግን፡ ዘወር፡ አለ፡ የሰማይንም፡ ጭፍራ፡ ያመልኩ፡ ዘንድ፡ አሳልፎ፡ ሰጣቸው ÷ በነቢያትም፡ መጽሐፍ፡— እናንተ፡ የእስራኤል፡ ቤት ÷ ሕርባ፡ ዓመት፡ በምድረ፡ በዳ፡ የታረደውን፡ ከብትና፡ መሥዋዕትን፡ አቀረባችሁልኝን ? ትሰ ግዱላቸውም፡ ዘንድ፡ የሠራችኋቸውን፡ ምስሎች፡ እነርሱንም፡ የሞሎክን፡ ድንኳንና፡ ሬፋም፡ የሚሉትን፡ የአምላካችሁን፡ ከዋክ፡ አኃችሁ ፤ እኔም፡ ከባቢሎን፡ ወዲያ፡ እሰዳችኋለሁ፡ ተብሎ፡ እንዲህ፡ ተጽፎአል ። ፳፬ እንዳየው፡ ምስል፡ አድርጎ፡ ይሠራት፡ ዘንድ፡ ሙሴን፡ ተናግሮ፡ እንዳዘዘው ÷ የምስክር፡ ድንኳን፡ ከአባቶቻችን፡ ዘንድ፡ በምድረ፡ በዳ፡ ነበረች ፤ ፳፮ አባቶቻችንም፡ ደግሞ፡ በተራ፡ ተቀብለው፡ እግዚአብሔር፡ በፊታቸው፡ ያወጣቸውን፡ የአሕዛብን፡ አገር፡ በያዙት፡ ጊዜ፡ ከአ

ያሱ፡ ጋር፡ አገቡአት ÷ እስከ፡ ዳዊት፡ ዘመንም፡ ድረስ፡ ኖረች ። ፳፮ እርሱም፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ ሞገስ፡ አግኝቶ፡ ለያዕቆብ፡ አምላክ፡ ማደሪያን፡ ያገኝ፡ ዘንድ፡ ለመነ ። ፳፯ ነገር፡ ግን፡ ሰሎሞን፡ ቤት፡ ሠራለት ። ፳፰ ነገር፡ ግን፡ ነቢዩ፡— ሰማይ፡ ዙፋኔ፡ ነው፡ ምድርም፡ የእግሬ፡ መረገጫ፡ ናት ፤ ለእኔ፡ ምን፡ ዓይነት፡ ቤት፡ ትሠራላችሁ ? ይላል ፤ ጌታ ÷ ወይስ፡ የማርፍበት፡ ስፍራ፡ ምንድር፡ ነው ? ፳፱ ይህንስ፡ ሁሉ፡ እጄ፡ የሠራችው፡ አያደለምን ? እንዳለ ÷ ልዑል፡ የሰው፡ እጅ፡ በሠራችው፡ አይኖርም ።

፴ እናንተ፡ አንገተ፡ደንዳኖች፡ ልባችሁና፡ ጆሮ፡ አችሁም፡ ያልተገረዛ፡ እናንተ፡ ሁልጊዜ፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ ትቃወማላችሁ ፤ አባቶቻችሁ፡ እንደ፡ ተቃወሙት፡ እናንተ፡ ደግሞ ። ፴፩ ከነቢያትስ፡ አባቶቻችሁ፡ ያላሳደዱት፡ ማን፡ ነው ? የጻድቁንም፡ መምጣት፡ አስቀድሞ፡ የተናገሩትን፡ ገድሉአቸው ፤ በመላእክት፡ ሥርዓት፡ ሕግን፡ ተቀብላችሁ፡ ያልጠበቃችሁት፡ እናንተም፡ አሁን፡ አርሱን፡ አሳልፋችሁ፡ ሰጣችሁት፡ ገደላችሁትም ።

፴፫ ይህንም፡ በሰሙ፡ ጊዜ፡ በልባቸው፡ በጣም፡ ተቈጡ፡ ጥርሶቻቸውንም፡ አፋጩበት ። ፴፬ መንፈስ፡ ቅዱስንም፡ ተሞልቶ፡ ወደ፡ ሰማይ፡ ትኵር፡ ብሎ፡ ሲመለከት ፥ የእግዚአብሔርን፡ ክብር፡ ኢየሱስንም፡ በእግዚአብሔር፡ ቀኝ፡ ቆሞ፡ አየና ፡— እነሆ፡ ሰማያት፡ ተከፍተው፡ የሰው፡ ልጅም፡ በእግዚአብሔር፡ ቀኝ፡ ቆሞ፡ አያለሁ፡ አለ ። ፴፭ በታላቅ፡ ድምፅም፡ እየጮኹ፡ ጆሮአቸውን፡ ደፈኑ ÷ በአንድ፡ ልብ፡ ሆነውም፡ ወደ፡ እርሱ፡ ሮጡ ÷ ከከተማም፡ ወደ፡ ውጭ፡ አውጥተው፡ ወገሩት ። ፴፮ ምስክሮችም፡ ልብሳቸውን፡ ሳውል፡ በሚሉት፡ በአንድ፡ ጎበዝ፡ እግር፡ አጠገብ፡ አኖሩ ። ፴፯ እስጢፋኖስም፡— ጌታ፡ ኢየሱስ፡ ሆይ ÷ ነፍሴን፡ ተቀበል ፡ ብሎ ፡ ሲጠራ ፡ ይመግሩት ፡ ነበር ። ፴፰ ተንበርክኮም ፡— ጌታ ፡ ሆይ ÷ ይህን ፡ ኃጢአት ፡ አትቍጠርባቸው ፡ ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኸ ። ፴፱ ይህንም ፡ ብሎ ፡ አንቀላፋ ። ሳውልም ፡ በእርሱ ፡ መገደል ፡ ተስማምቶ ፡ ነበር ።

ምዕራፍ ፰ ።

፩ በዚያን፡ ቀንም፡ በኢየሩሳሌም፡ ባለች፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ላይ፡ ታላቅ፡ ስደት፡ ሆነ ፤ ሁሉም፡ ከሐዋርያትም፡ በቀር፡ ወደ፡ ይሁዳና፡ ወደ፡ ሰማርያ፡ አገሮች፡ ተበተኑ ። ፪ በጸሎትም፡ የተጉ፡ ሰዎች፡ እስጢፋኖስን፡ ቀብረው፡ ታላቅ፡ ልቅሶም፡ አለቀሱለት ። ፫ ሳውል፡ ግን፡ ቤተ፡ ክርስ

ቲያንን፡ ያፈርስ፡ ነበር ፤ ወደ፡ ሁሉም፡ ቤት፡ እየገባ፡ ወንዶችንም፡ ሴቶችንም፡ እየጐተተ፡ ወደ፡ ወኅኒ፡ አሳልፎ፡ ይሰጥ፡ ነበር ።

፬ የተበተኑትም ፡ ቃሉን ፡ እየሰበኩ ፡ ዞሩ ። ፭ ፊልጶስም፡ ወደ፡ ሰማርያ፡ ከተማ፡ ወርዶ፡ ክርስቶስን፡ ሰበክላቸው ። ፮ ሕዝቡም፡ የፊልጶስን፡ ቃል፡ በሰሙ፡ ጊዜ፡ ያደርጋት፡ የነበረውንም፡ ምልክት፡ በዩ፡ ጊዜ ÷ የተናገረውን፡ በአንድ፡ ልብ፡ አደመጡ ። ፯ ርኵሳን፡ መናፍስት፡ በታላቅ፡ ድምፅ፡ እየጮኹ፡ ከብዙ፡ ሰዎች፡ ይወጡ፡ ነበርና ፤ ብዙም፡ ሽባዎችና፡ አንካሶች፡ ተፈወሱ ። ፰ በዚያችም፡ ከተማ፡ ታላቅ፡ ደስታ፡ ሆነ ።

፱ ሲሞን፡ የሚሉት፡ አንድ፡ ሰው፡ ግን፡— እኔ፡ ታላቅ፡ ነኝ፡ ብሎ፡ እየጠነቈለ፡ የሰማርያንም፡ ወገን፡ እያስገረመ፡ ቀድሞ፡ በከተማ፡ ነበረ ። ፲ ከታናናሾችም፡ ጀምሮ፡ እስከ፡ ታላላቆቹ፡ ድረስ፡— ታላቁ፡ የእግዚአብሔር፡ ኃይል፡ ይህ፡ ነው፡ እያሉ፡ ሁሉ፡ ያደምጡት፡ ነበር ። ፲፩ ከብዙ፡ ዘመንም፡ ጀምሮ፡ በጥንቈላ፡ ስላስገረማቸው፡ ያደምጡት፡ ነበር ። ፲፪ ነገር፡ ግን፡ ስለ፡ እግዚአብሔር፡ መንግሥትና፡ ስለ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስም፡ እየሰበከላቸው፡ ፊልጶስን፡ ባመኑት፡ ጊዜ ÷ ወንዶችም፡ ሴቶችም፡ ተጠመቁ ። ፲፫ ሲሞንም፡ ደግሞ፡ ራሱ፡ አመነ ፤ ተጠምቆም፡ ከፊልጶስ፡ ጋር፡ ይተባበር፡ ነበር ። የሚደረገውንም፡ ምልክትና፡ ታላቅ፡ ተአምራት፡ ባየ፡ ጊዜ፡ ተገረመ ።

፲፬ በኢየሩሳሌምም፡ የነበሩት፡ ሐዋርያት፡ የሰማርያ፡ ሰዎች፡ የእግዚአብሔርን፡ ቃል፡ እንደ፡ ተቀበሉ፡ ሰምተው፡ ጴጥሮስንና፡ ዮሐንስን፡ ሰደዱላቸው ። ፲፭ እነርሱም፡ በወረዱ፡ ጊዜ፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ ይቀበሉ፡ ዘንድ፡ ጸለዩላቸው ፤ ፲፮ በጌታ፡ በኢየሱስ፡ ስም፡ ብቻ፡ ተጠምቀው፡ ነበር፡ እንጂ፡ ከእነርሱ፡ በአንዱ፡ ላይ፡ ስንኳ፡ ገና፡ አልወረደም፡ ነበርና ። ፲፯ በዚያን፡ ጊዜ፡ እጃቸውን፡ ጫኑባቸው፡ መንፈስ፡ ቅዱስንም፡ ተቀበሉ ። ፲፰ ሲሞንም፡ በሐዋርያት፡ እጅ፡ መጫን፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ እንዲሰጥ፡ በየ፡ ጊዜ ÷ ገንዘብ፡ አመጣላቸውና፡— እጄን፡ የምጭንበት፡ ሁሉ፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ ይቀበል፡ ዘንድ፡ ለእኔ፡ ደግሞ፡ ይህን፡ ሥልጣን፡ ስጡኝ፡ አለ ። ፲፱ ጴጥሮስ፡ ግን፡ እንዲህ፡ አለው፡— የእግዚአብሔርን፡ ስጦታ፡ በገንዘብ፡ እንድታገኝ፡ አስበሃልና፡ ብርህ፡ ከአንተ፡ ጋር፡ ይጥፋ ። ፳ ልብህ፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ የቀና፡ አይደለምና፡ ከዚህ፡ ነገር፡ ዕድል፡ ወይም፡ ፈንታ፡ የለህም ። ፳፩ እንግዲህ፡ ክፋትህ፡ ንስሐ፡ ግባ፡ ምናልባትም፡ የልብህን፡ አሳብ፡ ይቅር፡ ይልህ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ ለምን ፤ በመራራ፡ መርዝና፡ በኀጢዕት፡ እስራት፡ እንዳለህ፡ አይሃለሁ፡ ይህ ። ፳፫ ሲሞንም ፡ መልሶ ፡— ከላችሁት ፡ አንዳች ፡ እንዳይደርስብኝ ፡ እናንተው ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ ለምኑልኝ ፡ አላቸው ።

፳፬ እነርሱም፡ ከመሰከሩና፡ የጌታን፡ ቃል፡ ከተናገሩ፡ በኋላ፡ ወደ፡ ኢየሩሳሌም፡ ተመለሱ ፤ በሳምራውያን፡ በብዙ፡ መንደሮችም፡ ወንጌልን፡ ሰበኩ ።

፳፭ የጌታም፡ መልአክ፡ ፊልጶስን፡ ተነሥተህ፡ በደቡብ፡ በኩል፡ ከኢየሩሳሌም፡ ወደ፡ ጋዛ፡ ወደሚያወርደው፡ ምድረ፡ በዳ፡ ወደ፡ ሆነ፡ መንገድ፡ ሂድ፡ አለው ። ፳፮ ተነሥቶም፡ ሄደ ። እነሆም ÷ ሃንደኬ፡ የተባለች፡ የኢትዮጵያ፡ ንግሥት፡ አዛዥና፡ ጃንደረባ፡ የነበረ፡ በገንዘብዋም፡ ሁሉ፡ የሠለጠነ፡ አንድ፡ የኢትዮጵያ፡ ሰው፡ ሊሰግድ፡ ወደ፡ ኢየሩሳሌም፡ መጥቶ፡ ነበር ፤ ሲመለስም፡ በሰረገላ፡ ተቀምጦ፡ የነቢዩን፡ የኢሳይያስን፡ መጽሐፍ፡ ያነብ፡ ነበር ። ፳፰ መንፈስም፡ ፊልጶስን፡— ወደዚህ፡ ሰረገላ፡ ቅረብና፡ ተገናኝ፡ አለው ። ፳፱ ፊልጶስም፡ ሮጦ፡ የነቢዩን፡ የኢሳይያስን፡ መጽሐፍ፡ ሰምቶ፡— በእውኑ፡ የምታነበውን፡ ታስተውለዋለህን ፥ አለው ። ፴ እርሱም ፡ — የሚመራኝ ፡ ሰይኖር ፡ ይህ፡ እንዴት፡ ይቻለኛል ? አለው ። ወጥቶም፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ይቀመጥ ፡ ዘንድ ፡ ፊልጶስን ፡ ለመነው ። ፴፩ ያነበውም ፡ የነበረ ፡ የመጽሐፉ ፡ ክፍል ፡ ይህ ፡ ነበረ ፤

እንደ፡ በግ፡ ወደ፡ መታረድ፡ ተነዳ ÷ የበግ፡ ጠቦትም፡ በሸላቹ፡ ፊት፡ ዝም፡ እንደሚል ÷ እንዲሁ፡ አፉን፡ አልከፈተም ። ፴፪ በውር፡ ደቁ፡ ፍርዱ፡ ተወገደ ፤ ሕይወቱ፡ ከምድር፡ ተወግዶለችና፡ ትውልዱንስ፡ ማን፡ ይናገራል ?

፴፫ ጃንደረባውም ፡ ለፊልጶስ ፡ መልሶ ፡— እባክህ ÷ ነቢዩ፡ ይህን፡ ስለ፡ ማን፡ ይናገራል ? ስለ፡ ራሱ፡ ነውን፡ ወይስ፡ ስለ፡ ሌላ ? አለው ። ፴፬ ፊልጶስም፡ አፉን፡ ከፈተ ÷ ከዚህም፡ መጽሐፍ፡ ጀምሮ፡ ስለ፡ ኢየሱስ፡ ወንጌልን፡ ሰበከለት ። ፴፭ በመንገድም ፡ ሲሄዱ ፡ ወደ ፡ ውኃ ፡ ደረሱ ። ጃንደረባውም ፡— እነሆ ፡ ውኃ ፡ እንዳልጠመቅ ፡ የሚከለክለኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ? አለው ። ፴፮ ፊልጶስም ፡— በፍጹም ፡ ልብህ ፡ ብታምን ÷ ተፈቅዶአል ፡ አለው ። መልሶም ፡— ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር፡ ልጅ፡ እንደ፡ ሆነ ፡ አምናለሁ፡ አለ ። ፴፯ ሰረገላውም ፡ ይቆም ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ÷ ፊልጶስና፡ ጃንደረባው፡ ሁለቱም፡ ወደ፡ ውኃ፡ ወረዱ ÷ አጠመቀውም ። ፴፰ ከውኃውም፡ ከወጡ፡ በኋላ፡ የጌታ፡ መንፈስ፡ ፊልጶስን፡ ነጠቀው ፤ ጃንደረባውም፡ ሁለተኛ፡ አላየውም ፤ ደስ፡ ብሎት፡ መንገዱን፡ ይሄድ፡ ነበርና ። ፴፱ ፊልጶስ፡ ግን፡ በአዛጦን፡ ተገኘ ÷ ወደ፡ ቂሣርያም፡ እስኪመጣ፡ ድረስ፡ እየዘረ፡ በከተማዎች፡ ሁሉ፡ ወንጌልን፡ ሰብክ፡ ነበር ።

ጌ፡ ፴፯ ፤ ዘዕኩ ፮ ÷ ፮—፲፱ ፥ ፳፱ ፤ ፻፱ ÷ ፳፭—፴፭ ፤ ፲፮ ÷ ፲፯—፲፯ ፥ ፲፯ ÷ ፳፭ ። ፴፯ ፤ ዘሥግ ፲፯ ÷ ፲፭ ፥ ፲፯ ። ፴፰ ፤ ዘዕኩ ፲፱ ። ፴፱ ፤ ዘዕኩ ፲፯ ÷ ፪ ፡ ፫ ። ፵ ፡ ፵፩ ፤ ዘዕኩ ፡ ፴፫ ÷ ፭ ። ፵፪ ፡ ፵፫ ፡ ኤር ፡ ፲፱ ÷ ፲፫ ፤ ጎሞ ፡ ፭ ÷ ፳፭—፳፯ ። ፵፫ ፤ ዘዕኩ ፵፭ ÷ ፴፬ ። ፵፬ ፤ መኀ ፡ ፻፴፭ ÷ ፭ ፡ ፯ ፡ ሳሙ ፡ ፮ ÷ ፭—፫ ። ፵፮ ፤ ፩ ነገሥ ፡ ፯ ÷ ፭—፲፱ ። ፵፯ ፤ ፩ ነገሥ ፡ ፰ ÷ ፳፯ ። ፵፱ ፤ ፱ ፡ ፶፩ ። ፶ ፡ ፶፩ ፤ ኢሳ ፡ ፷፮ ÷ ፩ ። ፶፩ ፤ ፩ ዜና ፳፯ ÷ ፲፯ ፤ ግሳ ፡ ፫ ÷ ፲፱ ። ፶፪ ፤ ዘሥግ ፲፯ ÷ ፯ ። ፶፫ ፤ መኀ ፡ ፻፴፭ ÷ ፯ ፡ ፲ ። ፶፬ ፤ ፩ ነገሥ ፡ ፰ ÷ ፳፭ ። ፶፭ ፤ ፪ ነገሥ ፡ ፲፱ ÷ ፲፭ ። ፶፮ ፤ ዘፍ ፡ ፲፰ ÷ ፳፪ ። ፶፯ ፤ ዘፍ ፡ ፳፪ ÷ ፲፫ ። ፶፰ ፤ ዘፍ ፡ ፳፩ ÷ ፲፮ ። ፶፱ ፤ ዘፍ ፡ ፳፭ ÷ ፳፬ ። ፷ ፤ ዘፍ ፡ ፳፭ ÷ ፳፭ ። ፷፩ ፤ ዘፍ ፡ ፳፭ ÷ ፳፮ ። ፷፪ ፤ ዘፍ ፡ ፳፭ ÷ ፳፰ ። ፷፫ ፤ ዘፍ ፡ ፳፭ ÷ ፴፩ ። ፷፬ ፤ ዘፍ ፡ ፳፭ ÷ ፴፬ ። ፷፭ ፤ ዘፍ ፡ ፳፮ ÷ ፭ ። ፷፮ ፤ ዘፍ ፡ ፳፮ ÷ ፮ ። ፷፯ ፤ ዘፍ ፡ ፳፮ ÷ ፲፩ ። ፷፰ ፤ ዘፍ ፡ ፳፮ ÷ ፲፭ ። ፷፱ ፤ ዘፍ ፡ ፳፮ ÷ ፳፭ ። ፸ ፤ ዘፍ ፡ ፳፮ ÷ ፴፭ ። ፸፩ ፤ ዘፍ ፡ ፳፯ ÷ ፭ ። ፸፪ ፤ ዘፍ ፡ ፳፯ ÷ ፲፭ ። ፸፫ ፤ ዘፍ ፡ ፳፯ ÷ ፳፭ ። ፸፬ ፤ ዘፍ ፡ ፳፯ ÷ ፴፭ ። ፸፭ ፤ ዘፍ ፡ ፳፰ ÷ ፭ ። ፸፮ ፤ ዘፍ ፡ ፳፰ ÷ ፲፭ ። ፸፯ ፤ ዘፍ ፡ ፳፰ ÷ ፳፭ ። ፸፰ ፤ ዘፍ ፡ ፳፰ ÷ ፴፭ ። ፸፱ ፤ ዘፍ ፡ ፳፱ ÷ ፭ ። ፹ ፤ ዘፍ ፡ ፳፱ ÷ ፲፭ ። ፹፩ ፤ ዘፍ ፡ ፳፱ ÷ ፳፭ ። ፹፪ ፤ ዘፍ ፡ ፳፱ ÷ ፴፭ ። ፹፫ ፤ ዘፍ ፡ ፴ ÷ ፭ ። ፹፬ ፤ ዘፍ ፡ ፴ ÷ ፲፭ ። ፹፭ ፤ ዘፍ ፡ ፴ ÷ ፳፭ ። ፹፮ ፤ ዘፍ ፡ ፴ ÷ ፴፭ ። ፹፯ ፤ ዘፍ ፡ ፴፩ ÷ ፭ ። ፹፰ ፤ ዘፍ ፡ ፴፩ ÷ ፲፭ ። ፹፱ ፤ ዘፍ ፡ ፴፩ ÷ ፳፭ ። ፺ ፤ ዘፍ ፡ ፴፩ ÷ ፴፭ ። ፺፩ ፤ ዘፍ ፡ ፴፪ ÷ ፭ ። ፺፪ ፤ ዘፍ ፡ ፴፪ ÷ ፲፭ ። ፺፫ ፤ ዘፍ ፡ ፴፪ ÷ ፳፭ ። ፺፬ ፤ ዘፍ ፡ ፴፪ ÷ ፴፭ ። ፺፭ ፤ ዘፍ ፡ ፴፫ ÷ ፭ ። ፺፮ ፤ ዘፍ ፡ ፴፫ ÷ ፲፭ ። ፺፯ ፤ ዘፍ ፡ ፴፫ ÷ ፳፭ ። ፺፰ ፤ ዘፍ ፡ ፴፫ ÷ ፴፭ ። ፺፱ ፤ ዘፍ ፡ ፴፬ ÷ ፭ ። ፻ ፤ ዘፍ ፡ ፴፬ ÷ ፲፭ ። ፻፩ ፤ ዘፍ ፡ ፴፬ ÷ ፳፭ ። ፻፪ ፤ ዘፍ ፡ ፴፬ ÷ ፴፭ ። ፻፫ ፤ ዘፍ ፡ ፴፭ ÷ ፭ ። ፻፬ ፤ ዘፍ ፡ ፴፭ ÷ ፲፭ ። ፻፭ ፤ ዘፍ ፡ ፴፭ ÷ ፳፭ ። ፻፮ ፤ ዘፍ ፡ ፴፭ ÷ ፴፭ ። ፻፯ ፤ ዘፍ ፡ ፴፮ ÷ ፭ ። ፻፰ ፤ ዘፍ ፡ ፴፮ ÷ ፲፭ ። ፻፱ ፤ ዘፍ ፡ ፴፮ ÷ ፳፭ ። ፻፲ ፤ ዘፍ ፡ ፴፮ ÷ ፴፭ ። ፻፲፩ ፤ ዘፍ ፡ ፴፯ ÷ ፭ ። ፻፲፪ ፤ ዘፍ ፡ ፴፯ ÷ ፲፭ ። ፻፲፫ ፤ ዘፍ ፡ ፴፯ ÷ ፳፭ ። ፻፲፬ ፤ ዘፍ ፡ ፴፯ ÷ ፴፭ ። ፻፲፭ ፤ ዘፍ ፡ ፴፰ ÷ ፭ ። ፻፲፮ ፤ ዘፍ ፡ ፴፰ ÷ ፲፭ ። ፻፲፯ ፤ ዘፍ ፡ ፴፰ ÷ ፳፭ ። ፻፲፰ ፤ ዘፍ ፡ ፴፰ ÷ ፴፭ ። ፻፲፱ ፤ ዘፍ ፡ ፴፱ ÷ ፭ ። ፻፳ ፤ ዘፍ ፡ ፴፱ ÷ ፲፭ ። ፻፳፩ ፤ ዘፍ ፡ ፴፱ ÷ ፳፭ ። ፻፳፪ ፤ ዘፍ ፡ ፴፱ ÷ ፴፭ ። ፻፳፫ ፤ ዘፍ ፡ ፵ ÷ ፭ ። ፻፳፬ ፤ ዘፍ ፡ ፵ ÷ ፲፭ ። ፻፳፭ ፤ ዘፍ ፡ ፵ ÷ ፳፭ ። ፻፳፮ ፤ ዘፍ ፡ ፵ ÷ ፴፭ ። ፻፳፯ ፤ ዘፍ ፡ ፵፩ ÷ ፭ ። ፻፳፰ ፤ ዘፍ ፡ ፵፩ ÷ ፲፭ ። ፻፳፱ ፤ ዘፍ ፡ ፵፩ ÷ ፳፭ ። ፻፴ ፤ ዘፍ ፡ ፵፩ ÷ ፴፭ ። ፻፴፩ ፤ ዘፍ ፡ ፵፪ ÷ ፭ ። ፻፴፪ ፤ ዘፍ ፡ ፵፪ ÷ ፲፭ ። ፻፴፫ ፤ ዘፍ ፡ ፵፪ ÷ ፳፭ ። ፻፴፬ ፤ ዘፍ ፡ ፵፪ ÷ ፴፭ ። ፻፴፭ ፤ ዘፍ ፡ ፵፫ ÷ ፭ ። ፻፴፮ ፤ ዘፍ ፡ ፵፫ ÷ ፲፭ ። ፻፴፯ ፤ ዘፍ ፡ ፵፫ ÷ ፳፭ ። ፻፴፰ ፤ ዘፍ ፡ ፵፫ ÷ ፴፭ ። ፻፴፱ ፤ ዘፍ ፡ ፵፬ ÷ ፭ ። ፻፵ ፤ ዘፍ ፡ ፵፬ ÷ ፲፭ ። ፻፵፩ ፤ ዘፍ ፡ ፵፬ ÷ ፳፭ ። ፻፵፪ ፤ ዘፍ ፡ ፵፬ ÷ ፴፭ ። ፻፵፫ ፤ ዘፍ ፡ ፵፭ ÷ ፭ ። ፻፵፬ ፤ ዘፍ ፡ ፵፭ ÷ ፲፭ ። ፻፵፭ ፤ ዘፍ ፡ ፵፭ ÷ ፳፭ ። ፻፵፮ ፤ ዘፍ ፡ ፵፭ ÷ ፴፭ ። ፻፵፯ ፤ ዘፍ ፡ ፵፮ ÷ ፭ ። ፻፵፰ ፤ ዘፍ ፡ ፵፮ ÷ ፲፭ ። ፻፵፱ ፤ ዘፍ ፡ ፵፮ ÷ ፳፭ ። ፻፶ ፤ ዘፍ ፡ ፵፮ ÷ ፴፭ ። ፻፶፩ ፤ ዘፍ ፡ ፵፯ ÷ ፭ ። ፻፶፪ ፤ ዘፍ ፡ ፵፯ ÷ ፲፭ ። ፻፶፫ ፤ ዘፍ ፡ ፵፯ ÷ ፳፭ ። ፻፶፬ ፤ ዘፍ ፡ ፵፯ ÷ ፴፭ ። ፻፶፭ ፤ ዘፍ ፡ ፵፰ ÷ ፭ ። ፻፶፮ ፤ ዘፍ ፡ ፵፰ ÷ ፲፭ ። ፻፶፯ ፤ ዘፍ ፡ ፵፰ ÷ ፳፭ ። ፻፶፰ ፤ ዘፍ ፡ ፵፰ ÷ ፴፭ ። ፻፶፱ ፤ ዘፍ ፡ ፵፱ ÷ ፭ ። ፻፷ ፤ ዘፍ ፡ ፵፱ ÷ ፲፭ ። ፻፷፩ ፤ ዘፍ ፡ ፵፱ ÷ ፳፭ ። ፻፷፪ ፤ ዘፍ ፡ ፵፱ ÷ ፴፭ ። ፻፷፫ ፤ ዘፍ ፡ ፶ ÷ ፭ ። ፻፷፬ ፤ ዘፍ ፡ ፶ ÷ ፲፭ ። ፻፷፭ ፤ ዘፍ ፡ ፶ ÷ ፳፭ ። ፻፷፮ ፤ ዘፍ ፡ ፶ ÷ ፴፭ ።

ምዕራፍ ፡ ፱ ።

፩ ሳውል ፡ ግን ፡ የጌታን ፡ ደቀ ፡ መዝሙርት ፡ እንዲገድላቸው ፡ ገና ፡ እየዛተ ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ካህ
፪ ናት ፡ ሄደ ፥ በዚህ ፡ መንገድ ፡ ያሉትንም ፡ ሰዎች ፡ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ቢያገኝ ÷ እያሰረ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ያመጣቸው ፡ ዘንድ ፡ በደ
፫ ማስቆ ፡ ላሉት ፡ ምኵራቦች ፡ ደብዳቤ ፡ ከእርሱ ፡ ለመነ ። ሲሄድም ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ድንገት ፡ በእርሱ ፡ ዙሪያ ፡ ከሰማይ ፡ ብር
፬ ሃን ፡ አንጸባረቀ ፤ በምድርም ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ ሰለ ፡— ሳውል ፡ ሳውል ÷ ስለ ፡ ምን ፡ ታሳድደኛ
፭ ለህ ? የሚለውን ፡ ድምፅ ፡ ሰማ ። ጌታ ፡ ሆይ ÷ ማን ፡ ነህ ? አለው ። እርሱም ፡— አንተ ፡ የም ታሳድደኛ ፡ እኔ ፡ ኢየሱስ ፡ ነኝ ፤ የመውጊያ
፮ ውን ፡ ብረት ፡ ብትቃወም ፡ ለአንተ ፡ ይብስብ ሃል ፡ አለው ። እየተንቀጠቀጠና ፡ እየተደነቀ ፡— ጌታ ፡ ሆይ ÷ ምን ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፡ ትወዳለህ ?
፯ አለው ። ጌታም ፡— ተነሥተህ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ግባና ፡ ታደርገው ፡ ዘንድ ፡ የሚያስፈልግህን ፡ ይነግሩሃል ፡ አለው ። ከእርሱም ፡ ጋር ፡ በመን
፰ ገድ ፡ የሄዱ ፡ ሰዎች ፡ ድምፁን ፡ እየሰሙ ፡ ማንን ፡ ግን ፡ ሳያዩ ፡ እንደ ፡ ዲዳዎች ፡ ቆሙ ። ሳውልም ፡ ከምድር ፡ ተነሣ ÷ ዓይኖቹም ፡ በተከፈቱ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ አላየም ፤ እጁንም ፡ ይዘው ፡ እየመሩ ፡
፱ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ አገቡት ። ሳያይም ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ኖረ ፤ አልበላምም ፡ አልጠጣምም ።

፲ በደማስቆም ፡ ሐናንያ ፡ የሚሉት ፡ አንድ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ነበረ ÷ ጌታም ፡ በራእይ ፡— ሐናንያ ፡ ሆይ ÷ አለው ። እርሱም ፡— ጌታ ፡ ሆይ ÷ እነ
፲፩ ሆኝ ፡ አለ ። ጌታም ፡— ተነሥተህ ፡ ቀን ፡ ወደ ሚባለው ፡ መንገድ ፡ ሂድ ÷ በይሁዳ ፡ ቤትም ፡ ሳውል ፡ የሚሉትን ፡ አንድ ፡ የጠርሴስ ፡ ሰው ፡
፲፪ ፈልግ ፤ እነሆ ÷ እርሱ ፡ ይጸልያልና ፤ ሐናንያ ፡ የሚሉትም ፡ ሰው ፡ ገብቶ ፡ ደግሞ ፡ እንዲያይ ፡
፲፫ እጁን ፡ ሲጭንበት ፡ አይቶአል ፡ አለው ። ሐና ንያም ፡ መልሶ ፡— ጌታ ፡ ሆይ ÷ በኢየሩሳሌም ፡ በቅዱሳንህ ፡ ላይ ፡ ስንት ፡ ክፉ ፡ እንዳደረገ ፡ ስለ
፲፬ ዚህ ፡ ሰው ፡ ከብዙዎች ፡ ሰምቼአለሁ ፤ በዚህም ፡ ስምህን ፡ የሚጠሩትን ፡ ሁሉ ፡ ለማሰር ፡ ከካ ህናት ፡ አለቆች ፡ ሥልጣን ፡ አለው ፡ አለ ።
፲፭ ጌታም ፡— ይህ ፡ በእሕዛብም ፡ በነገሥታትም ፡ በእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ስሜን ፡ ይሸከም ፡ ዘንድ ፡ ለእኔ ፡ የተመረጠ ፡ ዕቃ ፡ ነውና ፡ ሂድ ፤
፲፮ ስለ ፡ ስሜ ፡ ስንት ፡ መከራ ፡ ሊቀበል ፡ እንዲያ ስፈልገው ፡ እኔ ፡ አመለክተዋለሁና ፡ አለው ።
፲፯ ሐናንያም ፡ ሄዶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ገባ ÷ እጁንም ፡ ጭኖበት ፡— ወንድሜ ፡ ሳውል ፡ ሆይ ÷ ጌታ ÷ እርሱም ፡ በመጣህበት ፡ መንገድ ፡ የታየህ ፡ ኢየ ሱስ ፡ ነው ÷ ደግሞ ፡ ታይ ፡ ዘንድና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይሞላብህ ፡ ዘንድ ፡ ላከኝ ፡ አለ ። ወዲ
፲፰ ያውም ፡ እንደ ፡ ቅርፊት ፡ ያለ ፡ ከዓይኑ ፡ ወደቀ ÷ ያን ፡ ጊዜም ፡ ደግሞ ፡ አየ ፤ ተነሥቶም ፡ ተጠ
፲፱ መቀ ÷ መብልም ፡ በልቶ ፡ በረታ ።

በደማስቆም ፡ ካሉት ፡ ደቀ ፡ መዝሙርት ፡ ጋር ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ኖረ ። ወዲያውም ፡ ስለ ፡ ኢየ
፳ ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እርሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በምኵራቦቹ ፡ ሰበከ ። የሰሙትም ፡
፳፩ ሁሉ ፡ ተገረሙና ፡— ይህ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ይህን ፡ ስም ፡ የሚጠሩትን ፡ ያጠፋ ፡ አይደለምን ? ስለ ዚህስ ፡ ታስረው ፡ ወደ ፡ ካህናት ፡ አለቆች ፡ ይወ ስዳቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደዚህ ፡ አልመጣምን ? አሉ ።
፳፪ ሳውል ፡ ግን ፡ እየበረታ ፡ ሄደ ÷ በደማስቆም ፡ ለተቀመጡት ፡ አይሁድ ፡ ይህ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስረድቶ ፡ መልስ ፡ ያሰጣቸው ፡ ነበር ።

ብዙ ፡ ቀንም ፡ ሲሞላ ፡ አይሁድ ፡ ሊገድሉት ፡
፳፫ ተማከሩ ፤ ሳውል ፡ ግን ፡ አሳባቸውን ፡ አወቀ ።
፳፬ ይገድሉትም ፡ ዘንድ ፡ በሌሊትና ፡ በቀን ፡ የከተ ማይቱን ፡ በር ፡ ሁሉ ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ። ደቀ ፡
፳፭ መዝሙርት ፡ ግን ፡ በሌሊት ፡ ወስደው ፡ በቅጥር ፡ ላይ ፡ አሳልፈው ፡ በቅርጫት ፡ አወረዱት ።

ሳውልም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡
፳፮ ከደቀ ፡ መዝሙርት ፡ ጋር ፡ ይተባበር ፡ ዘንድ ፡ ሞከረ ። ሁሉም ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስላላመኑ ፡ ፈሩት ። በርናባስ ፡ ግን ፡ ወስዶ ፡ ወደ ፡ ሐዋርያት ፡ አገባውና ፡ ጌታን ፡ በመንገድ ፡ እንዴት ፡ እንዳየውና ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ በደማ ስቆም ፡ በኢየሱስ ፡ ስም ፡ ደፍሮ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ነገረ ፡ ተረከላቸው ። በጌታም ፡ በኢየሱስ ፡ ስም ፡
፳፰ ደፍሮ ፡ እየተናገረ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሲወጣና ፡ ሲገባ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ነበረ ። ከግሪክ ፡ አገርም ፡
፳፱ መጥተው ፡ ከነበሩት ፡ አይሁድ ፡ ጋር ፡ ይነጋገ ርና ፡ ይከራከር ፡ ነበር ። እነርሱ ፡ ግን ፡ ሊገድ ሉት ፡ ፈለጉ ። ወንድሞችም ፡ ይህን ፡ ባወቁ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ ወሰዱት ፡ ወደ ፡ ጠርሴ ስም ፡ ሰደዱት ።

በይሁዳም ፡ ሁሉና ፡ በገሊላ ፡ በሰማርያም ፡
፴፩ የነበሩት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በሰላም ፡ ኖሩ ፡ ታነጹም ። በእግዚአብሔርም ፡ ፍርሃ ትና ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መጽናናት ፡ እየሄዱ ፡ ይበዙ ፡ ነበር ።

፴፪ ጴጥሮስም ፡ በየስፍራው ፡ ሁሉ ፡ ሲዘር ፡ በልዳ ፡
፴፫ ወደሚኖሩ ፡ ቅዱሳን ፡ ደግሞ ፡ ወረደ ። በዚያም ፡ ከስምንት ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ በአልጋ ፡ ላይ ፡ ተኝቶ ፡ የነበረው ፡ ኤንያ ፡ የሚሉትን ፡ አንድ ፡
፴፬ ሰው ፡ አገኘ ። እርሱም ፡ ሽባ ፡ ነበረ ። ጴጥሮ ስም ፡— ኤንያ ፡ ሆይ ÷ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይፈ ውስሃል ፤ ተነሣ ፡ ለራስህም ፡ አንጥፍ ፡ አለው ።
፴፭ ወዲያውም ፡ ተነሣ ። በልዳና ፡ በሰሮናም ፡ የሚ ኖሩ ፡ ሁሉ ፡ እርሱን ፡ አይተው ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ ዘወር ፡ አሉ ።

በኢዮጴም ፡ ጣቢታ ፡ የሚሉአት ፡ አንዲት ፡
፴፮ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ነበረች ÷ ትርጓሜውም ፡ ዶርቃ ፡ ማለት ፡ ነው ። እርስዋም ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ የሞ ላባት ፡ ምጽዋትም ፡ የምታደርግ ፡ ነበረች ።
፴፯ በዚያም ፡ ወራት ፡ ታመመችና ፡ ሞተች ። አጥበ ውም ፡ በሰገነት ፡ አኖሩአት ። ልዳም ፡ ለኢዮጴ ፡ ቅርብ ፡ ናትና ፡ ደቀ ፡ መዝሙርት ፡ ጴጥሮስ ፡ በዚያ ፡ እንዳለ ፡ ሰምተው ÷ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ከመ
፴፰ ጣት ፡ እንዳይዘገይ ፡ እየለመኑ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ላኩ ። ጴጥሮስም ፡ ተነሥቶ ፡ ከእ ነርሱ ፡ ጋር ፡ መጣ ። በደረሰም ፡ ጊዜ ፡ በሰገነት ፡ አወጡት ። መበለቶችም ፡ ሁሉ ፡ እያለቀሱ ፡
፴፱ ዶርቃ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ሰለች ፡ ያደረገቻቸ ውን ፡ ቀሚሶችንና ፡ ልብሶችን ፡ ሁሉ ፡ እያሳዩት ፡ በፊቱ ፡ ቆሙ ። ጴጥሮስም ፡ ሁሉን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አስወጥቶ ፡ ተንበርክኩም ፡ ጸለየ ÷ ወደ ፡ ሬሳ ውም ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡— ጣቢታ ፡ ሆይ ÷ ተነሺ ፡ አላት ። እርስዋም ፡ ዓይኖችዋን ፡ ከፈተች ፡ ጴጥ
፵ ሮስንም ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ተቀመጠች ። እጁንም ፡ ለእርስዋ ፡ ሰጥቶ ፡ አስነሣት ፤ ቅዱሳንንና ፡ መበ ለቶችንም ፡ ጠራ ፡ ሕያውም ፡ ሆና ፡ በፊታቸው ፡
፵፩ አቆማት ። ይህም ፡ በኢዮጴ ፡ ሁሉ ፡ የታወቀ ፡
፵፪ ሆነ ÷ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ በጌታ ፡ አመኑ ። በኢዮ ጴም ፡ ስምዖን ፡ ከሚሉት ፡ ከአንድ ፡ ቀላዊስ ፡ ፋቂ ፡ ጋር ፡ አያሌ ፡ ቀን ፡ ኖረ ።

ምዕራፍ ፡ ፲ ።

፩ በቂሣርያም ፡ ኢጣሊቂ ፡ ለሚሉት ፡ ጭፍራ ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ የሆነ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ የሚሉት ፡
፪ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ። እርሱም ፡ ከቤተ ፡ ሰዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያመልክና ፡ የሚፈራ ፡ ለሕዝብም ፡ እጅግ ፡ ምጽዋት ፡ የሚ
፫ ያደርግ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሁልጊዜ ፡ የሚጸልይ ፡ ነበረ ። ከቀኑም ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡— ቆርኔሌዎስ ፡ ሆይ ፡ የሚለው ፡ የእግ ዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ሲገባ ፡ በራ
፬ እይ ፡ በግልጥ ፡ አየው ። እርሱም ፡ ትኵር ፡ ብሎ ፡ ሲመለከተው ፡ ደንግጦ ፡— ጌታ ፡ ሆይ ÷ ምንድር ፡ ነው ? አለ ። መልአኩም ፡ አለው ፡— ጸሎትህና ፡ ምጽዋትህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡
፭ ለመታሰቢያ ፡ እንዲሆን ፡ ወረገ ። አሁንም ፡ ወደ ፡ ኢዮጴ ፡ ሰዎችን ፡ ልከህ ፡ ጴጥሮስ ፡ የሚ
፮ ባለውን ፡ ስምዖንን ፡ አስመጣ ። እርሱ ፡ ቤቱ ፡ በባሕር ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ በቍርበት ፡ ፋቂው ፡ በስምዖን ፡ ዘንድ ፡ እንግድነት ፡ ተቀምጦአል ።
፯ ልታደርገው ፡ የሚገባህን ፡ እርሱ ፡ ይነግርሃል ። የተናገረውም ፡ መልአክ ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ÷ ከሎሌ
፰ ዎቹ ፡ ሁለቱን ÷ ከማይለዩትም ፡ ጭፍሮቹ ፡ እግ ዚአብሔርን ፡ የሚያመልክ ፡ አንዱን ፡ ወታደር ፡
፱ ጠርቶ ÷ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ ተረክላቸው ፡ ወደ ፡ ኢዮጴም ፡ ላካቸው ።

እነርሱም ፡ በነገው ፡ ሲሄዱ ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡
፲ ሲቀርቡ ÷ ጴጥሮስ ፡ በስድስት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ይጸልይ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ጣራው ፡ ወጣ ። ተር ቦም ፡ ሊበላ ፡ ወደደ ። ሲያዘጋጁለት ፡ ሳሉም ፡
፲፩ ተመስጦ ፡ መጣበት ። ሰማይም ፡ ተከፍቶ ፡ በአ ራት ፡ ማዕዘን ፡ የተያዘ ፡ ታላቅ ፡ ሸማ ፡ የሚመ ስል ፡ ዕቃ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ሲወርድ ፡ አየ ። በዚ
፲፪ ያውም ፡ አራት ፡ እግር ፡ ያላቸው ፡ ሁሉ ፡ አራ ዊትም ፡ በምድርም ፡ የሚንቀሳቀሱት ፡ የሰማይ ፡ ወፎችም ፡ ነበሩበት ። ጴጥሮስ ፡ ሆይ ÷ ተን
፲፫ ሣና ፡ አርደህ ፡ ብላ ፡ የሚልም ፡ ድምፅ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ መጣ ። ጴጥሮስ ፡ ግን ፡— ጌታ ፡ ሆይ ÷
፲፬ አይሆንም ፤ እንዳች ፡ ርኵስ ፡ የሚያስጸይፍም ፡ ከቶ ፡ በልቼ ፡ አላውቅምና ፡ አለ ። ደግሞም ፡
፲፭ ሁለተኛ ፡— እግዚአብሔር ፡ ያነጻውን ፡ አንተ ፡ አታርክሰው ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ መጣ ። ይህም ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ሆነ ÷ ወዲያውም ፡
፲፮ ዕቃው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ተወሰደ ።

ጴጥሮስም ፡ ስላየው ፡ ራእይ ፡— ምን ፡ ይሆን ?
፲፯ ብሎ ፡ በልቡ ፡ ሲያመነታ ÷ እነሆ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ የላካቸው ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ስምዖን ፡ ቤት ፡ ጠይ ቀው ፡ ወደ ፡ ደጁ ፡ ቀረቡ ፤ ድምፃቸውንም ፡
፲፰ ከፍ ፡ አድርገው ፡— ጴጥሮስ ፡ የተባለው ፡ ስም ፖን ፡ በዚህ ፡ እንግድነት ፡ ተቀምጦአልን ? ብለው ፡ ይጠይቁ ፡ ነበር ። ጴጥሮስም ፡ ስለ ፡ ራእዩ ፡ ሲያ
፲፱ ወጣ ፡ ሲያወርድ ፡ ሳለ ÷ መንፈስ ፡— እነሆ ÷ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ይፈልጉሃል ፤ ተነሥተህ ፡
፳ ውረድ ÷ እኔም ፡ ልኬአቸዋለሁና ፡ ሳትጠራ ጠር ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ሂድ ፡ አለው ። ጴጥሮ
፳፩ ስም ፡ ወደ ፡ ሰዎቹ ፡ ወርዶ ፡— እነሆ ÷ የምትፈ ልጉኝ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ የመጣችሁበትስ ፡ ምክን ያት ፡ ምንድር ፡ ነው ? አላቸው ። እነርሱም ፡—
፳፪ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔርንም ፡ የሚፈራ ፡ በአይሁድም ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ የተመሰከረለት ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ያስመ ጣህ ፡ ዘንድ ፡ ከአንተም ፡ ቃልን ፡ ይሰማ ፡ ዘንድ ፡ ከቅዱስ ፡ መልአክ ፡ ተረዳ ፡ አሉት ። እርሱም ፡
፳፫ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ጠርቶ ፡ እንግድነት ፡ ተቀበላ ቸው ።

በነገውም ፡ ተነሥቶ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ወጣ ÷
፳፬ በኢዮጴም ፡ ከነበሩት ፡ ወንድሞች ፡ አንዳንዶቹ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ ሄዱ ። በነገውም ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ ገቡ ። ቆርኔሌዎስም ፡ ዘመዶቹ
፳፭ ንና ፡ የቅርብ ፡ ወዳጆቹን ፡ በአንድነት ፡ ጠርቶ ፡ ይጠባበቃቸው ፡ ነበር ። ጴጥሮስም ፡ በገባ ፡
፳፮ ጊዜ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ተገናኝቶ ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ ወደቀና ፡ ሰገደለት ። ጴጥሮስ ፡ ግን ፡— ተነሣ ፤
፳፯ እኔ ፡ ራሴ ፡ ደግሞ ፡ ሰው ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ አስነሣው ። ከእርሱም ፡ ጋር ፡ እየተነጋገረ ፡ ገባ ÷ ብዙዎችም ፡
፳፰ ተከማችተው ፡ አግኝቶ ፡— አይሁዳዊ ፡ ሰው ፡ ከሌላ ፡ ወገን ፡ ጋር ፡ ይተባበር ፡ ወይም ፡ ይቃ ረብ ፡ ዘንድ ፡ እንዳልተፈቀደ ፡ እናንተ ፡ ታው ቃላችሁ ፤ ለእኔ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ማንንም ፡ ሰው ፡ ርኵስና ፡ የሚያስጸይፍ ፡ ነው ፡ እንዳልል ፡ አሳየኝ ። ስለዚህም ፡ ደግሞ ፡ ብትጠሩኝ ፡ ሳል
፳፱

፱ ። ፩—፲፱ ፤ ም. ፳፪÷፩—፲፮ ። ፳፮ ፡ ፱÷፲፮ ። ፩ ፡ ም. ፭÷፫ ። ፲፮ ፤ ፱ ቆሮ. ፲፭÷ ፳፫—፳፯ ። ፲፱ ፤ ገላ. ፩÷፲፰—፲፯ ። ፳፫ ፤ ገላ. ፩÷ ፲፰ ። ፳፬ ፡ ፳፭ ፤ ፱ ቆሮ. ፲፩÷ ፴፪ ፡ ፴፫ ። ፳፯ ፤ ም. ፱÷ ፴፭ ።

፲ ። ፩ ፡ ማቴ. ፱÷ ፳፭ ። ፱ ፤ ዮሐ. ፲፩÷ ፵፭ ።

፲ ። ፩ ፤ ም. ፭÷ ፲፱ ። ፯ ፤ ም. ፱÷ ፵፫ ። ፲፱ ፤ ዘሌዋ. ፲፭÷ ፱—፵፯ ። ፲፭ ፤ ማቴ. ፲፭÷ ፲፭ ። ፲፱ ፤ ም. ፭÷ ፳፱ ። ፳፭ ፤ ዮሐ. ፱÷ ፱ ፤ ፲፭ ÷ ፳፭ ።

ከራከር ፡ መጣው ። አሁንም ፡ በምን ፡ ምክን
ያት ፡ አስመጣችሁኝ ? ብዬ ፡ እጠይቃችኋለሁ ፡
አላቸው ።

፴፡ ቆርኔሌዎስም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡— በዚች ፡
ሰዓት ፡ የዛሬ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ የዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡
ጸሎት ፡ በቤቴ ፡ እጸልይ ፡ ነበር ፤ እነሆም ÷
የሚያንጸባርቅ ፡ ልብስ ፡ የለበሰ ፡ ሰው ፡ በፊቴ ፡
፴፩፡ ቆመና ፡— ቆርኔሌዎስ ፡ ሆይ ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ ጸሎትህ ፡ ተሰማ ፡ ምጽዋትህም ፡ ታሰበ ።
፴፪፡ እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ኢዮጴ ፡ ልከህ ፡ ጴጥሮስ ፡ የተ
ባለውን ፡ ስምዖንን ፡ አስጠራ ፤ እርሱ ፡ በቀ·ር
በት ፡ ፋቂው ፡ በስምዖን ፡ ቤት ፡ በባሕር ፡ አጠ
፴፫፡ ገብ ፡ እንግድነት ፡ ተቀምጦአል ፡ አለኝ ። ስለ
ዚህ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ላክሁ ÷ አንተም ፡
በመምጣትህ ፡ መልካም ፡ አድርገሃል ። እንግ
ዲህ ፡ አንተ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የታዘዝ
ኸውን ፡ ሁሉ ፡ እንድንሰማ ፡ እኛ ፡ ሁላችን ፡
አሁን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በዚህ ፡ አለን ።
፴፬፡፴፮፡ ጴጥሮስም ፡ አፉን ፡ ከፍቶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡—
እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ ፊት ፡ እንዳያደላ ፡ ነገር ፡
ግን ፡ በአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ እርሱን ፡ የሚፈራና ፡
ጽድቅን ፡ የሚያደርግ ፡ በእርሱ ፡ የተወደደ ፡
፴፯፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በእውነት ፡ አስተዋልሁ ። የሁሉ ፡
ጌታ ፡ በሚሆን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰላምን ፡
እየሰበከ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ ልጆች ፡
፴፰፡ ላከ ። ዮሐንስ ፡ ከሰበከው ፡ ጥምቀት ፡ በኋላ ፡
ከገሊላ ፡ ጀምሮ ፡ በይሁዳ ፡ ሁሉ ፡ የሆነውን ፡
፴፱፡ ነገር ፡ እናንተ ፡ ታውቃላችሁ ። እግዚአብሔር ፡
የናዝሬቱን ፡ ኢየሱስን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በኃ
ይልም ፡ ቀባው ÷ እርሱም ፡ መልካም ፡ እያደረገ ፡
ለዲያብሎስም ፡ የተገዙትን ፡ ሁሉ ፡ እየፈወሰ ፡
ዞረ ÷ እግዚአብሔር ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ነበረና ፤
፵፡ እኛም ፡ በአይሁድ ፡ አገርና ፡ በኢየሩሳሌም ፡
በደረጉው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ምስክሮች ፡ ነን ፤ እር
ሱንም ፡ በእንጨት ፡ ላይ ፡ ሰቅለው ፡ ገደሉት ።
፵፩፡ እርሱን ፡ እግዚአብሔር ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡
አስነሣው ፡ ይገለጥም ፡ ዘንድ ፡ ሰጠው ፤ ይኸ
ውም ፡ ለሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ አይደለም ፡ ነገር ፡ ግን ፡
በእግዚአብሔር ፡ አስቀድሞ ፡ የተመረጡ ፡ ምስ
ክሮች ፡ ለሆንን ፡ ለእኛ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ከሙታ
ንም ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የበላን ፡
፵፪፡ የጠጣንም ፡ እኛ ፡ ነን ። ለሕዝብም ፡ እንድንሰ
ብክና ፡ በሕያዋንና ፡ በሙታን ፡ ሊፈርድ ፡ በእ
ግዚአብሔር ፡ የተወሰነ ፡ እርሱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
፵፫፡ እንመሰክር ፡ ዘንድ ፡ አዘዘን ። በእርሱ ፡ የሚያ
ምን ፡ ሁሉ ፡ በስሙ ፡ የኃጢአቱን ፡ ስርየት ፡
እንዲቀበል ፡ ነቢያት ፡ ሁሉ ፡ ይመሰክሩለታል ።
፵፬፡ ጴጥሮስ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ገና ፡ ሲናገር ፡ ቃሉን ፡
በሰሙት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወረደ ።
፵፭፡ ከጴጥሮስም ፡ ጋር ፡ የመጡት ፡ ሁሉ ፡ ከተገረ
ዙት ፡ ወገን ፡ የሆኑ ፡ ምዕመናን ፡ በአሕዛብ ፡
ላይ ፡ ደግሞ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስጦታ ፡ ስለ ፡
፵፮፡ ፈሰሰ ፡ ተገረሙ ። በልሳኖች ፡ ሲናገሩ ፡ እግዚ
አብሔርንም ፡ ሲያከብሩ ፡ ሰምተዋቸዋልና ።
፵፯፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጴጥሮስ ፡ መልሶ ፡— እነዚህ ፡
እንደ ፡ እኛ ፡ ደግሞ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ የተ
ቀበሉ ፡ እንዳይጠመቁ ፡ ውኃን ፡ ይከለክላቸው ፡
ዘንድ ፡ የሚችል ፡ ማን ፡ ነው ? አለ ። በኢየ
፵፰፡ ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስምም ፡ ይጠመቁ ፡ ዘንድ ፡ አዘ
ዛቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ እንዲቀ
መጥ ፡ ለመኑት ።

ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

፩፡ ሐዋርያትና ፡ በይሁዳም ፡ የነበሩት ፡ ወንድ
ሞች ፡ አሕዛብ ፡ ደግሞ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡
እንደ ፡ ተቀበሉ ፡ ሰሙ ። ጴጥሮስም ፡ ወደ ፡ ኢየ
፪፡ ሩሳሌም ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ከተገረዙት ፡ ወገን ፡ የሆ
ኑት ፡ ሰዎች ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ተከራከረው ፡—
፫፡ ወዳልተገረዙ ፡ ሰዎች ፡ ገብተህ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡
፬፡ በላህ ፡ አሉት ። ጴጥሮስ ፡ ግን ፡ ከመጀመሪያው ፡
ጀምሮ ፡ በተራ ፡ ገለጠላቸው ፡ እንዲህም ፡ አለ ፡—
፭፡ እኔ ፡ በኢ·ጴ ፡ ከተማ ፡ ስጸልይ ፡ ሰለሙ ፡ ተመ
ስጩ ፡ ራእይን ፡ አየሁ ፤ ታላቅ ፡ ሸማ ፡ የመሰለ ፡
፮፡ ዕቃ ፡ በአራት ፡ ማዕዘን ፡ ተይዞ ፡ ከሰማይ ፡ ወረ
፯፡ ደና ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጣ ፤ ይህንም ፡ ትኵር ፡ ብዬ ፡
፰፡ ስመለከት ፡ አራት ፡ እግር ፡ ያላቸውን ፡ የምድር ፡
እንስሶች ፡ አራዊትንም ፡ ተንቀሳቃሾችንም ፡
የሰማይ ፡ ወፎችንም ፡ አየሁ ። ጴጥሮስ ፡ ሆይ ÷
፱፡ ተነሣና ፡ አርደህ ፡ ብላ ፡ የሚለኝንም ፡ ድምፅ ፡
፲፡ ሰማሁ ። እኔም ፡— ጌታ ፡ ሆይ ÷ አይሆንም ፤
ርኵስ ፡ ወይም ፡ የሚያስጸይፍ ፡ ከቶ ፡ ወደ ፡
፲፩፡ አፌ ፡ ገብቶ ፡ አያውቅምና ፡ አልሁ ። ሁለተ
ኛም ፡— እግዚአብሔር ፡ ያነጻውን ፡ አንተ ፡ አታ
ርክሰው ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ከሰማይ ፡ መለሰልኝ ።
፲፪፡ ይህም ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ሆነ ፤ እንደ ፡ ገና ፡ ሁሉ ፡
፲፫፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ተሳበ ። እነሆም ÷ ያን ፡ ጊዜ ፡
ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ከቂሣርያ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ተልከው ፡
፲፬፡ ወዳለሁበት ፡ ቤት ፡ ቀረቡ ። መንፈስም ፡ ሳል
ጠራጠር ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ እሄድ ፡ ዘንድ ፡ ነገ
ረኝ ። እነዚህም ፡ ስድስቱ ፡ ወንድሞች ፡ ደግሞ ፡
ከእኔ ፡ ጋር ፡ መጡ ፡ ወደዚያ ፡ ሰውም ፡ ቤት ፡
፲፭፡ ገባን ። እርሱም ፡ መልአክ ፡ በቤቱ ፡ ቆሞ ፡ እንዳ
የና ፡— ወደ ፡ ኢዮጴ ፡ ሰዎች ፡ ልከህ ፡ ጴጥሮስ ፡
፲፮፡ የተባለውን ፡ ስምዖንን ፡ አስመጣ ፤ እርሱም ፡
አንተና ፡ የቤትህ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የምትድኑበ
ትን ፡ ነገር ፡ ይነግርሃል ፡ እንዳለው ፡ ነገረን ።
፲፯፡ ለመናገርም ፡ በጀመርሁ ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ለእኛ ፡ ደግሞ ፡ በመጀመሪያ ፡ እንደ ፡ ወረደ ፡
፲፰፡ ለእነርሱ ፡ ወረደላቸው ። ዮሐንስ ፡ በውኃ ፡ አጠ
መቀ ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ትጠ
መቃላችሁ ፡ ያለው ፡ የጌታ ፡ ቃል ፡ ትዝ ፡
፲፱፡ አለኝ ። እንግዲህ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጌታ ፡ በኢ

የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ላመነው ፡ ለእኛ ፡ ደግሞ ፡
እንደ ፡ ሰጠን ፡ ያን ፡ ስጦታ ፡ ለእነርሱ ፡ ከሰጠ ÷
እግዚአብሔርን ፡ ለመከልከል ፡ እችል ፡ ዘንድ ፡
፲፯፡ እኔ ፡ ማን ፡ ነበርሁ ? ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜም ፡
ዝም ፡ አሉና ፡— እንኪያስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአ
ሕዛብ ፡ ደግሞ ፡ ለሕይወት ፡ የሚሆን ፡ ንስሐን ፡
ሰጣቸው ፡ እያሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አከበሩ ።
፲፱፡ በእስጢፋኖስም ፡ ላይ ፡ በተደረገው ፡ መከራ ፡
የተበተኑት ፡ እስከ ፡ ፊንቄ ፡ እስከ ፡ ቆጵሮስም ፡
እስከ ፡ አንጾኪያም ፡ ድረስ ፡ ዞሩ ÷ ቃሉንም ፡
ለአይሁድ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ለአንድ ፡ ስንኳ ፡ አይ
፳፡ ናገሩም ፡ ነበር ። ከእነርሱ ፡ ግን ፡ የቆጵሮስና ፡
የቀሬና ፡ ሰዎች ፡ የነበሩት ፡ አንዳንዶቹ ፡ ወደ ፡
አንጾኪያ ፡ መጥተው ፡ የጌታን ፡ የኢየሱስን ፡
ወንጌል ፡ እየሰበኩ ፡ ለግሪክ ፡ ሰዎች ፡ ተናገሩ ።
፳፩፡ የጌታም ፡ እጅ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ነበረ ፤ ቍጥ
ራቸውም ፡ እጅግ ፡ የሚሆን ፡ ሰዎች ፡ አምነው ፡
፳፪፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ ዘወር ፡ አሉ ። ወሬውም ፡ በኢየሩ
ሳሌም ፡ በለችው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለ ፡ እነ
ርሱ ፡ ተሰማ ÷ በርናባስንም ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡
፳፫፡ ላኩት ፤ እርሱም ፡ መጥቶ ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ጸጋ ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አለው ÷ ሁሉንም ፡ በልባ
ቸው ፡ ፈቃድ ፡ በጌታ ፡ ጸንተው ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡
፳፬፡ መከራቸው ፡ ደግ ፡ ሰውና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
እምነትም ፡ የሞላበት ፡ ነበረና ። ብዙ ፡ ሕዝብም ፡
፳፭፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ ተጨመሩ ። በርናባስም ፡ ሳውልን ፡
፳፮፡ ሊፈልግ ፡ ወደ ፡ ጠርሴስ ፡ ወጣ ፤ ባገኘውም ፡
ጊዜ ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ አመጣው ። በቤተ ፡
ክርስቲያንም ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ተሰበ
ሰቡ ÷ ብዙ ፡ ሕዝብንም ፡ አስተማሩ ፤ ደቀ ፡ መዛ
ሙርትም ፡ መጀመሪያ ፡ በአንጾኪያ ፡ ክርስቲ
ያን ፡ ተባሉ ።
፳፯፡ በዚያም ፡ ወራት ፡ ነቢያት ፡ ከኢየሩሳሌም ፡
፳፰፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ወረዱ ። ከእነርሱም ፡ አጋቦስ ፡
የሚሉት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተነሥቶ ፡ በዓለም ፡
ሁሉ ፡ ታላቅ ፡ ራብ ፡ ሊሆን ፡ እንዳለው ፡ በመን
ፈሱ ፡ አመለከተ ፤ ይህም ፡ በቀላውዴዎስ ፡ ቄሣር ፡
፳፱፡ ዘመን ፡ ሆነ ። ደቀ ፡ መዛሙርትም ፡ እያንዳንዳ
ቸው ፡ እንደ ፡ ችሎታቸው ፡ መጠን ፡ አዋጥተው ፡
በይሁዳ ፡ ለሚኖሩት ፡ ወንድሞች ፡ እርዳታን ፡
፴፡ ይልኩ ፡ ዘንድ ፡ ወሰኑ ። እንዲህም ፡ ደግሞ ፡
አደረጉ ÷ በበርናባስና ፡ በሳውልም ፡ እጅ ፡ ወደ ፡
ሽማግሌዎቹ ፡ ሰደዱት ።

ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

፩፡ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ንጉሥ ፡ ሄሮድስ ፡ መከራ ፡
ያጸናባቸው ፡ ዘንድ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ በአ
፪፡ ንዳንዶቹ ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ጫነባቸው ። የዮሐን
ስንም ፡ ወንድም ፡ ያዕቆብን ፡ በሰይፍ ፡ ገደለው ።
፫፡ አይሁድንም ፡ ደስ ፡ እንዳሰኛቸው ፡ አይቶ ፡
ጨምሮ ፡ ጴጥሮስን ፡ ደግሞ ፡ ያዘው ። የቂጣ ፡
በዓልም ፡ ወራት ፡ ነበረ ። በያዘውም ፡ ጊዜ ፡ ፬፡
ወደ ፡ ወኅኒ ፡ አገባው ፤ ከሃ·ሲካም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡
ሕዝብ ፡ ያወጣው ፡ ዘንድ ፡ አስቦ ፡ አያንዳንዱ ፡
አራት ፡ ወታደሮች ፡ ሆነው ፡ እንዲጠብቁት ፡
ለአራት ፡ ጭፍራ ፡ ክፍል ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠው ።
ጴጥሮስም ፡ በወኅኒ ፡ ይጠበቅ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ፭፡
ግን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ ወደ ፡
እግዚአብሔር ፡ ጸሎት ፡ አጥብቆ ፡ ይደረግ ፡
ነበር ።
ሄሮድስም ፡ ሊያወጣው ፡ ባሰበ ፡ ጊዜ ÷ በዚ ፮፡
ያች ፡ ሌሊት ፡ ጴጥሮስ ፡ በሁለት ፡ ሰንሰለት ፡
ታስሮ ፡ ከሁለት ፡ ወታደሮች ፡ መካከል ፡ ተኝቶ ፡
ነበር ፤ ጠባቂዎችም ፡ በደጁ ፡ ፊት ፡ ሆነው ፡
ወኅኒውን ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ። እነሆም ÷ የጌታ ፡ ፯፡
መልአክ ፡ ቀረበ ፡ በቤትም ፡ ውስጥ ፡ ብርሃን ፡
በራ ፤ ጴጥሮስንም ፡ ጎድኑን ፡ መትቶ ፡ አነቃ
ውና ፡— ፈጥነህ ፡ ተነሣ ፡ አለው ። ሰንሰለቶቹም ፡
ከእጁ ፡ ወደቁ ። መልአኩም ፡— ታጠቅና ፡ ፰፡
ጫማህን ፡ አጥበ ፡ አለው ÷ እንዲሁም ፡ አደረገ ።
ልብስህንም ፡ ልበስና ፡ ተከተለኝ ፡ አለው ። ወጥ ፱፡
ቶም ፡ ተከተለው ፤ ራእይንም ፡ የሚያይ ፡ ይመ
ስለው ፡ ነበር ፤ እንጂ ፡ በመልአኩ ፡ የሚደረገው ፡
ነገር ፡ እውነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አላወቀም ። የመ ፲፡
ጀመሪያውንና ፡ የሁለተኛውንም ፡ ዘብ ፡ አል
ፈው ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ወደሚያወጣው ፡ ወደ ፡
ብረቱ ፡ መዝጊያ ፡ ደረሱ ፤ እርሱም ፡ አውቆ ፡
ተከፈተላቸው ፤ ወጥተውም ፡ እንዳት ፡ ስላች ፡
አለፉ ፡ ወዳያውም ፡ መልአኩ ፡ ከእርሱ ፡ ተለየ ።
ጴጥሮስም ፡ ወደ ፡ ልቡ ፡ ተመልሶ ፡— ጌታ ፡ መል ፲፩፡
አኩን ፡ ልኮ ፡ ከሄሮድስ ፡ እጅና ፡ የአይሁድ ፡
ሕዝብ ፡ ይጠብቁት ፡ ከነበረው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡
አዳነኝ ፡ አሁን ፡ በእውነት ፡ አወቅሁ ፡ አለ ።
ብስተዋለም ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ሰዎች ፡ ተከማ ፲፪፡
ችተው ፡ ይጸልዩበት ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡ ማርቆስ ፡
ወደ ፡ ተባለው ፡ ወደ ፡ ዮሐንስ ፡ እናት ፡ ወደ ፡
ማርያም ፡ ቤት ፡ መጣ ። ጴጥሮስም ፡ የደጁን ፡
፲፫፡ መዝጊያ ፡ በንኳኳ ፡ ጊዜ ፡ ሮዴ ፡ የሚሉአት ፡
አንዲት ፡ ገረድ ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ፡ ቀረበች ፤ የጴ
፲፬፡ ጥሮስ ፡ ድምፅ ፡ መሆኑንም ፡ በወቀች ፡ ጊዜ ፡
ከደስታዋ ፡ የተነሣ ፡ ደጁን ፡ አልከፈተችም ÷
ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ሮጣ ፡ ጴጥሮስ ፡ በደጅ ፡
ፊት ፡ ቆሞ ፡ እንዳለ ፡ አወራች ። እነርሱም ፡— ፲፭፡
አብደሽል ፡ አሉአት ። እርስዋ ፡ ግን ፡ እንዲሁ ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ ታስረግጥ ፡ ነበር ። እነርሱም ፡—
መልአኩ ፡ ነው ፡ አሉ ። ጴጥሮስ ፡ ግን ፡ ማንኳ ፲፮፡
ኳቱን ፡ አዘወተረ ፤ ከፍተውም ፡ አዩትና ፡ ተገ
ረሙ ። ግን ፡ ዝም ፡ እንዲሉ ፡ በእጁ ፡ ጠቅሶ ፡ ፲፯፡
ጌታ ፡ ከወኅኒ ፡ እንዲት ፡ እንዳወጣው ፡ ተረከላ
ቸውና ፡— ይህን ፡ ለያዕቆብና ፡ ለወንድሞች ፡
ንገሩ ፡ አላቸው ። ወጥቶም ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡
ሄደ ።

፲፰፤ በነጋም ፡ ጊዜ ፡— ጴጥሮስን ፡ ምን ፡ አግኝቶት ፡
ይሆን ? ብለው ፡ በጭፍሮች ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡
፲፱፤ ሁከት ፡ ሆነ ። ሄሮድስም ፡ አስፈልጎ ፡ ባጣው ፡
ጊዜ ፡ ጠባቂዎችን ፡ መረመረ ፡ ይገድሉአቸውም ፡
ዘንድ ፡ አዘዘ ፤ ከይሁዳም ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡
ወርዶ ፡ በዚያ ፡ ተቀመጠ ።
፳፤ ከጢሮስና ፡ ከሲዶና ፡ ሰዎችም ፡ ጋር ፡ ተጣ
ልቶ ፡ ነበር ፤ በአንድ ፡ ልብ ፡ ሆነውም ፡ ወደ ፡
እርሱ ፡ መጡ ÷ የንጉሥንም ፡ ቢትወደድ ፡ ብላ
ስጦስን ፡ እሺ ፡ አሰኝተው ፡ ዕርቅ ፡ ለመኑ ÷ አገ
ራቸው ፡ ከንጉሥ ፡ አገር ፡ ምግብ ፡ ያገኝ ፡ ነበ
፳፩፤ ርና ። በተቀጠረ ፡ ቀንም ፡ ሄሮድስ ፡ ልብሰ ፡ መን
ግሥቱን ፡ ለብሶ ፡ በዙፋኑ ፡ ተቀመጠ ፡ እነርሱ
፳፪፤ ንም ፡ ተናገራቸው ፤ ሕዝቡም ፡— የእግዚአብ
ሔር ፡ ድምፅ ፡ ነው ፡ የሰውም ፡ አይደለም ፡
፳፫፤ ብለው ፡ ጮኹ ። ለእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡
ስላልሰጠ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የጌታ ፡ መልአክ ፡ መታው ፡
በትልም ፡ ተበልቶ ፡ ሞተ ።
፳፬፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ግን ፡ ያድግና ፡ ይበዛ ፡
ነበር ።
፳፭፤ በርናባስና ፡ ሳውልም ፡ አገልግሎታቸውን ፡
ፈጽመው ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ተመለሱ ÷ ማርቆስ ፡
የተባለውን ፡ ዮሐንስንም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ይዘ
ውት ፡ መጡ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

፩፤ በአንጾኪያም ፡ ባለችው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ነቢያትና ፡ መምህራን ፡ ነበሩ ፤ እነርሱም ፡ በርና
ባስ ÷ ኔጌር ፡ የተባለው ፡ ስምዖንም ÷ የቀሬናው ፡
ሉክዮስም ÷ የአራተኛው ፡ ክፍል ፡ ገዥ ፡ የሄሮ
ድስም ፡ ባለምዋል ፡ ምናሔ ÷ ሳውልም ፡ ነበሩ ።
፪፤ እነዚህም ፡ ጌታን ፡ ሲያመልኩና ፡ ሲጦሙ ፡
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡— በርናባስንና ፡ ሳውልን ፡ ለጠ
፫፤ ራኋቸው ፡ ሥራ ፡ ለዩልኝ ፡ አለ ። በዚያን ፡
ጊዜም ፡ ከጦሙ ፡ ከጸለዩም ፡ እጃቸውንም ፡
ከጫኑ ፡ በኋላ ፡ አሰናበቱአቸው ።
፬፤ እነርሱም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተልከው ፡
ወደ ፡ ሴሌውቅያ ፡ ወረዱ ፤ ከዚያም ፡ በመር
፭፤ ከብ ፡ ወደ ፡ ቆጵሮስ ፡ ሄዱ ። በስልማናም ፡ በነ
በሩ ፡ ጊዜ ፡ በአይሁድ ፡ ምኵራቦች ፡ የእግዚአ
ብሔርን ፡ ቃል ፡ ሰበኩ ፤ አገልጋይም ፡ ዮሐንስ ፡
፮፤ ነበራቸው ። ደሴቲቱንም ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ ጳፉ ፡
በዞሩ ፡ ጊዜ ÷ በርያሱስ ፡ የሚሉትን ፡ ጠንቋይና ፡
ሐሰተኛ ፡ ነቢይ ፡ የሆነውን ፡ አንድ ፡ አይሁዳዊ ፡
፯፤ ሰው ፡ አገኙ ፤ እርሱም ፡ አስተዋይ ፡ ሰው ፡ ከሆ
ነው ፡ ሰርግዮስ ፡ ጳውሎስ ፡ ከሚባለው ፡ አገረ ፡
ገዥ ፡ ጋር ፡ ነበረ ። ይህም ፡ በርናባስንና ፡ ሳው
ልን ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ጠርቶ ፡ የእግዚአብሔርን ፡
፰፤ ቃል ፡ ሊሰማ ፡ ፈለገ ። ጠንቋዩ ፡ ግን ፡ ኤል
ማስ ÷ ስሙ ፡ እንዲሁ ፡ ይተረጐማልና ÷ አገረ ፡
ገዡን ፡ ከማመን ፡ ሊያጣምም ፡ ፈልጎ ፡ ተቃወ
ማቸው ። ጳውሎስ ፡ የተባለው ፡ ሳውል ፡ ግን ፡ ፱፤
መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተሞልቶ ፡ ትኵር ፡ ብሎ ፡
ሲመለከተው ፡— አንተ ፡ ተንኰል ፡ ሁሉ ፡ ክፋ ፲፤
ትም ፡ ሁሉ ፡ የሞላብህ ÷ የዲያብሎስ ፡ ልጅ ÷
የጽድቅም ፡ ሁሉ ፡ ጠላት ÷ የቀናውን ፡ የጌታን ፡
መንገድ ፡ ከማጣመም ፡ አታርፍምን ? አሁንም ÷ ፲፩፤
እነሆ ÷ የጌታ ፡ እጅ ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ ናት ÷ ዕው
ርም ፡ ትሆናለህ ፡ እስከ ፡ ጊዜውም ፡ ፀሐይን ፡
አታይም ፡ አለው ። ያን ፡ ጊዜም ፡ ጭጋግና ፡
ጨለማ ፡ ወደቀበት ÷ በእጁም ፡ የሚመራውን ፡
እየዞረ ፡ ፈለገ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አገረ ፡ ገዡ ፡ ፲፪፤
የተደረገውን ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ ከጌታ ፡ ትምህርት ፡
የተነሣ ፡ ተገርሞ ፡ አመነ ።
ጳውሎስም ፡ ከጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ ከጳፉ ፡ ተነሥቶ ፡ ፲፫፤
የጵንፍልያ ፡ ወደምትሆን ፡ ወደ ፡ ጴርጌን ፡ መጣ ፤
ዮሐንስም ፡ ከእነርሱ ፡ ተለይቶ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳ
ሌም ፡ ተመለሰ ። እነርሱ ፡ ግን ፡ ከጴርጌን ፡ አል ፲፬፤
ፈው ፡ የጲስድያ ፡ ወደምትሆን ፡ ወደ ፡ አንጾ
ኪያ ፡ ደረሱ ፤ በሰንበትም ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ምኵ
ራብ ፡ ገብተው ፡ ተቀመጡ ። ሕግና ፡ ነቢያትም ፡ ፲፭፤
ከተነበቡ ፡ በኋላ ፡ የምኵራቡ ፡ አለቆች ፡— ወን
ድሞች ፡ ሆይ ÷ ሕዝብን ፡ የሚመክር ፡ ቃል ፡
እንዳላችሁ ፡ ተናገሩ ፡ ብለው ፡ ላኩባቸው ።
ጳውሎስም ፡ ተነሥና ፡ በእጁ ፡ ጠቅሶ ፡ እንዲህ ፡ ፲፮፤
አለ ፡—
የእስራኤል ፡ ሰዎችና ፡ እግዚአብሔርን ፡ የም
ትፈሩት ፡ ሆይ ÷ ስሙ ። የዚህ ፡ የእስራኤል ፡ ፲፯፤
ሕዝብ ፡ አምላክ ፡ አባቶቻችንን ፡ መርጠ ፡ በግብፅ ፡
አገር ፡ በእንግድነት ፡ ሳሉ ፡ ሕዝቡን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡
አደረጋቸው ÷ ከፍ ፡ ባለችውም ፡ ክንዱ ፡ ከዚያ ፡
አወጣቸው ። በበረሀም ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ፲፰፤
መገባቸው ። በከነዓንም ፡ አገር ፡ ሰባት ፡ አሕዛ ፲፱፤
ብን ፡ አጥፍቶ ፡ ምድራቸውን ፡ አወረሳቸው ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ነቢዩ ፡ እስከ ፡ ሳሙኤል ፡ ፳፤
ድረስ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡
መሳፍንትን ፡ ሰጣቸው ። ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ፳፩፤
ንጉሥን ፡ ያነግሥላቸው ፡ ዘንድ ፡ ለመኑ ÷ እግ
ዚአብሔርም ፡ ከብንያም ፡ ወገን ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡
የቂስን ፡ ልጅ ፡ ሳኦልን ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ሰጣቸው ፤
እርሱንም ፡ ከሻረው ፡ በኋላ ፡ ዳዊትን ፡ በእነርሱ ፡ ፳፪፤
ላይ ፡ እንዲነግሥ ፡ አስነሣው ÷ ሲመሰክርለ
ትም ፡— እንደ ፡ ልቤ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ፈቃዴንም ፡
ሁሉ ፡ የሚያደርግ ፡ የእሴይን ፡ ልጅ ፡ ዳዊትን ፡
አገኘሁ ፡ አለ ። ከዚህም ፡ ሰው ፡ ዘር ፡ እግዚአ ፳፫፤
ብሔር ፡ እንደ ፡ ተስፋው ፡ ቃል ፡ ለእስራኤል ፡
መድኃኒትን ፡ እርሱም ፡ ኢየሱስን ፡ አመጣ ።
ከመምጣቱ ፡ በፊት ፡ ዮሐንስ ፡ አስቀድሞ ፡ ለእስ ፳፬፤

፲፪። ፳፫፤ ፩ ነገሥ. ፳፭፥፱፤ ፲፭፤ ሕዝ. ፳፰፥፲፯። ፳፫፤ ምዕ. ፳፭፥፲፱። ፳፭፤ ምዕ. ፲፩፥፳፱፤ ፴።
፲፫። ፪፤ ምዕ. ፳፥፳፱። ፫፤ ምዕ. ፮፥፮። ፭፤ ምዕ. ፲፪፥፲፪፤ ፳፭። ፲፤ ሆሴ. ፲፱፥፱፤ ዮሐ. ፰፥፵፬። ፲፭፤ ሉቃ. ፬፥፲፯። ፲፯፤ ዘፀአ. ፮፥፮፤ ፯። ፲፰፤ ዘኍል. ፲፬፥፴፫፤ መዝ. ፺፭፥፱፤ ፲። ፲፱፤ ዘዳግ. ፯፥፩፤ ኢያ. ፲፱፥፩፤ ፱። ፳፤ መሳ. ፪፥፲፯። ፳፩፤ ፩ ሳሙ. ፰፥፭፤ ፲፥፩፤ ፳፩፤ ፳፬። ፳፪፤ ፩ ሳሙ. ፲፭፥፳፫፤ ፲፯፥፩፤ ፲፫፤ ፲፫፥፲፬፤ መዝ. ፹፰፥፳። ፳፫፤ ኢሳ. ፲፩፥፩። ፳፬፤ ማር. ፩፥፬።

ራኤል ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ የንስሐን ፡ ጥምቀት ፡
፳፭፤ ሰብኮ ፡ ነበር ። ዮሐንስም ፡ ሩጫውን ፡ ሲፈ
ጽም ፡ ሳለ ፡— እኔ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ ታስበ
ላችሁ ? እኔስ ፡ እርሱን ፡ አይደለሁም ፤ ነገር ፡
ግን ፡ እነሆ ÷ የእግሩን ፡ ጫማ ፡ እፈታ ፡ ዘንድ ፡
ከማይገባኝ ፡ ከእኔ ፡ በኋላ ፡ ይመጣል ፡ ይል ፡
ነበር ።
፳፮፤ እናንተ ፡ ወንድሞቻችን ÷ የአብርሃም ፡ ዘር ፡
ልጆች ፡ ከእናንተ ፡ መካከልም ፡ እግዚአብሔ
ርን ፡ የምትፈሩ ፡ ሆይ ÷ ለእናንተ ፡ የዚህ ፡ የመ
፳፯፤ ዳን ፡ ቃል ፡ ተላከ ። በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩ ፡
ሰዎችና ፡ አለቆቻቸው ፡ እርሱንና ፡ በየሰንበቱ ፡
የሚነበቡትን ፡ የነቢያትን ፡ ድምፆች ፡ ስላላወቁ ፡
፳፰፤ በፍርዳቸው ፡ ፈጽመዋልና ፤ ለሞትም ፡ የሚ
ያደርስ ፡ ምክንያት ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ ባያገኙ
በት ÷ ይገድለው ፡ ዘንድ ፡ ጲላጦስን ፡ ለመኑት ፤
፳፱፤ ስለ ፡ እርሱም ፡ የተጻፈውን ፡ ሁሉ ፡ በፈጸሙ ፡
ጊዜ ፡ ከእንጨት ፡ አውርደው ፡ በመቃብር ፡ አኖ
፴፤ ሩት ። እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ከሙታን ፡ አስነ
፴፩፤ ሣው ፤ በሕዝብም ፡ ዘንድ ፡ ምስክሮቹ ፡ ለሆኑት ፡
ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ከገሊላ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
፴፪፤ ለወጡት ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ታያቸው ። እኛም ፡ ለአ
ባቶች ፡ የተሰጠውን ፡ ተስፋ ፡ የምስራቹን ፡ ለእ
፴፫፤ ናንተ ፡ እንሰብካለን ፤ ይህን ፡ ተስፋ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ በሁለተኛው ፡ መዝሙር ፡ ደግሞ ፡—
አንተ ፡ ልጄ ፡ ነህ ÷ እኔ ፡ ዛሬ ፡ ወለድሁህ ፡
ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ÷ ኢየሱስን ፡ አስነሥቶ ፡
፴፬፤ ለእኛ ፡ ለልጆቻቸው ፡ ፈጽሞአልና ። እንደ ፡
ገናም ፡ ወደ ፡ መበስበስ ፡ እንዳይመለስ ፡ ከሙ
ታን ፡ እንደ ፡ አስነሣው ÷ እንዲህ ፡— የታመነ
ውን ፡ የዳዊትን ፡ ቅዱስ ፡ ተስፋ ፡ እሰጣችኋለሁ ፡
፴፭፤ ብሎአል ። ደግሞ ፡ በሌላው ፡ ስፍራ ፡— ቅዱ
ስህን ፡ መበስበስን ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ አትሰጠውም ፡
፴፮፤ ይላልና ። ዳዊትም ፡ በራሱ ፡ ዘመን ፡ የእግዚ
አብሔርን ፡ አሳብ ፡ ካገለገለ ፡ በኋላ ፡ አንቀላፋ ÷
ከአባቶቹም ፡ ጋር ፡ ተጨምሮ ፡ መበስበስን ፡ አየ ፤
፴፯፤ ይህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያስነሣው ፡ ግን ፡ መበስበ
፴፰፡፴፱፤ ስን ፡ አላየም ። እንግዲህ ፡ ወንድሞች ፡ ሆይ ÷
በእርሱ ፡ በኩል ፡ የኃጢአት ፡ ስርየት ፡ እንዲነገ
ርላችሁ ÷ በሙሴም ፡ ሕግ ፡ ትጸድቁበት ፡ ዘንድ ፡
ከማይቻላችሁ ፡ ሁሉ ፡ ያመነ ፡ ሁሉ ፡ በእርሱ ፡
እንዲጸድቅ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ይሁን ።
፵፡፵፩፤ እንግዲህ ፡—
እናንተ ፡ የምትንቁ ÷ እዩ ፡ ተደነቁም ፡
ጥፉም ፤ አንድ ፡ ስንኳ ፡ ቢተርክላችሁ ፡
የማታምኑትን ፡ ሥራ ፡ በዘመናችሁ ፡ እኔ ፡
እሠራለሁና ፡
ተብሎ ፡ በነቢያት ፡ የተነገረው ፡ እንዳይደርስባ
ችሁ ፡ ተጠንቀቁ ።
በወጡም ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በሚመጣው ፡ ፵፪፤
ሰንበት ፡ ይነግሩአቸው ፡ ዘንድ ፡ ለመኑአቸው ።
ጉባኤውም ፡ ከተፈታ ፡ በኋላ ፡ ከአይሁድና ፡ ፵፫፤
ወደ ፡ ይሁዲነት ፡ ገብተው ፡ ከሚያመልኩ ፡ ብዙ
ዎች ፡ ጳውሎስንና ፡ በርናባስን ፡ ተከተሉአቸው ÷
እነርሱም ፡ ሲነግሩአቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡
ጸጋ ፡ ጸንተው ፡ እንዲኖሩ ፡ አስረዱአቸው ።
በሁለተኛውም ፡ ሰንበት ፡ ከጥቂቶቹ ፡ በቀር ፡ ፵፬፤
የከተማው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ቃል ፡ ይሰሙ ፡ ዘንድ ፡ ተሰበሰቡ ። አይሁድም ፡ ፵፭፤
ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ በዩ ፡ ጊዜ ፡ ቅንዓት ፡ ሞላባቸው ÷ እየ
ተሳደቡም ፡ ጳውሎስ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ተቃ
ወሙ ። ጳውሎስና ፡ በርናባስም ፡ ገልጠው ፡— ፵፮፤
የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አስቀድሞ ፡ ለእናንተ ፡
ይነገር ፡ ዘንድ ፡ ያስፈልጋል ፤ ከገፋችሁትና ፡
የዘላለም ፡ ሕይወት ፡ እንዳይገባችሁ ፡ በራሳችሁ ፡
ከፈረዳችሁ ፡ ግን ÷ እነሆ ÷ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ ዘወር ፡
እንላለን ። እንዲሁ ፡ ጌታ ፡— ፵፯፤
እስከ ፡ ምድር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ለማዳን ፡
ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ለአሕዛብ ፡ ብርሃን ፡ አድር
ጌሃለሁ ፡
ብሎ ፡ አዞናልና ፡ አሉ ።
አሕዛብም ፡ ሰምተው ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡ የእግ ፵፰፤
ዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ አከበሩ ÷ ለዘላለም ፡ ሕይ
ወትም ፡ የተዘጋጁ ፡ ሁሉ ፡ አመኑ ፤ የጌታም ፡ ፵፱፤
ቃል ፡ በአገሩ ፡ ሁሉ ፡ ተስፋፋ ። አይሁድ ፡ ግን ፡ ፶፤
የሚያመልኩትን ፡ የከበሩትንም ፡ ሴቶችና ፡ የከ
ተማውን ፡ መኳንንት ፡ አወኩ ÷ በጳውሎስና ፡
በበርናባስም ፡ ላይ ፡ ስደትን ፡ አስነሥተው ፡ ከአ
ገራቸው ፡ አወጡአቸው ። እነርሱ ፡ ግን ፡ የእ ፶፩፤
ግራቸውን ፡ ትቢያ ፡ አራግፈውባቸው ፡ ወደ ፡
ኢቆንዮን ፡ መጡ ። በደቀ ፡ መዛሙርትም ፡ ፶፪፤
ደስታና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሞላባቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

በኢቆንዮንም ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ ወደ ፡ አይ ፩፤
ሁድ ፡ ምኵራብ ፡ ገብተው ፡ ከአይሁድና ፡ ከግ
ሪክ ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ እስኪያምኑ ፡ ድረስ ፡ ተናገሩ ።
ያላመኑት ፡ አይሁድ ፡ ግን ፡ የአሕዛብን ፡ ልብ ፡ ፪፤
በወንድሞች ፡ ላይ ፡ አነሣሡ ፡ አስከፉም ። ምል ፫፤
ክትና ፡ ድንቅ ፡ በእጃቸው ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡
እየሰጠ ፡ ለጸጋው ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ መሰከረው ፡ ስለ ፡
ጌታ ፡ ገልጠው ፡ እየተናገሩ ፡ ረጅም ፡ ወራት ፡
ተቀመጡ ። የከተማውም ፡ ሕዝብ ፡ ተከፍለው ፡ ፬፤
እኵሌቶቹ ፡ ከአይሁድ ፡ እኵሌቶቹም ፡ ከሐዋር
ያት ፡ ጋር ፡ ሆኑ ። አሕዛብና ፡ አይሁድ ፡ ግን ፡ ፭፤
ከአለቆቻቸው ፡ ጋር ፡ ሊያንገላቱአቸውና ፡ ሊወ
ግሩአቸው ፡ ባሰቡ ፡ ጊዜ ÷ አውቀው ፡ ልስጥራ ፮፤
ንና ፡ ደርቤን ፡ ወደሚባሉት ፡ ወደ ፡ ሊቃኦንያ ፡

፲፫። ፳፭፤ ዮሐ. ፩፥፳ ፳፯። ፳፯፤ ምዕ. ፫፥፲፯፤ ዮሐ. ፲፯፥፫። ፳፰፤ ሉቃ. ፳፫፥፳፪፤ ፳፫። ፳፱፤ ዮሐ. ፲፱፥፳፰—፵፪፤
፴፯ ፴፯፤ ፵—፵፪። ፴፩፤ ምዕ. ፩፥፫። ፴፫፤ መዝ. ፪፥፯። ፴፬፤ ኢሳ. ፶፭፥፫። ፴፭፤ መዝ. ፲፭፥፲። ፴፮፤
ምዕ. ፪፥፳፱። ፴፰፤ ሉቃ. ፳፬፥፵፯። ፵፩፤ እንባ. ፩፥፭። ፵፮፤ ምዕ. ፫፥፳፮፤ ማቴ. ፲፥፮፤ ፳፩፥፵፫። ፵፯፤
ኢሳ. ፵፱፥፮። ፵፰፤ ሮሜ ፳፥፳፱፤ ፴። ፶፩፤ ሉቃ. ፱፥፭።
፲፬። ፮፤ ማቴ. ፲፥፳፫።

ከተማዎች ፡ በእነርሱም ፡ ዙሪያ ፡ ወዳለው ፡ አገር ፡
፯፡ ሸሹ ፤ በዚያም ፡ ወንጌልን ፡ ይሰብኩ ፡ ነበር ።
፰፡ በልስጥራንም ፡ እግሩ ፡ የሰለለ ፥ ከእናቱም ፡
ማኅፀን ፡ ጀምሮ ፡ አንካሳ ፡ የሆነ ፥ ከቶም ፡ ሄዶ ፡
የማያውቅ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ።
፱፡ ይህም ፡ ሰው ፡ ጳውሎስ ፡ ሲናገር ፡ ይሰማ ፡ ነበር ፤
እርሱም ፡ ትኵር ፡ ብሎ ፡ ተመለከተውና ፡ ይድን ፡
፲፡ ዘንድ ፡ እምነት ፡ እንዳለው ፡ በየ ፡ ጊዜ ፥ በታ
ላቅ ፡ ድምፅ ፡— ቀጥ ፡ ብለህ ፡ በእግርህ ፡ ቁም ፡
አለው ። ብድግ ፡ ብሎም ፡ ተነሥቶ ፡ ይመላለስ ፡
፲፩፡ ነበር ። ሕዝቡም ፡ ጳውሎስ ፡ ያደረገውን ፡ በዩ ፡
ጊዜ ፡ ድምፃቸውን ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ በሊቃኦ
ንያ ፡ ቋንቋ ፡— አማልክት ፡ ሰዎችን ፡ መስለው ፡
፲፪፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ወርደዋል ፡ አሉ ፤ በርናባስንም ፡
ድያ ፡ አሉት ፤ ጳውሎስንም ፡ እርሱ ፡ በመናገር ፡
፲፫፡ ዋና ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ሄርሜን ፡ አሉት ። በከተማ
ውም ፡ ፊት ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ያለው ፡ የድያ ፡
ካህን ፡ ኮርማዎችንና ፡ የአበባን ፡ አክሊሎች ፡ ወደ ፡
ደጃፍ ፡ አምጥቶ ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ሊሠ
፲፬፡ ዋላቸው ፡ ወደደ ። ሐዋርያት ፡ በርናባስና ፡ ጳው
ሎስ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ልብሳቸውን ፡
ቀደው ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ መካከል ፡ እየጮኹ ፡
፲፭፡ ሮጡ ፥ እንዲህም ፡ አሉ ፡— እናንተ ፡ ሰዎች ፥
ይህን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ታደርጋላችሁ ? እኛ ፡ ደግሞ ፡
እንደ ፡ እናንተ ፡ የምንሰማ ፡ ሰዎች ፡ ነን ፥ ከዚ
ህም ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ባሕር
ንም ፡ በእነርሱም ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ፈጠረ ፡
ወደ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘወር ፡ ትሉ ፡
፲፮፡ ዘንድ ፡ ወንጌልን ፡ እንሰብካለን ። እርሱ ፡ ባለ
ፉት ፡ ትውልዶች ፡ አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ በገዛ ፡ ራሳ
፲፯፡ ቸው ፡ ጐዳና ፡ ይሄዱ ፡ ዘንድ ፡ ተዋቸው ። ከዚ
ህም ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ እየሠራ ፥ ከሰ
ማይ ፡ ዝናብን ፡ ፍሬ ፡ የሚሆንበትንም ፡ ወራት ፡
ሲሰጠን ፥ ልባችንንም ፡ በመብልና ፡ በደስታ ፡
ሲሞላው ፡ ራሱን ፡ ያለ ፡ ምስክር ፡ አልተወም ።
፲፰፡ ይህንም ፡ ብለው ፡ እንዳይሠውላቸው ፡ ሕዝቡን ፡
በጭንቅ ፡ አስተዉአቸው ።
፲፱፡ አይሁድ ፡ ግን ፡ ከአንጾኪያና ፡ ከኢቆንዮን ፡
መጡ ፤ ሕዝቡንም ፡ አባብለው ፡ ጳውሎስን ፡
ወገሩ ፡ የሞተም ፡ መስሎአቸው ፡ ከከተማ ፡ ወደ ፡
፳፡ ውጭ ፡ ጐተቱት ። ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ግን ፡
ከበውት ፡ ሳሉ ፥ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ገባ ።
በነገውም ፡ ከበርናባስ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ደርቤን ፡
፳፩፡፳፪፡ ወጣ ። በዚያችም ፡ ከተማ ፡ ወንጌልን ፡ ሰብ
ከው ፡ እጅግ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርትን ፡ ካደረጉ ፡
በኋላ ፥ የደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ ልብ ፡ እያጸኑ ፡
በሃይማኖትም ፡ ጸንተው ፡ እንዲኖሩ ፡ እየመከ
ሩና ፡— ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡
በብዙ ፡ መከራ ፡ እንገባ ፡ ዘንድ ፡ ያስፈልገናል ፡
እያሉ ፥ ወደ ፡ ልስጥራን ፡ ወደ ፡ ኢቆንዮንም ፡
፳፫፡ ወደ ፡ አንጾኪያም ፡ ተመለሱ ። በየቤተ ፡ ክርስ
ቲያኑም ፡ ሽማግሌዎችን ፡ ከሾሙላቸው ፡ በኋላ ፡
ጦመውም ፡ ከጸለዩ ፡ በኋላ ፥ ላመኑበት ፡ ለጌታ ፡
አደራ ፡ ሰጡአቸው ።
በጲስድያም ፡ አልፈው ፡ ወደ ፡ ጵንፍልያ ፡ ፳፬፡
መጡ ፡ በጴርጌንም ፡ ቃሉን ፡ ከተናገሩ ፡ በኋላ ፡ ፳፭፡
ወደ ፡ አጣልያ ፡ ወረዱ ፥ ከዚያም ፡ ስለ ፡ ፈጸ ፳፮፡
ሙት ፡ ሥራ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ አደራ ፡
ወደ ፡ ተሰጡበት ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ በመርከብ ፡
ሄዱ ። በደረሱም ፡ ጊዜ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ፳፯፡
ሰብስበው ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ያደ
ረገውን ፡ ሁሉ ፡ ለአሕዛብም ፡ የሃይማኖትን ፡
ደጅ ፡ እንደ ፡ ከፈተላቸው ፡ ተናገሩ ። ከደቀ ፡ ፳፰፡
መዛሙርትም ፡ ጋር ፡ አያሌ ፡ ቀን ፡ ተቀመጡ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፭ ።

አንዳንዶችም ፡ ከይሁዳ ፡ ወረዱና ፡— እንደ ፡ ፩፡
ሙሴ ፡ ሥርዓት ፡ ካልተገረዛችሁ ፡ ትድኑ ፡ ዘንድ ፡
አትችሉም ፡ ብለው ፡ ወንድሞችን ፡ ያስተምሩ ፡
ነበር ። በእነርሱና ፡ በጳውሎስ ፡ በበርናባስም ፡ ፪
መካከል ፡ ብዙ ፡ ጥልና ፡ ክርክር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡
ስለዚህ ፡ ክርክር ፡ ጳውሎስና ፡ በርናባስ ፡ ከእነር
ሱም ፡ አንዳንዶች ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ሐዋ
ርያት ፡ ወደ ፡ ቀሳውስትም * ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
ይወጡ ፡ ዘንድ ፡ ተቈረጠ ። ቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ ፫፡
በመንገድ ፡ እየረዳቸው ፡ እነርሱ ፡ የአሕዛብን ፡
መመለስ ፡ እየተረኩ ፡ በፊንቄና ፡ በሰማርያ ፡
አለፉ ፥ ወንድሞችንም ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አሰ
ኙአቸው ። ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ በደረሱ ፡ ፬፡
ጊዜ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ሐዋርያት ፡ ሽማግሌዎ
ችም ፡ ተቀበሉአቸው ፥ እግዚአብሔርም ፡ ከእ
ነርሱ ፡ ጋር ፡ ያደረገውን ፡ ሁሉ ፡ አወሩ ። ከፈ ፭፡
ሪሳውያን ፡ ወገን ፡ ግን ፡ ያመኑት ፡ አንዳንዶቹ ፡
ተነሥተው ፡— ትገርዙአቸው ፡ ዘንድና ፡ የሙ
ሴን ፡ ሕግ ፡ እንዲጠብቁ ፡ ታዙአቸው ፡ ዘንድ ፡
ይገባል ፡ አሉ ።
ሐዋርያትና ፡ ቀሳውስትም * ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ፮፡
ለመመካከር ፡ ተሰበሰቡ ። ከብዙ ፡ ክርክርም ፡ ፯፡
በኋላ ፡ ጴጥሮስ ፡ ተነሥቶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡
ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ አሕዛብ ፡ ከአፌ ፡ የወንጌልን ፡
ቃል ፡ ሰምተው ፡ ያምኑ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡
በመጀመሪያው ፡ ዘመን ፡ ከእናንተ ፡ እኔን ፡ እንደ ፡
መረጠኝ ፡ እናንተ ፡ ታውቃላችሁ ። ልብንም ፡ ፰፡
የሚያውቅ ፡ አምላክ ፡ ለእኛ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡
ሰጠን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በመስጠት ፡ መሰከ
ረላቸው ፤ ልባቸውንም ፡ በእምነት ፡ ሲያነጻ ፡ ፱፡
በእኛና ፡ በእነርሱ ፡ መካከል ፡ አንዳች ፡ አልለ
የም ። እንግዲህ ፡ አባቶቻችንና ፡ እኛ ፡ ልንሸ ፲፡
ከመው ፡ ያልቻልነውን ፡ ቀንበር ፡ በደቀ ፡ መዛ
ሙርት ፡ ጫንቃ ፡ ላይ ፡ በመጫን ፡ እግዚአብሔ
ርን ፡ አሁን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትፈታተናላችሁ ? ነገር ፡ ፲፩፡
ግን ፡ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ እንደ ፡

፲፬ ። ፱ ፤ ማቴ. ፫ ፥ ፳፰ ። ፲፭ ፤ ኤር. ፲፬ ፥ ፳፪ ። ፲፯ ፤ መዝ. ፻፵፯ ፥ ፰—፲፫ ። ፳፪ ፤ ማቴ. ፲፯ ፥ ፳፬ ፤ ሉቃ. ፳፪ ፥ ፳፰ ፡ ፳፱ ።
፳፯ ፤ ም. ፲፲ ፥ ፲—፲፫ ።
፲፭ ። ፩ ፤ ዘሌዋ. ፲፪ ፥ ፫ ። ፯ ፤ ም. ፲ ፥ ፲፱—፲፯ ። ፲ ፤ ሉቃ. ፲፩ ፥ ፵፮ ፤ ገላ. ፫ ፥ ፲ ። ፲፩ ፤ ገላ. ፪ ፥ ፲፮ ፤ ኤፌ. ፫ ፥ ፭ ፡ ፰ ።
፲፭ ፡ ፪ ፡ በግሪኩ « ሽማግሌዎች » ይላል ።
፲፭ ፡ ፮ በግሪኩ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ይላል ።

እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ እንድን ፡ ዘንድ ፡ እናምናለን ።
፲፪፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ዝም ፡ አሉ ፥ በርናባስና ፡
ጳውሎስም ፡ እግዚአብሔር ፡ በእጃቸው ፡ በአሕ
ዛብ ፡ መካከል ፡ ያደረገውን ፡ ምልክትና ፡ ድንቅ ፡
፲፫፡ ሁሉ ፡ ሲተርኩላቸው ፡ ይሰሙ ፡ ነበር ። እነር
ሱም ፡ ዝም ፡ ካሉ ፡ በኋላ ፡ ያዕቆብ ፡ እንዲህ ፡
ብሎ ፡ መለሰ ፡— ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ስሙኝ ።
፲፬፡ እግዚአብሔር ፡ ለስሙ ፡ የሚሆንን ፡ ወገን ፡ ከአ
ሕዛብ ፡ ይወስድ ፡ ዘንድ ፡ አስቀድሞ ፡ እንዴት ፡
፲፭፡ እንደ ፡ ጐበኘ ፡ ስምዖን ፡ ተርኮአል ። ከዚህም ፡
ጋር ፡ የነቢያት ፡ ቃል ፡ ይሰማማል ፥ እንዲህ ፡
ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡—
፲፮፡፲፯፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የቀሩቱ ፡ ሰዎችና ፡ በስሜ ፡
የተጠሩት ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ጌታን ፡ ይፈ
ልጉ ፡ ዘንድ ፡ እመለሳለሁ ፥ የወደቀችው
ንም ፡ የዳዊትን ፡ ድንኳን ፡ እንደ ፡ ገና ፡
እሠራታለሁ ፥ ፍራሽዋንም ፡ እንደ ፡ ገና ፡
እሠራታለሁ ፡ እንደ ፡ ገናም ፡ አቆማታለሁ ፡
፲፰፡ ይላል ፡ ይህን ፡ የሚያደርግ ፡ ጌታ ። ከጥ
ንት ፡ ጀምሮ ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአ
ብሔር ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።
፲፱፡ ስለዚህ ፡ ከአሕዛብ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የዞሩ
፳፡ ትን ፡ እንዳናስቸግራቸው ፥ ነገር ፡ ግን ፡ ከጣዖት ፡
ርኵሰትና ፡ ከዝሙት ፡ ከታነቀም ፡ ከደምም ፡
ይርቁ ፡ ዘንድ ፡ እንድንጽፍላቸው ፡ እቈርጣለሁ ።
፳፩፡ ሙሴስ ፡ ከቀደሙት ፡ ትውልድ ፡ ጀምሮ ፡ በሰን
በት ፡ በሰንበት ፡ በምኵራቦቹ ፡ ሲያነቡ ፡ በየከ
ተማው ፡ እርሱን ፡ የሚሰብኩ ፡ አሉት ።
፳፪፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ሐዋርያትና ፡ ቀሳውስት * ከቤተ ፡
ክርስቲያኑ ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ከእነርሱ ፡ የተመረጡ
ትን ፡ ሰዎች ፡ ከጳውሎስና ፡ ከበርናባስ ፡ ጋር ፡
ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ይልኩ ፡ ዘንድ ፡ ፈቀዱ ፤ እነር
ሱም ፡ በወንድሞች ፡ መካከል ፡ ዋናዎች ፡ ሆነው ፡
በርስያን ፡ የተባለው ፡ ይሁዳና ፡ ሲላስ ፡ ነበሩ ።
፳፫፡ እንዲህም ፡ ጽፈው ፡ በእነርሱ ፡ እጅ ፡ ላኩ ፡—
ሐዋርያትና ፡ ቀሳውስት * ፡ ወንድሞችም ፡ በአ
ንጾኪያና ፡ በሶርያ ፡ በኪልቅያም ፡ ለሚኖሩ ፡ ከአ
ሕዛብ ፡ ወገን ፡ ለሆኑ ፡ ወንድሞች ፡ ሰላምታ ፡
፳፬፡ ያቀርባሉ ። ያላዘዝናቸው ፡ ሰዎች ፡ ከእኛ ፡ ወጥ
ተው ፡— ትገረዙ ፡ ዘንድና ፡ ሕግን ፤ ትጠብቁ ፡
ዘንድ ፡ ይገባችኋል ፡ ብለው ፡ ልባችሁን ፡ እያ
ወኩ ፡ በቃል ፡ እንዳናወጡአችሁ ፡ ስለ ፡ ሰማን ፥
፳፭፡፳፮፡ ስለ ፡ ጌታችን ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡
ነፍሳቸውን ፡ ከሰጡት ፡ ከምንወዳቸው ፡ ከበርና
ባስና ፡ ከጳውሎስ ፡ ጋር ፡ የተመረጡትን ፡ ሰዎች ፡
ወደ ፡ እናንተ ፡ እንልክ ፡ ዘንድ ፡ በአንድ ፡ ልብ ፡
፳፯፡ ሆነን ፡ ፈቀድን ። ራሳቸውም ፡ ደግሞ ፡ በቃላ
ቸው ፡ ያንኑ ፡ ይነግሩአችሁ ፡ ዘንድ ፡ ይሁዳንና ፡
፳፰፡፳፱፡ ሲላስን ፡ ልከናል ። ለጣዖት ፡ ከተሠዋ ፥ ከደ
ምም ፥ ከታነቀም ፥ ከዝሙትም ፡ ትርቁ ፡ ዘንድ ፡
ከዚህ ፡ ከሚያስፈልገው ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሸክም ፡
እንዳንጭንባችሁ ፡ እኛና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ፈቅደናልና ፤ ከዚህም ፡ ሁሉ ፡ ራሳችሁን ፡ ብት
ጠብቁ ፡ በመልካም ፡ ትኖራላችሁ ። ጤና ፡ ይስ
ጣችሁ ።
እነርሱም ፡ ተሰናብተው ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ፴፡
ወረዱ ፥ ሕዝቡንም ፡ ሰብስበው ፡ ደብዳቤውን ፡
ሰጡአቸው ። ባነበቡትም ፡ ጊዜ ፡ ከምክሩ ፡ የተ ፴፩፡
ነሣ ፡ ደስ ፡ አላቸው ። ይሁዳና ፡ ሲላስም ፡ ደግሞ ፡ ፴፪፡
ነቢያት ፡ ነበሩና ፡ ወንድሞችን ፡ በብዙ ፡ ቃል ፡
መከረው ፡ አጸኑአቸው ። አያሌ ፡ ቀንም ፡ ከተ ፴፫፡
ቀመጡ ፡ በኋላ ፡ ከወንድሞች ፡ በሰላም ፡ ተሰና
ብተው ፡ ወደ ፡ ሐዋርያት ፡ ሄዱ ። ሲላስ ፡ ግን ፡ ፴፬፡
በዚያ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ፈቀደ ። ጳውሎስና ፡ በር ፴፭፡
ናባስም ፡ ከሌሎች ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ደግሞ ፡
የጌታን ፡ ቃል ፡ እያስተማሩና ፡ ወንጌልን ፡ እየ
ሰበኩ ፡ በአንጾኪያ ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ።
ከጥቂት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ጳውሎስ ፡ በርናባ ፴፮፡
ስን ፡— ተመልሰን ፡ የጌታን ፡ ቃል ፡ በተናገርን
በት ፡ በየከተማው ፡ ሁሉ ፡ ወንድሞችን ፡ እን
ጐብኛቸው ፥ እንዴት ፡ እንዳሉም ፡ እንወቅ ፡
አለው ። በርናባስም ፡ ማርቆስ ፡ የተባለውን ፡ ፴፯፡
ዮሐንስን ፡ ደግሞ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ይወስድ ፡
ዘንድ ፡ አሰበ ፤ ጳውሎስ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ከእ ፴፰፡
ነርሱ ፡ ጋር ፡ ሊወስድ ፡ አልፈቀደም ፥ ከእነ
ርሱ ፡ ዘንድ ፡ ከጵንፍልያ ፡ ተለይቶ ፡ ነበርና ፥
ወደ ፡ ሥራም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ አልመጣም ፡
ነበርና ። ስለዚህም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እስኪ ፴፱፡
ለያዩ ፡ ድረስ ፡ መከፋፋት ፡ ሆነ ፥ በርናባስም ፡
ማርቆስን ፡ ይዞ ፡ በመርከብ ፡ ወደ ፡ ቆጵሮስ ፡
ሄደ ። ጳውሎስ ፡ ግን ፡ ሲላስን ፡ መረጠ ፥ ወን ፵፡
ድሞችም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ አደራ ፡ ከሰ
ጡት ፡ በኋላ ፡ ወጣ ፤ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፵፩፡
ንም ፡ እያጸና ፡ በሶርያና ፡ በኪልቅያ ፡ ይዞር ፡
ነበር ።

ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

ወደ ፡ ደርቤንና ፡ ወደ ፡ ልስጥራንም ፡ ደረሰ ። ፩፡
እነሆም ፥ በዚያ ፡ የአንዲት ፡ ያመነች ፡ አይሁዳ
ዊት ፡ ልጅ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ደቀ ፡
መዝሙር ፡ ነበረ ፤ አባቱ ፡ ግን ፡ የግሪክ ፡ ሰው ፡
ነበረ ። ለእርሱም ፡ በልስጥራንና ፡ በኢቆንዮን ፡ ፪፡
ያሉ ፡ ወንድሞች ፡ መሰከሩለት ። ጳውሎስ ፡ ፫፡
ይህ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ይወጣ ፡ ዘንድ ፡ ወደደ ፥
በእነዚያም ፡ ስፍራዎች ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ አይሁድ ፡
ይዞ ፡ ገረዘው ፤ አባቱ ፡ የግሪክ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡
ሆነ ፤ ሁሉ ፡ ያውቁ ፡ ነበርና ። በከተማዎችም ፡ ፬፡
ሲዞሩ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የነበሩት ፡ ሐዋርያትና ፡
ቀሳውስት * ፡ የቈረጡትን ፡ ሥርዓት ፡ ይጠብቁ ፡
ዘንድ ፡ ሰጡአቸው ። አብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፡ ፭፡
በሃይማኖት ፡ ይበረቱ ፡ ነበር ፥ በቍጥርም ፡ ዕለት ፡
ዕለት ፡ ይበዙ ፡ ነበር ።

፲፭ ። ፲፮ ፡ ፲፯ ፤ ዓሞ. ፱ ፥ ፲፩ ፡ ፲፪ ። ፳ ፤ ፩ ቆሮ. ፲ ፥ ፳ ፡ ፳ ፡ ፳፩ ፤ ዘፍጥ. ፱ ፥ ፬ ። ፳፩ ፤ ም. ፲፫ ፥ ፲፭ ። ፳፮ ፤ ም. ፲፫ ፥
፶ ። ፴፰ ፤ ም. ፲፫ ፥ ፲፫ ።
፲፮ ። ፩ ፤ ፪ ጢሞ. ፩ ፥ ፭ ። ፬ ፤ ም. ፲፭ ፥ ፳፰ ፡ ፳፱ ።
፲፭ ፡ ፳፪ በግሪኩ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ይላል ።
፲፮ ፡ ፬ በግሪኩ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ይላል ።

ገ፡ በእስያም ፡ ቃሉን ፡ እንዳይናገሩ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስለ ፡ ከለከላቸው ፡ በፍርግያና ፡ በገላትያ ፡
ፂ፡ አገር ፡ አለፉ ። በሚስያም ፡ አንጻር ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ቢታንያ ፡ ይሄዱ ፡ ዘንድ ፡ ሞከሩ ÷
የኢየሱስ ፡ መንፈስም ፡ አልፈቀደላቸውም ።
ጅ፡ በሚስያም ፡ አጠገብ ፡ አልፈው ፡ ወደ ፡ ጢሮአዳ ፡
ሄ፡ ወረዱ ። ራእይም ፡ ለጳውሎስ ፡ በሌሊት ፡ ታየው ። አንድ ፡ የመቄዶንያ ፡ ሰው ፡ ቆሞ ፡ መቄዶንያ ፡ ተሻገርና ፡ እርዳን ፡ እያለ ፡ ቆሞ ፡
ፈ፡ ሲለምነው ፡ ነበር ። ራእዩንም ፡ ባየ ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡ ወደ ፡ መቄዶንያ ፡ ልንወጣ ፡ ፈለግን ÷
ወንጌልን ፡ እንሰብክላቸው ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ጠራን ፡ መስሎናልና ።
፲፩፡ ከጢሮአዳም ፡ ተነሥተን ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ሳሞትራቄ ፡ በነገውም ፡ ወደ ፡ ናጰሊ ፡ በመር
፲፪፡ ከብ ፡ ሄድን ። ከዚያም ፡ ወደ ፡ ፊልጵስዩስ ፡ ደረስን ። እርስዋም ፡ የመቄዶንያ ፡ ከተማ ፡ ሆና ÷
የወረዳ ፡ ዋና ፡ ከተማና ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ ናት ። በዚህችም ፡ ከተማ ፡ እንዳንሄድ ፡ ቀን ፡ እንቀመጥ ፡
፲፫፡ ነበር ። በሰንበት ፡ ቀንም ፡ ከከተማው ፡ በር ፡ ውጭ ፡ የጸሎት ፡ ስፍራ ፡ በዚያ ፡ መሆኑን ፡ ስላ
ሰብን ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ወጣን ። ተቀም
፲፬፡ ጠንም ፡ ለተሰበሰቡት ፡ ሴቶች ፡ ተናገርን ። ከት ያጥሮን ፡ ከተማም ፡ የመጣች ፡ ቀይ ፡ ሐር ፡ ሻጭ ፡
እግዚአብሔርን ፡ የምታመልክ ፡ ልድያ ፡ የሚ ሉአት ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ትሰማ ፡ ነበረች ። ጳው
ሎስም ፡ የሚናገረውን ፡ ታዳምጥ ፡ ዘንድ ፡ ጌታ ፡
፲፭፡ ልብዋን ፡ ከፈተላት ። እርስዋም ፡ ከቤተ ፡ ሰዎ ችዋ ፡ ጋር ፡ ከተጠመቀች ፡ በኋላ ፡ — በጌታ ፡ የማምን ፡ እንድሆን ፡ ከፈረዳችሁልኝ ÷ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ግብታችሁ ፡ ኑሩ ፡ ብላ ፡ ለመነችን ። በግ ድም ፡ አለችን ።
፲፮፡ ወደ ፡ ጸሎት ፡ ስፍራም ፡ ስንሄድ ÷ የምዋርት ኻነት ፡ መንፈስ ፡ የነበረባት ፡ ለጌቶችዋም ፡ እየ ጠነቈለች ፡ ብዙ ፡ ትርፍ ፡ ታመጣ ፡ የነበረች ፡
፲፯፡ አንዲት ፡ ገረድ ፡ አገኘችን ። እርስዋ ፡ ጳውሎ ስንና ፡ እኛን ፡ እየተከተለች ፡ — የመዳንን ፡ መን ገድ ፡ የሚነግሩአችሁ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ የልዑል ፡ አምላክ ፡ ባሪያዎች ፡ ናቸው ፡ ብላ ፡ ትጮኽ ፡
፲፰፡ ነበር ። ይህንም ፡ እጅግ ፡ ቀን ፡ አደረገች ። ጳው ሎስ ፡ ግን ፡ ተቸገረና ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ መንፈ ሱን ፡ — ከእርስዋ ፡ እንድትወጣ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ አዝሃለሁ ፡ አለው ፡ በዚያም ፡ ሰዓት ፡ ወጣ ።
፲፱፡ ጌቶችዋም ፡ የትርፋቸው ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስንና ፡ ሲላስን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ በሹማምት ፡ ፊት ፡ ጐተቱአቸው ።
፳፡ ወደ ፡ ገዢዎችም ፡ አቅርበው ፡ — እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ አይሁድ ፡ ሆነው ፡ ከተማችንን ፡ እጅግ ፡ ያናው
፳፩፡ ጣሉ ። እኛም ፡ የሮሜ ፡ ሰዎች ፡ ሆነን ፡ እንቀ በላቸውና ፡ እናደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡ ያልተፈቀ
፳፪፡ ደልንን ፡ ልማዶች ፡ ይናገራሉ ፡ አሉ ። ሕዝቡም አብረው ፡ ተነሡባቸው ÷ ገዢዎቹም ፡ ልብሳ ቸውን ፡ ገፈው ፡ በበትር ፡ ይመቱአቸው ፡ ዘንድ ፡
፳፫፡ አዘዙ ። በብዙም ፡ ከደበደቡአቸው ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ወኅኒ ፡ ጣሉአቸው ÷ የወኅኒውንም ፡ ጠባቂ ፡
፳፬፡ ተጠንቅቆ ፡ እንዲጠብቃቸው ፡ አዘዙት ። እር ሱም ፡ የዚህን ፡ ዓይነት ፡ ትእዛዝ ፡ ተቀብሎ ፡ ወደ ፡ ውስጠኛው ፡ ወኅኒ ፡ ጣላቸው ÷ እግራቸ ውንም ፡ በግንድ ፡ አጣብቆ ፡ ጠረቃቸው ።
፳፭፡ በመንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ግን ፡ ጳውሎስና ፡ ሲላስ ፡ እየጸለዩ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በዜማ ፡ ያመሰግኑ ፡
ነበር ÷ አስረኞቹም ፡ ያደምጡአቸው ፡ ነበር ፤
፳፮፡ ድንገትም ፡ የወኅኒው ፡ መሠረት ፡ እስኪናወጥ ፡ ድረስ ፡ ታላቅ ፡ የምድር ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ሆነ ፤
በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ደጆቹ ፡ ሁሉ ፡ ተከፈቱ ፡ የሁ
፳፯፡ ሉም ፡ እስራት ፡ ተፈታ ። የወኅኒውም ፡ ጠባቂ ፡ ከእንቅልፉ ፡ ነቅቶ ፡ የወኅኒው ፡ ደጆች ፡ ተከፍ ተው ፡ ባየ ፡ ጊዜ ÷ እስረኞቹ ፡ ያመለጡ ፡ መስ ሎት ፡ ራሱን ፡ ይገድል ፡ ዘንድ ፡ አስቦ ፡ ሰይፉን ፡
፳፰፡ መዘዘ ። ጳውሎስ ፡ ግን ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ — ሁላችን ፡ ከዚህ ፡ አለንና ፡ በራስህ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አታድርግ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ። መብራትም ፡ ሰምኖ ፡
፳፱፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ሮጠ ÷ እየተንቀጠቀጠም ፡ ከጳው ሎስና ፡ ከሲላስ ፡ ፊት ፡ ተደፋ ። ወደ ፡ ውጭም ፡
፴፡ አውጥቶ ፡ — ጌቶች ፡ ሆይ ÷ እድን ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይገባኛል ? አላቸው ። እነርሱም ፡ —
፴፩፡ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እመን ፡ አንተና ፡ ቤተ ፡ ሰዎችህም ፡ ትድናላችሁ ፡ አሉት ። ለእ
፴፪፡ ርሱና ፡ በቤቱም ፡ ላሉት ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔ ርን ፡ ቃል ፡ ተናገሩአቸው ። በሌሊትም ፡ በዚ
፴፫፡ ያች ፡ ሰዓት ፡ ወስዶ ፡ ቍስላቸውን ፡ አጠበላ ቸው ÷ ያን ፡ ጊዜውንም ፡ እርሱ ፡ ከቤተ ፡ ሰዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ተጠመቀ ። ወደ ፡ ቤቱም ፡ አው
፴፬፡ ጥቶ ፡ ማዕድ ፡ አቀረበላቸው ÷ በእግዚአብሔ ርም ፡ ስላመነ ፡ ከቤተ ፡ ሰዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ሐሤት ፡ አደረገ ።
፴፭፡ በነጋም ፡ ጊዜ ፡ ገዢዎቹ ፡ — እነዚያን ፡ ሰዎች ፡
፴፮፡ ፍታቸው ፡ ብለው ፡ ሎሌዎቻቸውን ፡ ላኩ ። የወኅኒውም ፡ ጠባቂ ፡ — ተፈቱ ፡ ዘንድ ፡ ገገር
፴፯፡ ዎቹ ፡ ልከዋል ። እንግዲህ ፡ አሁን ፡ ወጥታችሁ ፡ በሰላም ፡ ሂዱ ፡ ብሎ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ለጳውሎስ ፡ ነገረው ። ጳውሎስ ፡ ግን ፡ — እኛ ፡ የሮሜ ፡
፴፰፡ ሰዎች ፡ ስንሆን ፡ ያለ ፡ ፍርድ ፡ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ ደብድበው ፡ በወኅኒ ፡ ጣሉን ፤ አሁንም ፡ በስ ውር ፡ ይጥሉናልን ? አይሆንም ፤ ራሳቸው ፡
፴፱፡ ግን ፡ መጥተው ፡ ያውጡን ፡ አሉአቸው ። ሎሌ ዎቹም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ለገዢዎች ፡ ነገሩ ። የሮሜ ፡ ሰዎችም ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ፈሩ ፤
፵፡ መጥተውም ፡ ማለዱአቸው ÷ አውጥተውም ፡ ከከተማ ፡ ይወጡ ፡ ዘንድ ፡ ለመኑአቸው ። ከወ ኅኒውም ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ልድያ ፡ ቤት ፡ ገቡ ÷ ወንድሞችንም ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ አጽናኑአቸውና ፡ ሄዱ ።

ፕሮፌሰር ፡ ፲፮ ፡ 121 የሐዋርያት ፡ ሥራ ። ፲፯ ፡ ፈሪሳ

ምዕራፍ ፡ ፲፯ ።

፩፡ በአንፊጵልና ፡ በአጵሎንያም ፡ ከሰፉ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ተሰሎንቄ ፡ መጡ ÷ በዚያም ፡ የአይሁድ ፡
፪፡ ምኵራብ ፡ ነበረ ። ጳውሎስም ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ገባ ÷ ሦስት ፡ ሰንበትም ፡ ያህል ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ከመጻሕፍት ፡ እየጠቀሰ ፡ ይነጋ
፫፡ ገር ፡ ነበር ፤ ሲተረጕምም ፡ ክርስቶስ ፡ መከራ ፡ እንዲቀበልና ፡ ከሙታን ፡ እንዲነሣ ፡ ይገባው ፡ ዘንድ ፡ እያስረዳ ፡ — ይህ ፡ እኔ ፡ የምሰብክላችሁ ፡ ኢየሱስ ፡ እርሱ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ ይል ፡ ነበር ።
፬፡ ከእነርሱም ፡ አንዳንዶቹ ፡ ተረድተው ÷ ከሚያ መልኩም ፡ ከግሪክ ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ከከበሩትም ፡ ሴቶች ፡ ዋቂቶች ፡ ያይደሉ ÷ ከጳውሎስና ፡ ከሲ
፭፡ ላስ ፡ ጋር ፡ ተባበሩ ። አይሁድ ፡ ግን ፡ ቀንተው ፡ ከሥራ ፡ ፈቶች ፡ ክፉ ፡ ሰዎችን ፡ አመጡ ፡ ሕዝ ብንም ፡ ሰብስበው ፡ ከተማውን ፡ አወኩ ÷ ወደ ፡ ሕዝብም ፡ ያወጡአቸው ፡ ዘንድ ፡ ፈልገው ፡
፮፡ ወደ ፡ ኢያሶንን ፡ ቤት ፡ ቀረቡ ፤ በላገኙአቸ ውም ፡ ጊዜ ፡ ኢያሶንንና ፡ ከወንድሞች ፡ አንዳ ንዶችን ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ አለቆች ፡ ጮኽተው ፡ —
ዓለምን ፡ ያወኩ ፡ እነዚህ ፡ ወደዚህ ፡ ደግሞ ፡
፯፡ መጥተዋል ÷ ኢያሶንም ፡ ተቀብሎአቸዋል ፤ እነዚህም ፡ ሁሉ ፡ — ኢየሱስ ፡ የሚሉት ፡ ሌላ ፡ ንጉሥ ፡ አለ ፡ እያሉ ፡ የቄሣርን ፡ ትእዛዝ ፡ ይቃ
፰፡ ወማሉ ፡ ብለው ፡ ጮኹ ። ሕዝቡና ፡ የከተማ ውም ፡ አለቆች ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡
፱፡ ታወኩ ÷ ከኢያሶንና ፡ ከሌሎቹም ፡ ዋስ ፡ ተቀብ ለው ፡ ለቀቁአቸው ።
፲፡ ወዲያውም ፡ ወንድሞች ፡ ጳውሎስንና ፡ ሲላ ስን ፡ በሌሊት ፡ ወደ ፡ ቤርያ ፡ ሰደዱአቸው ÷ በደ ረሱም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አይሁድ ፡ ምኵራብ ፡ ገቡ ፤
፲፩፡ እነዚህም ፡ ቡተሰሎንቄ ፡ ከሚኖሩት ፡ ይልቅ ፡ ልበ ፡ ሰፊዎች ፡ ነበሩና ፡ — ነገሩ ፡ እንደዚሁ ፡ ይሆንን ? ብለው ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ መጻሕፍትን ፡ እየመረመሩ ፡ ቃሉን ፡ በሙሉ ፡ ተቀ
፲፪፡ በሉ ። ስለዚህም ፡ ከእነርሱ ፡ ብዙ ÷ ከግሪክኛም ፡ የከበሩት ፡ ሴቶችና ፡ ወንዶች ፡ ጥቂት ፡ ያይደሉ ÷
፲፫፡ አመኑ ። በተሰሎንቄ ፡ ያሉት ፡ አይሁድ ፡ ግን ፡ ጳውሎስ ፡ በቤርያ ፡ ደግሞ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ሰበከ ፡ ባወቁ ፡ ጊዜ ÷ ወደዚያው ፡
፲፬፡ ደግሞ ፡ መጡና ፡ ሕዝቡን ፡ አወኩ ። በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ወንድሞቹ ፡ ወዲያው ፡ ጳውሎስን ፡ እስከ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ ሰደዱት ፤
፲፭፡ ሲላስና ፡ ጢሞቴዎስም ፡ በዚያው ፡ ቀሩ ። ጳው ሎስን ፡ የሸኙት ፡ ግን ፡ እስከ ፡ አቴና ፡ አደረሱት ÷ እንደሚቻላቸውም ፡ በፍጥነት ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሲላስና ፡ ወደ ፡ ጢሞቴ ዎስ ፡ ትእዛዝ ፡ ተቀብለው ፡ ሄዱ ።
፲፮፡ ጳውሎስም ፡ በአቴና ፡ ሲጠብቃቸው ፡ ሳለ ÷ በከተማው ፡ ጣዖት ፡ መሙላቱን ፡ እየተመለከተ ፡
፲፯፡ መንፈሱ ፡ ተበሳጨበት ። ስለዚህም ፡ በምኵ

ራብ ፡ ከአይሁድና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከሚያመ ልኩ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ በየቀኑም ፡ በገበያ ፡ ከሚያ ገኛቸው ፡ ጋር ፡ ይነጋገር ፡ ነበር ። ከኤፊቆርስ ፡
፲፰፡ ወንጎና ፡ ኢስጦኢክም ፡ ከተባሉት ፡ ፈላስፎች ፡ አንዳንዶቹ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ተገናኙ ። አንዳን ዶቹም ፡ — ይህ ፡ ለፍላፊ ፡ ምን ፡ ሊናገር ፡ ይወ ዳል ? አሉ ፤ ሌሎችም ፡ የኢየሱስንና ፡ የትን ሣኤውን ፡ ወንጌል ፡ ሰጪ ፡ ሰበከላቸው ፡ — አዲሶ ችን ፡ አማልክት ፡ የሚያወራ ፡ ይመስላል ፡ አሉ ።
፲፱፡ ይዘውም ፡ — ይህ ፡ የምትናገረው ፡ አዲስ ፡ ትም ህርት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ ይቻለናልን ? በጆሮአችን ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ታሰ
፳፡ ማናለህና ፤ እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ እንፈቅዳለን ፡ ብለው ፡
፳፩፡ አርዮስፋጎስን ፡ ወደ ፡ ተባለው ፡ ስፍራ ፡ ወሰዱት ። የአቴና ፡ ሰዎች ፡ ሁሉና ፡ በዚያ ፡ የኖሩ ፡ እንግ ዶች ፡ አዲስ ፡ ነገርን ፡ ከመናገርና ፡ ከመስማት ፡
፳፪፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ ጉዳይ ፡ አይውሉም ፡ ነበርና ።
ጳውሎስም ፡ በአርዮስፋጎስ ፡ መካከል ፡ ቆሞ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ —
የአቴና ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ÷ እናንተ ፡ በሁሉ ፡ ነገር ፡ አማልክትን ፡ እጅግ ፡ እንደምትፈሩ ፡ እመለከ
፳፫፡ ታለሁ ። የምታመልኩትን ፡ እየተመለከትሁ ፡ ሳልፍ ፡ — ለማይታወቅ ፡ አምላክ ፡ የሚል ፡ ጽሕ ፈት ፡ ያለበትን ፡ መሠዊያ ፡ ደግሞ ፡ አግኝቼአለ ሁና ። እንግዲህ ፡ ይህን ፡ ሳታውቁ ፡ የምታመል ኩትን ፡ እኔ ፡ እነግራችኋለሁ ። ዓለሙንና ፡ በእ
፳፬፡ ርሱ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ የፈጠረ ፡ አምላክ ፡ እርሱ ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ጌታ ፡ ነውና ፡ እጅ ፡ በሠራው ፡ መቅደስ ፡ አይኖርም ። እርሱም ፡ ሕይወትንና ፡
፳፭፡ እስትንፋስን ፡ ሁሉንም ፡ ለሁሉ ፡ ይሰጣልና ፡ እን ዳች ፡ እንደሚጐድለው ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ አይገለገ
፳፮፡ ለም ። ምናልባትም ፡ እየመረመሩ ፡ ያገኙት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይፈልጉ ፡ ዘንድ ፡
፳፯፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ እንዲኖሩ ፡ የሰውን ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ ከአንድ ፡ ፈጠረ ÷ የተወሰኑት ንም ፡ ዘመኖችና ፡ ለሚኖሩበት ፡ ስፍራ ፡ ዳርቻ ፡
፳፰፡ መደበላቸው ። ቢሆንም ፡ ከእያንዳንዳችን ፡ የራቀ ፡ አይደለም ። ከእናንተ ፡ ከበለ ፡ ቅኔዎች ፡
፳፱፡ አንዳንዶች ፡ ደግሞ ፡ — እኛ ፡ ደግሞ ፡ ዘመዶቹ ፡ ነንና ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ተናገሩ ÷ በእርሱ ፡ ሕያ ዋን ፡ ነንና ፡ እንንቀሳቀሳለን ፡ እንኖርማለን ።
፴፡ እንግዲህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዘመዶች ፡ ከሆንን ÷ አምላክ ፡ በሰው ፡ ብልሃትና ፡ አሳብ ፡ የተቀረጸ ውን ፡ ወርቅ ፡ ወይም ፡ ብር ፡ ወይም ፡ ድንጋይ ፡ እንዲመስል ፡ እናስብ ፡ ዘንድ ፡ አይገባንም ።
፴፩፡ እንግዲህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያለማወቅን ፡ ወራት ፡ አሳልፎ ፡ አሁን ፡ በየቦታቸው ፡ ንስሐ ፡ ይገቡ ፡
፴፪፡ ዘንድ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ያዛል ። ቀን ፡ ቀጥሮአ ልና ÷ በዚያም ፡ ቀን ፡ በዘጋጀው ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ በዓለሙ ፡ ላይ ፡ በጽድቅ ፡ ሊፈርድ ፡ አለው ፤

፲፯። ፫ ፡ ፫ ። ም. ፭÷፳፱ ። ፲፱ ። ዮሐ. ፮÷፵፬ ። ፲፯ ። ግር. ፭÷፮ ። ፴፭ ። ም. ፲፭÷፲፱ ። ዮሐ. ፫÷፲፭ ። ፴፮ ። ም. ፳፪÷፳፭ ። ፴፯ ። ም. ፳፪÷፳፭ ። ፴፰ ። ማቴ. ፭÷፴፱ ።

፲፯። ፫ ፡ ሉቃ. ፳፬÷፳፮ ። ፭ ፡ ሉቃ. ፳፫÷፮ ። ፳፬ ፡ ም. ፮÷፵፭—፶ ። ፳፭ ፡ መዝ. ፵፱÷፭—፲፪ ። ፳፮ ፡ ዘፍጥ. ፴፪÷፰ ፡ ኢዮብ ፲፪÷፭ ። ፳፰ ፡ ኢዮብ ፲፪÷፲ ። ፳፱ ፡ ኢሳ. ፵÷፲፰ ። ፴ ፡ ም. ፲፱÷፲፯ ፡ ግር. ፭÷፲፱ ፡ ፲፭ ። ፴፩ ፡ ም. ፲÷፵፪ ፡ መዝ. ፺፮÷፲፫ ።

ስለዚህም ፡ እርሱን ፡ ከሙታን ፡ በማስነሣቱ ፡ ሁሉን ፡ አረጋግጦአል ።

፴፪፡ የሙታንንም ፡ ትንሣኤ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ አኩ ሌቶቹ ፡ አፌዙበት ፡ እኩሌቶቹ ፡ ግን ፡ ስለ ዚህ ፡ ነገር ፡ ሁለተኛ ፡ እንሰማሃለን ፡ አሉት ።
፴፫፡ እንዲሁም ፡ ጳውሎስ ፡ ከመከከላቸው ፡ ወጣ ።
፴፬፡ አንዳንዶች ፡ ወንዶች ፡ ግን ፡ ተባብረው ፡ አመ ኑት ፡ ከእነርሱ ፡ ደግሞ ፡ በአርዮስፋጎስ ፡ ያለው ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ፈራጅ ፡ ዲዮናስዮስ ፡ ደማሪስ ፡ የሚሉአትም ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ሌሎችም ፡ ከእ ነርሱ ፡ ጋር ፡ ነበሩ ።

ምዕራፍ ፲፰ ።

፩፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጳውሎስ ፡ ከአቴና ፡ ወጥቶ ፡
፪፡ ወደ ፡ ቆሮንቶስ ፡ መጣ ። በወገኑም ፡ የጳንጦስ ፡ ሰው ፡ የሚሆን ፡ አቂላ ፡ የሚሉትን ፡ አንድ ፡ አይ ሁዳዊ ፡ አገኘ ፡ እርሱም ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ከሚስቱ ፡ ከጵርስቅላ ፡ ጋር ፡ ከኢጣልያ ፡ መጥቶ ፡ ነበር ፡ ስለ ፡ አይሁድ ፡ ከሮሜ ፡ ይወጡ ፡ ዘንድ ፡ ቀላ ውዕያስ ፡ አዘ ፡ ነበርና ፤ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ቀረበ ፡
፫፡ ሥራቸውም ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተቀምጦ ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ ሠሩ ፤ ሥራ
፬፡ ቸው ፡ ድንኳን ፡ መስፋት ፡ ነበረና ። በየሰንበ ቱም ፡ ሁሉ ፡ በምኵራብ ፡ ይነጋገር ፡ ነበር ፡ አይ ሁድንና ፡ የግሪክንም ፡ ሰዎች ፡ ያስረዳ ፡ ነበር ።
፭፡ ሲላስና ፡ ጢሞቴዎስም ፡ ከመቄዶንያ ፡ በወ ረዱ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ ኢየሱስ ፡ እርሱ ፡ ክር ስቶስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለአይሁድ ፡ እየመሰከረ ፡
፮፡ ለቃሉ ፡ ይተጋ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በተቃወሙ ትና ፡ በተሳደቡ ፡ ጊዜ ፡ ልብሱን ፡ እያራገፈ ፡ — ደማችሁ ፡ በራሳችሁ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ እሄዳለሁ ፡
፯፡ አላቸው ። ከዚያም ፡ ወጥቶ ፡ ኢዮስጦስ ፡ ወደ ሚባል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ወደሚያመልክ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ገባ ፤ ቤቱም ፡ በምኵራብ ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ።
፰፡ የምኵራብ ፡ አለቃ ፡ ቀርስጲስም ፡ ከቤተ ፡ ሰዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ በጌታ ፡ አመነ ፡ ከቆሮንቶስ ፡ ሰዎ ችም ፡ ብዙ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ አምነው ፡ ተጠመቁ ።
፱፡ ጌታም ፡ ሌሊት ፡ በራእይ ፡ ጳውሎስን ፡ — አንቴ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ነኝ ፡ ማንም ፡ ክፉ ፡ ሊያደርግብህ ፡ የሚነሣብህ ፡ የለምና ፡ አትፍራ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ተና ገር ፡ ዝምም ፡ አትበል ፤ በዚህ ፡ ቤተማ ፡ ብዙ ፡
፲፩፡ ሕዝብ ፡ አሉኝና ፡ አለው ። በመከከላቸውም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እያስተማረ ፡ ዓመት ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ ተቀመጠ ።
፲፪፡ ጋልዮስም ፡ በአካይያ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ አይሁድ ፡ በአንድ ፡ ልብ ፡ ሆነው ፡ በጳው ሎስ ፡ ላይ ፡ ተነሡ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ወንበርም ፡
፲፫፡ አምጥተው ፡ — ይህ ፡ ሕግን ፡ ተቃውሞ ፡ እግዚ አብሔርን ፡ ያመልኩት ፡ ዘንድ ፡ ሰዎችን ፡ ያበ
፲፬፡ ብላል ፡ አሉ ። ጳውሎስም ፡ አፉን ፡ ሊከፍት ፡ በሰበ ፡ ጊዜ ፡ ጋልዮስ ፡ አይሁድን ፡ — አይሁድ ፡

፲፭፡ ሆይ ፡ ዓመፃ ፡ ወይም ፡ ክፉ ፡ በደል ፡ በሆነ ፡ እን ድታማኙት ፡ በተገባኝ ፡ ስለ ፡ ቃልና ፡ ስለ ፡ ስሞች ፡ ስለ ፡ ሕጋችሁም ፡ የምትከራከሩ ፡ ከሆነ ፡ ግን ፡ ራሳችሁ ፡ ተጠንቀቁ ፡ እኔ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ፈራጅ ፡ አሆን ፡ ዘንድ ፡ አልፈቅድምና ፡ አላ
፲፮፡ ቸው ። ከፍርድ ፡ ወንበርም ፡ ፊት ፡ አስወጣ
፲፯፡ ቸው ። የግሪክ ፡ ሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ የምኵራብ ፡ አለቃ ፡ ሶስቴንስን ፡ ይዘው ፡ በወንበሩ ፡ ፊት ፡ መቱት ፤ በእነዚህም ፡ ነገሮች ፡ ጋልዮስ ፡ ግድ ፡ የለውም ፡ ነበር ።

፲፰፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጳውሎስ ፡ እጅግ ፡ ቀን ፡ ተቀ ምጦ ፡ ወንድሞቹንም ፡ ተሰናብቶ ፡ በመርከብ ፡ ወደ ፡ ሶርያ ፡ ሄደ ፤ ስለትም ፡ ነበረበትና ፡ ራሱን ፡ በክንክራአስ ፡ ተላጨ ፤ ጵርስቅላና ፡ አቂላም ፡
፲፱፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ነበሩ ። ወደ ፡ ኤፌሶንም ፡ በደ ረሱ ፡ ጊዜ ፡ እነዚያን ፡ ከዚያ ፡ ተዋቸው ፡ ራሱ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ምኵራብ ፡ ገብቶ ፡ ከአይሁድ ፡ ጋር ፡
፳፡ ይነጋገር ፡ ነበር ። እነርሱም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እን ዲቀመጥላቸው ፡ ሲለምኑት ፡ እሺ ፡ አላለም ፤
፳፩፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሲሰናበታቸው ፡ — የሚመጣውን ፡ በዓል ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፡ ይገባ ኛል ፤ እግዚአብሔር ፡ ቢፈቅድ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እና ንተ ፡ ደግሞ ፡ እመለሳለሁ ፡ አላቸው ። ከኤፌ ሶንም ፡ በመርከብ ፡ ተነሣ ።
፳፪፡ ወደ ፡ ቂሣርያም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ወጥቶ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰላምታ ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡
፳፫፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ወረደ ። ጥቂት ፡ ቀንም ፡ ቆይቶ ፡ ወጣ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርትንም ፡ ሁሉ ፡ እያጸና ፡ በገላትያ ፡ አገርና ፡ በፍርግያ ፡ በተራ ፡ አለፈ ።
፳፬፡ በወንዱም ፡ የእስክንድርያ ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ አዋቂ ፡ የነበረ ፡ አጵሎስ ፡ የሚሉት ፡ አንድ ፡ አይ ሁዳዊ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ኤፌሶን ፡ ወረደ ፤ እርሱም ፡ በመጻሕፍት ፡ እውቀት ፡ የበረታ ፡ ነበረ ። እርሱ ፡
፳፭፡ የጌታን ፡ መንገድ ፡ የተማረ ፡ ነበረ ፡ የዮሐን ስንም ፡ ጥምቀት ፡ ብቻ ፡ አውቆ ፡ በመንፈስ ፡ ሲቃጠል ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ይናገርና ፡ በትክክል ፡ ያስተምር ፡ ነበር ። እርሱም ፡ በምኵራብ ፡ ገልጦ ፡
፳፮፡ ይናገር ፡ ጀመር ። ጵርስቅላና ፡ አቂላም ፡ በሰ ሙት ፡ ጊዜ ፡ ወስደው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መን ገድ ፡ ከፊት ፡ ይልቅ ፡ በትክክል ፡ ገለጡለት ።
እርሱም ፡ ወደ ፡ አካይያ ፡ ማለፍ ፡ በፈቀደ ፡ ጊዜ ፡
፳፯፡ ወንድሞቹ ፡ አጸናኑት ፡ ይቀበሉትም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ጻፉለት ። በደረሰም ፡ ጊዜ ፡ አምነው ፡ የነበሩትን ፡ በጸጋ ፡ እጅግ ፡ ይጠ
፳፰፡ ቅማቸው ፡ ነበር ። ኢየሱስ ፡ እርሱ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከመጻሕፍት ፡ እየገለጠ ፡ ለአይሁድ ፡ በሁሉ ፡ ፊት ፡ በጽኑ ፡ ያስረዳቸው ፡ ነበርና ።

ምዕራፍ ፲፱ ።

፩፡ አጵሎስም ፡ በቆሮንቶስ ፡ ሳለ ፡ ጳውሎስ ፡ በላ ይኛው ፡ አገር ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ ኤፌሶን ፡ መጣ ፡

፪፡ አንዳንድ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርትንም ፡ አገኘ ። ባመ ናቸው ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀበላች ሁን ? አላቸው ። እነርሱም ፡ — አልተቀበል ንም ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንዳለ ፡ ስንኳ ፡ አል
፫፡ ሰማንም ፡ አሉት ። እንኪያ ፡ በምን ፡ ተጠመቃ ችሁ ? አላቸው ። እነርሱም ፡ — በዮሐንስ ፡ ጥም
፬፡ ቀት ፡ አሉት ። ጳውሎስም ፡ — ዮሐንስ ፡ ከእ ርሱ ፡ በኋላ ፡ በሚመጣው ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስ ቶስ ፡ ያምኑ ፡ ዘንድ ፡ ለሕዝብ ፡ እየተናገረ ፡ በን
፭፡ ስሐ ፡ ጥምቀት ፡ አጠመቀ ፡ አላቸው ። ይህንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ስም ፡ ተጠ
፮፡ መቁ ። ጳውሎስም ፡ እጁን ፡ በሚነካቸው ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወረደባቸው ፡ በልሳኖችም ፡
፯፡ ተናገሩ ፡ ትንቢትም ፡ ተናገሩ ። ሰዎቹም ፡ ሁሉ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ያህሉ ፡ ነበር ።
፰፡ ወደ ፡ ምኵራብም ፡ ገብቶ ፡ ስለ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ መንግሥት ፡ እየተነጋገረና ፡ እያስረዳ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ያህል ፡ በግልጥ ፡ ይናገር ፡
፱፡ ነበር ። አንዳንዶች ፡ ግን ፡ አልከኞች ፡ ሆነው ፡ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ መንገዱን ፡ እየሰደቡ ፡ በላመኑ ፡ ጊዜ ፡ ከእነርሱ ፡ ርቆ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርትን ፡ ለየ ፡ ጢራኖስም ፡ በሚሉት ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡
፲፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ይነጋገር ፡ ነበር ። በእስያም ፡ የኖሩት ፡ ሁሉ ፡ አይሁድም ፡ የግሪክ ፡ ሰዎችም ፡ የጌታን ፡ ቃል ፡ እስኪሰሙ ፡ ድረስ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ።
፲፩፡ እግዚአብሔርም ፡ በጳውሎስ ፡ እጅ ፡ የሚያስ
፲፪፡ ገርም ፡ ተአምራት ፡ ያደርግ ፡ ነበር ። ስለዚህም ፡ ከእሱ ፡ ጨርቅ ፡ ወይም ፡ ልብስ ፡ ወደ ፡ ድው ዮች ፡ ይወስዱ ፡ ነበር ። ደዌያቸውም ፡ ይለቃ ቸው ፡ ነበር ፡ ክፉዎች ፡ መናፍስትም ፡ ይወጡ ፡
፲፫፡ ነበር ። አጋንንትንም ፡ እያወጡ ፡ ይዞሩ ፡ ከነበ ሩት ፡ አይሁድ ፡ አንዳንዶች ፡ — ጳውሎስ ፡ በሚ ሰብከው ፡ በኢየሱስ ፡ እናምላችኋለን ፡ እያሉ ፡ ክፉዎች ፡ መናፍስት ፡ በሉባቸው ፡ ላይ ፡ የጌ ታን ፡ የኢየሱስን ፡ ስም ፡ ይጠሩባቸው ፡ ዘንድ ፡
፲፬፡ ሞከሩ ። የካህናትም ፡ አለቃ ፡ ለሆነ ፡ አስቂዋ ፡ ለሚሉት ፡ ለአንድ ፡ አይሁዳዊ ፡ ይህን ፡ ያደረጉ ፡
፲፭፡ ሰባት ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ። ክፉው ፡ መንፈስ ፡ ግን ፡ መልሶ ፡ — ኢየሱስንስ ፡ አውቀዋለሁ ፤ ጳው ሎስንም ፡ አውቀዋለሁ ፤ አናንተስ ፡ እነማን ፡
፲፮፡ ናችሁ ? አላቸው ። ክፉው ፡ መንፈስም ፡ ያለ በት ፡ ሰው ፡ ዘለልባቸው ፡ ቄስለውም ፡ ከዚያ ፡ ቤት ፡ ዕራቁታቸውን ፡ አስኪሸሹ ፡ ድረስ ፡ በረ
፲፯፡ ታባቸው ፡ አሸነፋቸውም ። ይህም ፡ በኤፌሶን ፡ በሚኖሩት ፡ ሁሉ ፡ በአይሁድና ፡ በግሪክ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ሆነ ፤ በሁሉቱም ፡ ላይ ፡ ፍር ሃት ፡ ወደቀባቸው ፤ የጌታም ፡ የኢየሱስ ፡ ስም ፡
፲፰፡ ተከበረ ፤ አምነውም ፡ ከነበሩት ፡ እጅግ ፡ ሰዎች ፡ ያደረጉትን ፡ እየተናዘዙና ፡ እየተናገሩ ፡ ይመጡ ፡
፲፱፡ ነበር ። ከእስማተኞችም ፡ ብዙዎቹ ፡ መጽሐፋ ቸውን ፡ ሰብስበው ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ አቃ

ጠሉት ፡ ዋጋውም ፡ ቢታሰብ ፡ አምሳ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ ። እንዲህም ፡ የጌታ ፡ ቃል ፡ ፳
በኀይል ፡ ያድግና ፡ ያሸንፍ ፡ ነበር ።
ይህም ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ — ወደ ፳፩፡
ዚያ ፡ ደርሼ ፡ ሮሜን ፡ ዳግሞ ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ ይገ ባኛል ፡ ብሎ ፡ በመቄዶንያና ፡ በአካይያ ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንዲሄድ ፡ በመንፈስ ፡ አሰበ ። ከሚያገለግሉትም ፡ ሁለቱን ፡ ጢሞቴ ፳፪፡
ዎስንና ፡ ኤርስጦንን ፡ ወደ ፡ መቄዶንያ ፡ ልከ ፡ ራሱ ፡ በእስያ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ቆየ ።
በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ስለዚህ ፡ መንገድ ፡ ብዙ ፡ ፳፫፡
ሁከት ፡ ሆነ ። ብር ፡ ሠሪ ፡ የሆነ ፡ ድሜጥሮስ ፡ ፳፬፡
የሚሉት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የአርጤምስን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ምስሎች ፡ በብር ፡ እየሠራ ፡ ለእንዋ ረኞች ፡ እጅግ ፡ ትርፍ ፡ ያገኝ ፡ ነበርና ፤ እነዚህ ፳፭፡
ንም ፡ ይህንም ፡ የሚመስለውን ፡ ሥራ ፡ የሠሩ ትን ፡ ሰብስቦ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ — ሰዎች ፡ ሆይ ፡ ትርፋችን ፡ በዚህ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ታውቃላችሁ ። ይህም ፡ ጳውሎስ ፡ — በእጅ ፡ ፳፮፡
የተሠሩቱ ፡ አማልክት ፡ አይደሉም ፡ ብሎ ፡ በኤ ፌሶን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከጥቂት ፡ ክፍል ፡ በቀር ፡ በእስያ ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብን ፡ እንደ ፡ አስረዳና ፡ እንደ ፡ አሳተ ፡ አይታችኋል ፡ ሰምታችሁማል ። ሥራችንም ፡ እንዲናቅ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ እስያ ፡ ፳፯፡
ሁሉ ፡ ዓለሙም ፡ የሚያመልካት ፡ የታላቂቱ ፡ አምላክ ፡ የአርጤምስ ፡ መቅደስ ፡ ምናምን ፡ ሆኖ ፡ እንዲቈጠር ፡ እንጂ ፡ ታላቅነትዋም ፡ ደግሞ ፡ እንዳይሻር ፡ ያስፈራል ።
ይህንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ቍጣ ፡ ሞላባቸው ፡ — ፳፰፡
የኤፌሶን ፡ አርጤምስ ፡ ታላቅ ፡ ናት ፡ እያሉም ፡ ጮኹ ። ከተማውም ፡ በሙሉው ፡ ተደበለቀ ፡ ፳፱፡
የመቄዶንያም ፡ ሰዎች ፡ የጳውሎስን ፡ ጓደኞች ፡ ጋይዮስንና ፡ አርስጥርኮስን ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ነጥቀው ፡ በአንድ ፡ ልብ ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ ጨዋታ ፡ ስፍራ ፡ ሮጡ ። ጳውሎስም ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ ፴፡
ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ በፈቀደ ፡ ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ከለከሉት ። ከእስያም ፡ አለቆች ፡ ወዳጆቹ ፡ የሆ ፴፩፡
ኑት ፡ አንዳንዶች ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ልከው ፡ ወደ ፡ ጨዋታ ፡ ስፍራ ፡ ራሱን ፡ እንዳይሰጥ ፡ ለመኑት ። ወዲያና ፡ ወዲህም ፡ እያሉ ፡ ይጮኹ ፡ ፴፪፡
ነበር ፤ በጉባኤው ፡ ድብልቅልቅ ፡ ሆኖ ፡ የሚ ይጨጡት ፡ ስንኳ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ተሰበሰቡ ፡ አላወቁም ፡ ነበርና ። አይሁድም ፡ ሲያቀርቡት ፡ ፴፫፡
እስክንድሮስን ፡ ከሕዝቡ ፡ መከከል ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ገፉት ። እስክንድሮስም ፡ በእጁ ፡ ጠቅሶ ፡ በሕ ዝብ ፡ ፊት ፡ እንዲምዋገትላቸው ፡ ወደደ ። አይ ፴፬፡
ሁዳዊ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባወቁ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡ ድምፅ ፡ የኤፌሶን ፡ አርጤምስ ፡ ታላቅ ፡ ናት ፡ እያሉ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ጮኹ ። የከተማይቱም ፡ ጸሐፊ ፡ ሕዝቡን ፡ ጸጥ ፡ ፴፭፡
አሰኝቶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ — የኤፌሶን ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፡ የኤፌሶን ፡ ከተማ ፡ ለታላቂቱ ፡ አርጤ

ምስ ፡ ከሰማይም ፡ ለወረደው ፡ ጣዖትዋ ፡ የመ
ቅደስ ፡ ጠባቂ ፡ መሆንዋን ፡ የማያውቅ ፡ ሰው ፡
፴፭ ፤ ማን ፡ ነው ? ይህንም ፡ የሚክደው ፡ ከሌሰ ÷
ጻዋ ፡ እንድትሉና ፡ አንዳች ፡ በችኰላ ፡ እንዳታ
፴፮ ፤ ደርጉ ፡ ይገበል ። የመቅደስን ፡ ዕቃ ፡ ያልሰረቁ ፡
አምላካችንንም ፡ ያልሰደቡ ፡ እነዚህን ፡ ሰዎች ፡
፴፯ ፤ አምጥታችኋቸዋልና ። ድሜጥሮስና ፡ ከእርሱ ፡
ጋር ፡ ያሉት ፡ አንጥረኞች ፡ ግን ፡ በሰው ፡ ላይ ፡
ነገር ፡ እንዳላቸው ÷ የመጋቢያ ፡ ቀንና ፡ አገረ ፡
ገዢዎች ፡ አሉ ፤ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይምዋገቱ ።
፴፱ ፤ ስለ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ አንዳች ፡
ብትፈልጉ ÷ በተደነገገው ፡ ጉባኤ ፡ ይፈታል ።
፵ ፤ ዛሬ ፡ ስለ ፡ ተደረገው ፡ — ሁከት ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡
እንዳይከሱን ፡ ያስፈራልና ፤ ስለዚህም ፡ ስብሰባ፡
ምለሽ ፡ መስጠት ፡ አንችልም ÷ ምክንያት ፡ የለ
፵፩ ፤ ምና ። ይህንም ፡ ብሎ ፡ ጉባኤውን ፡ ፈታው ።

ምዕራፍ ፡ ፳ ።

፩ ፤ ሁከቱም ፡ ከቀረ ፡ በኋላ ፡ ጳውሎስ ፡ ደቀ ፡ መዛ
ሙርቱን ፡ አስመጥቶ ፡ መከራቸው ፡ ተሰናብቶ
አቸውም ፡ ወደ ፡ መቄዶንያ ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡
፪ ፤ ወጣ ። ያንም ፡ አገር ፡ እያለፈ ፡ በብዙ ፡ ቃል ፡
ከመከራቸው ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ግሪክ ፡ አገር ፡ መጣ ።
፫ ፤ በዚያም ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ ሶርያ ፡
በመርከብ ፡ ሊሄድ ፡ በሰበ ፡ ጊዜ ÷ አይሁድ ፡
ሴራ ፡ ስላደረጉበት ፡ በመቄዶንያ ፡ አልፎ ፡ ይመ
፬ ፤ ለስ ፡ ዘንድ ፡ ቈረጠ ። የሸኙትም ፡ የቤርያው ፡
ሱሲጳጥሮስ ፡ ከተሰሎንቄ ፡ ሰዎችም ፡ አርስጥሮ
ኮስና ፡ ሲከንዱስ ፡ የደርቤኑም ፡ ጋይዮስና ፡ ጢሞ
ቴዎስ ፡ የእስያ ፡ ሰዎችም ፡ ቲኪቆስ ፡ ጥሮፊሞ
፭ ፤ ስም ፡ ነበሩ ። እነዚህም ፡ ወደ ፡ ፊታችን ፡ አል
፮ ፤ ፈው ፡ በጢሮአዳ ፡ ቆዩን ። እኛ ፡ ግን ፡ ከቂጣ ፡
በዓል ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ከፊልጵስዩስ ፡ በመርከብ ፡
ተነሥተን ፡ በአምስት ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ጢሮአዳ ፡
ወደ ፡ እነርሱ ፡ ደረስንና ፡ በዚያ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡
፯ ፤ ተቀመጥን ።

ከሳምንቱም ፡ በመጀመሪያ ፡ ቀን ፡ እንጀራ ፡
ለመቍረስ ፡ ተሰብስበን ፡ ሳለን ÷ ጳውሎስ ፡ በነ
ገው ፡ ሊሄድ ፡ ስላሰበ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ይነጋ
ገር ፡ ነበር ÷ እስከ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊትም ፡ ነገሩን ፡
፰ ፤ አስረዘመ ። ተሰብስበንም ፡ በነበርንበት ፡ ሰገ
፱ ፤ ነት ፡ እጅግ ፡ መብራት ፡ ነበረ ። አውጤኪስ ፡
የሚሉትም ፡ አንድ ፡ ጎበዝ ፡ በመስኮት ፡ ተቀ
ምጦ ፡ ታላቅ ፡ እንቅልፍ ፡ አንቀላፍቶ ፡ ነበር ፤
ጳውሎስም ፡ ነገርን ፡ በስረዘመ ፡ ጊዜ ፡ እንቅ
ልፍ ፡ ከብቦት ፡ ከሦስተኛው ፡ ደርብ ፡ ወደ ፡ ታች ፡
፲ ፤ ወደቀ ÷ ሞቶም ፡ አነሡት ። ጳውሎስም ፡ ወርዶ ፡
በላዩ ፡ ወደቀ ÷ አቅፎም ፡ — ነፍሱ ፡ አለችበትና ፡
፲፩ ፤ አትንጫጩ ፡ አላቸው ። ወጥቶም ፡ እንጀራ ፡
ቈርሶም ፡ በላ ፤ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ እስኪነጋ ፡ ድረስ ፡
፲፪ ፤ ተነጋገረ ፡ እንዲህም ፡ ሄደ ። ብላቴናውንም ፡
ደኅና ፡ ሆኖ ፡ ወሰዱት ፡ እጅግ ፡ ፡ ተጽናኑ ።

እኛ ፡ ግን ፡ ጳውሎስን ፡ ከዚያ ፡ እንቀበለው ፡ ፲፫
ዘንድ ፡ ስላለን ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡ ቀድመን ፡ ሄድ
ንና ፡ ወደ ፡ አሶን ፡ ተነሣን ፤ እርሱ ፡ በመሬት ፡
ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ ስላሰበ ፡ እንደዚህ ፡ አዘ ፡ ነበርና ።
፲፬ ፤ በአሶንም ፡ በገኘን ፡ ጊዜ ፡ ተቀብለነው ፡ ወደ ፡
፲፭ ፤ ሚጢሊኒ ፡ መጣን ። በማግሥቱም ፡ ከዚያ ፡ በባ
ሕር ፡ ተነሥተን ፡ በኪዮ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ደረስን ÷
በነገውም ፡ ወደ ፡ ሳሞን ፡ ተሻገርን ። በትሮጊ
ሊዮም ፡ አድረን ፡ በማግሥቱ ፡ ወደ ፡ ሚሊጢን ፡
፲፮ ፤ መጣን ። ጳውሎስ ፡ በእስያ ፡ እጅግ ፡ እንዳይቀ
መዋ ፡ ኤፌሶንን ፡ ይተው ፡ ዘንድ ፡ ቈርጦ ፡ ነበ
ርና ። ቢቻለውም ፡ በዓለ ፡ ኀምሳን ፡ በኢየሩሳ
ሌም ፡ ይውል ፡ ዘንድ ፡ ይቸኵል ፡ ነበርና ።

ከሚሊጢንም ፡ ወደ ፡ ኤፌሶን ፡ ልከ ፡ የቤተ ፡ ፲፯
ክርስቲያንን ፡ ቀሳውስት * አስጠራቸው ፤
፲፰፤፳፬ ወደ ፡ እርሱም ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ አላ
ቸው ፡ —

ወደ ፡ እስያ ፡ ከገባሁበት ፡ ከመጀመሪያ ፡ ቀን ፡
ጀምሮ ÷ በትሕትና ፡ ሁሉና ፡ በእንባ ፡ ከእይ
ሁድም ፡ ሴራ ፡ በደረሰብኝ ፡ ፈተና ፡ ለጌታ ፡
እየተገዛሁ ፡ ዘመኑን ፡ ሁሉ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ እን
፳ ፤ ዴት ፡ እንደ ፡ ኖርሁ ፡ እናንተው ፡ ታውቃላችሁ ፤
፳፩፤፳፮ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ንስሐንና ፡ በጌታ
ችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ማመንን ፡ ለአይሁ
ድና ፡ ለግሪክ ፡ ሰዎች ፡ እየመሰከርሁ ፡ በጉባኤም ፡
በየቤታችሁም ፡ አወራሁላችሁና ፡ አስተማርኋ
፳፪ ፤ ችሁ ፡ እንጂ ÷ ከሚጠቅማችሁ ፡ ነገር ፡ አንዳች ፡
ስንኳ ፡ አላስቀረሁብችሁም ። አሁንም ÷ እነሆ ÷
፳፫ ፤ እኔ ፡ በመንፈስ ፡ ታስሬ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እሄ
ዳለሁ ÷ በዚያም ፡ የሚያገኘኝ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
፳፬ ፤ አላውቅም ። ነገር ፡ ግን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ —
አስራትና ፡ መከራ ፡ ይቆይሃል ፡ ብሎ ፡ በየከተ
፳፭ ፤ ማው ፡ ሁሉ ፡ ይመሰክርልኛል ። ነገር ፡ ግን ፡
ሩጫዬንና ፡ ከጌታ ፡ ከኢየሱስ ፡ የተቀበልሁትን ፡
አገልግሎት ፡ እርሱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጸጋ ፡
ወንጌልን ፡ መመስከር ፡ እፈጽም ፡ ዘንድ ፡ ነፍሴን ፡
በእኔ ፡ ዘንድ ፡ እንደማትከበር ፡ እንደ ፡ ከንቱ ፡
፳፮ ፤ ነገር ፡ አቈጥራለሁ ። አሁንም ÷ እነሆ ÷ እኔ ፡
የአግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ እየሰበክሁ ፡
በመከከላችሁ ፡ የዘርሁ ፡ ሁላችሁ ፡ ከእንግዲህ ፡
ወዲህ ፡ ፊቴን ፡ እንዳታዩ ፡ አውቃለሁ ። ስለ ፡
፳፯ ፤ ዚህ ፡ እኔ ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ ደም ፡ ንጹሕ ፡ እንደ ፡
ሆንሁ ፡ ዛሬ ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ እመሰክርላችኋለሁ ።
የእግዚአብሔርን ፡ ምክር ፡ ሁሉ ፡ ነግሬአችኋል
፳፰ ፤ ሁና ÷ ምንም ፡ አላስቀረሁባችሁም ። በገዛ ፡
፳፱ ፤ ደሙ ፡ የዋጃትን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤተ ፡ ክር
ስቲያን ፡ ትጠብቁአት ፡ ዘንድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
እናንተን ፡ ጳጳሳት ፡ አድርጎ ፡ ለሾመበት ፡ ለመን
፴ ፤ ጋው ፡ ሁሉና ፡ ለራሳችሁ ፡ ተጠንቀቁ ። ከጌ ፡ ፳፱፤፴
ድሁ ፡ በኋላ ፡ ለመንጋው ፡ የማይራሩ ፡ ጨካኞች ፡
ተኵላዎች ፡ እንዲገቡባችሁ ÷ ደቀ ፡ መዛሙርት
፴፩ ፤ ንም ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ይስቡ ፡ ዘንድ ፡ ጠማማ ፡

፰ ፤ ም. ፲፱ ÷ ፳፬ ። ፯ ፤ ም. ፮ ÷ ፵፪ ። ፵፭ ። ፲ ፤ ፪ ነገሥ. ፱ ÷ ፴፬ ። ፲፯ ፤ ም. ፪ ÷ ፭ ። ፳፫ ፤ ም. ፳ ÷ ፴፬ ። ፳፮ ፤ ም. ፵ ÷ ፵፱ ። ፳፰ ፤ ሉኤ. ፪ ÷ ፩ ።

፳ ። ፲፯ በገሪክ ፡ "ሽማግሌዎች ፡ ይላል ።

ነገርን ፡ የሚናገሩ ፡ ሰዎች ፡ በመካከላችሁ ፡ እን
፴፩ ፤ ዲነሡ ። እኔ ፡ አውቃለሁ ። ስለዚህ ፡ ሦስት ፡
ዓመት ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ በእንባ ፡ እያንዳንዳች
ሁን ፡ ከመገሠጽ ፡ እንዳላቋረጥሁ ፡ እያሰባችሁ ፡
፴፪ ፤ ትኑ ። አሁንም ፡ ለእግዚአብሔርና ፡ ያንጻችሁ ፡
ዘንድ ፡ በቅዱሳንም ፡ ሁሉ ፡ መካከል ፡ ርስትን ፡
ይሰጣችሁ ፡ ዘንድ ፡ ለሚችል ፡ ለጸጋው ፡ ቃል ፡
፴፫ ፤ አደራ ፡ ሰዋቻችኋለሁ ። ከማንም ፡ ብር ፡ ወይም ፡
፴፬ ፤ ወርቅ ፡ ወይም ፡ ልብስ ፡ አልተመኘሁም ፤ እን
ዚህ ፡ እጆቼ ፡ በሚያስፈልገኝ ፡ ነገር ፡ ለእኔና ፡
ከእኔ ፡ ጋር ፡ ላሉት ፡ እንዳገለገሉ ፡ እናንተ ፡ ታው
፴፭ ፤ ቃላችሁ ። እንዲሁ ፡ እየደከማችሁ ፡ ድውዮ
ችን ፡ ልትረዱና ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ — ከሚቀበል ፡
ይልቅ ፡ የሚሰጥ ፡ ብፁዕ ፡ ነው ፡ እንዳለ ፡ የጌ
ታን ፡ የኢየሱስን ፡ ቃል ፡ ልታስቡ ፡ ይገባችሁ ፡
ዘንድ ፡ በሁሉ ፡ አሳየኋችሁ ።

፴፮ ፤ ይህንም ፡ ብሎ ፡ ተንበርክኮ ፡ ከሁላቸው ፡
፴፯ ፤ ጋር ፡ ጸለየ ። ሁሉም ፡ እጅግ ፡ አለቀሱ ÷ ጳው
ሎስንም ፡ አንገቱን ፡ አቅፈው ፡ ይስሙት ፡ ነበር ፤
፴፰ ፤ ይልቁንም ፡ — ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ፊቴን ፡ አታ
ዩም ፡ ስላላቸው ፡ ነገር ፡ እጅግ ፡ አዘኑ ። እስከ ፡
መርከብም ፡ ድረስ ፡ ሸኙት ።

ምዕራፍ ፡ ፳፩ ።

፩ ፤ ከእነርሱም ፡ ተለይተን ፡ ተነሣን ፤ በቀጥታም ፡
ሄደን ፡ ወደ ፡ ቆስ ፡ በነገውም ፡ ወደ ፡ ሩድ ፡ ከዚ
፪ ፤ ያም ፡ ወደ ፡ ጳጥራ ፡ መጣን ፤ ወደ ፡ ፊንቄም ፡ የሚ
ሻገር ፡ መርከብ ፡ አግኝተን ፡ ገባንና ፡ ተነሣን ።
፫ ፤ ቆጵሮስንም ፡ ባየናት ፡ ጊዜ ፡ በስተ ፡ ግራችን ፡
ተውናት ፡ ወደ ፡ ሶርያም ፡ ሄደን ፡ ወደ ፡ ጢሮስ ፡
ደረስን ÷ መርከቡ ፡ ሸክሙን ፡ በዚያ ፡ የሚያ
፬ ፤ ራግፍ ፡ ነበርና ። ደቀ ፡ መዛሙርትንም ፡ በገ
ኘን ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ተቀመጥን ፤
እነርሱም ፡ ጳውሎስን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እን
፭ ፤ ዳይወጣ ፡ በመንፈስ ፡ አሉት ። ጊዜውንም ፡ በፈ
ጸምን ፡ ጊዜ ፡ ወጥተን ፡ ሄድን ፤ ሁላቸውም ፡ ከሚ
ስቶቻቸውና ፡ ከልጆቻቸው ፡ ጋር ፡ እስከ ፡ ከተ
፮ ፤ ማው ፡ ውጭ ፡ ድረስ ፡ ሸኙን ÷ በባሕሩም ፡ ዳር ፡
፯ ፤ ተንበርክከን ፡ ጸለይን ፤ እርስ ፡ በርሳችንም ፡
ተሰነባብተን ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡ ወጣን ÷ እነዚያም ፡
ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ተመለሱ ።

፰ ፤ እኛም ፡ የበሕሩን ፡ መንገድ ፡ ጨርሰን ፡ ከጢ
ሮስ ፡ ወደ ፡ አካ ፡ ደረስን ፡ ለወንድሞችም ፡ ሰላ
፱ ፤ ምታ ፡ ሰጥተን ፡ ከእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡
፲ ፤ ተቀመጥን ። በነገውም ፡ ወጥተን ፡ ወደ ፡ ቂሣ
ርያ ፡ መጣን ÷ ከሰባቱም ፡ አንድ ፡ በሚሆን ፡ በወ
፲፩ ፤ ንጌላዊው ፡ ፊልጶስ ፡ ቤት ፡ ገብተን ፡ በእርሱ ፡
ዘንድ ፡ ተቀመጥን ። ለእርሱም ፡ ትንቢት ፡ የሚ
፲፪ ፤ ናገሩ ፡ አራት ፡ ደናግል ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ነበ
፲፫ ፤ ሩት ። አያሴ ፡ ቀንም ፡ ተቀምጠን ፡ ሳለን ፡ ነቢይ ፡
የነበረ ፡ አጋቦስ ፡ የሚሉት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከይ

ሁዳ ፡ ወረደ ። ወደ ፡ እኛም ፡ መጣና ፡ የጳውሎ
፲፩ ፤ ስን ፡ መታጠቂያ ፡ ወስዶ ፡ የገዛ ፡ እጁንና ፡ እግ
ሩን ፡ አስሮ ፡ — እንዲሁ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ —
ይህ ፡ መታጠቂያ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ አይሁድ ፡ በኢ
የሩሳሌም ፡ እንደዚህ ፡ ያስሩታል ፡ በአሕዛብም ፡
እጅ ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጡታል ፡ ይላል ፡ አለ ።
፲፪ ፤ ይህንም ፡ በሰማን ፡ ጊዜ ፡ እኛም ፡ በዚያ ፡ የሚ
ኖሩትም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንዳይወጣ ፡ ለመ
ንነው ። ጳውሎስ ፡ ግን ፡ መልሶ ፡ — እያለቀሳ
፲፫ ፤ ችሁ ፡ ልቤንም ፡ እየሰበራችሁ ፡ ምን ፡ ማድረጋ
ችሁ ፡ ነው ? እኔ ፡ ስለ ፡ ጌታ ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ስም ፡
በኢየሩሳሌም ፡ ለመሞት ፡ እንኳ ፡ ተሰናድቼአ
ለሁ ፡ እንጂ ፡ ለእስራት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ አለ ።
፲፬ ፤ ምክርንም ፡ ሊቀበል ፡ አልቻለም ፡ ብለን ፡ ዝም ፡ አልን ።
ከዚህም ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ተዘጋጅተን ፡ ወደ ፡ ፲፭
፲፮ ፤ ኢየሩሳሌም ፡ ወጣን ። በቂሣርያም ፡ ከነበሩ ፡
ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ አንዳንዶች ፡ ደግሞ ፡ ከእኛ ፡
ጋር ፡ መጡ ÷ እነርሱም ፡ ወደምናድርበት ፡ ወደ ፡
ቀደመው ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ወደ ፡ ቆጵሮሱ ፡
ምናሶን ፡ ወደሚሉት ፡ ቤት ፡ መሩን ።

ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በደረስን ፡ ጊዜ ፡ ወንድ ፲፯
፲፰ ፤ ሞች ፡ በደስታ ፡ ተቀበሉን ። በነገውም ፡ ጳው ፲፰፤፳፫
ሎስ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘንድ ፡ ገባ ፡
ሽማግሌዎችም ፡ ሁሉ ፡ መጡ ። ሰላምታም ፡ ከቀ ፲፱
ረበላቸው ፡ በኋላ ፡ በእርሱ ፡ ማገልገል ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ያደረገውን ፡ በእ
ያንዳንዱ ፡ ተረከላቸው ። እነርሱም ፡ በሰሙ ፡ ፳፩
ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑ ፡ አሉትም ፡ —
ወንድም ፡ ሆይ ÷ በእይሁድ ፡ መካከል ፡ አምነው ፡
የነበሩት ፡ ስንት ፡ አእላፋት ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ታያ
ለህ ፤ ሁላቸውም ፡ ለሕግ ፡ የሚቀኑ ፡ ናቸው ።
ልጆቻቸውንም ፡ እንዳይገርዙ ፡ በሥርዓትም ፡ ፳፩
እንዳይሄዱ ፡ ብለህ ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ያሉት ፡
አይሁድ ፡ ሁሉ ፡ ሙሴን ፡ ይክዱ ፡ ዘንድ ፡ እንድ
ታስተምር ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ነግረዋቸዋል ። እንግ ፳፪
ዲህ ፡ ምን ፡ ይሁን ? የአንተን ፡ መምጣት ፡ ይሰማ
ሉና ፡ ብዙዎች ፡ የግድ ፡ ሰይሰበሰቡ ፡ አይቀሩም ።
እንግዲህ ፡ ይህን ፡ የምንልህን ፡ አድርግ ፡ ስለት ፡ ፳፫
ያለባቸው ፡ አራት ፡ ሰዎች ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ አሉ ።
እነዚህንም ፡ ይዘህ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ንጹ ÷ ራሳ ፳፬
ቸውንም ፡ እንዲላጩ ፡ ገንዘብ ፡ ክፈልላቸው ፤
ሁሉም ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ የተማሩት ፡ ከንቱ ፡ እንደ ፡
ሆነና ፡ አንተ ፡ ራስህ ፡ ደግሞ ፡ ሕጉን ፡ እየጠበ
ቅህ ፡ በሥርዓት ፡ እንድትመላለስ ፡ ያውቃሉ ።
አምነው ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ አሕዛብ ፡ ግን ፡ ለጣዖት ፡ ፳፭
ከተሠዋ ፡ ከደምም ፡ ከታነቀም ፡ ከዝሙትም ፡
ነፍሳቸውን ፡ እንዲጠብቁ ፡ ፈርደን ፡ እኛ ፡ ጽፈ
ንላቸዋል ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ ሰዎችን ፡ ፳፮
ይዞ ፡ በማግሥቱ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ እየነጻ ÷ መንጻ
ታቸውን ፡ የሚፈጽሙበትን ፡ ቀን ፡ አስታውቆ ፡

፩ ። ፴፪ ፤ ም. ፲፫ ÷ ፫ ። ፲፫ ፤ ም. ፲፭ ÷ ፳፰ ። ፳፭ ፤ ም. ፳፩ ÷ ፳፭ ። ፳፰ ፤ ም. ፲፮ ÷ ፳፪ ። ፳፱ ፤ ም. ፲፯ ÷ ፳፭ ።

ወደ ፡ መቅደስ ፡ ገባ ። በዚያም ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ እያ
ንዳንዳቸው ፡ መሥዋዕትን ፡ አቀረቡ ።
፳፭፡፳፮፡ ሰባቱ ፡ ቀንም ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ሲቀርብ ፡
ከእስያ ፡ የመጡ ፡ አይሁድ ፡ በመቅደስ ፡ አይተ
ውት ፡ ሕዝብን ፡ ሁሉ ፡ አወኩና ፡— የእስራኤል ፡
ሰዎች ፡ ሆይ ፥ እርዱን ፤ ሕዝብን ፡ ሕግንም ፡ ይህ
ንም ፡ ስፍራ ፡ ሲቃወም ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ በየስ
ፍራው ፡ የሚያስተምረው ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ ነው ፤
ጨምሮም ፡ የግሪክን ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡
መቅደስ ፡ አግብቶ ፡ ይህን ፡ የተቀደሰ ፡ ስፍራ ፡
አርክሶአል ፡ ብለው ፡ እየጮኹ ፡ እጃቸውን ፡
፳፱፡ ጫኑበት ። በፊት ፡ የኤፌሶኑን ፡ ጥሮፊሞስን ፡
ከእርሱ ፡ ጋር ፡ በከተማ ፡ አይተውት ፡ ነበርና ፤
ጳውሎስም ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ያገባው ፡ መስሎ
፴፡ አቸው ፡ ነው ። ከተማውም ፡ ሁሉ ፡ ታወከ ፡
ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ተሰበሰቡ ፤ ጳውሎስንም ፡
ይዘው ፡ ከመቅደስ ፡ ውጭ ፡ ጐተቱት ፥ ወዲያ
፴፩፡ ውም ፡ ደጆች ፡ ተዘጉ ። ሊገድሉትም ፡ ሰፈ
ልጉ ፡—ኢየሩሳሌም ፡ ፈጽማ ፡ ታወከች ፡ የሚል ፡
፴፪፡ ወሬ ፡ ወደ ፡ ጭፍራው ፡ ሻለቃ ፡ ወጣ ፤ እርሱም ፡
ያን ፡ ጊዜ ፡ ወታደሮችን ፡ ከመቶ ፡ አለቆች ፡
ጋር ፡ ይዞ ፡ እየሮጠ ፡ ወረደባቸው ፤ እነርሱም ፡
የሻለቃውንና ፡ ወታደሮችን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ጳው
፴፫፡ ሎስን ፡ መምታት ፡ ተዉ ። በዚያን ፡ ጊዜም ፡
የሻለቃው ፡ ቀርቦ ፡ ያዘውና ፡ በሁለት ፡ ሰንሰለት ፡
ይታሰር ፡ ዘንድ ፡ አዘ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ ምን ፡
፴፬፡ እንዳደረገ ፡ ጠየቀ ። ሕዝቡም ፡ እኵሌቶቹ ፡
እንዲህ ፡ እኵሌቶቹም ፡ እንዲያ ፡ እያሉ ፡ ይጮኹ ፡
ነበር ፤ ስለ ፡ ጫጫታውም ፡ እርግጡን ፡ ማወቅ ፡
ባልተቻለ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ወታደሮች ፡ ሰፈር ፡ ይወ
፴፭፡ ስዱት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ። ወደ ፡ ደረጃውም ፡ በደ
ረሰ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ግፊያ ፡ ወታደሮች ፡
፴፮፡ እንዲሸከሙት ፡ ሆነ ፤ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ተከተሉ ፡ አሰው
ግደው ፡ እያሉና ፡ እየጮኹ ፡ ይከተሉ ፡ ነበርና ።
፴፯፡ ወደ ፡ ሰፈርም ፡ ሊያገቡት ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡
ጳውሎስ ፡ የሻለቃውን ፡— አንድ ፡ ነገር ፡ ብነግ
ርህ ፡ ትፈቅዳለህን ፧ አለው ። እርሱም ፡— የግ
፴፰፡ ሪክ ፡ ቋንቋ ፡ ታውቃለህን ፧ አንተ ፡ ከዚህ ፡
ዘመን ፡ አስቀድሞ ፡ ከነፍስ ፡ ገዳዮች ፡ አራቱን ፡
ሺህ ፡ ሰዎች ፡ አሸፍተህ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡
ያወጣህ ፡ የግብፅ ፡ ሰው ፡ አይደለህምን ፧ አለ ።
፴፱፡ ጳውሎስ ፡ ግን ፡— እኔስ ፡ አይሁዳዊ ፡ በኪልቅያ ፡
ያለው ፡ የጠርሴስ ፡ ሰው ፡ ሆኜ ፡ ስመ ፡ ዋር ፡
በሆነ ፡ ከተማ ፡ የምኖር ፡ ነኝ ፤ ለሕዝቡ ፡ እናገር ፡
ዘንድ ፡ እንድትፈቅድልኝ ፡ አለምንህለሁ ፡ አለ ።
፵፡ በፈቀደለትም ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ በደረጃው ፡
ላይ ፡ ቆሞ ፡ በእጁ ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ ጠቀሰ ፤ እጅ
ግም ፡ ጸጥታ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በዕብራይስጥ ፡ ቋንቋ ፡
እየተናገረ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

፩፡ እናንተ ፡ ወንድሞች ፡ አባቶችም ፡ አሁን ፡ ለእ
ናንተ ፡ ነገሬን ፡ ስገልጥ ፡ ስሙኝ ።
፪፡ በዕብራይስጥም ፡ ቋንቋ ፡ ሲናገር ፡ በሰሙ ፡
ጊዜ ፡ ከፊት ፡ ይልቅ ፡ ዝም ፡ አሉ ። እርሱም ፡
አለ ፡—
፫፡ እኔ ፡ የኪልቅያ ፡ በምትሆን ፡ በጠርሴስ ፡ የተወ
ለድሁ ፡ በዚችም ፡ ከተማ ፡ በገማልያል ፡ እግር ፡
አጠገብ ፡ ያደግሁ ፡ የአባቶችንም ፡ ሕግ ፡ ጠን
ቅቄ ፡ የተማርሁ ፡ ዛሬውንም ፡ እናንተ ፡ ሁሉ ፡
እንድትሆኑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቀናተኛ ፡ የሆንሁ ፡
አይሁዳዊ ፡ ሰው ፡ ነኝ ። ወንዶችንም ፡ ሴቶች
፬፡ ንም ፡ እያሰርሁ ፡ ወደ ፡ ወኅኒም ፡ አሳልፌ ፡ እየሰ
ጠሁ ፡ ይህን ፡ መንገድ ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ አሳ
ደድሁ ። እንዲህም ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ደግሞ ፡
፭፡ ሽማግሌዎቹም ፡ ሁሉ ፡ ይመሰክሩልኛል ፤ ከእነ
ርሱ ፡ ደግሞ ፡ መልእክትን ፡ ለወንድሞቻቸው ፡
ተቀብዬ ፡ በደማስቆ ፡ ያሉትን ፡ ደግሞ ፡ ታስ
ረው ፡ እንዲቀጡ ፡ ውጭ ፡ ጐተቱት ፡ ወዲ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ላመጣ ፡
ወደዚያ ፡ እሄድ ፡ ነበር ።
፮፡ ስሄድም ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ በቀረብሁ ፡ ጊዜ ፡
ቀትር ፡ ሲሆን ፡ ድንገት ፡ ከሰማይ ፡ ታላቅ ፡ ብር
ሃን ፡ በዙሪያዬ ፡ አንጸባረቀ ፤ በምድርም ፡ ላይ ፡
ወድቄ ፡— ሳውል ፡ ሳውል ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ታሳድደ
ኛለህ ፧ የሚለኝን ፡ ድምፅ ፡ ሰማሁ ። እኔም ፡
፰፡ መልሼ ፡— ጌታ ፡ ሆይ ፡ አንተ ፡ ማን ፡ ነህ ፧
አልሁ ። እርሱም ፡— አንተ ፡ የምታሳድደኝ ፡
የናዝሬቱ ፡ ኢየሱስ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አለኝ ። ከእኔ ፡
፱፡ ጋር ፡ የነበሩትም ፡ ብርሃኑን ፡ አይተው ፡ ፈሩ ፡
የሚናገረኝን ፡ የእርሱን ፡ ድምፅ ፡ ግን ፡ አልሰ
ሙም ። ጌታ ፡ ሆይ ፡ ምን ፡ ላድርግ ፧ አልሁት ።
፲፡ ጌታም ፡— ተነሥተህ ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ ሂድና ፡
ታደርገው ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ታዘዘው ፡ ሁሉን ፡
በዚያ ፡ ይነግሩሃል ፡ አለኝ ። ከዚያ ፡ ብርሃንም ፡
ከብር ፡ የተነሣ ፡ ማየት ፡ በይሆንልኝ ፡ ከእኔ ፡
ጋር ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ እጄን ፡ ይዘው ፡ እየመ
ሩኝ ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ ደረስሁ ።
፲፪፡ በዚያም ፡ የኖሩት ፡ አይሁድ ፡ ሁሉ ፡ የመሰከሩ
ለት ፡ እንደ ፡ ሕጉም ፡ በጸሎት ፡ የተጋ ፡ ሐናንያ ፡
፲፫፡ የሚሉት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ። እርሱም ፡ ወደ ፡
እኔ ፡ መጥቶ ፡ በአጠገቤም ፡ ቆሞ ፡— ወንድሜ ፡
ሳውል ፡ ሆይ ፡ እይ ፡ አለኝ ። እኔም ፡ ያን ፡ ጊዜ
፲፬፡ ውን ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ አየሁ ። እርሱም ፡ አለኝ ፡—
የአባቶቻችን ፡ አምላክ ፡ ፈቃዱን ፡ ታውቅ ፡
ዘንድና ፡ ጻድቁን ፡ ታይ ፡ ዘንድ ፡ ከአፉም ፡ ድም
፲፭፡ ፅን ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ፡ አስቀድሞ ፡ መርጦሃል ፤
በዋኸውና ፡ በሰማኸው ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡
፲፮፡ ምስክር ፡ ትሆንለታለህና ። አሁንስ ፡ ለምን ፡
፲፯፡ ትዘገያለህ ፧ ተነሣና ፡ ስሙን ፡ እየጠራህ ፡ ተጠ
መቅ ፡ ኀጢአትህም ፡ ታጠብ ።
፲፯፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ከተመለስሁ ፡ በኋላ ፡
፲፰፡ በመቅደስ ፡ ስጸልይ ፡ ተመሰጥ ፡ መጣብኝ ፥ እር
ሱም ፡— ፍጠን ፡ ከኢየሩሳሌምም ፡ ቶሎ ፡
ውጣ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ የምትመሰክረውን ፡ አይቀበ

፲፱፡ ሉህምና ፡ ሲለኝ ፡ አየሁት ። እኔም ፡— ጌታ ፡
ሆይ ፡ በእንተ ፡ የሚያምኑትን ፡ በምኵራብ ፡
ሁሉ ፡ እኔ ፡ በወኅኒ ፡ አገባና ፡ እደበድብ ፡ እንደ ፡
፳፡ ነበርሁ ፡ እነርሱ ፡ ያውቃሉ ፤ የሰማዕትህንም ፡
የእስጢፋኖስን ፡ ደም ፡ ባፈሰሱ ፡ ጊዜ ፡ ራሴ ፡
ደግሞ ፡ በአጠገባቸው ፡ ስቆም ፡ ተስማምቼ ፡
የገዳዮችን ፡ ልብስ ፡ እጠብቅ ፡ ነበር ፡ አልሁ ።
፳፩፡ እርሱም ፡— ሂድ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ ከዚህ ፡
ወደ ፡ ሩቅ ፡ እልክሃለሁና ፡ አለኝ ።
፳፪፡ እስከዚህም ፡ ቃል ፡ ድረስ ፡ ይሰሙት ፡ ነበር ፡
ድምፃቸውንም ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡— እንደዚህ ፡
ያለውን ፡ ሰው ፡ ከምድር ፡ አስወግደው ፤ በሕይ
ወት ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ አይገባውምና ፡ አሉ ።
፳፫፡ ሲጮኹና ፡ ልብሳቸውን ፡ ሲወረውሩ ፡ ትቢያ
፳፬፡ ንም ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ሲበትኑ ፡ የሻለቃው ፡ ወደ ፡
ሰፈሩ ፡ እንዲያገቡት ፡ አዘዘ ፡ እንደዚህም ፡ የጮ
ኹበትን ፡ ምክንያት ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡— እየገ
፳፭፡ ረፋቸው ፡ መርምሩት ፡ አላቸው ። በጠፍጋ ፡
በገተሩት ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ በአጠገቡ ፡ የቆመ
ውን ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡— የሮሜን ፡ ሰው ፡ ያለ ፡
ፍርድ ፡ ትገርፉ ፡ ዘንድ ፡ ተፈቅዶላችኋልን ፧
፳፮፡ አለው ። የመቶ ፡ አለቃውም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡
ወደ ፡ ሻለቃው ፡ ቀርቦ ፡— ይህ ፡ ሰው ፡ ሮማዊ ፡
ነውና ፡ ታደርገው ፡ ዘንድ ፡ ካለህ ፡ ተጠበቅ ፡
፳፯፡ ብሎ ፡ ነገረው ። የሻለቃውም ፡ ቀርቦ ፡— አንተ ፡
ሮማዊ ፡ ነህን ፧ ንገረኝ ፡ አለው ። እርሱም ፡—
፳፰፡ አዎን ፡ አለ ። የሻለቃውም ፡ መልሶ ፡— እኔ ፡
ይህን ፡ ዜግነት ፡ በብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አገኘሁት ፡
አለ ። ጳውሎስም ፡— እኔ ፡ ግን ፡ በእርስዋ ፡ ተወ
፳፱፡ ለድሁ ፡ አለ ። ስለዚህም ፡ ሊመረምሩት ፡ ያሰ
ቡት ፡ ከእርሱ ፡ ወዲያው ፡ ተለዩ ። የሻለቃውም ፡
ደግሞ ፡ ሮማዊ ፡ መሆኑን ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ፈራ ፡
፴፡ አሳሰሮት ፡ ነበርና ።
በማግሥቱም ፡ አይሁድ ፡ የከሰሱት ፡ በምን ፡
ምክንያት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እርግጡን ፡ ያውቅ ፡
ዘንድ ፡ አሰበ ፡ ፈታው ፡ የከህናት ፡ አለቆችና ፡
ሸንጎውም ፡ ሁሉ ፡ ይሰበሰቡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡
ጳውሎስንም ፡ አውርዶ ፡ በፊታቸው ፡ አቆ
መው ።

ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

፩፡ ጳውሎስም ፡ ሸንጎውን ፡ ትኵር ፡ ብሎ ፡ ተመ
ልክቶ ፡— ወንድሞች ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ እስከዚች ፡
ቀን ፡ ድረስ ፡ በመልካም ፡ ሕሊና ፡ ሁሉ ፡ በእግ
፪፡ ዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ኖሬአለሁ ፡ አለ ። ሊቀ ፡ ካህ
ናቱም ፡ ሐናንያ ፡ አፉን ፡ ይመቱት ፡ ዘንድ ፡ በአ
፫፡ ጠገቡ ፡ ቆመው ፡ የነበሩትን ፡ አዘዘ ። በዚያን ፡
ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡— አንተ ፡ በኖራ ፡ የተለሰነ ፡ ግድ
ግዳ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንተን ፡ ይመታ ፡ ዘንድ ፡
አለው ፤ አንተ ፡ በሕግ ፡ ልትፈርድብኝ ፡ ተቀ

ረኛው ፡ ጳውሎስ ፡ ጠርቶ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ እንድ
፲፱ ወስደው ፡ ለመነኝ ፡ አለው ። የሽለቃውም ፡
እጁን ፡ ይዞ ፡ ፈቀቅ ፡ አለና ፡ ለብቻው ፡ ሆኖ ፡—
የምታወራልኝ ፡ ነገር ፡ ምንድር ፡ ነው ? ብሎ ፡
፳፩ ጠየቀው ። እርሱም ፡— አይሁድ ፡ ስለ ፡ ጳው
ሎስ ፡ ከፊት ፡ ይልቅ ፡ አጥብቀህ ፡ እንደምትመ
ረምር ፡ መስለህ ÷ ነገ ፡ ወደ ፡ ሸንጎ ፡ ታወርደው ፡
፳፪ ዘንድ ፡ ሊለምኑህ ፡ ተስማምተዋል ። እንግዲህ ፡
አንተ ፡ በጅ ፡ አትበላቸው ። እስኪገድሉት ፡
ድረስ ፡ እንዳይበሉና ፡ እንዳይጠጡ ፡ ተማም
ለው ፡ ከእነርሱ ፡ ከአርባ ፡ የሚበዙ ፡ ሰዎች ፡ ያደቡ
በታልና ። አውንም ፡ የተዘጋጁ ፡ ናቸው ፡ የአን
፳፫ ተንም ፡ ምላሽ ፡ ይጠብቃሉ ፡ አለው ። የሽለቃ
ውም ፡— ይህን ፡ ነገር ፡ ለእኔ ፡ ማመልከትህን ፡
ለማንም ፡ እንዳትገልጥ ፡ ብሎ ፡ ከዘዘ ፡ በኋላ ፡
ብላቴናውን ፡ አሰናበተው ።
፳፫ ከመቶ ፡ አለቆቹም ፡ ሁለት ፡ ጠርቶ ፡— ወደ ፡
ቂሣርያ ፡ ይሄዱ ፡ ዘንድ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ወታደ
ሮችንና ፡ ሰባ ፡ ፈረሰኞችን ፡ ሁለት ፡ መቶም ፡
ባለ ፡ ጦር ፡ መሣሪያዎችን ፡ ከሌሊቱ ፡ በሦስተ
፳፬ ኛው ፡ ሰዓት ፡ አዘጋጁ ፡ አላቸው ። ጳውሎስ
ንም ፡ ወደ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ወደ ፡ ፊልክስ ፡ በደኅና ፡
እንዲያደርሱት ፡ የሚያስቀምጡበትን ፡ ከብት ፡
፳፭ ያዘጋጁ ፡ ዘንድ ፡ አዘዛቸው ። ደብዳቤም ፡ ጻፈ ፡
እንዲህ ፡ የሚል ፡—
፳፮ ከቀላውዴዎስ ፡ ሉስዮስ ፡ ወደ ፡ ክቡር ፡ አገረ ፡
ገዥ ፡ ወደ ፡ ፊልክስ ። ሰላም ፡ ለአንተ ፡ ይሁን ።
፳፯ ይህን ፡ ሰው ፡ አይሁድ ፡ ይዘው ፡ ሊገድሉት ፡
በሰቡ ፡ ጊዜ ፡ ከጭፍሮቹ ፡ ጋር ፡ ደርሼ ፡ አዳን
ሁት ÷ ሮማዊ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አውቄ ፡ ነበርና ።
፳፰ የሚከሰስበትንም ፡ ምክንያት ፡ አውቅ ፡ ዘንድ ፡
፳፱ አስቤ ፡ ወደ ፡ ሸንጎአቸው ፡ አወረድሁት ። በሕ
ጋቸውም ፡ ስለ ፡ መከራከር ፡ እንደ ፡ ከሰሱት ፡
አገኘሁ ፡ እንጂ ፡ ለሞት ፡ ወይም ፡ ለእስራት ፡
፴ የሚያደርስ ፡ ክስ ፡ አይደለም ። በዚህም ፡ ሰው ፡
አይሁድ ፡ ሴራ ፡ እንዲያደርጉበት ፡ በመለከ
ቹኝ ፡ ጊዜ ፡ ያን ፡ ጊዜውን ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ሰደ
ድሁት ÷ ከሳሾቹንም ፡ ደግሞ ፡ በፊትህ ፡ ይከ
ሱት ፡ ዘንድ ፡ አዘዝኋቸው ። ደኅና ፡ ሁን ።
፴፩ ወታደሮቹም ፡ እንደ ፡ ታዘዙት ፡ ጳውሎስን ፡
ይዘው ፡ በሌሊት ፡ ወደ ፡ አንቲጳጥሮስ ፡ አደረ
፴፪ ሱት ። በነገውም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ይሄዱ ፡ ዘንድ ፡
ፈረሰኞችን ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ሰፈር ፡ ተመለሱ ።
፴፫ እነዚያም ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ ገብተው ፡ ደብዳቤ
ውን ፡ ለአገረ ፡ ገዥ ፡ በሰጡ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎ
፴፬ ስን ፡ ደግሞ ፡ በፊቱ ፡ አቆሙት ። ከነበበውም ፡
በኋላ ፡ የወዴት ፡ አውራጃ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጠየ
ቀው ። የኪልቅያ ፡ ሰው ፡ መሆኑንም ፡ ባወቀ ፡
፴፭ ጊዜ ፡— ከሳሾችህ ፡ ደግሞ ፡ ሲመጡ ፡ እሰማሃ
ለሁ ፡ አለው ። በሄሮድስ ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ይጠ
ብቁት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ።

ምዕራፍ ፳፬ ።

ከአምስት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ፩
ሐናንያ ፡ ከሽማግሌዎችና ፡ ጠርጠሉስ ፡ ከሚ
ሉት ፡ ከአንድ ፡ ጠበቃ ፡ ጋር ፡ ወረደ ። እነርሱም ፡
ስለ ፡ ጳውሎስ ፡ ለአገረ ፡ ገዥ ፡ አመለከቱት ።
፪ በተጠራም ፡ ጊዜ ፡ ጠርጠሉስ ፡ ይከሰው ፡ ዘንድ ፡
፫ ጀመረ ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡—
ከቡር ፡ ፊልክስ ፡ ሆይ ÷ በእንተ ፡ በኩል ፡ ብዙ ፡
ሰላም ፡ ስለምናገኝ ፡ ለዚህም ፡ ሕዝብ ፡ በአሳብህ ፡
በየነገሩ ፡ በየስፍራውም ፡ መልካም ፡ መሻሻል ፡
ስለሚሆንለት ÷ በፍጹም ፡ ምስጋና ፡ እንቀበለዋ
፬ ለን ። ነገር ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ እንዳላቆይህ ፡ በቸርነ
ትህ ፡ በአጭሩ ፡ ትሰማኝ ፡ ዘንድ ፡ እለምንሃለሁ ።
፭ ይህ ፡ ሰው ፡ በሽታ ፡ ሆኖ ፡ በዓለም ፡ ባሉት ፡ አይ
ሁድ ፡ ሁሉ ፡ ሁከት ፡ ሲያስነሣ ÷ የመናፍቃን ፡
የናዝራውያን ፡ ወገን ፡ መሪ ፡ ሆኖ ፡ አግኝተነዋ
፮ ልና ። መቅደስንም ፡ ደግሞ ፡ ሊያረክስ ፡ ሲሞ
ክር ፡ ያዝነው ÷ እንደ ፡ ሕጋችንም ፡ እንፈርድ
፯ በት ፡ ዘንድ ፡ ወደድን ። ነገር ፡ ግን ፡ የሻለቃው ፡
ሉስዮስ ፡ መጥቶ ፡ በብዙ ፡ ኃይል ፡ ከእጃችን ፡
፰ ወሰደው ÷ ከሳሾቹንም ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ይመጡ ፡
ዘንድ ፡ አዘዘ ። አንተም ፡ ራስህ ፡ እርሱን ፡ መር
ምረህ ፡ እኛ ፡ ስለምንከስበት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ልታ
ውቅ ፡ ትችላለህ ።
፱ አይሁድም ፡ ደግሞ ፡— ይህ ፡ ነገር ፡ እንዲሁ ፡
ነው ፡ እያሉ ፡ ተስማሙ ።
፲ ገዥም ፡ በጠቀሰው ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ መለሰ ፡
እንዲህ ፡ ሲል ፡—
ከብዙ ፡ ዘመን ፡ ጀምረህ ፡ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ አንተ ፡
ፈራጅ ፡ እንደ ፡ ሆንህ ፡ አውቃለሁና ፡ ደስ ፡ እያ
፲፩ ለኝ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ነገር ፡ እመልሳለሁ ። እሰግድ ፡
ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ከወጣሁ ፡ ከአሥራ ፡
ሁለት ፡ ቀን ፡ እንዳይበልጥ ፡ ልታውቀው ፡ ትች
፲፪ ላለህ ። ከእንድም ፡ ስንኳ ፡ ስንጋገር ፡ ወይም ፡
ሕዝብን ፡ ስሰበስብ ፡ በመቅደስ ፡ ቢሆን ፡ በምሥ
ራብም ፡ ቢሆን ፡ በከተማም ፡ ቢሆን ፡ አላገኙ
፲፫ ኝም ። አሁንም ፡ ስለሚከሱኝ ፡ ያስረዱህ ፡
፲፬ ዘንድ ፡ አይችሉም ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ እመሰክ
ርልሃለሁ ። በሕገ ፡ ያለውን ፡ በነቢያት ፡ የተጻ
ፉትን ፡ ሁሉ ፡ አምኜ ÷ የአባቶቼን ፡ አምላክ ፡ እን
ርሱ ፡ ኑፋቄ ፡ ብለው ፡ እንደሚጠሩት ፡ መንገድ ፡
አመልካለሁ ። እነዚህም ፡ ራሳቸው ፡ ደግሞ ፡
፲፭ የሚጠብቁት ÷ ጻድቃንም ፡ ዓመፀኞችም ፡ ከሙ
ታን ፡ ይነሡ ፡ ዘንድ ፡ እንዳላቸው ፡ ተስፋ ፡ በእ
ግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አለኝ ። ስለዚህ ፡ እኔ ፡
ደግሞ ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ሁል
ጊዜ ፡ ነውር ፡ የሌለበት ፡ ሕሊና ፡ ትኖረኝ ፡ ዘንድ ፡
፲፮ እተጋለሁ ። ከብዙ ፡ ዓመትም ፡ በኋላ ፡ ለሕ
ዝቤ ፡ ምጽዋትና ፡ መሥዋዕት ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፡
፲፯ መጣሁ ። ይህንም ፡ ሳደርግ ፡ ሳለሁ ፡ ሕዝብ ፡ ሳይ
ሰበሰብ ፡ ሁከትም ፡ ሳይሆን ፡ በመቅደስ ፡ ስነጻ ፡

ግጽ ። ፳፫ ፤ ም· ፳፭ ÷ ፴—፴፪ ፤ ፳፪ ÷ ፳፭ ። ፳፭ ፤ ም· ፳፪ ÷ ፴ ።
ግጽ ። ፭ ፤ ም· ፳፫ ÷ ፪ ። ፮ ፤ ም· ፲፯ ÷ ፯ ፣ ፯ ። ፲፩ ፤ ዳን· ፲፪ ÷ ፪ ።

፲፱ አገኙኝ ። ነገር ፡ ግን ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ነገር ፡ ያላ
ቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ÷ በፊትህ ፡ መጥተው ፡ ይከሱኝ ፡
ዘንድ ፡ የሚገባቸው ፡ ከእስያ ፡ የመጡ ፡ አንዳ
፳፩፳፪ ንድ ፡ አይሁድ ፡ አሉ ። ወይም ፡ በመካከላቸው ፡
ቆሜ ፡— ዛሬ ፡ ስለ ፡ ሙታን ፡ መነሣት ፡ በፊታ
ችሁ ፡ በእኔ ፡ ይፈርዱብኛል ፡ ብዬ ፡ ከጮኽሁት ፡
ከዚህ ፡ ከአንድ ፡ ነገር ፡ በቀር ÷ በሸንጎ ፡ ፊት ፡
ቆሜ ፡ ሳለሁ ፡ በእኔ ፡ አንድ ፡ ዓመፃ ፡ ያገኙ ፡
እንደ ፡ ሆን ፡ እነዚህ ፡ ራሳቸው ፡ ይናገሩ ።
፳፬ ፊልክስ ፡ ግን ፡ የመንገዱን ፡ ነገር ፡ አጥብቆ ፡
አውቆአልና ፡— የሻለቃው ፡ ሉስዮስ ፡ በወረደ ፡
ጊዜ ፡ ነገራችሁን ፡ እቋርጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡
፳፫ አዘገያቸው ። የመቶውንም ፡ አለቃ ፡ ጳውሎ
ስን ፡ ሲጠብቅ ፡ እንዲያይላለት ÷ ከወዳጆቹም ፡
ማንም ፡ ሲያገለግለው ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡
ሲመጣ ፡ እንዳይከለክልበት ፡ አዘዘው ።
፳፬ ከጥቂት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ፊልክስ ፡ አይሁዳ
ዊት ፡ ከነበረች ፡ ድሩሲላ ፡ ከሚሉአት ፡ ከሚስቱ ፡
ጋር ፡ መጥቶ ፡ ጳውሎስን ፡ አስመጣ ÷ በኢየሱስ ፡
ክርስቶስም ፡ ስለ ፡ ማመን ፡ የሚናገረውን ፡
፳፭ ሰማው ። እርሱም ፡ ስለ ፡ ጽድቅና ፡ ራስን ፡ ስለ ፡
መግዛት ፡ ስለሚመጣውም ፡ ሁኔኔ ፡ ሲነጋገር ፡
ሳለ ፡ ፊልክስ ፡ ፈርቶ ፡— አውንስ ፡ ሂድ ÷ በተ
መቸኝም ፡ ጊዜ ፡ ልኬ ፡ አስጠራሃለሁ ፡ ብሎ ፡
፳፮ መለሰለት ። ያን ፡ ጊዜም ፡ ደግሞ ፡ እንዲፈታው ፡
ጳውሎስ ፡ ገንዘብ ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡
አደረገ ። ስለዚህ ፡ ደግሞ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እያስ
፳፯ መጣ ፡ ያነጋግረው ፡ ነበር ። ሁለት ፡ ዓመትም ፡
ከሞላ ፡ በኋላ ፡ ጶርቅዮስ ፡ ፌስጦስ ፡ በፊልክስ ፡
ፈንታ ፡ ተተካ ። ፊልክስም ፡ አይሁድን ፡ ደስ ፡
ያሰኝ ፡ ዘንድ ፡ ወዶ ፡ ጳውሎስን ፡ እንደ ፡ ታሰረ ፡
ተወው ።

ምዕራፍ ፳፭ ።

፩ ፌስጦስም ፡ ወደ ፡ አውራጃው ፡ ገብቶ ፡ ከሦ
ስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ከቂሣርያ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳ
፪ ሌም ፡ ወጣ ። የካህናቱ ፡ አለቆችና ፡ የአይሁ
ድም ፡ ታላላቆች ፡ በጳውሎስ ፡ ላይ ፡ አመለከቱ ÷
፫ ጳውሎስንም ፡ ሲቃወሙ ፡ እንዲያደላላቸው ፡
እየለመኑ ÷ በመንገድ ፡ ሸምቀው ፡ ይገድሉት ፡
ዘንድ ፡ አስበው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንዲያስ
፬ መጣው ፡ ማለዱት ። ፌስጦስ ፡ ግን ፡ ጳውሎስ ፡
በቂሣርያ ፡ እንዲጠበቅ ፡ እርሱም ፡ ራሱ ፡ ወደ
ዚያ ፡ ፈጥኖ ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ እንዳለው ፡ መለሰ
፭ ላቸው ። እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ ክፋት ፡ ቢሆን ፡
ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ያሉት ፡ በለ ፡ ሥልጣኖች ፡
ከእኔ ፡ ጋር ፡ ወርደው ፡ ይክሰሱት ፡ አላቸው ።
፮ በእነርሱም ፡ ዘንድ ፡ ከስምንት ፡ ወይም ፡ ከአ
ሥር ፡ የማይበልጥ ፡ ቀን ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ ቂሣ
ርያ ፡ ወረደ ። በነገውም ፡ በፍርድ ፡ ወንበር ፡
ተቀምጦ ፡ ጳውሎስን ፡ ያመጡት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ።
፯ በቀረበም ፡ ጊዜ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ የወረዱት ፡
አይሁድ ፡ ከበውት ፡ ቆሙ ÷ ይረቱበትም ፡ ዘንድ ፡
የማይችሉትን ፡ ብዙና ፡ ከባድ ፡ ክስ ፡ አነሡበት ።
፰ ጳውሎስም ፡ ሲምዋገት ፡— የአይሁድን ፡ ሕግ ፡ ፰፤
ቢሆን ፡ መቅደስንም ፡ ቢሆን ፡ ቄሣርንም ፡ ቢሆን ፡
አንዳች ፡ ስንኳ ፡ አልበደልሁም ፡ አለ ። ፌስ
፱ ጦስ ፡ ግን ፡ አይሁድን ፡ ደስ ፡ ያሰኝ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡
ጳውሎስን ፡— ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጥተህ ፡
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ከዚያው ፡ በፊቴ ፡ ትፋረድ ፡
ዘንድ ፡ ትወዳለህን ? ብሎ ፡ መለሰለት ። ጳው ፲፤
ሎስ ፡ ግን ፡— እፋረድበት ፡ ዘንድ ፡ በሚገባኝ ፡
በቄሣር ፡ ፍርድ ፡ ወንበር ፡ ፊት ፡ ቆሜአለሁ ።
አንተው ፡ ደግሞ ፡ ፈጽመህ ፡ እንደምታውቅ ፡
አይሁድን ፡ ምንም ፡ አልበደልሁም ። እንግዲህ ፲፩፤
በድዬ ፡ ወይም ፡ ሞት ፡ የሚገባውን ፡ ነገር ፡ አድ
ርጌ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሞት ፡ ልዳን ፡ አልልም ፤
እነዚህ ፡ የሚከሱኝ ፡ ክስ ፡ ከንቱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
ግን ፡ ለእነርሱ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጠኝ ፡ ዘንድ ፡
ማንም ፡ አይችልም ። ወደ ፡ ቄሣር ፡ ይግባኝ ፡
ብዬአለሁ ፡ አለ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ፌስጦስ ፡ ከአ ፲፪፤
ማካሪዎቹ ፡ ጋር ፡ ተማክሮ ፡— ወደ ፡ ቄሣር ፡
ይግባኝ ፡ ብለሃል ። ወደ ፡ ቄሣር ፡ ትሄዳለህ ፡
ብሎ ፡ መለሰለት ።
ከጥቂት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ አግሪጳ ፡ ፲፫፤
በርኒቄም ፡ ለፌስጦስ ፡ ሰላምታ ፡ እንዲያቀርቡ ፡
ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ ወረዱ ። በዚያውም ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ፲፬፤
ስለ ፡ ተቀመጡ ፡ ፌስጦስ ፡ የጳውሎስን ፡ ነገር ፡
ለንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ገለጠ ፡— ፊልክስ ፡
አስሮ ፡ የተወው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ አለ ። ፲፭፤
በኢየሩሳሌምም ፡ ሳለሁ ፡ የካህናት ፡ አለቆችና ፡
የአይሁድ ፡ ሽማግሌዎች ፡ እፈርድበት ፡ ዘንድ ፡
እየለመኑ ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ አመለከቱኝ ። እኔም ፡— ፲፮፤
ተከሳሹ ፡ በከሳሾቹ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ሳይቆም ፡
ለተከሰሰበትም ፡ መልስ ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ፈንታ ፡
ሳያገኝ ÷ ማንንም ፡ ቢሆን ፡ አሳልፎ ፡ መስጠት ፡
የሮማውያን ፡ ሥርዓት ፡ አይደለም ፡ ብዬ ፡ መለስ
ሁላቸው ። ስለዚህም ፡ በዚህ ፡ በተሰበሰቡ ፡ ፲፯፤
ጊዜ ÷ ሳልዘገይ ፡ በማግሥቱ ፡ በፍርድ ፡ ወንበር ፡
ተቀምጬ ፡ ያንን ፡ ሰው ፡ ያመጡት ፡ ዘንድ ፡ አዘ
ዝሁ ። ከሳሾቹም ፡ በቆሙ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ ያሰብ ፲፰፤
ሁትን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ክስ ፡ ምንም ፡ አላመጡበ
ትም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ገዛ ፡ ሃይማኖታቸውና ፲፱፤
ጳውሎስ ፡— ሕያው ፡ ነው ፡ ስለሚለው ፡ ስለ ፡
ሞተው ፡ ኢየሱስ ፡ ስለ ፡ ተባለው ፡ ከእርሱ ፡
ጋር ፡ ይከራከሩ ፡ ነበር ። እኔም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ፳፤
እንዴት ፡ እንድመረምር ፡ አመንትቼ ፡— ወደ ፡
ኢየሩሳሌም ፡ ሄደህ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ከዚያ ፡ ልት
ፋረድ ፡ ትወዳለህን ? አልሁት ። ጳውሎስ ፡ ግን ፡ ፳፩፤
አውግስጦስ ፡ ቄሣር ፡ እስኪቄርጥ ፡ ድረስ ፡ እን
ዲጠበቅ ፡ ይግባኝ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ÷ ወደ ፡ ቄሣር ፡
እስክሰደው ፡ ድረስ ፡ ይጠበቅ ፡ ዘንድ ፡ አዘዝሁ ።
፳፪ አግሪጳም ፡ ፌስጦስን ፡— ያንንስ ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ ፳፪፤
ዳግም ፡ እከ ፡ እሰማው ፡ ዘንድ ፡ አወድ ፡ ነበር ፡

ግጽ ። ፳፱ ፤ ም· ፳፫ ÷ ፮ ። ፴ ፤ ሚክ· ፮ ÷ ፫ ።
ግጽ ። ፮ ፤ ም· ፳፬ ÷ ፳ ። ፳፪ ፤ ም· ፱ ÷ ፲፭ ።

አለው ። እርሱም ፡— ነገ ፡ ትሰማዋለህ ፡ አለው ።
፳፫፡ በነገውም ፡ አግሪጳና ፡ በርኒቄ ፡ በብዙ ፡ ግርማ ፡ መጥተው ፡ ከሻለቆችና ፡ ከከተማው ፡ ታላላቆች ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ገቡ ፤ ፌስጦስም ፡
፳፬፡ ባዘዘ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስን ፡ አመጡት ። ፌስጦስም ፡ አለ ፡— አግሪጳ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ እናንተም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ያላችሁ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በሕይወት ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ እንዳ ይገባው ፡ እየጮኹ ፡ የአይሁድ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በዚህም ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ የለመኑ
፳፭፡ ኝን ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ ታዩታላችሁ ። እኔ ፡ ግን ፡ ሞት ፡ የሚገባውን ፡ ነገር ፡ እንዳላደረገ ፡ አስተዋ ልሁ ፡ እርሱም ፡ ወደ ፡ አውግስጦስ ፡ ይግባኝ ፡
፳፮፡ ስላለ ፡ እሰደው ፡ ዘንድ ፡ ቈረጥሁ ። ስለ ፡ እር ሱም ፡ ወደ ፡ ጌታዬ ፡ የምጽፈው ፡ እርግጥ ፡ ነገር ፡ የለኝም ፤ ስለዚህ ፡ ከተመረመረ ፡ በኋላ ፡ የምጽፈውን ፡ ነገር ፡ አገኝ ፡ ዘንድ ፡ በፊታችሁ ፡ ይልቁንም ፡ በፊትህ ፡ ንጉሥ ፡ አግሪጳ ፡ ሆይ ፡
፳፯፡ አመጣሁት ፤ አስረኛ ፡ ሲላክ ፡ የተከሰሰበትን ፡ ምክንያት ፡ ደግሞ ፡ አለማመልከት ፡ ሞኝነት ፡ መስሎኛልና ።

ምዕራፍ ፡ ፳፮ ።

፩፡ አግሪጳም ፡ ጳውሎስን ፡— ስለ ፡ ራስህ ፡ ትና ገር ፡ ዘንድ ፡ ተፈቅዶልሃል ፡ አለው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ መለሰ ፡ እን ዲህ ፡ ሲል ፡—
፪፡፫፡ ንጉሥ ፡ አግሪጳ ፡ ሆይ ፡ የአይሁድን ፡ ሥር ዓት ፡ ክርክርንም ፡ ሁሉ ፡ አጥብቀህ ፡ አውቀሃ ልና ፡ በአይሁድ ፡ በተከሰስሁበት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ዛሬ ፡ በፊትህ ፡ ስለምመልስ ፡ ራሴን ፡ እጅግ ፡ እንደ ፡ ተመረቀ ፡ አድርጌ ፡ እቈጥረዋለሁ ፤ ስለ ዚህ ፡ በትዕግሥት ፡ ትሰማኝ ፡ ዘንድ ፡ እለምን ሃለሁ ።
፬፡ ከመጀመሪያ ፡ አንሥቶ ፡ በሕዝቤ ፡ መካከል ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሆነውን ፡ ከታናሽነቴ ፡ ጀምሬ ፡ የኖርሁትን ፡ ኑሮዬን ፡ አይሁድ ፡ ሁሉ ፡ ያው ቃሉ ፤ ሊመሰክሩ ፡ ይወዱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በእ ምልከአችን ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ሕግን ፡ በመጠን ቀቅ ፡ እንደሚተጋ ፡ ወገን ፡ ፈሪሳዊ ፡ ሆኜ ፡ እንደ ፡ ኖርሁ ፡ ከዋንት ፡ ጀምረው ፡ አውቀውኛልና ።
፮፡ አሁንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ለአበቶቻ ችን ፡ ስለ ፡ ተሰጠው ፡ ስለ ፡ ተስፋ ፡ ቃል ፡ አለ
፯፡ ኝታ ፡ ልፋረድ ፡ ቆሜአለሁ ። ወደዚህም ፡ ወደ ፡ ተስፋ ፡ ቃል ፡ አሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖቻችን ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ በትጋት ፡ እያመለኩ ፡ ይደርሱ ፡ ዘንድ ፡ አለኝታ ፡ አላቸው ፤ ስለዚህም ፡ አለ ኝታ ፡ ንጉሥ ፡ አግሪጳ ፡ ሆይ ፡ ከአይሁድ ፡ እነ
፰፡ ሰሳለሁ ። እግዚአብሔር ፡ ሙታንን ፡ የሚያስ ነሣ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የማይታመን ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ ይቈጠራል ?

፱፡ እኔም ፡ ራሴ ፡ የናዝሬቱን ፡ የኢየሱስን ፡ ስም ፡ የሚቃወም ፡ እጅግ ፡ ነገር ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፡ እን ዲገባኝ ፡ ይመስለኝ ፡ ነበር ። ይህንም ፡ ደግሞ ፡
፲፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደረግሁት ፤ ከካህናት ፡ አለቆ ችም ፡ ሥልጣን ፡ ተቀብዬ ፡ እኔ ፡ ከቅዱሳን ፡ ብዙ ዎችን ፡ በወኅኒ ፡ አሳሰርኋቸው ፡ ሲገድሉአቸ ውም ፡ አብሬ ፡ ተቸኮሁ ። በምኵራብም ፡ ሁሉ ፡
፲፩፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እየቀጣሁ ፡ ይሰድቡት ፡ ዘንድ ፡ ግድ አልኋቸው ፤ ያለ ፡ ልክ ፡ ስቄጣባቸውም ፡ እስከ ውጭ ፡ አገር ፡ ከተማዎች ፡ ድረስ ፡ እንኳ ፡ አሳ ድድ ፡ ነበር ።
፲፪፡ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ ከካህናት ፡ አለቆች ፡ ሥል ጣንና ፡ ትእዛዝ ፡ ተቀብዬ ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ ስሄድ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ በመንገድ ፡ ሳለሁ ፡ እኩል
፲፫፡ ቀን ፡ ሲሆን ፡ በዙሪያዬና ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ በሄ ዱት ፡ ዙሪያ ፡ ከፀሐይ ፡ ብሩህነት ፡ የበለጠ ፡ ብርሃን ፡ ከሰማይ ፡ ሲበራ ፡ አየሁ ፤ ሁላችንም ፡
፲፬፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በወደቅን ፡ ጊዜ ፡ ሳውል ፡ ሳውል ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ታሳድደኛለህ ? የመውጊ ያውን ፡ ብረት ፡ ብትቃወም ፡ ለአንተ ፡ ይብስብ ሃል ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ በዕብራይስጥ ፡ ቋንቋ ፡ ሲናገረኝ ፡ ሰማሁ ። እኔም ፡— ጌታ ፡ ሆይ ፡ ማን ፡
፲፭፡ ነህ ? አልሁ ። እርሱም ፡ አለኝ ፡— አንተ ፡ የም ታሳድደኝ ፡ እኔ ፡ ኢየሱስ ፡ ነኝ ። ነገር ፡ ግን ፡
፲፮፡ ተነሣና ፡ በእግርህ ፡ ቁም ፤ ስለዚህ ፡ እኔን ፡ ባየ ሀበት ፡ ነገር ፡ ለአንተም ፡ በምታይበት ፡ ነገር ፡ አገልጋይና ፡ ምስክር ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ልሾምህ ፡ ታይቼልሃለሁና ። የኃጢአትንም ፡ ስርየት ፡ በእ
፲፯፡፲፰፡ ኔም ፡ በማመን ፡ በተቀደሱት ፡ መካከል ፡ ርስትን ፡ ያገኙ ፡ ዘንድ ፡ ከጨለማ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ ከሰይ ጣንም ፡ ሥልጣን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘወር ፡ እንዲሉ ፡ ዓይናቸውን ፡ ትከፍት ፡ ዘንድ ፡ ከሕ ዝቡና ፡ ወደ ፡ አንርሱ ፡ ከምልከህ ፡ ከአሕዛብ ፡ አድንሃለሁ ።
፲፱፡ ንጉሥ ፡ አግሪጳ ፡ ሆይ ፡ ስለዚህ ፡ ከሰማይ ፡ የታየችን ፡ ራእይ ፡ እምቢ ፡ አላልሁም ። ነገር ፡ ግን ፡ አስቀድሜ ፡ በደማስቆ ፡ ላሉት ፡ በኢየሩሳ ሌምም ፡ በይሁዳም ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ለአሕዛብም ፡ ንስሐ ፡ ይገቡ ፡ ዘንድና ፡ ለንስሐ ፡ የሚገባ ፡ ነገር ፡ እያደረጉ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘወር ፡ ይሉ ፡ ዘንድ ፡ ተናገርሁ ። ስለዚህ ፡ አይሁድ ፡ በመቅ
፳፩፡ ደስ ፡ ያዙኝ ፡ ሊገድሉኝም ፡ ሞከሩ ። ከእግዚ አብሔርም ፡ ዘንድ ፡ ረድኤት ፡ ተቀብዬ ፡ ለታና ሹም ፡ ለታላቁም ፡ ስመሰክር ፡ እስከዚች ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ቆሜአለሁ ፤ ነቢያትና ፡ ሙሴ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ያልሁን ፡ ክርስቶስ ፡ መከራን ፡ እንዲቀ በል ፡ በመታንም ፡ ትንሣኤ ፡ ለሕዝብና ፡ ለአሕ ዛብ ፡ ብርሃንን ፡ በመጀመሪያ ፡ ሊሰብክ ፡ እንዳ ለው ፡ ከተናገሩት ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ የተ ናገርሁት ፡ የለም ።
፳፪፡ እንዲህም ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ሲመልስ ፡ ፌስ ፳፫፡

ጦስ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡— ጳውሎስ ፡ ሆይ ፡ አብ ድሃል ፡ እኮ ፤ ብዙ ፡ ትምህርትህ ፡ ወደ ፡ እብ
፳፬፡ ደት ፡ ያዘርሃል ፡ አለው ። ጳውሎስ ፡ ግን ፡ እን ዲህ ፡ አለ ፡— ክቡር ፡ ፌስጦስ ፡ ሆይ ፡ የእውነት ንና ፡ የአእምሮን ፡ ነገር ፡ እናገራለሁ ፡ እንጂ ፡ እብ
፳፭፡ ደትስ ፡ የለብኝም ። በእርሱ ፡ ፊት ፡ ደግሞ ፡ በግልጥ ፡ የምናገረው ፡ ንጉሥ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ያውቃል ፤ ከዚህ ፡ ነገር ፡ አንዳች ፡ እንዳይሰወ ርበት ፡ ተረድቼአለሁና ፤ ይህ ፡ በስውር ፡ የተደ
፳፮፡ ረገ ፡ አይደለምና ። ንጉሥ ፡ አግሪጳ ፡ ሆይ ፡ ነቢ ያትን ፡ ታምናለህን ? እንድታምናቸው ፡ አው
፳፯፡ ቃለሁ ። አግሪጳም ፡ ጳውሎስን ፡— በጥቂት ፡ ክርስቲያን ፡ ልታደርገኝ ፡ ትወዳለህ ፡ አለው ።
፳፱፡ ጳውሎስም ፡— በጥቂት ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ አይደለህም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዛሬ ፡ የሚሰሙኝ ፡ ሁሉ ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ እስራት ፡ በቀር ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ እለምናለሁ ፡ አለው ።
፴፡ ንጉሡም ፡ አገረ ፡ ገዥም ፡ በርኒቄም ፡ ከእነር ሱም ፡ ጋር ፡ ተቀምጠው ፡ የነበሩት ፡ ተነሡ ፡÷
፴፩፡ ፈቀቅ ፡ ብለውም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡— ይህ ፡ ሰው ፡ እንኳንስ ፡ ለሞት ፡ ለእስራትም ፡ የሚገባ ፡
፴፪፡ ምንም ፡ አላደረገ ፡ ብለው ፡ ተነጋገሩ ። አግሪ ጳም ፡ ፌስጦስን ፡— ይህ ፡ ሰው ፡ እኮ ፡ ወደ ፡ ቄሣር ፡ ይግባኝ ፡ ብይል ፡ ይፈታ ፡ ዘንድ ፡ ይቻል ፡ ነበር ፡ አለው ።

ምዕራፍ ፡ ፳፯ ።

፩፡ ወደ ፡ ኢጣሊያም ፡ በመርከብ ፡ እንሄድ ፡ ዘንድ ፡ በተቈረጠ ፡ ጊዜ ፡÷ ጳውሎስንና ፡ ሌሎችን ፡ እስ ረኞች ፡ ከአውግስጦስ ፡ ጭፍራ ፡ ለዠበረ ፡ ዩል ዮስ ፡ ለሚሉት ፡ ለመቶ ፡ አለቃ ፡ አሳልፈው ፡
፪፡ ሰጡአቸው ። በእስያም ፡ ዳርቻ ፡ ወዳሉ ፡ ስፍ ራዎች ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ በለው ፡ በአድራሚቲስ ፡ መርከብ ፡ ገብተን ፡ ተነሣን ፤ የመቄዶንያም ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ የተሰሎንቄው ፡ አርስጥሮኮስ ፡ ከእኛ ፡
፫፡ ጋር ፡ ነበረ ። በነገውም ፡ ወደ ፡ ሲዶና ፡ ስንደ ርስ ፡ ዩልዮስ ፡ ለጳውሎስ ፡ ቸርነት ፡ አድርጎ ፡ እርዳታቸውን ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ወዳ
፬፡ ጆቹ ፡ እንዲሄድ ፡ ፈቀደለት ። ከዚያም ፡ ተነ ሥተን ፡ ነፋሱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ነበረና ፡ በቆጵ
፭፡ ሮስ ፡ ተተግነን ፡ ሄድን ፤ በኪልቅያና ፡ በጵንፍ ልያም ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ባሕር ፡ ከተሻገርን ፡ በኋላ ፡ በሉቅያ ፡ ወዳለ ፡ ወደ ፡ ሙራ ፡ ደረስን ።
፮፡ የመቶ ፡ አለቃውም ፡ በዚያ ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ የሚሄድ ፡ የእስክንድርያውን ፡ መርከብ ፡ አግ
፯፡ ኝቶ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ አገበን ። ብዙ ፡ ቀንም ፡ እያ ዘገምን ፡ ሄደን ፡ በጭንቅ ፡ ወደ ፡ ቀኒዶስ ፡ አን ጻር ፡ ደረስን ፤ ነፋሱም ፡ ስለ ፡ ከለከለን ፡ በቀርጤስ ፡
፰፡ ተተግነን ፡ በሰልሞና ፡ አንጻር ፡ ሄድን ፤ በጭን ቅም ፡ ጥግ ፡ ጥጉን ፡ አልፈን ፡ ለላሲያ ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ቀረበች ፡ መልካም ፡ ወደብ ፡ ወደሚሉ

አት ፡ ስፍራ ፡ መጣን ።
፱፡ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ ከለፈ ፡ በኋላ ፡÷ የጦም ፡ ወራት ፡ አሁን ፡ አልፎ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በመርከብ ፡ ለመሄድ ፡ አሁን ፡ የሚያስፈራ ፡ ነበርና ፡ ጳውሎስ ፡— እና
፲፡ ንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፡÷ ይህ ፡ በጥፋትና ፡ በብዙ ፡ ጕዳት ፡ እንዲሆን ፡ አያለሁ ፤ ጥፋቱም ፡ በገዛ ፡ ሕይወታችን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በጭነቱና ፡ በመር ከቡ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ መከራቸው ።
፲፩፡ የመቶ ፡ አለቃው ፡ ግን ፡ ጳውሎስ ፡ ከተናገረው ፡ ይልቅ ፡ የመርከብ ፡ መሪውንና ፡ የመርከቡን ፡ ባለቤት ፡ ይሰማ ፡ ነበር ። ያም ፡ ወደብ ፡ ይከር
፲፪፡ ሙበት ፡ ዘንድ ፡ የማይመች ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡÷ የሚበ ዙቱ ፡ ቢቻላቸው ፡ በሰሜንና ፡ በደቡብ ፡ ምዕ ራብ ፡ ትይዩ ፡ ወዳለው ፡ ፍንቄ ፡ ወደሚሉት ፡ ወደ ፡ ቀርጤስ ፡ ወደብ ፡ ደርሰው ፡ ይከርሙ ፡ ዘንድ ፡ ከዚያ ፡ እንዲነሡ ፡ መከሩ ።
፲፫፡ ልከኛም ፡ የደቡብ ፡ ነፋስ ፡ በነፈሰ ፡ ጊዜ ፡÷ እን ዳሰቡት ፡ የሆነላቸው ፡ መስሎአቸው ፡ ተነሡ ፡ በቀርጤስም ፡ አጠገብ ፡ ጥግ ፡ ጥጉን ፡ አለፉ ።
፲፬፡ ነገር ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ ሳይዘገይ ፡ አውራቂስ ፡ የሚ
፲፭፡ ሉት ፡ ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ከዚያ ፡ ወረደባቸው ፤ መር ከቡም ፡ ተነጥቆ ፡ ነፋሱን ፡ ሲቃወም ፡ መሄድ ፡ ስላልቻለ ፡ ለቀነው ፡ ተነዳን ። ቂዳ ፡ በሚሉአ
፲፮፡ ትም ፡ ደሴት ፡ በተተገንን ፡ ጊዜ ፡ ታንኳይቱን ፡ ለመግዛት ፡ በጭንቅ ፡ ቻልን ፤ ወደ ፡ ላይም ፡
፲፯፡ ከወጡአት ፡ በኋላ ፡ መርከቡን ፡ በገመድ ፡ አስታ ጥቀው ፡ አጸኑ ፤ ስርቲስም ፡ ወደሚሉት ፡ ወደ ፡ አሸዋ ፡ እንዳይወድቁ ፡ ፊርተው ፡ ሸራውን ፡ አውርደው ፡ እንዲሁ ፡ ተነዱ ። ነፋሱም ፡ በር
፲፰፡ ትዶ ፡ ሲያስጨንቀን ፡ በማግሥቱ ፡ ከጭነቱ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ይጥሉ ፡ ነበር ፡÷ በሦስተኛውም ፡
፲፱፡ ቀን ፡ የመርከቡን ፡ ዕቃ ፡ በእጃችን ፡ ወረወርን ። ብዙ ፡ ቀንም ፡ ፀሐይን ፡ ከዋክብትንም ፡ ሳናይ ፡
፳፡ ትልቅ ፡ ነፋስም ፡ ሲበረታብን ፡ ጊዜ ፡÷ ወደ ፡ ፊት ፡ እንድናለን ፡ የማለት ፡ ተስፋ ፡ ሁሉ ፡ ተቈረጠ ።
፳፩፡ ሳይበሉም ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ በመካከላቸው ፡ ቆሞ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡— እናንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፡ ሰምታችሁኝ ፡ በሆነ ፡ ኖሮ ፡ ከቀርጤስ ፡ እንዳትነሡ ፡ ይህንም ፡ ጥፋትና ፡ ጕዳት ፡ እንዳታገኙ ፡ ይገባችሁ ፡ ነበር ።
፳፪፡ አሁንም ፡— አይዞአችሁ ፡ ብዬ ፡ እመክራችኋ ለሁ ፤ ይህ ፡ መርከብ ፡ እንጂ ፡ ከእናንተ ፡ አንድ ፡
፳፫፡ ነፍስ ፡ እንኳ ፡ አይጠፋምና ። የእርሱ ፡ የምሆ ንና ፡ ደግሞ ፡ የማመልከው ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ በዚች ፡ ሌሊት ፡ በእጠገቤ ፡ ቆሞ ፡
፳፬፡ ነበርና ፡ እርሱም ፡— ጳውሎስ ፡ ሆይ ፡ አትፍራ ፤ በቄሣር ፡ ፊት ፡ ልትቆም ፡ ይገባሃል ፤ እነሆም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእንተ ፡ ጋር ፡ የሚጄዱትን ፡
፳፭፡ ሁሉ ፡ ሰጥቶሃል ፡ አለኝ ። ስለዚህም ፡ እናንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፡ አይዞአችሁ ፤ እንደ ፡ ተናገረኝ ፡ እንዲሁ ፡ እንዲሆን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አምናለ
፳፮፡ ሁና ። ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ አንዲት ፡ ደሴት ፡ እን

ድንወድቅ ፡ ያስፈልገናል ።

፳፪፥፩ በአሥራ ፡ አራተኛውም ፡ ሴሊት ፡ በአድርያ ፡ ባሕር ፡ ወዲህና ፡ ወዲያ ፡ ስንነዳ ፡ መርከበኞች ፡ በእኩለ ፡ ሴሊት ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ምድር ፡ የቀ
፳፪፥፳ ረቡ ፡ መሰላቸው ። መለከኪያ ፡ ገመድም ፡ ቢጥሉ ፡ ሀያ ፡ በሰው ፡ ቁመት ፡ አገኙ ፡ ጥቂትም ፡ ቆይተው ፡ ሁለተኛ ፡ ቢጥሉ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ በሰው ፡
፳፪፥፳፩ ቁመት ፡ አገኙ ። ድንጋያማም ፡ ወደ ፡ ሆነ ፡ ስፍራ ፡ እንዳይወድቁ ፡ ፈርተው ፡ ከመርከቡ ፡ በስተ ፡ ኋላ ፡ አራት ፡ መልሕቅ ፡ አወረዱ ፡ ቀንም ፡ እን
፳፪፥፩ ፡ ሲሆን ፡ ተመኙ ። መርከበኞቹም ፡ ከመርከቡ ፡ ይሸሹ ፡ ዘንድ ፡ ፈልገው ፡ ከመርከቡ ፡ በስተ ፡ ፊት ፡ መልሕቅ ፡ መጣል ፡ እንዳላቸው ፡ አመካ
ኙተው ፡ ታንኳይቱን ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ባወረዱ ፡ ፲፯ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ ለመቶ ፡ አለቃውና ፡ ለወታደ
፳፪፥፲፰ ሮች ፡ — እነዚህ ፡ በመርከቡ ፡ ካልቆዩ ፡ እናንተ ፡ ትድኑ ፡ ዘንድ ፡ አትችሉም ፡ አላቸው ። ያን ፡
፳፪፥፲፱ ጊዜ ፡ ወታደሮቹ ፡ የታንኳይቱን ፡ ገመድ ፡ ቈር ጠው ፡ ትወድቅ ፡ ዘንድ ፡ ተዉአት ።

፳፪፥፳፫ ቀንም ፡ ሲነጋ ፡ ጳውሎስ ፡ ምግብ ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ ሁሉን ፡ ይለምን ፡ ነበር ፡ እንዲህም ፡ አላ
ቸው ፡— እየጠበቃችሁ ፡ ምንም ፡ ሳትቀበሉ ፡ ጠማችሁን ፡ ከሰነበታችሁ ፡ ዛሬ ፡ አሥራ ፡ አራ
፳፪፥፳፬ ተኛ ፡ ቀናችሁ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ምግብ ፡ ትበሉ ፡ ዘንድ ፡ እለምናችኋለሁ ፤ ይህ ፡ ለደኅንነታችሁ ፡
፳፪፥፳፭ ይሆናልና ፤ ከእናንተ ፡ ከአንዱ ፡ የራስ ፡ ጠጕር ፡ እንኳ ፡ አትጠፋምና ። ይህንም ፡ ብሎ ፡ እንጀ
፳፪፥፳፮ ራን ፡ ይዞ ፡ በሁሉ ፡ ፊት ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመ ሰገነ ፡ ቈርሶም ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ ጀመረ ። ሁሉም ፡
፳፪፥፴፭ ተጽናንተው ፡ ራሳቸው ፡ ደግሞ ፡ ምግብ ፡ ተቀ በሉ ። በመርከቡም ፡ ያለን ፡ ሁላችን ፡ ሁለት ፡
፳፪፥፴፯ መቶ ፡ ሰባ ፡ ስድስት ፡ ነፍስ ፡ ነበርን ። በልተ ውም ፡ በጠገቡ ፡ ጊዜ ፡ ስንዴውን ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ እየጣሉ ፡ መርከቡን ፡ አቃለሉት ።

፳፪፥፴፱ በነጋም ፡ ጊዜ ፡ ምድሩን ፡ አላወቁትም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የአሸዋ ፡ ዳር ፡ ያለውን ፡ የባሕር ፡ ስርጥ ፡ ተመለከቱ ፡ ቢቻላቸውም ፡ መርከቡን ፡ ወደዚያ ፡
፳፪፥፵ ይገፋ ፡ ዘንድ ፡ ቈረጡ ። መልሕቆቹንም ፡ ፈት ተው ፡ በባሕር ፡ ተዉአቸው ፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ የመቅዘፊያውን ፡ ማሠሪያ ፡ ፈቱት ፤ ታናሹንም ፡ ሸራ ፡ ለነፋስ ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ዳር ፡ አቅ
፳፪፥፵፩ ንተው ፡ ይጄዱ ፡ ዘንድ ፡ ጀመሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁለት ፡ ባሕር ፡ በተገናኙበት ፡ ስፍራ ፡ ወድቀው ፡ መርከቡን ፡ በዲብ ፡ ላይ ፡ ነዱ ፤ በስተ ፡ ፊቱም ፡ ተተክሎ ፡ የማይነቃነቅ ፡ ሆነ ፡ በስተ ፡ ኋላው ፡ ግን ፡ ከማዕበሉ ፡ ግፊ ፡ የተነሣ ፡ ይሰበር ፡ ነበር ።
፳፪፥፵፪ ወታደሮቹም ፡ ከእስረኞች ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ ዋኝቶ ፡ እንዳያመልጥ ፡ ይገድሉአቸው ፡ ዘንድ ፡ ተማ
፳፪፥፵፫ ከሩ ። የመቶ ፡ አለቃው ፡ ግን ፡ ጳውሎስን ፡ ያድ ነው ፡ ዘንድ ፡ አስቦ ፡ ምክራቸውን ፡ ከለከለ ፤ ዋና ፡ የሚያውቁትም ፡ ከመርከብ ፡ ራሳቸውን ፡ አየወረወሩ ፡ አስቀድመው ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ይወጡ ፡ ዘንድ ፡ የቀሩትም ፡ እኵሌቶቹ ፡ በሳን ቃዎች ፡ ላይ ፡ እኵሌቶቹም ፡ በመርከቡ ፡ ስባሪ ፡ ይወጡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ። እንዲሁም ፡ ሁሉ ፡ በደ ኅና ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ደረሱ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፰ ።

፳፰፥፩ በደኅና ፡ ከደረስን ፡ በኋላ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ደሴቲቱ ፡ መላጥያ ፡ እንድትባል ፡ አወቅን ።
፳፰፥፪ አረማውያንም ፡ የሚያስገርም ፡ ቸርነት ፡ አደረ ጉልን ። ዝናብ ፡ ስለ ፡ ሆነም ፡ ስለ ፡ ብርዱም ፡ እሳት ፡ አንድደው ፡ ሁላችንን ፡ ተቀበሉን ።
፳፰፥፫ ጳውሎስ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ጭራሮ ፡ አከማችቶ ፡ ወደ እሳት ፡ ሲጨምር ፡ እፉኝት ፡ ከሙቀት ፡ የተነሣ ፡ ወጥታ ፡ እጁን ፡ ነደፈችው ። አረማውያንም ፡
፳፰፥፬ እባብ ፡ በእጁ ፡ ተንጠልጥላ ፡ በዩ ፡ ጊዜ ፡ እርስ በርሳቸው ፡— ይህ ፡ ሰው ፡ በእርግጥ ፡ ነፍሰ ገዳይ ፡ ነው ፡ ከባሕርም ፡ ስንኳ ፡ በደኅና ፡ ቢወጣ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ በሕይወት ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ አልተወውም ፡ አሉ ። እርሱ ፡ ግን ፡
፳፰፥፭ እባቢቱን ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ አራገፋት ፡ አንዳችም ፡ አልጐዳችውም ። እነርሱም ፡— ሊያብጥ ፡ ወይም ፡ ወዲያው ፡ ሞቶ ፡ ሊወድቅ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ይጠባበቁት ፡ ነበር ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ሲጠባበቁ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ የሚያስገርም ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ በላዩ ፡ ጊዜ ፡— ይህስ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አሳባቸውን ፡ ለወጡ ።

፳፰፥፯ በዚያም ፡ ስፍራ ፡ አጠገብ ፡ ፑፐልዮስ ፡ የሚ ሉት ፡ የደሴት ፡ አለቃ ፡ መሬት ፡ ነበረ ፡ እርሱም ፡ እንግድነት ፡ ተቀብሎን ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ በፍቅር ፡ አሳደረን ። የፑፐልዮስም ፡ አባት ፡ በንዳድና ፡
፳፰፥፰ በተቅማጥ ፡ ታሞ ፡ ተኝቶ ፡ ነበር ። ጳውሎስም ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ገብቶ ፡ ጸለየለት ፡ እጁንም ፡ በላዩ ፡ ጭኖ ፡ ፈወሰው ። ይህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የቀ
፳፰፥፱ ሩት ፡ ደግሞ ፡ በደሴቲቱ ፡ ደዌ ፡ የነበረባቸው ፡ እየመጡ ፡ ተፈወሱ ። በብዙ ፡ ክብርም ፡ ደግሞ ፡
፳፰፥፲ አከበሩን ። በተነሣንም ፡ ጊዜ ፡ በመርከብ ፡ ላይ ፡ የሚያስፈልገንን ፡ ነገር ፡ አኖሩልን ።

፳፰፥፲፩ ከሦስት ፡ ወርም ፡ በኋላ ፡ በደሴቲቱ ፡ ከርሞ ፡ በነበረው ፡ በእስክንድርያው ፡ መርከብ ፡ ተነሣን ፡ በእርሱም ፡ የዲዮስቆሮስ ፡ አላማ ፡ ነበረበት ።
፳፰፥፲፪ ወደ ፡ ሰራኩስም ፡ በገባን ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ተቀመጥን ። ከዚያም ፡ እየተዛወርን ፡ ወደ ፡ ሬጊ
፳፰፥፲፫ ዩም ፡ ደረስን ። ከአንድ ፡ ቀን ፡ በኋላም ፡ የደ ቡብ ፡ ነፋስ ፡ በነፈሰ ፡ ጊዜ ፡ በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ፑቲዮሉስ ፡ መጣን ። በዚያም ፡ ወንድሞ
፳፰፥፲፬ ችን ፡ አግኝተን ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ እንድንቅመጥ ፡ ለመኑን ። እንዲሁም ፡ ወደ ፡ ሮሜ ፡ መጣን ። ከዚያም ፡ ወንድሞች ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ሰምተው ፡ እስከ ፡ አፍዩስ ፡ ፋሩስና ፡ ሦስት ፡ ማደሪያ ፡ እስከሚባለው ፡ ሊቀበሉን ፡ ወጡ ።
፳፰፥፲፭ ጳውሎስም ፡ ባያቸው ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገነ ፡ ልቡም ፡ ተጽናና ። ወደ ፡ ሮሜም ፡ በገባን ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ ከሚጠብቀው ፡ ወታ ደር ፡ ጋር ፡ ለብቻው ፡ ይቀመጥ ፡ ዘንድ ፡ ተፈቀ ደለት ።

፳፰፥፲፮ ከሦስት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ጳውሎስ ፡ የአይሁ ድን ፡ ታላላቆች ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ጠራ ። በተሰበ ሰቡም ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡— ወንድሞች ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ ሕዝቡን ፡ ወይም ፡ የአባቶችን ፡ ሥር ዓት ፡ የሚቃወም ፡ አንዳች ፡ ሳላደርግ ፡ ከኢየ ሩሳሌም ፡ እንደ ፡ ታሰርሁ ፡ በሮማውያን ፡ እጅ ፡
፳፰፥፲፯ አሳልፈው ፡ ሰጡኝ ። እነርሱም ፡ መርምረው ፡ ለሞት ፡ የሚገባ ፡ ምክንያት ፡ ስላልነበረብኝ ፡
፳፰፥፲፰ ሊፈቱኝ ፡ አሰቡ ። አይሁድ ፡ ግን ፡ በተቃወሙ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ቄሣር ፡ ይግባኝ ፡ እንድል ፡ ግድ ፡ ሆነብኝ ፡ እንጂ ፡ ሕዝቤን ፡ የምከስበት ፡ ነገር ፡
፳፰፥፲፱ ኖሮኝ ፡ አይደለም ። ስለዚህም ፡ ምክንያት ፡ እያችሁና ፡ እንግራችሁ ፡ ዘንድ ፡ ጠራኋችሁ ፤ ስለ ፡ አስራኤል ፡ ተስፋ ፡ ይህን ፡ ሰንሰለት ፡ ለብ
፳፰፥፳ ሻለሁና ። እነርሱም ፡— እኛ ፡ ከይሁዳ ፡ ስለ ፡ እንተ ፡ ደብዳቤ ፡ አልተቀበልንም ፡ ከወንድሞ ችም ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ መጥቶ ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አላወራልንም ፡ ወይም ፡ አልተናገረብ
፳፰፥፳፩ ህም ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለዚህ ፡ ወገን ፡ በየስፍራው ፡ ሁሉ ፡ እንዲቃወሙ ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ታውቆአ ልና ፡ የምታስበውን ፡ ከአንተ ፡ እንሰማ ፡ ዘንድ ፡ እንፈቅዳለን ፡ አሉት ።

፳፰፥፳፫ ቀንም ፡ ቀጥረውለት ፡ ብዙ ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ መኖሪያው ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ መጡ ። ስለ ፡ እግዚ አብሔር ፡ መንግሥትም ፡ እየመሰከረ ፡ ስለ ፡ ኢየ ሱስም ፡ ከሙሴ ፡ ሕግና ፡ ከነቢያት ፡ ጠቅሶ ፡ እያ ስረዳቸው ፡ ከጥዋት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ይገልጥላቸው ፡ ነበር ። እኵሌቶቹም ፡ የተናገረውን ፡ አመኑ ፡ እኵሌቶቹ ፡ ግን ፡ አላ መኑም ። እርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ባልተስማሙ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዲት ፡ ቃል ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ ሄዱ ። እንዲህም ፡ አለ ፡— መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በነቢዩ ፡ በኢሳይያስ ፡ ለአበቶቻችን ፡—
፳፰፥፳፮ ወደዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ሂድና ፡— መስማትን ፡ ትሰማላችሁና ፡ አታስተውሉም ፡ ማየት ንም ፡ ታያላችሁና ፡ አትመለከቱም ። በኀይ
፳፰፥፳፯ ናቸው ፡ እንዳያዩ ፡ በጆሮአቸውም ፡ እንዳ ይሰሙ ፡ በልባቸውም ፡ እንዳያስተውሉ ፡ ተመልሰውም ፡ እንዳልፈውሳቸው ፡ የዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ልብ ፡ ደንዝዞአል ፡ ጆሮአቸውም ፡ ደንቁሮአል ፡ ዓይናቸውንም ፡ ጨፍነዋል ፡ በላቸው ።

፳፰፥፳፰ ሲል ፡ መልካም ፡ ተናገረ ። እንግዲህ ፡ ይህ ፡ የእ ግዚአብሔር ፡ ድኀንት ፡ ለአሕዛብ ፡ እንደ ፡ ተላከ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ይሁን ። እነርሱ ፡
፳፰፥፳፱ ደግሞ ፡ ይሰሙታል ። ይህንም ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ አይሁድ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እጅግ ፡ እየ ተከራከሩ ፡ ሄዱ ።

፳፰፥፴ ጳውሎስም ፡ በተከራየው ፡ ቤት ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ተቀመጠ ። ወደ ፡ እርሱም ፡ የሚመጡትን ፡ ሁሉ ፡ ይቀበል ፡ ነበር ። ማንም ፡
፳፰፥፴፩ ሳይከለክለው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ እየሰበከ ፡ ስለ ፡ ጌታ ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እጅግ ፡ ገልጦ ፡ ያስተምር ፡ ነበር ።

የሐዋርያው ፡ የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ሮሜ ፡ ሰዎች ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩፥፩ ሐዋርያ ፡ ሊሆን ፡ የተጠራ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስ ቶስ ፡ ባሪያ ፡ ጳውሎስ ፡ በነቢያቱ ፡ አፍ ፡ በቅዱ ሳን ፡ መጻሕፍት ፡ አስቀድሞ ፡ ተስፋ ፡ ለሰጠው ፡
፩፥፪ ለእግዚአብሔር ፡ ወንጌል ፡ ተለየ ። ይህም ፡ ወንጌል ፡ በሥጋ ፡ ከዳዊት ፡ ዘር ፡ ስለ ፡ ተወለደ ፡ እንደ ፡ ቅድስና ፡ መንፈስ ፡ ግን ፡ ከሙታን ፡ መነ ሣት ፡ የተነሣ ፡ በኃይል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ ተገለጠ ፡ ስለ ፡ ልጁ ፡ ነው ፤ እርሱም ፡
፩፥፭ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ። በእር ሱም ፡ ስለ ፡ ስሙ ፡ በአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ መከከል ፡ ከእምነት ፡ የሚነሣ ፡ መታዘዝ ፡ እንዲገኝ ፡ ጸጋ ፡ እና ፡ ሐዋርያነትን ፡ ተቀበልን ፤ በእነርሱም ፡ መከከል ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ልትሆኑ ፡ የተ
፩፥፮ ጠራችሁ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ናችሁ ። በእግዚ አብሔር ፡ ለተወደዳችሁና ፡ ቅዱሳን ፡ ልትሆኑ ፡ ለተጠራችሁ ፡ በሮሜ ፡ ላላችሁት ፡ ሁሉ ፡ ከእግ ዚአብሔር ፡ ከአባታችን ፡ ከጌታም ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋና ፡ ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ይሁን ።
፩፥፰ እምነታችሁ ፡ በዓለም ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ተሰማች ፡ አስቀድሜ ፡ ስለ ፡ ሁላችሁ ፡ አምላኬን ፡ በኢየ ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አመሰግናለሁ ። በልጁ ፡ ወን
፩፥፲ ጌል ፡ በመንፈሴ ፡ የማገለግለው ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስክሬ ፡ ነውና ፤ ምናልባት ፡ ብዙ ፡ ቆይቼ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ አው ፡ እንድመጣ ፡ በእግዚአብ ሔር ፡ ፈቃድ ፡ መንገዴን ፡ እንዲያቀናልኝ ፡ እየ ለመንሁ ፡ ሁልጊዜ ፡ በጸልዩ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ሳላ

፳፪ ፡ ፲፯ ፡ ም· ፳፭÷፭ ። ፲፰ ፡ ም· ፳፫÷፳፬ ፡ ፳፮ ፡ ፴፪ ። ፲፱ ፡ ም· ፳፭÷፲፭ ። ፳ ፡ ም· ፳፯÷፲፭ ፡ ፲፮ ። ፳፩ ፡ ም· ፳፯÷፯ ። ፳፪ ፡ ፳፯ ፡ ኢሳ· ፮÷፱ ፡ ፲ ።
፳፫ ፡ ፩ ፡ የሐዋ· ፱÷፲፭ ፡ ፲፫÷፩ ። ፫ ፡ ማቴ· ፭÷፭—፲፯ ። ፱ ፡ የሐዋ· ፲፫÷፴፫ ። ፲ ፡ ገላ· ፩÷፲፭ ፡ ፲፯ ። ፲፩ ፡ ፪ ጢሞ· ፩÷፫ ። ፲፪ ፡ ፲ ፡ ም· ፲፭÷፳፭ ፡ ፴፪ ፡ የሐዋ· ፲፱÷፳፭ ።

፩ ቋርጥ ፡ አሳስባለሁ ። ትጸኑ ፡ ዘንድ ፡ መንፈሳዊ ፡ ስጦታ ፡ እንዳከፍላችሁ ፡ ላያችሁ ፡ እናፍቃለ
፪ ሁና ። ይህንም ፡ ማለቴ ፡ በመካከላችን ፡ ባለች ፡ በእናንተና ፡ በእኔ ፡ እምነት ፡ አብረን ፡ በእናንተ ፡
፲፫ አንድንጽናና ፡ ነው ። ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ በሌ ሎቹ ፡ አሕዛብ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በእናንተም ፡ ፍሬ ፡ አገኝ ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ልመጣ ፡ እንዳሰብሁ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ እንደ ፡
፲፬ ተከለከልሁ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ እወዳለሁ ። ለግ ሪክ ፡ ሰዎችና ፡ ላልተማሩም ፥ ለጥበበኞችና ፡
፲፭ ለማያስተውሉም ፡ ዕዳ ፡ አለብኝ ፤ ስለዚህም ፡ በሚቻለኝ ፡ መጠን ፡ በሮሜ ፡ ላላችሁ ፡ ለእና ንተ ፡ ደግሞ ፡ ወንጌልን ፡ ልሰብክ ፡ ተዘጋጅቼ ፡ አለሁ ።

፲፮ በወንጌል ፡ አላፍርምና ፤ አስቀድሞ ፡ ለአይሁ ዳዊ ፡ ደግሞም ፡ ለግሪክ ፡ ሰው ፥ ለሚያምኑ ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ለማዳን ፡ ነውና ።
፲፯ ጻድቅ ፡ በእምነት ፡ ይኖራል ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጽድቅ ፡ ከእምነት ፡ ወደ ፡ እምነት ፡ በእርሱ ፡ ይገለጣልና ።

፲፰ እውነትን ፡ በዓመፃ ፡ በሚከለክሉ ፡ ሰዎች ፡ በኃ ጢአተኝነታቸውና ፡ በዓመፃቸው ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ከሰማይ ፡ ይገለጣልና ፤
፲፱ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ገለጠላቸው ፡ ስለ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ሊታወቅ ፡ የሚቻለው ፡ በእነርሱ ፡
፳፣፳፩ ዘንድ ፡ ግልጥ ፡ ነውና ። የማይታየው ፡ በሕይይ እርሱም ፡ የዘላለም ፡ ኃይሉ ፡ ደግሞም ፡ አምላ ክነቱ ፡ ከዓለም ፡ ፍጥረት ፡ ጀምሮ ፡ ከተሠሩት ፡ ታውቆ ፡ ግልጥ ፡ ሆኖ ፡ ይታያልና ፤ ስለዚህም ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያወቁ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔ ርነቱ ፡ መጠን ፡ ስላላከበሩትና ፡ ስላላመሰገኑት ፡ የሚያመካኙት ፡ አጡ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በአሳባቸው ፡ ከንቱ ፡ ሆኑ ፡ የማያስተውለውም ፡ ልባቸው ፡ ጨለመ ። ጥበበኞች ፡ ነን ፡ ሲሉ ፡ ደንቆሮ ፡ ሆኑ ፥
፳፪ የማይጠፋ ውንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ክብር ፡ በሚጠፋ ፡ ሰውና ፡ በወፎች ፡ አራት ፡ እግር ፡ ባላቸውም ፡ በሚንቀሳቀሱትም ፡ መልክ ፡ መስ ለው ፡ ለወጡ ።

፳፬ ስለዚህ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሥጋቸውን ፡ ሊያ ዋርዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ በልባቸው ፡ ፍትወት ፡
፳፭ ወደ ፡ ርኵስነት ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ። ይህም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ እውነት ፡ በውሸት ፡ ስለ ፡ ለወጡ ፡ በፈጣሪም ፡ ፈንታ ፡ የተፈጠረውን ፡ ስላ መለኩና ፡ ስላገለገሉ ፡ ነው ፤ እርሱም ፡ ለዘላለም ፡ የተባረከ ፡ ነው ፤ አሜን ።

፳፮ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሚያስነውር ፡ ምኞት ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፤ ሴቶቻቸውም ፡ ለባ ሕርያቸው ፡ የሚገባውን ፡ ሥራ ፡ ለባሕርያቸው ፡
፳፯ በማይገባው ፡ ለወጡ ፤ እንዲሁም ፡ ወንዶች ፡ ደግሞ ፡ ለባሕርያቸው ፡ የሚገባውን ፡ ሴቶችን ፡ መገናኘት ፡ ትተው ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ በፍት ወታቸው ፡ ተቃጠሉ ፤ ወንዶችም ፡ በወንዶች ፡ ነውር ፡ አድርገው ፡ በስሕተታቸው ፡ የሚገባ ውን ፡ ብድራት ፡ በራሳቸው ፡ ተቀበሉ ።

፳፰ እግዚአብሔርን ፡ ለማወቅ ፡ በልወደዱት ፡ መጠን ፡ እግዚአብሔር ፡ የማይገባውን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ለማይረባ ፡ አእምሮ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፤
፳፱ ዓመፃ ፡ ሁሉ ፡ ግፍ ፡ መመኘት ፡ ክፋት ፡ ሞላባ ቸው ፤ ቅናትን ፡ ነፍስ ፡ መግደልን ፡ ክርክርን ፡ ተንኰልን ፡ ክፉ ፡ ጠባይን ፡ ተሞሉ ፤ የሚያሾ ኩ ፡ ሐሜተኞች ፡ አምላክን ፡ የሚጠሉ ፡
፴ የሚያንገላቱ ፡ ትዕቢተኞች ፡ ትምክህተኞች ፡ ክፋትን ፡ የሚፈላለጉ ፡ ለወላጆቻቸው ፡ የማይ ታዘዙ ፡
፴፩ የማያስተውሉ ፡ ውል ፡ የሚያፈርሱ ፡ ፍቅር ፡ የሌላቸው ፡ ምሕረት ፡ ያጡ ፡ ናቸው ፤
፴፪ እንደነዚህ ፡ ለሚያደርጉት ፡ ሞት ፡ ይገበቸዋል ፡ የሚለውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ እያወቁ ፡ እነዚህን ፡ ከሚያደርጉ ፡ ጋር ፡ ይስማማሉ ፡ እንጂ ፡ አድራጊዎች ፡ ብቻ ፡ አይደሉም ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ ስለዚህ ፡ እንት ፡ የምትፈርድ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሆይ ፥ የምታመካኝው ፡ የለህም ፤ በሌላው ፡ በም ትፈርድበት ፡ ነገር ፡ ራስህን ፡ ትኰንናለህና ፤ አንተው ፡ ፈራጁ ፡ እነዚያን ፡ ታደርጋለህና ።
፪ እንደዚህም ፡ በሚያደርጉት ፡ ላይ ፡ የእግዚአብ ሔር ፡ ፍርድ ፡ እውነተኛ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እናውቃለን ። አንተም ፡ እንደዚህ ፡ በሚያደርጉ ፡ የም ፫ ትፈርድ ፡ ያንም ፡ የምታደርግ ፡ ሰው ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ የምታመልጥ ፡ ይመስልሃልን ? ወይስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቸር ፬ ነት ፡ ወደ ፡ ንስሐ ፡ እንዲመራህ ፡ ሳታውቅ ፡ የቸ ርነቱንና ፡ የመቻሉን ፡ የትዕግሥቱንም ፡ በለ ፡ ጠግነት ፡ ትንቃለህን ? ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ዋንከ ፭ ሬህና ፡ ንስሐ ፡ እንደማይገባ ፡ ልብህ ፡ የእግዚ አብሔር ፡ ቍጣ ፡ ፍርድ ፡ በሚገለጥበት ፡ በቍጣ ፡ ቀን ፡ ቍጣን ፡ በራስህ ፡ ላይ ፡ ታከማቻለህ ።
፮ እርሱ ፡ ለእያንዳንዱ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ያስረክ በዋል ። ፯ በበጎ ፡ ሥራ ፡ በመጽናት ፡ ምስጋናንና ፡ ክብርን ፡ የማይጠፋንም ፡ ሕይወት ፡ ለሚፈልጉ ፡ የዘላለምን ፡ ሕይወት ፡ ይሰጣቸዋል ። ፰ ለዓመፃ ፡ በሚታዘዙ ፡ እንጂ ፡ ለእውነት ፡ በማይታዘዙ ትና ፡ በአድመኞች ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ቍጣና ፡ መቅ ሠፍት ፡ ይሆንባቸዋል ። ፱ ክፋውን ፡ በሚያደ ርግ ፡ ሰው ፡ ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ መከራና ፡ ጭንቀት ፡ ይሆንበታል ፥ አስቀድሞ ፡ በአይሁዳዊ ፡ ደግ ሞም ፡ በግሪክ ፡ ሰው ። ፲ ነገር ፡ ግን ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ለሚያደርጉ ፡ ሁሉ ፡ ምስጋናና ፡ ክብር ፡ ሰላምም ፡

፩ ፡ ፲፮ ፤ ፩ ቆሮ. ፩ ÷ ፲፰ ፡ ፳፬ ። ፲፮ ፤ ም. ፫ ÷ ፳፭ ፡ ፳፱ ። እንባ. ፪ ÷ ፱ ። ፲፱ ፤ የሐዋ. ፲፱ ÷ ፲፯ ። ፳ ፤ መዝ. ፲፰ ÷ ፩—፫ ። ፳፩ ፤ ኤፌ. ፱ ÷ ፲፯ ፤ ፲፰ ። ፳፪ ፤ ኤር. ፭ ÷ ፱ ፤ ፩ ቆሮ. ፩ ÷ ፳ ። ፳፫ ፤ ዘዳግ. ፱ ÷ ፲፩—፲፯ ፤ መዝ. ፻፭ ÷ ፳ ። ፳፬ ፤ መዝ. ፻፮ ÷ ፴ ። ፳፭ ፤ ዘሌዋ. ፲፯ ÷ ፳፪ ። ፳፮ ፤ ዘፍ. ፮ ÷ ፲፪ ። ፳፯ ፤ ሕዝ. ፳፫ ÷ ፲፯ ፤ ፲፰ ። ፳፰ ፤ ኢዮ. ፳፩ ÷ ፲፬ ። ፳፱ ፤ ፩ ዮሐ. ፪ ÷ ፲፮ ። ፴ ፤ ፩ ጢሞ. ፩ ÷ ፲፫ ። ፴፩ ፤ ዘዳግ. ፳፬ ÷ ፲፮ ። ፴፪ ፤ ዘፍ. ፳፰ ÷ ፲፭ ።

፪ ፡ ፩ ፤ ማቴ. ፯ ÷ ፳፩ ፤ ፪ ። ፪ ፤ ዘዳግ. ፴፪ ÷ ፵ ። ፫ ፤ ሮሜ. ፪ ÷ ፩ ። ፬ ፤ ፩ ጴጥ. ፫ ÷ ፱ ። ፭ ፤ ዘዳግ. ፱ ÷ ፭ ። ፮ ፤ ማቴ. ፲፮ ÷ ፳፯ ። ፯ ፤ ሮሜ. ፭ ÷ ፬ ። ፰ ፤ ገላ. ፭ ÷ ፳፪ ። ፱ ፤ ፩—፪ ፤ ፲፮ ÷ ፱—፲ ። ፲ ፤ ዘዳግ. ፲፮ ÷ ፲፯ ። ፲፩ ፤ ሐዋ. ፲፭ ÷ ፱ ። ፲፪ ፤ ሮሜ. ፫ ÷ ፲፱ ። ፲፫ ፤ ያዕ. ፩ ÷ ፳፪—፳፭ ። ፲፬ ፤ የሐዋ. ፲ ÷ ፴፭ ። ፲፭ ፤ መክ. ፲፪ ÷ ፲፬ ፤ የሐዋ. ፲፯ ÷ ፴፩ ። ፲፮ ፤ ማቴ. ፫ ÷ ፱ ፤ ሮሐ. ፯ ÷ ፴፫ ። ፲፱ ፤ ማቴ. ፲፭ ÷ ፲፱ ። ፳፪ ፤ ኢሳ. ፶፪ ÷ ፭ ፤ ሕዝ. ፴፮ ÷ ፳ ። ፳፭ ፤ ማቴ. ፲፪ ÷ ፵፭ ። ፳፱ ፤ ዘዳግ. ፴ ÷ ፮ ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

፩ እንግዲህ ፡ የአይሁዳዊ ፡ ብልጫው ፡ ምንድር ፡ ነው ? ወይስ ፡ የመገረዝ ፡ ዋቅሙ ፡ ምንድር ፡
፪ ነው ? በሁሉ ፡ ነገር ፡ ብዙ ፡ ነው ። አስቀድሞ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃላት ፡ አደራ ፡ ተሰጡአቸው ።
፫ ታዲያ ፡ ምንድር ፡ ነው ? የማያምኑ ፡ ቢኖሩ ፡ አለማመናቸው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታማኝነት ፡ ያስቀራልን ? እንዲህ ፡ አይሁን ፤
፬ በቃልህ ፡ ትጸድቅ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ በገባህም ፡ ጊዜ ፡ ትረታ ፡ ዘንድ ፡
ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፥ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ውሸተኛ ፡ ከሆነ ፡ እግዚአብሔር ፡ እውነተኛ ፡ ይሁን ። ፭ ነገር ፡ ግን ፡ ዓመፃችን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጽድቅ ፡ የሚያስረዳ ፡ ከሆነ ፡ ምን ፡ እንላለን ? ቍጣን ፡ የሚያመጣ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዓመፀኛ ፡ ነውን ?
፮ እንደ ፡ ሰው ፡ ልምድ ፡ እላለሁ ። እንዲህ ፡ አይ ፯ ሁን ፤ እንዲህ ፡ ቢሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ በዓለም ፡ እንዴት ፡ ይፈርዳል ? በእኔ ፡ ውሸት ፡ ግን ፡ የእ ፯ ግዚአብሔር ፡ እውነት ፡ ለክብሩ ፡ ከላቀ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ በእኔ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ኃጢአተኛ ፡ ገና ፡ ይፈርድብኛል ? ስለ ፡ ምንስ ፡ መልካም ፡ እን ፰ዲመጣ ፡ ክፉ ፡ እናደርግም ? እንዲሁ ፡ ይሰድ ቡናልና ፡ እንዳንዱም ፡ እንዲሁ ፡ እንድንል ፡ ይናገራሉና ። የእነርሱም ፡ ፍርድ ፡ ቅን ፡ ነው ።
፱ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ይሁን ? ከእነርሱ ፡ እንበል ጣለንን ? ከቶ ፡ አይደለም ፤ አይሁድም ፡ የግ ሪክ ፡ ሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ ከኃጢአት ፡ በታች ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ አስቀድመን ፡ ከሰናቸዋልና ፤ እንዲህ ፡ ፲ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡—
፲፩ ጻድቅ ፡ የለም ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፤ አስተዋ ፲፪ ይም ፡ የለም ፤ እግዚአብሔርንም ፡ የሚፈ ፲፫ ልግ ፡ የለም ፤ ሁሉ ፡ ተሰስተዋል ፥ በአን ድነትም ፡ የማይጠቅሙ ፡ ሆነዋል ፤ ቸር ፲፬ ነት ፡ የሚያደርግ ፡ የለም ፥ አንድ ፡ ስንኳ ፡ የለም ። ፲፫ ጕሮሯቸው ፡ እንደ ፡ ተከፈተ ፡ መቃብር ፡ ነው ፥ በመላሳቸውም ፡ ሸንገለ ፲፬ ዋል ። የአፋቸው ፡ መርዝ ፡ ከከንፈሮቻቸው ፡ ፲፭ በታች ፡ አለ ። ፲፬ አፋቸውም ፡ እርግማንና ፡ መራርነት ፡ ሞልቶበታል ። ፲፭ እግሮቻቸው ፡ ደምን ፡ ለማፍሰስ ፡ ፈጣኖች ፡ ናቸው ። ፲፮ ፡ ፲፯ ትና ፡ ጕስቍልና ፡ በመንገዳቸው ፡ ይገኛል ፥
፲፰ የሰላምንም ፡ መንገድ ፡ አያውቁም ። ፲፱ በኀ ፲፯፣፲፰ ፡ ፲፱ ልኖቻቸው ፡ ፊት ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍ ራት ፡ የለም ።

አፍም ፡ ሁሉ ፡ ይዘጋ ፡ ዘንድ ፡ ዓለምም ፡ ሁሉ ፡ ፲፱

ጋና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከሰው ፡ አይደለም ።

፯ ይሆንላቸዋል ÷ አስቀድሞ ፡ ለአይሁዳዊ ፡ ደግ ሞም ፡ ለግሪክ ፡ ሰው ። እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ ፊት ፡ አያደላምና ።
፲ ያለ ፡ ሕግ ፡ ኃጢአት ፡ ያደረጉ ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ ደግሞ ፡ ይጠፋሉና ፤ ሕግም ፡ ሳላቸው ፡ ኃጢአት ፡ ያደረጉ ፡ ሁሉ ፡ በሕግ ፡ ይፈረድባቸ ፲፩ ዋል ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሕግን ፡ የሚያ ደርጉት ፡ ይጸድቃሉ ፡ እንጂ ፡ ሕግን ፡ የሚሰሙ ፡ ፲፪ ጻድቃን ፡ አይደሉምና ። ሕግ ፡ የሌላቸው ፡ አሕ ዛብ ፡ ከባሕርያቸው ፡ የሕግን ፡ ትእዛዝ ፡ ሲያደ ርጉ ÷ እነዚያ ፡ ሕግ ፡ ባይኖራቸው ፡ እንኳ ፡ ለራ ፲፫ ሳቸው ፡ ሕግ ፡ ናቸውና ፤ እነርሱም ፡ ሕሊና ቸው ፡ ሲመሰክርላቸው ÷ አሳባቸውም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲካሰስ ፡ ወይም ፡ ሲያመካኝ ፡ በል ፲፬ ቸው ፡ የተጻፈውን ፡ የሕግ ፡ ሥራ ፡ ያሳያሉ ። ይህም ፡ እግዚአብሔር ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እኔ ፡ በወንጌል ፡ እንዳስተማርሁ ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ የተሰወረውን ፡ በሚፈርድበት ፡ ቀን ፡ ይሆናል ። ፲፮
፲፯ አንተ ፡ ግን ፡ አይሁዳዊ ፡ ብትባል ፡ በሕግም ፡ ብትደገፍ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ብትመካ ፡ ፊቃ ፲፰ ዱንም ፡ ብታውቅ ፡ ከሕግም ፡ ተምረህ ፡ የሚሻ ፲፱፡፳ ለውን ፡ ፈትነህ ፡ ብትወድ ፤ በሕግም ፡ የእውቀ ትና ፡ የእውነት ፡ መልክ ፡ ስላለህ ÷ የዕውሮች ፡ መሪ ÷ በጨለማም ፡ ላሉ ፡ ብርሃን ÷ የሰነፎች ፡ አስተማሪ ÷ የሕፃናትም ፡ መምህር ፡ እንደ ፡ ሆንህ ፲፩ በራስህ ፡ ብትታመን ፤ እንግዲህ ፡ አንተ ፡ ሌላ ውን ፡ የምታስተምር ፡ ራስህን ፡ አታስተምር ፲፪ ምን ? አትስረቅ ፡ ብለህ ፡ የምትሰብክ ፡ ትሰርቃ ለህን ? አታመንዝር ፡ የምትል ፡ ታመነዝራለ ህን ? ጣዖትን ፡ የምትጸየፍ ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፲፫ ትዘርፋለህን ? በሕግ ፡ የምትመካ ፡ ሕግን ፡ በመ ተላለፍ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ታስነቅራለህን ? በእ ፲፬ ናንተ ፡ ሰበብ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ይሰደባልና ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ። ፲፭ ሕግን ፡ ብታደርግ ፡ መገረዝስ ፡ ይጠቅማል ። ሕግን ፡ ተላላፊ ፡ ብትሆን ፡ ግን ፡ መገረዝህ ፡ አለ ፲፮ መገረዝ ፡ ሆኖአል ። እንግዲህ ፡ ያልተገረዘ ፡ ሰው ፡ የሕግን ፡ ሥርዓት ፡ ቢጠብቅ ፡ አለመገረዙ ፡ እንደ ፡ መገረዝ ፡ ሆኖ ፡ አይቈጠርለትምን ? ከፍ ፲፯ ጥረቱም ፡ ያልተገረዘ ፡ ሕግን ፡ የሚፈጽም ፡ ሰው ፡ የሕግ ፡ መጽሐፍና ፡ መገረዝ ፡ ሳለህ ፡ ሕግን ፡ በምትተላለፈው ፡ በእንተ ፡ ይፈርድብሃል ። በግ ፳ ልጥ ፡ አይሁዳዊ ፡ የሆነ ፡ አይሁዳዊ ፡ አይደለ ምና ÷ በግልጥ ፡ በሥጋ ፡ የሚደረግ ፡ መገረዝም ፡ ፳፩ መገረዝ ፡ አይደለምና ። ፳ ዳሩ ፡ ግን ፡ በስውር ፡ አይሁዳዊ ፡ የሆነ ፡ አይሁዳዊ ፡ ነው ÷ መገረዝም ፡ በመንፈስ ፡ የሚደረግ ፡ የልብ ፡ መገረዝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በመጽሐፍ ፡ አይደለም ። የእርሱ ፡ ምስ

፲ ፡ ፲፮ ፤ ዘዳግ. ፮ ÷ ፲፮ ፤ የሐዋ. ፲ ÷ ፴፬ ። ፲፫ ፤ ማቴ. ፯ ÷ ፳፩ ፤ ያዕ. ፩ ÷ ፳፪—፳፭ ። ፲፬ ፤ የሐዋ. ፲ ÷ ፴፭ ። ፲፭ ፤ መክ. ፲፪ ÷ ፲፬ ፤ የሐዋ. ፲፯ ÷ ፴፩ ። ፲፮ ፤ ማቴ. ፫ ÷ ፱ ፤ ሮሐ. ፯ ÷ ፴፫ ። ፲፱ ፤ ማቴ. ፲፭ ÷ ፲፱ ። ፳፪ ፤ ኢሳ. ፶፪ ÷ ፭ ፤ ሕዝ. ፴፮ ÷ ፳ ። ፳፭ ፤ ማቴ. ፲፪ ÷ ፵፭ ። ፳፱ ፤ ዘዳግ. ፴ ÷ ፮ ።

፪ ፡ ፩ ፤ ዘዳግ. ፬ ÷ ፰ ። ፪ ፤ ዘዳግ. ፴፪ ÷ ፵ ። ፫ ፤ ሮሜ. ፪ ÷ ፩ ። ፬ ፤ ፩ ጴጥ. ፫ ÷ ፱ ። ፭ ፤ ዘዳግ. ፱ ÷ ፭ ። ፮ ፤ ማቴ. ፲፮ ÷ ፳፯ ። ፯ ፤ ሮሜ. ፭ ÷ ፬ ። ፰ ፤ ገላ. ፭ ÷ ፳፪ ። ፱ ፤ ፩—፪ ፤ ፲፮ ÷ ፱—፲ ። ፲ ፤ ዘዳግ. ፲፮ ÷ ፲፯ ። ፲፩ ፤ ሐዋ. ፲፭ ÷ ፱ ። ፲፪ ፤ ሮሜ. ፫ ÷ ፲፱ ። ፲፫ ፤ ያዕ. ፩ ÷ ፳፪—፳፭ ። ፲፬ ፤ የሐዋ. ፲ ÷ ፴፭ ። ፲፭ ፤ መክ. ፲፪ ÷ ፲፬ ፤ የሐዋ. ፲፯ ÷ ፴፩ ። ፲፮ ፤ ማቴ. ፫ ÷ ፱ ፤ ሮሐ. ፯ ÷ ፴፫ ። ፲፱ ፤ ማቴ. ፲፭ ÷ ፲፱ ። ፳፪ ፤ ኢሳ. ፶፪ ÷ ፭ ፤ ሕዝ. ፴፮ ÷ ፳ ። ፳፭ ፤ ማቴ. ፲፪ ÷ ፵፭ ። ፳፱ ፤ ዘዳግ. ፴ ÷ ፮ ።

ከእግዚአብሔር፡ፍርድ፡በታች፡ይሆን፡ዘንድ፡
ሕግ፡የሚናገረው፡ሁሉ፡ከሕግ፡በታች፡ላሉት፡
፳፤ እንዲናገር ፡ እናውቃለን ፤ ይህም ፡ የሕግን ፡
ሥራ ፡ በመሥራት ፡ ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ ሁሉ ፡ በእ
ርሱ ፡ ፊት ፡ ስለማይጸድቅ ፡ ነው ፤ ኃጢአት ፡
በሕግ ፡ ይታወቃልና ።
፳፩፤ አሁን ፡ ግን ፡ በሕግና ፡ በነቢያት ፡ የተመሰከረ
ለት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጽድቅ ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ ተገ
፳፪፤ ልጦአል ፥ እርሱም ፥ ለሚያምኑ ፡ ሁሉ ፡ የሆነ ፥
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በማመን ፡ የሚገኘው ፡
የእግዚአብሔር ፡ ጽድቅ ፡ ነው ፤ ልዩነት ፡ የለ
፳፫፤ ምና ፤ ሁሉ ፡ ኃጢአትን ፡ ሠርተዋልና ፡ የእግ
፳፬፤ ዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ጎድሎአቸዋል ፤ በኢ
የሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ በሆነው ፡ ቤዛነት ፡ በኩል ፡
፳፭፤ እንዲያው ፡ በጸጋው ፡ ይጸድቃሉ ። እርሱንም ፡
እግዚአብሔር ፡ በእምነት ፡ የሚገኝ ፡ በደሙም ፡
የሆነ ፡ ማስተስሪያ ፡ አድርጎ ፡ አቆመው ፤ ይህም ፡
በፊት ፡ የተደረገውን ፡ ኃጢአት ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ችሎታ ፡ ስለ ፡ መተው ፡ ጽድቁን ፡ ያሳይ ፡
፳፮፤ ዘንድ ፡ ነው ፥ ራሱም ፡ ጻድቅ ፡ እንዲሆን ፡ በኢ
የሱስም ፡ የሚያምነውን ፡ እንዲያጸድቅ ፡ አሁን ፡
በዚህ ፡ ዘመን ፡ ጽድቁን ፡ ያሳይ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።
፳፯፤ ትምክህት ፡ እንግዲህ ፡ ወዴት ፡ ነው ? እርሱ ፡
ቀርቶአል ። በየትኛው ፡ ሕግ ፡ ነው ? በሥራ ፡
ሕግ ፡ ነውን ? አይደለም ፥ በእምነት ፡ ሕግ ፡ ነው ፡
፳፰፤ እንጂ ። ሰው ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ ሥራ ፡ በእምነት ፡
፳፱፡፴፤ እንዲጸድቅ ፡ እንቈጥራለንና ። ወይስ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ የአይሁድ ፡ ብቻ ፡ አምላክ ፡ ነውን ?
የአሕዛብስ ፡ ደግሞ ፡ አምላክ ፡ አይደለምን ?
አዎን ፥ የተገረዘን ፡ ስለ ፡ እምነት ፡ ያልተገረዘ
ንም ፡ በእምነት ፡ የሚያጸድቅ ፡ አምላክ ፡ አንድ ፡
ስለ ፡ ሆነ ፡ የአሕዛብ ፡ ደግሞ ፡ አምላክ ፡ ነው ።
፴፩፤ እንግዲህ ፡ ሕግን ፡ በእምነት ፡ እንሽራለን ? አይ
ደለም ፤ ሕግን ፡ እናጸናለን ፡ እንጂ ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

፩፤ እንግዲህ ፡ በሥጋ ፡ አባታችን ፡ የሆነ ፡ አብር
፪፤ ሃም ፡ ምን ፡ አገኘ ፡ እንላለን ? አብርሃም ፡ በሥራ ፡
ጸድቆ ፡ ቢሆን ፡ የሚመካበት ፡ አለውና ፥ ነገር ፡
፫፤ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አይደለም ። መጽ
ሐፍስ ፡ ምን ፡ አለ ? አብርሃምም ፡ እግዚአብሔ
ርን ፡ አመነ ፡ ጽድቅም ፡ ሆኖ ፡ ተቈጠረለት ።
፬፤ ለሚሠራ ፡ ደመወዝ ፡ እንደ ፡ ዕዳ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
፭፤ እንደ ፡ ጸጋ ፡ አይቈጠርለትም ፤ ነገር ፡ ግን ፡
ለማይሠራ ፥ ኃጢአተኛውንም ፡ በሚያጸድቅ ፡
ለሚያምን ፡ ሰው ፡ እምነቱ ፡ ጽድቅ ፡ ሆኖ ፡ ይቈ
፮፤ ጠርለታል ። እንደዚህ ፡ ዳዊት ፡ ደግሞ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ጽድቅን ፡ ስለሚቈጥ
ርለት ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ብፅዕና ፡ ይናገራል ፡ እንዲህ ፡
ሲል ፡—
ዓመፃቸው ፡ የተሰረየላቸው ፡ ኃጢአታቸ ፯፤
ውም ፡ የተከደነላቸው ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፤
ጌታ ፡ ኃጢአቱን ፡ የማይቈጥርበት ፡ ሰው ፡ ፰፤
ብፁዕ ፡ ነው ።
እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ብፅዕና ፡ ስለ ፡ መገረዝ ፡ ተነ ፱፤
ገረ ? ወይስ ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ አለመገረዝ ? እም
ነቱ ፡ ለአብርሃም ፡ ጽድቅ ፡ ሆኖ ፡ ተቈጠረለት ፡
እንላለንና ። እንዴት ፡ ተቈጠረለት ? ተገርዞ ፡ ፲፤
ሳለ ፡ ነውን ? ወይስ ፡ ሳይገረዝ ? ተገርዞስ ፡ አይ
ደለም ፥ ሳይገረዝ ፡ ነበር ፡ እንጂ ። ሳይገረዝም ፡ ፲፩፤
በነበረው ፡ እምነት ፡ ያገኘው ፡ የጽድቅ ፡ ማኅ
ተም ፡ የሆነ ፡ የመገረዝን ፡ ምልክት ፡ ተቀበለ ፤
ይህም ፡ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ ጻድቃን ፡ ሆነው ፡ ይቈ
ጠሩ ፡ ዘንድ ፡ ሳይገረዙ ፡ ለሚያምኑ ፡ ሁሉ ፡
አባት ፡ እንዲሆን ፡ ነው ፥ ለተገረዙትም ፡ አባት ፡ ፲፪፤
እንዲሆን ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ለተገረዙት ፡ ብቻ ፡
አይደለም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አባታችን ፡ አብርሃም ፡
ሳይገረዝ ፡ የነበረውን ፡ የእምነቱን ፡ ፍለጋ ፡
ደግሞ ፡ ለሚከተሉ ፡ ነው ።
የዓለምም ፡ ወራሽ ፡ እንዲሆን ፡ ለአብርሃምና ፡ ፲፫፤
ለዘሩ ፡ የተሰጠው ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ በእምነት ፡
ጽድቅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሕግ ፡ አይደለም ። ከሕግ ፡ ፲፬፤
የሆኑትስ ፡ ወራሾች ፡ ከሆኑ ፡ እምነት ፡ ከንቱ ፡
ሆኖአል ፡ የተስፋውም ፡ ቃል ፡ ተሽሮአል ፤ ሕጉ ፡ ፲፭፤
መቅሠፍትን ፡ ያደርጋልና ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሕግ ፡
በሌለበት ፡ መተላለፍ ፡ የለም ።
ስለዚህ ፡ ከሕግ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከአብርሃም ፡ ፲፮፡፲፯፤
እምነት ፡ ደግሞ ፡ ለሆነ ፡ ለዘሩ ፡ ሁሉ ፡ የተስ
ፋው ፡ ቃል ፡ እንዲጸና ፡ እንደ ፡ ጸጋ ፡ ይሆን ፡
ዘንድ ፡ በእምነት ፡ ነው ፤ እርሱም ፡— ለብዙ ፡
አሕዛብ ፡ አባት ፡ አደረግሁህ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡
ተጻፈ ፥ ለሙታን ፡ ሕይወት ፡ በሚሰጥ ፡ የሌለ
ውንም ፡ እንዳለ ፡ አድርጎ ፡ በሚጠራ ፡ ባመነበት ፡
በአምላክ ፡ ፊት ፡ የሁላችን ፡ አባት ፡ ነው ። ዘርህ ፡ ፲፰፤
እንዲሁ ፡ ሊሆን ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ተባለ ፥ ተስፋ ፡
ባልሆነው ፡ ጊዜ ፡ የብዙ ፡ አሕዛብ ፡ አባት ፡ እን
ዲሆን ፡ ተስፋ ፡ ይዞ ፡ አመነ ። የመቶ ፡ ዓመትም ፡ ፲፱፤
ሽማግሌ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ምውት ፡ የሆነውን ፡
የራሱን ፡ ሥጋና ፡ የሳራ ፡ ማኅፀን ፡ ምውት ፡ መሆ
ኑን ፡ በእምነቱ ፡ ሳይደክም ፡ ተመለከተ ፤ ለእ ፳፡፳፩፤
ግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ እየሰጠ ፥ የሰጠውንም ፡
ተስፋ ፡ ደግሞ ፡ ሊፈጽም ፡ እንዲችል ፡ አጥብቆ ፡
እየተረዳ ፥ በእምነት ፡ በረታ ፡ እንጂ ፡ በአለማ
መን ፡ ምክንያት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተስፋ ፡ ቃል ፡
አልተጠራጠረም ። ስለዚህ ፡ ደግሞ ፡ ጽድቅ ፡ ፳፪፤
ሆኖ ፡ ተቈጠረለት ። ነገር ፡ ግን ፡— ተቈጠረ ፳፫፤
ለት ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ የተ

፫። ፳ ፤ መዝ. ፻፵፪ ፥ ፪ ፤ ገላ. ፪ ፥ ፲፮ ። ፳፪ ፤ የሐዋ. ፲፭ ፥ ፱ ። ፳፫ ፤ ገላ. ፫ ፥ ፳፪ ። ፳፬ ፤ ማቴ. ፳ ፥ ፳፰ ፤ ቲቶ ፫ ፥ ፯ ። ፳፭ ፤ ዘሌዋ. ፲፯ ፥ ፲፩ ፡ ፲፯ ፤ ፩ ዮሐ. ፪ ፥ ፪ ። ፳፰ ፤ የሐዋ. ፲፫ ፥ ፴፱ ፤ ገላ. ፪ ፥ ፲፮ ። ፴፩ ፤ ማቴ. ፭ ፥ ፲፯ ።
፬። ፫ ፤ ዘፍጥ. ፲፭ ፥ ፮ ። ፱ ፤ ማቴ. ፳ ፥ ፲፫ ፡ ፲፱ ። ፭ ፤ ም. ፫ ፥ ፳፰ ። ፯ ፡ ፰ ፤ መዝ. ፴፩ ፥ ፩ ፡ ፪ ። ፲፩ ፤ ዘፍጥ. ፲፯ ፥ ፲ ። ፲፫ ፤ ዘፍጥ. ፲፯ ፥ ፬—፯ ። ፲፬ ፤ ገላ. ፫ ፥ ፲፰ ፡ ፲፰ ። ፲፭ ፤ ም. ፯ ፥ ፯ ፡ ፲ ። ፲፯ ፤ ዘፍጥ. ፳፪ ፥ ፲፰ ። ፲፯ ፤ ዘፍጥ. ፲፯ ፥ ፭ ፤ ዮሐ. ፭ ፥ ፳፩ ። ፲፰ ፤ ዘፍጥ. ፲፭ ፥ ፭ ። ፲፱ ፤ ዘፍጥ. ፲፯ ፥ ፲፯ ፤ ፲፰ ፥ ፲፩ ። ፳፫ ፤ ም. ፲፭ ፥ ፬ ።

፳፬፡፳፭፤ ጻፈ ፡ አይደለም ፥ ስለ ፡ እኛም ፡ ነው ፡ እንጂ ፤
ስለ ፡ በደላችን ፡ አልፎ ፡ የተሰጠውን ፡ እኛን ፡
ስለ ፡ ማጽደቅም ፡ የተነሣውን ፡ ጌታችንን ፡ ኢየ
ሱስን ፡ ከሙታን ፡ ባስነሣው ፡ ለምናምን ፡ ለእኛ ፡
ይቈጠርልን ፡ ዘንድ ፡ አለው ።

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

፩፤ እንግዲህ ፡ በእምነት ፡ ከጸደቅን ፡ በእግዚአ
ብሔር ፡ ዘንድ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስ
፪፤ ቶስ ፡ ሰላምን ፡ እንያዝ ፤ በእርሱም ፡ ደግሞ ፡
ወደ ፡ ቆምንበት ፡ ወደዚህ ፡ ጸጋ ፡ በእምነት ፡
መግባትን ፡ አግኝተናል ፤ በእግዚአብሔር ፡ ክብ
፫፡፬፤ ርም ፡ ተስፋ ፡ እንመካለን ። ይህም ፡ ብቻ ፡ አይ
ደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፡ መከራ ፡ ትዕግሥትን ፡
እንዲያደርግ ፥ ትዕግሥትም ፡ ፈተናን ፡ ፈተ
ናም ፡ ተስፋን ፡ እንዲያደርግ ፡ እያወቅን ፥ በመ
፭፤ ከራችን ፡ ደግሞ ፡ እንመካለን ፤ በተሰጠንም ፡
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡
በልባችን ፡ ስለ ፡ ፈሰሰ ፡ ተስፋ ፡ አያሳፍርም ።
፮፤ ገና ፡ ደካሞች ፡ ሳለን ፡ ክርስቶስ ፡ ዘመኑ ፡ ሲደ
፯፤ ርስ ፡ ስለ ፡ ኃጢአተኞች ፡ ሞቶአልና ። ስለ ፡
ጻድቅ ፡ የሚሞት ፡ በጭንቅ ፡ ይገኛልና ፤ ስለ ፡
ቸር ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ሊሞት ፡ እንኳ ፡ የሚደፍር ፡
፰፤ ምናልባት ፡ ይገኝ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ገና ፡
ኃጢአተኞች ፡ ሳለን ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ሞቶ
አልና ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእኛ ፡ ያለውን ፡ የራ
፱፤ ሱን ፡ ፍቅር ፡ ያስረዳል ። ይልቁንስ ፡ እንግዲህ ፡
አሁን ፡ በደሙ ፡ ከጸደቅን ፡ በእርሱ ፡ ከቍጣው ፡
፲፤ እንድናለን ። ጠላቶች ፡ ሳለን ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ጋር ፡ በልጁ ፡ ሞት ፡ ከታረቅን ፥ ይልቁንም ፡
ከታረቅን ፡ በኋላ ፡ በሕይወቱ ፡ እንድናለን ፤
፲፩፤ ይህም ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡
መታረቁን ፡ ባገኘንበት ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ በኩል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ደግሞ ፡
እንመካለን ።
፲፪፤ ስለዚህ ፡ ምክንያት ፡ ኃጢአት ፡ በአንድ ፡
ሰው ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ገባ ፡ በኃጢአትም ፡ ሞት ፥
እንደዚሁም ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአትን ፡ ስላደረጉ ፡ ሞት ፡
፲፫፤ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ደረሰ ፤ ሕግ ፡ እስከ ፡ መጣ ፡ ድረስ ፡
ኃጢአት ፡ በዓለም ፡ ነበረና ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሕግ ፡
፲፬፤ በሌለበት ፡ ጊዜ ፡ ኃጢአት ፡ አይቈጠርም ፤ ነገር ፡
ግን ፡ በአዳም ፡ መተላለፍ ፡ ምሳሌ ፡ ኃጢአትን ፡
ባልሠሩት ፡ ላይ ፡ እንኳ ፥ ከአዳም ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡ ሙሴ ፡ ድረስ ፡ ሞት ፡ ነገሠ ፤ አዳም ፡
ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ላለው ፡ ለእርሱ ፡ አምሳሉ ፡
ነውና ።
፲፭፤ ነገር ፡ ግን ፡ ስጦታው ፡ እንደ ፡ በደሉ ፡ መጠን ፡
እንደዚያው ፡ አይደለም ፤ በአንድ ፡ ሰው ፡ በደል ፡
ብዙዎቹ ፡ ሞተዋልና ፥ ነገር ፡ ግን ፡ የእግዚአብ
ሔር ፡ ጸጋና ፡ በአንድ ፡ ሰው ፡ በኢየሱስ ፡ ክር
ስቶስ ፡ ጸጋ ፡ የሆነው ፡ ስጦታ ፡ ከዚያ ፡ ይልቅ ፡
ለብዙዎች ፡ በዛ ። አንድ ፡ ሰውም ፡ ኃጢአትን ፡ ፲፮፤
በማድረጉ ፡ እንደ ፡ ሆነው ፡ መጠን ፡ እንደዚያው ፡
ስጦታው ፡ አይደለም ፤ ፍርድ ፡ ከአንድ ፡ ሰው ፡
ለኵነኔ ፡ መጥቶአልና ፥ ስጦታው ፡ ግን ፡ በብዙ ፡
በደል ፡ ለማጽደቅ ፡ መጣ ። በአንዱም ፡ በደል ፡ ፲፯፤
ሞት ፡ በአንዱ ፡ በኩል ፡ ከነገሠ ፥ ይልቁን ፡ የጸ
ጋን ፡ ብዛትና ፡ የጽድቅን ፡ ስጦታ ፡ ብዛት ፡ የሚ
ቀበሉ ፡ በአንዱ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በኩል ፡
በሕይወት ፡ ይነግሣሉ ።
እንግዲህ ፡ በአንድ ፡ በደል ፡ ምክንያት ፡ ፍርድ ፡ ፲፰፤
ለኵነኔ ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ መጣ ፥ እን
ዲሁም ፡ በአንድ ፡ ጽድቅ ፡ ምክንያት ፡ ስጦታው ፡
ሕይወትን ፡ ለማጽደቅ ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ መጣ ።
በአንዱ ፡ ሰው ፡ አለመታዘዝ ፡ ብዙዎች ፡ ኃጢ ፲፱፤
አተኞች ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፥ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ በአ
ንዱ ፡ መታዘዝ ፡ ብዙዎች ፡ ጻድቃን ፡ ይሆናሉ ።
በደልም ፡ እንዲበዛ ፡ ሕግ ፡ ጭምር ፡ ገባ ፤ ዳሩ ፡ ፳፡፳፩፤
ግን ፡ ኃጢአት ፡ በበዛበት ፥ ኃጢአት ፡ በሞት ፡
እንደ ፡ ነገሠ ፥ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ ጸጋ ፡ ከጌታ
ችን ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተነሣ ፡ በጽድቅ ፡
ምክንያት ፡ ለዘላለም ፡ ሕይወት ፡ ይነግሥ ፡ ዘንድ ፥
ጸጋ ፡ ከመጠን ፡ ይልቅ ፡ በለጠ ።

ምዕራፍ ፡ ፮ ።

እንግዲህ ፡ ምን ፡ እንላለን ? ጸጋ ፡ እንዲበዛ ፡ ፩፤
በኃጢአት ፡ ጸንተን ፡ እንኑርን ? አይደለም ። ፪፤
ለኃጢአት ፡ የሞትን ፡ እኛ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንዴት ፡
አድርገን ፡ በእርሱ ፡ እንኖራለን ? ወይስ ፡ ከክ ፫፤
ርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡
የተጠመቅን ፡ ሁላችን ፡ ከሞቱ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡
እንሆን ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተጠመቅን ፡ አታውቁ
ምን ? እንግዲህ ፡ ክርስቶስ ፡ በአብ ፡ ክብር ፡ ፬፤
ከሙታን ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ እንዲሁ ፡ እኛም ፡ በአ
ዲስ ፡ ሕይወት ፡ እንድንመላለስ ፥ ከሞቱ ፡ ጋር ፡
አንድ ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡ በጥምቀት ፡ ከእርሱ ፡
ጋር ፡ ተቀበርን ።
ሞቱንም ፡ በሚመስል ፡ ሞት ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ፭፤
ከተባበርን ፡ ትንሣኤውን ፡ በሚመስል ፡ ትን
ሣኤ ፡ ደግሞ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ እንተባበራለን ፤
ከእንግዲህስ ፡ ወዲያ ፡ ለኃጢአት ፡ እንዳንገዛ ፡ ፮፤
የኃጢአት ፡ ሥጋ ፡ ይሻር ፡ ዘንድ ፡ አሮጌው ፡ ሰዋ
ችን ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ተሰቀለ ፡ እናውቃ
ለን ፤ የሞተስ ፡ ከኃጢአቱ ፡ ጸድቆአልና ። ነገር ፡ ፯፡፰፤
ግን ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋር ፡ ከሞትን ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡

፬። ፳፭ ፤ ኢሳ. ፶፫ ፥ ፭ ።
፭። ፩ ፤ ም. ፫ ፥ ፳፰ ፤ ፪ ቆሮ. ፭ ፥ ፲፰ ። ፪ ፤ ኤፌ. ፪ ፥ ፲፰ ፤ ፫ ፥ ፲፪ ። ፫ ፤ ማቴ. ፭ ፥ ፲፪ ፤ ያዕ. ፩ ፥ ፫ ። ፭ ፤ መዝ. ፻፲፰ ፥ ፻፲፯ ፤ ፊልጵ. ፩ ፥ ፳ ። ፰ ፤ ዮሐ. ፫ ፥ ፲፯ ፤ ፩ ዮሐ. ፬ ፥ ፲ ። ፱ ፤ ም. ፩ ፥ ፲፰ ። ፲ ፤ ቈላ. ፩ ፥ ፳፩ ፤ ዕብ. ፯ ፥ ፳፭ ። ፲፪ ፤ ዘፍጥ. ፪ ፥ ፲፯ ፤ ፫ ፥ ፮ ። ፲፬ ፤ ፩ ቆሮ. ፲፭ ፥ ፳፪ ፡ ፵፭ ። ፲፰ ፡ ፲፱ ፤ ኢሳ. ፶፫ ፥ ፲፩ ። ፳ ፤ ፩ ጢሞ. ፩ ፥ ፲፫ ፡ ፲፬ ።
፮። ፩ ፤ ም. ፫ ፥ ፰ ። ፪ ፤ ፩ ጴጥ. ፪ ፥ ፳፬ ። ፬ ፤ ቈላ. ፪ ፥ ፲፪ ። ፯ ፤ ገላ. ፪ ፥ ፳ ፤ ፭ ፥ ፳፬ ። ፯ ፤ ፩ ጴጥ. ፬ ፥ ፩ ። ፰ ፤ ፪ ጢሞ. ፪ ፥ ፲፩ ።

ደግሞ ፡ በሕይወት ፡ እንድንኖር ፡ እናምናለን ። ፱ ክርስቶስ ፡ ከሙታን ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንዳ
ይሞት ፡ ሞትም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንዳይገዛው ፡ እና ፲ ውቃለንና ። መሞትን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ
ለኃጢአት ፡ ሞቶአልና ፡ በሕይወት ፡ መኖርን ፡ ግን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይኖራል ። እንዲሁም ፡ ፲፩
እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ለኃጢአት ፡ እንደ ፡ ሞታችሁ ÷ ግን ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ በጌታችን ፡ ሆናችሁ
ለእግዚአብሔር ፡ ሕያዋን ፡ እንደ ፡ ሆናችሁ ፡ ራሳ
ችሁን ፡ ቍጠሩ ።

፲፪ እንግዲህ ፡ ለምኞቱ ፡ እንድትታዘዙ ፡ በሚ ፲፫
ሞት ፡ ሥጋችሁ ፡ ኃጢአት ፡ አይንገሥ ፤ ብል
ቶቻችሁንም ፡ የዓመፃ ፡ የጦር ፡ ዕቃ ፡ አድርጋ
ችሁ ፡ ለኃጢአት ፡ አታቅርቡ ÷ ነገር ፡ ግን ፡ ከሙ
ታን ፡ ተለይታችሁ ፡ በሕይወት ፡ እንደምትኖሩ ፡
ራሳችሁን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አቅርቡ ÷ ብልቶ
ቻችሁንም ፡ የጽድቅ ፡ የጦር ፡ ዕቃ ፡ አድርጋችሁ ፡ ፲፬
ለእግዚአብሔር ፡ አቅርቡ ። ኃጢአት ፡ አይገዛ
ችሁምና ፡ ከጸጋ ፡ በታች ፡ እንጂ ፡ ከሕግ ፡ በታች ፡
አይደላችሁምና ።

፲፭ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ይሁን ? ከጸጋ ፡ በታች ፡
እንጂ ፡ ከሕግ ፡ በታች ፡ ስላይደለን ፡ ኃጢአትን ፡
እንሥራን ? አይደለም ። ለመታዘዝ ፡ ባሪያ ፲፮
ዎች ፡ እንድትሆኑ ፡ ራሳችሁን ፡ ለምታቀርቡ
ለት ÷ ለእርሱ ፡ ለምትታዘዙለት ፡ ባሪያዎች ፡
እንደ ፡ ሆናችሁ ፡ አታውቁምን ? ወይም ፡ ለሞት ፡
የኃጢአት ፡ ባሪያዎች ፡ ወይም ፡ ለጽድቅ ፡ የመ
ታዘዝ ፡ ባሪያዎች ፡ ናችሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ አስቀ ፲፯፡፲፰
ድማችሁ ፡ የኃጢአት ፡ ባሪያዎች ፡ ከሆናችሁ ÷
ለተሰጣችሁለት ፡ ለትምህርት ፡ ዓይነት ፡ ከልባ
ችሁ ፡ ስለ ፡ ታዘዛችሁ ÷ ከኃጢአትም ፡ አርነት ፡
ወጥታችሁ ፡ ለጽድቅ ፡ ስለ ፡ ተገዛችሁ ፡ ለእግ ፲፱
ዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ። ስለ ፡ ሥጋችሁ ፡
ድክም ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ልማድ ፡ እላለሁ ። ብል
ቶቻችሁ ፡ ዓመፃ ፡ ሊያደርጉ ፡ ለርኵስነትና ፡ ለዓ
መፃ ፡ ባሪያዎች ፡ አድርጋችሁ ፡ እንዳቀረባችሁ ÷
እንደዚሁ ፡ ብልቶቻችሁ ፡ ሊቀደሱ ፡ ለጽድቅ ፡
ባሪያዎች ፡ አድርጋችሁ ፡ አሁን ፡ አቅርቡ ።

፳ የኃጢአት ፡ ባሪያዎች ፡ ሳላችሁ ፡ ከጽድቅ ፡ ፳፩
ነፃ ፡ ነበራችሁና ። እንግዲህ ፡ ዛሬ ፡ ከምታፍሩ
በት ፡ ነገር ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ፍሬ ፡ ነበራችሁ ? ፳፪
የዚህ ፡ ነገር ፡ መጨረሻው ፡ ሞት ፡ ነውና ። አሁን ፡
ግን ፡ ከኃጢአት ፡ አርነት ፡ ወጥታችሁ ፡ ለእግ
ዚአብሔርም ፡ ተገዝታችሁ ÷ ልትቀደሱ ፡ ፍሬ ፡
አላችሁ ፤ መጨረሻውም ፡ የዘላለም ፡ ሕይወት ፡
ነው ። የኃጢአት ፡ ደመወዝ ፡ ሞት ፡ ነውና ፤ ፳፫
የእግዚአብሔር ፡ የጸጋ ፡ ስጦታ ፡ ግን ፡ በክርስ
ቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ በጌታችን ፡ የዘላለም ፡ ሕይወት ፡
ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፯ ።

ወንድሞች ፡ ሆይ ÷ ሕግን ፡ ለሚያውቁ ፡ እናገ ፩
ራለሁና ፡ ሰው ፡ ባለበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ሕግ ፡
እንዲገዛው ፡ አታውቁምን ? ያገባች ፡ ሴት ፡ ፪
ባልዋ ፡ በሕይወት ፡ ሲኖር ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ በሕግ ፡
ታስራለችና ፤ ባልዋ ፡ ቢሞት ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ባል ፡
ከሆነው ፡ ሕግ ፡ ተፈትታለች ። ስለዚህ ፡ ባልዋ ፡ ፫
በሕይወት ፡ ሳለ ፡ ለሌላ ፡ ወንድ ፡ ብትሆን ፡ አመ
ንዝራ ፡ ትባላለች ፤ ባልዋ ፡ ቢሞት ፡ ግን ፡ ከሕጉ ፡
እርነት ፡ ወጥታለችና ፡ ለሌላ ፡ ወንድ ፡ ብትሆን ፡
አመንዝራ ፡ አይደለችም ።

እንዲሁ ÷ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ÷ እናንተ ፡ ደግሞ ፬
በክርስቶስ ፡ ሥጋ ፡ ለሕግ ፡ ተገድላችኋል ፤ ለእ
ግዚአብሔር ፡ ፍሬ ፡ እንድናፈራ ÷ እናንተ ፡ ለሌ
ላው ፡ ከሙታን ፡ ለተነሣው ÷ ለእርሱ ፡ ትሆኑ ፡
ዘንድ ። በሥጋ ፡ ሳለን ፡ በሕግ ፡ የሚሠን ፡ የኃጢ ፭
አት ፡ መሻት ፡ ለሞት ፡ ፍሬ ፡ ሊያፈራ ፡ በብልቶ
ቻችን ፡ ይሠራ ፡ ነበርና ፤ አሁን ፡ ግን ፡ ለእርሱ ፡
ለታሰርንበት ፡ ስለ ፡ ሞትን ÷ ከሕግ ፡ ተፈትተ ፮
ናል ÷ ስለዚህም ፡ በአዲሱ ፡ በመንፈስ ፡ ኑሮ ፡
እንገዛለን ፡ እንጂ ፡ በእርጌው ፡ በፊደል ፡ ኑሮ ፡
አይደለም ።

እንግዲህ ፡ ምን ፡ እንላለን ? ሕግ ፡ ኃጢአት ፯
ነውን ? አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በሕግ ፡ ባይሆን ፡
ኃጢአትን ፡ በላወቅሁም ፡ ነበር ። ሕጉ ፡ — አት
መኝ ፡ በላለ ፡ ምኞትን ፡ በላወቅሁም ፡ ነበርና ። ፰
ኃጢአት ፡ ግን ፡ ምክንያት ፡ አግኝቶ ፡ ምኞትን ፡
ሁሉ ፡ በትእዛዝ ፡ ሠራብኝ ፤ ኃጢአት ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡
ሙት ፡ ነውና ። እኔም ፡ ዱሮ ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ ፱
ሕያው ፡ ነበርሁ ፤ ትእዛዝ ፡ በመጣች ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡
ኃጢአት ፡ ሕያው ፡ ሆነ ፡ እኔም ፡ ሞትሁ ። ለሕ ፲
ይወትም ፡ የተሰጠችውን ፡ ትእዛዝ ፡ እርስዋን ፡
ለሞት ፡ ሆና ፡ አገኘኋት ። ኃጢአት ፡ ምክንያት ፡ ፲፩
አግኝቶ ፡ በትእዛዝ ፡ አታሎኛልና ፡ በእርስዋም ፡
ገድሎኛል ። ስለዚህ ፡ ሕጉ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፡ ትእ ፲፪
ዛዚቱም ፡ ቅድስትና ፡ ጻድቅት ፡ በጎም ፡ ናት ።

እንግዲህ ፡ በጎ ፡ የሆነው ፡ ነገር ፡ ለእኔ ፡ ሞት ፡ ፲፫
ሆነብኝን ? አይደለም ÷ ነገር ፡ ግን ፡ ኃጢአት ፡
ሆነ ፤ ኃጢአትም ፡ በትእዛዝ ፡ ምክንያት ፡ ያለ ፡
ልክ ፡ ኃጢአተኛ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ÷ ኃጢአትም ፡
እንዲሆን ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ በጎ ፡ በሆነው ፡ ነገር ፡
ለእኔ ፡ ሞትን ፡ ይሠራ ፡ ነበር ። ሕግ ፡ መንፈሳዊ ፡ ፲፬
እንደ ፡ ሆነ ፡ እናውቃለንና ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ከኃጢ
አት ፡ በታች ፡ ልሆን ፡ የተሸጥሁ ፡ የሥጋ ፡ ነኝ ።
የማደርገውን ፡ አላውቅምና ፤ የምጠላውን ፡ ፲፭
ያን ፡ አደርጋለሁና ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ የምወደውን ፡
እርሱን ፡ አላደርገውም ። የማልወደውን ፡ ግን ፡ ፲፮
የማደርግ ፡ ከሆንሁ ፡ ሕግ ፡ መልካም ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ እመሰክራለሁ ። እንደዚህ ፡ ከሆነ ፡ ያን ፡ ፲፯

የማደርገው ፡ አሁን ፡ እኔ ፡ አይደለሁም ÷ በእኔ ፲፯
የሚያድር ፡ ኃጢአት ፡ ነው ። እንጂ ። በእኔ ፡
ማለት ፡ በሥጋዬ ፡ በኀ ፡ ነገር ፡ እንዳይኖር ፡ አው
ቃለሁና ፤ ፈቃድ ፡ አለኝና ÷ መልካሙን ፡ ግን ፡ ፲፰
ማድረግ ፡ የለኝም ። የማልወደውን ፡ ክፋን ፡
ነገር ፡ አደርጋለሁና ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ የምወደውን ፡
በጎውን ፡ ነገር ፡ አላደርገውም ። የማልወደውን ፡ ፲፱
የማደርግ ፡ ከሆንሁ ፡ ግን ፡ ያን ፡ የማደርገው ፡
አሁን ፡ እኔ ፡ አይደለሁም ÷ በእኔ ፡ የሚኖር ፡ ኃጢ
አት ፡ ነው ፡ እንጂ ።

እንግዲያስ ፡ መልካሙን ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፡ ፳፩
ስወድ ፡ በእኔ ፡ ክፉ ፡ እንዲያድርብኝ ፡ ሕግን ፡
አገኛለሁ ። በውስጡ ፡ ሰውነቴ ፡ በእግዚአብ ፳፪
ሔር ፡ ሕግ ፡ ደስ ፡ ይለኛልና ÷ ነገር ፡ ግን ፡ በብል ፳፫
ቶቼ ፡ ከአእምሮዬ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ የሚዋጋውንና ፡
በብልቶቼ ፡ ባለ ፡ በኃጢአት ፡ ሕግ ፡ የሚማርከ
ኝን ፡ ሌላ ፡ ሕግ ፡ አያለሁ ። እኔ ፡ ምንኛ ፡ ጕስ ፳፬
ቍላ ፡ ሰው ፡ ነኝ ! ለዚህ ፡ ሞት ፡ ከተሰጠ ፡ ሰው
ነት ፡ ማን ፡ ያድነኛል ? በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፳፭
በጌታችን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ።
እንግዲያስ ፡ እኔ ፡ በአእምሮዬ ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ ሕግ ÷ በሥጋዬ ፡ ግን ፡ ለኃጢአት ፡ ሕግ ፡
እገዛለሁ ።

ምዕራፍ ፡ ፰ ።

እንግዲህ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ላሉት ፡ ፩
አሁን ፡ ኵነኔ ፡ የለባቸውም ። በክርስቶስ ፡ ኢየ ፪
ሱስ ፡ ያለው ፡ የሕይወት ፡ መንፈስ ፡ ሕግ ፡ ከኃጢ
አትና ፡ ከሞት ፡ ሕግ ፡ አውጥቶኛልና ። ፫፡፬
ከሥጋ ፡ የተነሣ ፡ ስለ ፡ ደከመ ፡ ለሕግ ፡ ያልተቻ
ለውን ÷ እግዚአብሔር ፡ የገዛ ፡ ልጁን ፡ በኃጢ
አተኛ ፡ ሥጋ ፡ ምሳሌ ፡ በኃጢአትም ፡ ምክንያት ፡
ልክ ፡ አድርጎአልና ፤ እንደ ፡ መንፈስ ፡ ፈቃድ ፡
እንጂ ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ በማንመላለስ ፡
በእኛ ፡ የሕግ ፡ ትእዛዝ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ኃጢ
አትን ፡ በሥጋ ፡ ኰነነ ። እንደ ፡ ሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ ፭
የሚኖሩ ፡ የሥጋን ፡ ነገር ፡ ያስባሉና ÷ እንደ ፡
መንፈስ ፡ ፈቃድ ፡ የሚኖሩ ፡ ግን ፡ የመንፈስን ፡
ነገር ፡ ያስባሉ ። ስለ ፡ ሥጋ ፡ ማሰብ ፡ ሞት ፡ ፮
ነውና ÷ ስለ ፡ መንፈስ ፡ ማሰብ ፡ ግን ፡ ሕይወትና ፡
ሰላም ፡ ነው ። ስለ ፡ ሥጋ ፡ ማሰብ ፡ በእግዚአ ፯
ብሔር ፡ ዘንድ ፡ ጥል ፡ ነውና ፤ ለእግዚአብሔር ፡
ሕግ ፡ አይገዛምና ÷ መገዛትም ፡ ተስኖታል ፤ ፰
በሥጋ ፡ ያሉትም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ሊያ
ሰኙት ፡ አይችሉም ።

እናንተ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ፱
በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ቢኖር ÷ በመንፈስ ፡ እንጂ ፡
በሥጋ ፡ አይደላችሁም ። የክርስቶስ ፡ መንፈስ ፡
የሌለው ፡ ከሆነ ፡ ግን ፡ ይኸው ፡ የእርሱ ፡ ወገን ፡
አይደለም ። ክርስቶስ ፡ በእናንተ ፡ ውስጥ ፡ ፲
ቢሆን ፡ ሰውነታችሁ ፡ በኃጢአት ፡ ምክንያት ፡
የሞተ ፡ ነው ÷ መንፈሳችሁ ፡ ግን ፡ በጽድቅ ፡
ምክንያት ፡ ሕያው ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ኢየሱ ፲፩
ስን ፡ ከሙታን ፡ ያስነሣው ፡ የእርሱ ፡ መንፈስ ፡
በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ቢኖር ÷ ክርስቶስን ፡ ኢየሱስን ፡
ከሙታን ፡ ያስነሣው ፡ እርሱ ፡ በእናንተ ፡ በሚ
ኖረው ፡ በመንፈሱ ÷ ለሚሞተው ፡ ሰውነታችሁ ፡
ደግሞ ፡ ሕይወትን ፡ ይሰጠዋል ።

እንግዲህ ÷ ወንድሞች ፡ ሆይ ÷ ዕዳ ፡ አለብን ÷ ፲፪
እንደ ፡ ሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ ግን ፡ እንኖር ፡ ዘንድ ፡
ለሥጋ ፡ አይደለም ። እንደ ፡ ሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ ፲፫
ብትኖሩ ፡ ትሞቱ ፡ ዘንድ ፡ አላችሁና ፤ በመን
ፈስ ፡ ግን ፡ የሰውነትን ፡ ሥራ ፡ ብትገድሉ ፡ በሕ
ይወት ፡ ትኖራላችሁ ። በእግዚአብሔር ፡ መን ፲፬
ፈስ ፡ የሚመሩ ፡ ሁሉ ፡ እነዚህ ፡ የእግዚአብ
ሔር ፡ ልጆች ፡ ናቸውና ። አባ ፡ አባት ፡ ብለን ፡ ፲፭
የምንጮኽበትን ፡ የልጅነትን ፡ መንፈስ ፡ ተቀ
በላችሁ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለፍርሃት ፡ የባር
ነትን ፡ መንፈስ ፡ አልተቀበላችሁምና ። የእግ ፲፮
ዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ መሆናችንን ፡ ያ ፡ መን
ፈስ ፡ ራሱ ፡ ከመንፈሳችን ፡ ጋር ፡ ይመሰክራል ።
ልጆች ፡ ከሆንን ፡ ወራሾች ፡ ደግሞ ፡ ነን ፤ ማለት ፡
የእግዚአብሔር ፡ ወራሾች ፡ ነን ÷ አብረንም ፡
እንድንከበር ፡ አብረን ፡ መከራ ፡ ብንቀበል ፡
ከክርስቶስ ፡ ጋር ፡ አብረን ፡ ወራሾች ፡ ነን ።

ለእኛም ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ ካለው ፡ ክብር ፡ ፲፰
ጋር ፡ ቢመዛዘን ፡ የአሁኑ ፡ ዘመን ፡ ሥቃይ ፡
ምንም ፡ እንዳይደለ ፡ አስባለሁ ። የፍጥረት ፡ ፲፱
ናፍቆት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ልጆች ፡ መገለጥ ፡
ይጠባበቃልና ። ፍጥረት ፡ ለከንቱነት ፡ ተገዝ ፳
ቶአልና ÷ በተስፋ ፡ ስላስገዛው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
በፈቃዱ ፡ አይደለም ፤ ተስፋውም ፡ ፍጥረት ፡ ፳፩
ራሱ ፡ ደግሞ ፡ ከጥፋት ፡ በርነት ፡ ነፃነት ፡ ወጥቶ ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ወደሚሆን ፡ ክብር ፡
ነፃነት ፡ እንዲደርስ ፡ ነው ። ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ፳፪
እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ አብሮ ፡ በመቃተትና ፡
በምጥ ፡ መኖሩን ፡ እናውቃለንና ። እርሱም ፡ ፳፫
ብቻ ፡ አይደለም ÷ ነገር ፡ ግን ፡ የመንፈስ ፡ በኩ
ራት ፡ ያለን ፡ ራሳችን ፡ ደግሞ ፡ የሰውነታችን ፡
ቤዛ ፡ የሆነውን ፡ ልጅነት ፡ እየተጠባበቅን ፡ ራሳ
ችን ፡ በውስጣችን ፡ እንቃትታለን ። በተስፋ ፡ ፳፬
ድነናልና ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ተስፋ ፡ የሚደረግበቱ ፡
ነገር ፡ ቢታይ ፡ ተስፋ ፡ አይደለም ። የሚያየ
ውንማ ፡ ማን ፡ ተስፋ ፡ ያደርገዋል ? የማናየ ፳፭
ውን ፡ ግን ፡ ተስፋ ፡ ብናደርገው ፡ በትዕግሥት ፡
እንጠባበቃለን ።

፳፮ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ መንፈስ ፡ ድካማችንን ፡
ያግዛል ፤ እንዴት ፡ እንድንጸልይ ፡ እንደሚገ
ባን ፡ አናውቅምና ÷ ነገር ፡ ግን ፡ መንፈስ ፡ ራሱ ፡
፳፯ በማይነገር ፡ መቃተት ፡ ይማልድልናል ፤ ልብ
ንም ፡ የሚመረምረው ፡ የመንፈስ ፡ አሳብ ፡ ምን ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ ያውቃል ÷ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ፈቃድ ፡ ስለ ፡ ቅዱሳን ፡ ይማልዳልና ።
፳፰ እግዚአብሔርንም ፡ ለሚወዱት ፡ እንደ ፡ አሳ
ቡም ፡ ለተጠሩት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለበጎ ፡ እንዲደ
፳፱ ረግ ፡ እናውቃለን ። ልጁ ፡ በብዙ ፡ ወንድሞች ፡
መካከል ፡ በኵር ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ÷ አስቀድሞ ፡
ያወቃቸው ፡ የልጁን ፡ መልክ ፡ እንዲመስሉ ፡
፴ አስቀድሞ ፡ ደግሞ ፡ ወሰናቸውና ፤ አስቀድ
ሞም ፡ የወሰናቸውን ፡ እነዚህን ፡ ደግሞ ፡ ጠራ
ቸው ፤ የጠራቸውንም ፡ እነዚህን ፡ ደግሞ ፡
አጸደቃቸው ፤ ያጸደቃቸውንም ፡ እነዚህን ፡
ደግሞ ፡ አከበራቸው ።
፴፩ እንግዲህ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ምን ፡ እንላለን ?
እግዚአብሔር ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ከሆነ ፡ ማን ፡ ይቃ
፴፪ ወመናል ? ለገዛ ፡ ልጁ ፡ ያልራራለት ፡ ነገር ፡
ግን ፡ ስለ ፡ ሁላችን ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠው ፡ ያው ፡
ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ደግሞ ፡ ሁሉን ፡ ነገር ፡ እንዲያው ፡
፴፫ እንዴት ፡ አይሰጠንም ? እግዚአብሔር ፡ የመ
ረጣቸውን ፡ ማን ፡ ይከሳቸዋል ? የሚያጸድቅ ፡
፴፬ እግዚአብሔር ፡ ነው ÷ የሚኰንንስ ፡ ማን ፡ ነው ?
የሞተው ÷ ይልቁንም ፡ ከሙታን ፡ የተነሣው ÷
በእግዚአብሔር ፡ ቀኝ ፡ ያለው ÷ ደግሞ ፡ ስለ ፡
እኛ ፡ የሚማልደው ፡ ክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ነው ።
፴፭ ከክርስቶስ ፡ ፍቅር ፡ ማን ፡ ይለየናል ? መከራ ÷
ወይስ ፡ ጭንቀት ÷ ወይስ ፡ስደት ÷ ወይስ ፡ ራብ ÷
ወይስ ፡ ራቁትነት ÷ ወይስ ፡ ፍርሃት ÷ ወይስ ፡
ሰይፍ ፡ ነውን ?
፴፮ ስለ ፡ አንተ ፡ ቀኑን ፡ ሁሉ ፡ እንገደላለን ÷
እንደሚታረዱ ፡ በጎች ፡ ተቈጠርን ፡
ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ነው ።
፴፯ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ በወደደን ፡ በእርሱ ፡ ከአሸ
፴፰ ናፊዎች ፡ እንበልጣለን ። ሞት ፡ ቢሆን ÷ ሕይወ
ትም ፡ ቢሆን ÷ መላእክትም ፡ ቢሆኑ ÷ ግዛትም ፡
ቢሆን ÷ ያለውም ፡ ቢሆን ÷ የሚመጣውም ፡
፴፱ ቢሆን ÷ ኃይላትም ፡ ቢሆኑ ÷ ከፍታም ፡ ቢሆን ÷
ዝቅታም ፡ ቢሆን ÷ ልዩ ፡ ፍጥረትም ፡ ቢሆን ፡
በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ በጌታችን ፡ ካለ ፡ ከእግዚ
አብሔር ፡ ፍቅር ፡ ሊለየን ፡ እንዳይችል ፡ ተረድ
ቼአለሁ ።

ምዕራፍ ፡ ፱ ።

ብዙ ፡ ኀዘን ፡ የማያቋርጥም ፡ ጭንቀት ፡ በልቤ ፡ ፩፡፪፡
አለብኝ ፡ ስል ፡ በክርስቶስ ፡ ሆኜ ፡ እውነትን ፡
እናገራለሁ ፤ አልዋሽምም ፤ ሕሊናዬም ፡ በመ
ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመሰክርልኛል ። በሥጋ ፡ ዘመ ፫፡
ዶቼ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ስለ ፡ ወንድሞቼ ፡ ከክርስቶስ ፡
ተለይቼ ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ የተረገምሁ ፡ እንድሆን ፡
እጸልይ ፡ ነበርና ። እነርሱ ፡ እስራኤላውያን ፡ ፬፡
ናቸውና ÷ ልጅነትና ፡ ክብር ፡ ኪዳንም ፡ የሕ
ግም ፡ መሰጠት ፡ የመቅደስም ፡ ሥርዓት ፡ የተስ
ፋውም ፡ ቃላት ፡ ለእነርሱ ፡ ናቸውና ፤ አባቶ ፭፡
ችም ፡ ለእነርሱ ፡ ናቸውና ፤ ከእነርሱም ፡ ክርስ
ቶስ ፡ በሥጋ ፡ መጣ ÷ እርሱም ፡ ከሁሉ ፡ በላይ ፡
ሆኖ ፡ ለዘላለም ፡ የተባረከ ፡ አምላክ ፡ ነው ፤
አሜን ።
ነገር ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የተሻረ ፡ ፮፡
አይደለም ። እነዚህ ፡ ከእስራኤል ፡ የሚወለዱ ፡
ሁሉ ፡ እስራኤል ፡ አይደሉምና ፤ የአብርሃምም ፡ ፯፡
ዘር ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ሁላቸው ፡ ልጆች ፡ አይደሉም ÷
ነገር ፡ ግን ፡— በይስሐቅ ፡ ዘር ፡ ይጠራልሃል ፡
ተባለ ። ይህም ÷ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ልጆች ፡ ዘር ፡ ፰፡
ሆነው ፡ ይቈጠራሉ ፡ እንጂ ፡ እነዚህ ፡ የሥጋ ፡
ልጆች ፡ የሆኑ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ አይደ
ሉም ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህ ፡— በዚህ ፡ጊዜ ፡ እመ ፱፡
ጣለሁ ፡ ለሳራም ፡ ልጅ ፡ ይሆንላታል ፡ የሚል ፡
የተስፋ ፡ ቃል ፡ ነውና ። ይህ ፡ ብቻ ፡ አይደ ፲፡
ለም ÷ ነገር ፡ ግን ፡ ርብቃ ፡ ደግሞ ፡ ከአንዱ ፡ ከአ
ባታችን ፡ ከይስሐቅ ፡ በፀነሰች ፡ ጊዜ ÷ ልጆቹ ፡ ፲፩፡
ገና ፡ ሳይወለዱ ÷ በጎ ፡ ወይም ፡ ክፉ ፡ ምንም ፡
ሳያደርጉ ÷ ከጠሪው ፡ እንጂ ፡ ከሥራ ፡ ሳይሆን ፡
በምርጫ ፡ የሚሆን ፡ የእግዚአብሔር ፡ አሳብ ፡
ይጸና ፡ ዘንድ ÷ ለእርስዋ ፡— ታላቁ ፡ ለታናሹ ፡ ፲፪፡
ይገዛል ፡ ተባለላት ። ያዕቆብን ፡ ወደድሁ ፡ ኤሳ ፲፫፡
ውን ፡ ግን ፡ ጠላሁ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ነው ።
እንግዲህ ፡ ምን ፡ እንላለን ? በእግዚአብሔር ፡ ፲፬፡
ዘንድ ፡ ዓመፃ ፡ አለ ፡ ወይ ? አይደለም ። ለሙሴ ፡— ፲፭፡
የምምረውን ፡ ሁሉ ፡ እምረዋለሁ ፡ ለምራራለ
ትም ፡ ሁሉ ፡ እራራለታለሁ ፡ ይላልና ። እንግ ፲፮፡
ዲህ ፡ ምሕረት ፡ ለወደደ ፡ ወይም ፡ ለሮጠ ፡ አይደ
ለም ÷ ከሚምር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንጂ ።
መጽሐፍ ፡ ፈርዖንን ፡— ኃይሌን ፡ በአንተ ፡ አሳይ ፡ ፲፯፡
ዘንድ ፡ ስሜም ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ይነገር ፡ ዘንድ ፡
ለዚህ ፡ አስነሣሁህ ፡ ይላልና ። እንግዲህ ፡ የሚ ፲፰፡
ወደውን ፡ ይምረዋል ÷ የሚወደውንም ፡ እል

፰። ፳፯፤ ቈላ· ፯፤ መዝ· ፻፴፰ ÷ ፩ ። ፳፰፤ ዘፍጥ· ፶ ÷ ፳ ፤ ኤፌ· ፩ ÷ ፲፩ ። ፳፱፤ ፊልጵ· ፫ ÷ ፳፩ ፤ ቈላ· ፩ ÷ ፲፭ ። ፴፤ ፩ ቆሮ· ፮ ÷ ፲፩ ። ፴፩፤ መዝ· ፻፲፯ ÷ ፮ ። ፴፪፤ ዮሐ· ፫ ÷ ፲፮ ፤ ፩ ቆሮ· ፫ ÷ ፳፩—፳፫ ። ፴፫፤ ኢሳ· ፶ ÷ ፰ ፤ ፱ ። ፴፬፤ ዕብ· ፯ ÷ ፳፭ ፤ ፩ ዮሐ· ፪ ÷ ፩ ። ፴፭፤ ዮሐ· ፲ ÷ ፳፰ ። ፴፮፤ መዝ· ፵፫ ÷ ፳፪ ። ፴፯፤ ፩ ቆሮ· ፲፭ ÷ ፶፯ ። ፴፰፤ ኤፌ· ፯ ÷ ፲፪ ። ፴፱፤ ዮሐ· ፲፯ ÷ ፳፯ ።

፱። ፫፤ ዘፀአ· ፴፪ ÷ ፴፪ ። ፬፤ ዘፀአ· ፬ ÷ ፳፪ ፤ ፵ ÷ ፴፬ ፤ ዘፍጥ· ፲፯ ÷ ፪ ፤ ዘፀአ· ፪ ÷ ፳፬ ፤ ዘዳግ· ፩ ÷ ፲፪ ፤ ፲፫ ፤ ዕብ· ፱ ÷ ፩ ፤ ዘፍጥ· ፲፪ ÷ ፪ ፤ ፫ ። ፭፤ ዘዳግ· ፲ ÷ ፲፭ ፤ ማቴ· ፩ ÷ ፲፮ ፤ ዮሐ· ፩ ÷ ፩ ። ፮፤ ዘኍል· ፳፫ ÷ ፲፱ ። ፯፤ ዘፍጥ· ፳፩ ÷ ፲፪ ። ፰፤ ገላ· ፫ ÷ ፳፱ ፤ ፬ ÷ ፳፫ ፤ ፳፰ ። ፱፤ ዘፍጥ· ፲፰ ÷ ፲ ። ፲፤ ዘፍጥ· ፳፭ ÷ ፳፩ ። ፲፪፤ ዘፍጥ· ፳፭ ÷ ፳፫ ። ፲፫፤ ሚል· ፩ ÷ ፪ ፤ ፫ ። ፲፬፤ መዝ· ፺፩ ÷ ፲፭ ። ፲፭፤ ዘፀአ· ፴፫ ÷ ፲፱ ። ፲፮፤ ኤፌ· ፪ ÷ ፰ ። ፲፯፤ ዘፀአ· ፱ ÷ ፲፮ ። ፳፤ ኢሳ· ፵፭ ÷ ፱ ። ፳፩፤ ኤር· ፲፰ ÷ ፮ ።

ክኛ ፡ ያደርገዋል ።
፲፱ እንግዲህ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡
ይነቅፉል ? ፈቃዱንስ ፡ የሚቃወም ፡ ማን ፡ ነው ?
፳ ትለኝ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ÷ አንተ ፡ ሰው ፡
ሆይ ÷ ለእግዚአብሔር ፡ የምትመልስ ፡ ማን ፡ ነህ ?
ሥራ ፡ ሠሪውን ፡— ስለ ፡ ምን ፡ እንዲህ ፡ አድር
፳፩ ገህ ፡ ሠራኸኝ ፡ ይለዋልን ? ወይም ፡ ሸክላ ፡
ሠሪ ፡ ከአንዱ ፡ ጭቃ ፡ ክፍል ፡ አንዱን ፡ ዕቃ ፡
ለክብር ፡ አንዱንም ፡ ለውርደት ፡ ሊሠራ ፡ በጭቃ ፡
፳፪ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ የለውምን ? ነገር ፡ ግን ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ኃይሉን ፡ የሚገልጽበትን ፡ ቅጣቱን ፡
ሊያሳይ ፡ ቢወድ ፡ ትዕግሥቱን ፡ ካሳየ ፡ በኋላ ፡ ለማ
ጥፋት ፡ የተዘጋጁትን ፡ ቁጣውን ፡ የሚገልጽበት ፡
መላእክትን ፡ ያመጣል * ።
፳፫ ዳግመኛም ፡ የጌትነቱን ፡ ብዛት ፡ ሊያሳይ ፡
ቢወድ ፡ አስቀድሞ ፡ መርጦ ፡ በወደዳቸው ፡ ለይቅ
ርታ ፡ የተዘጋጁ ፡ የይቅርታ ፡ መላእክትን ፡ ያመ
፳፬ ጣል * ። ወደ ፡ ክብሩ ፡ የጠራን ፡ የሰበሰበን ፡ እኛ ፡
ነን ፤ ከአይሁድ ፡ አይደለም ፤ ከአሕዛብም ፡
፳፭ እንጂ ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ በሆሴዕ ፡
ሕዝቤ ፡ ያልሆነውን ፡ ሕዝቤ ፡ ብዬ ፡ ያል
ተወደደችውንም ፡ የተወደደችው ፡ ብዬ ፡
፳፮ እጠራለሁ ፤ እናንተ ፡ ሕዝቤ ፡ አይደላችሁም ፡
በተባለላቸውም ፡ ስፍራ ፡ በዚያ ፡ የሕያው ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ተብለው ፡ ይጠራሉ ፡
ይላል ።
፳፯፡፳፰፡ ኢሳይያስም ፡— የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ቍጥር ፡
ምንም ፡ እንደ ፡ በሕር ፡ አሸዋ ፡ ቢሆን ፡ ቅሬታው ፡
ይድናል ፤ ጌታ ፡ ነገሩን ፡ ፈጽሞና ፡ ቈርጦ ፡ በም
ድር ፡ ላይ ፡ ያደርገዋልና ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ እስራ
፳፱ ኤል ፡ ይጮኻል ። ኢሳይያስም ፡ እንደዚሁ ፡—
ጌታ ፡ ፀባዖት ፡ ዘር ፡ ባላስቀረልን ፡ እንደ ፡
ሰዶም ፡ በሆንን ፡ ገሞራንም ፡ በመሰልን ፡
ነበር ፡
ብሎ ፡ አስቀድሞ ፡ ተናገረ ።
፴ እንግዲህ ፡ ምን ፡ እንላለን ? ጽድቅን ፡ ያል
ተከተሉት ፡ አሕዛብ ፡ ጽድቅን ፡ አገኙ ÷ እርሱ ፡
፴፩ ግን ፡ ከእምነት ፡ የሆነ ፡ ጽድቅ ፡ ነው ፤ እስራ
ኤል ፡ ግን ፡ የጽድቅን ፡ ሕግ ፡ እየተከተሉ ፡ ወደ ፡
፴፪፡ ፴፫፡ ሕግ ፡ አልደረሱም ። ይህስ ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡
ነው ? በሥራ ፡ እንጂ ፡ በእምነት ፡ ጽድቅን ፡
ስላልተከተሉ ፡ ነው ፤
እነሆ ÷ በጽዮን ፡ የእንቅፋት ፡ ድንጋይና ፡
የማሰናከያ ፡ ዓለት ፡ አኖራለሁ ፡ በእርሱም ፡
የሚያምን ፡ አያፍርም ፡
ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ በእንቅፋት ፡ ድንጋይ ፡
ተሰናከሉ ።

ምዕራፍ ፡ ፲ ።

ወንድሞች ፡ ሆይ ÷ የልቤ ፡ በጎ ፡ ፈቃድና ፡ ስለ ፡ ፩፡
እስራኤል ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልመናዬ ፡
እንዲድኑ ፡ ነው ። በእውቀት ፡ አይቅኑ ፡ እንጂ ፡ ፪፡
ለእግዚአብሔር ፡ እንዲቀኑ ፡ እመሰክርላቸዋ
ለሁና ። የእግዚአብሔርን ፡ ጽድቅ ፡ ሳያውቁ ፡ ፫፡
የራሳቸውንም ፡ ጽድቅ ፡ ሊያቆሙ ፡ ሲፈልጉ ÷
ለእግዚአብሔር ፡ ጽድቅ ፡ አልተገዙም ። የሚ ፬፡
ያምኑ ፡ ሁሉ ፡ ይጸድቁ ፡ ዘንድ ፡ ክርስቶስ ፡
የሕግ ፡ ፍጻሜ ፡ ነውና ።
ሙሴ ፡ ከሕግ ፡ የሆነውን ፡ ጽድቅ ፡ የሚያደር ፭፡
ገው ፡ ሰው ፡ በእርሱ ፡ በሕይወት ፡ እንዲኖር ፡
ጽፎአልና ። ከእምነት ፡ የሆነ ፡ ጽድቅ ፡ ግን ፡ ፮፡
እንዲህ ፡ ይላል ፡— በልብህ ፡— ማን ፡ ወደ ፡
ሰማይ ፡ ይወጣል ? አትበል ፤ ይህ ፡ ክርስቶ
ስን ፡ ለማውረድ ፡ ነው ፤ ወይም ፡— በልብህ ፡— ፯፡
ወደ ፡ ጥልቁ ፡ ማን ፡ ይወርዳል ? አትበል ፤
ይህ ፡ ክርስቶስን ፡ ከሙታን ፡ ለማውጣት ፡ ነው ።
ነገር ፡ ግን ፡ ምን ፡ ይላል ? በአፍህ ፡ በልብህም ፡ ፰፡
ሆኖ ፡ ቃሉ ፡ ቀርቦልሃል ፤ ይህም ፡ የምንሰብ
ከው ፡ የእምነት ፡ ቃል ፡ ነው ። ኢየሱስ ፡ ጌታ ፡ ፱፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ በአፍህ ፡ ብትመሰክር ፡ እግዚአብ
ሔርም ፡ ከሙታን ፡ እንዳስነሣው ፡ በልብህ ፡ ብታ
ምን ፡ ትድናለህና ፤ ሰው ፡ በልቡ ፡ አምኖ ፡ ይጸ ፲፡
ድቃልና ፡ በአፉም ፡ መስክሮ ፡ ይድናልና ።
መጽሐፍ ፡— በእርሱ ፡ የሚያምን ፡ ሁሉ ፡ አያ ፲፩፡
ፍርም ፡ ይላልና ። በአይሁዳዊና ፡ በግሪክ ፡ ፲፪፡
ሰው ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ የለምና ፤ አንዱ ፡
ጌታ ፡ የሁሉ ፡ ጌታ ፡ ነውና ÷ ለሚጠሩትም ፡ ሁሉ ፡
ባለ ፡ ጠጋ ፡ ነው ፤ የጌታን ፡ ስም ፡ የሚጠራ ፡ ፲፫፡
ሁሉ ፡ ይድናልና ።
እንግዲህ ፡ ያላመኑበትን ፡ እንዴት ፡ አድር ፲፬፡
ገው ፡ ይጠሩታል ? ባልሰሙትስ ፡ እንዴት ፡
ያምናሉ ? ያለ ፡ ሰባኪስ ፡ እንዴት ፡ ይሰማሉ ?
መልካሙን ፡ የምሥራች ፡ የሚያወሩ ፡ እግሮቻ ፲፭፡
ቸው ፡ እንዴት ፡ ያማሩ ፡ ናቸው ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡
ተጻፈ ፡ ካልተላኩ ፡ እንዴት ፡ ይሰብካሉ ? ነገር ፡ ፲፮፡
ግን ፡ ሁሉ ፡ ለምሥራቹ ፡ ቃል ፡ አልታዘዙም ።
ኢሳይያስ ፡— ጌታ ፡ ሆይ ÷ ምስክርነታችንን ፡
ማን ፡ አመነ ? ብሎአልና ። እንግዲያስ ፡ እም ፲፯፡
ነት ፡ ከመስማት ፡ ነው ፡ መስማትም ፡ በእግዚአ
ሔር ፡ ቃል ፡ ነው ።
ዳሩ ፡ ግን ፡— በይሰሙ ፡ ነው ፡ ወይ ? እላለሁ ። ፲፰፡
በእውነት ፡—
ድምፃቸው ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቃላቸ
ውም ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ዳርቻ ፡ ወጣ ።
ነገር ፡ ግን ፡— እስራኤል ፡ ባያውቁ ፡ ነው ፡ ወይ ? ፲፱፡

፱። ፳፪፤ ምሳ· ፲፮ ÷ ፱ ። ፳፫፤ ም· ፰ ÷ ፳፱ ። ፳፬፤ ም· ፫ ÷ ፳፱ ። ፳፭፤ ሆሴ· ፪ ÷ ፳፫ ። ፳፮፤ ሆሴ· ፪ ÷ ፩ ። ፳፯፤ ፳፰፤ ኢሳ· ፲ ÷ ፳፪ ፤ ፳፫ ። ፳፱፤ ኢሳ· ፩ ÷ ፱ ፤ ዘፍጥ· ፲፱ ÷ ፳፬ ፤ ፳፭ ። ፴፪፤ ዮሐ· ፯ ÷ ፳፰ ፤ ፳፱ ። ፴፫፤ ኢሳ· ፳፰ ÷ ፲፯ ፤ ፰ ÷ ፲፬ ።

፲። ፪፤ የሐዋ· ፳፪ ÷ ፫ ። ፬፤ ማቴ· ፭ ÷ ፲፯ ፤ ገላ· ፫ ÷ ፳፬ ። ፭፤ ዘሌዋ· ፲፰ ÷ ፭ ። ፮—፰፤ ዘዳግ· ፴ ÷ ፲፪—፲፬ ። ፱፤ ማቴ· ፲ ÷ ፴፪ ። ፲፩፤ ም· ፱ ÷ ፴፫ ። ፲፪፤ ም· ፫ ÷ ፳፪ ፤ ፳፱ ፤ የሐዋ· ፲ ÷ ፴፬ ፤ ፴፭ ። ፲፫፤ ኢዩ· ፪ ÷ ፴፪ ። ፲፭፤ ኢሳ· ፶፪ ÷ ፯ ። ፲፮፤ ኢሳ· ፶፫ ÷ ፩ ፤ ዮሐ· ፲፪ ÷ ፴፯ ፤ ፴፰ ። ፲፯፤ ዮሐ· ፲፯ ÷ ፳ ። ፲፰፤ መዝ· ፲፰ ÷ ፬ ። ፲፱፤ ዘዳግ· ፴፪ ÷ ፳፩ ።
፱ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ « የቊጣ ፡ መላእክት » እና « የምሕረት ፡ መላእክት » የሚለው ፡ በግሪኩ ፡
« የቊጣ መሣሪያዎች » እና « የምሕረት ፡ መሣሪያዎች » ይላል ።

እላለሁ ። ሙሴ ፡ አስቀድሞ ፡—
እኔ ፡ ሕዝብ ፡ በማይሆነው ፡ አስቀናችኋለሁ ፡
በማያስተውልም ፡ ሕዝብ ፡ አስቈጣችኋ
ለሁ ፡
፳፤ ብሎአል ። ኢሳይያስም ፡ ደፍሮ ፡—
ላልፈለጉኝ ፡ ተገኘሁ ÷ ላልጠየቁኝም ፡ ተገ
ለጥሁ ፡
፳፩፤ አለ ። ስለ ፡ እስራኤል ፡ ግን ፡— ቀኑን ፡ ሁሉ ፡
ወደማይታዘዝና ፡ ወደሚቃወም ፡ ሕዝብ ፡ እጆ
ቼን ፡ ዘረጋሁ ፡ ይላል ።

ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

፩፤ እንግዲህ ፡— እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ ጣላ
ቸውን ? እላለሁ ። አይደለም ፤ እኔ ፡ ደግሞ ፡
እስራኤላዊና ፡ ከአብርሃም ፡ ዘር ፡ ከብንያምም ፡
፪፤ ወገን ፡ ነኝና ። እግዚአብሔር ፡ አስቀድሞ ፡ ያወ
ቃቸውን ፡ ሕዝብ ፡ አልጣላቸውም ። መጽሐፍ ፡
ስለ ፡ ኤልያስ ፡ በተጻፈው ፡ የሚለውን ÷ በእግዚ
አብሔር ፡ ፊት ፡ እስራኤልን ፡ እንዴት ፡ እንደሚ
፫፤ ከስ ÷ አታውቁምን ? ጌታ ፡ ሆይ ÷ ነቢያትህን ፡
ገደሉ ፡ መሠዊያዎችህንም ፡ አፈረሱ ፡ እኔም ፡
፬፤ ብቻዬን ፡ ቀረሁ ፡ ነፍሴንም ፡ ይሹአታል ። ነገር ፡
ግን ፡ አምላካዊ ፡ መልስ ፡ ምን ፡ አለው ? ለበ
ዓል ፡ ያልሰገዱትን ፡ ሰባት ፡ ሺህ ፡ ሰዎች ፡ ለእኔ ፡
፭፤ አስቀርቼአለሁ ። እንደዚሁም ፡ በአሁን ፡ ዘመን ፡
ደግሞ ፡ በጸጋ ፡ የተመረጡ ፡ ቅሬታዎች ፡ አሉ ።
፮፤ በጸጋ ፡ ከሆነ ፡ ግን ፡ ከሥራ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶአል ፤
ጸጋ ፡ ያለዚያ ፡ ጸጋ ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶአል ።
፯፤ እንግዲህ ፡ ምንድር ፡ ነው ? እስራኤል ፡ የሚ
ፈልጉትን ፡ አላገኙትም ፤ የተመረጡት ፡ ግን ፡
፰፤ አገኙት ፤ ሌሎቹም ፡ ደነዘዙ ፤ እንዲሁም ፡—
ዓይኖቻቸው ፡ እንዳያዩ ፡ ጆሮቻቸውም ፡ እንዳይ
ሰሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ የእንቅልፍ ፡ መንፈስን ፡
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ሰጣቸው ፡ ተብሎ ፡ ተጽፎ
፱፤ አል ። ዳዊትም ፡—
ማዕዳቸው ፡ ወጥመድና ፡ አሽክላ ፡ ማሰና
፲፤ ከያም ፡ ፍዳም ፡ ይሁንባቸው ፤ ዓይኖቻ
ቸው ፡ እንዳያዩ ፡ ይጨልሙ ÷ ጀርባቸው
ንም ፡ ዘወትር ፡ አጕብጥ ፡
ብሎአል ።
፲፩፤ እንግዲህ ፡— የተሰናከሉ ፡ እስኪወድቁ ፡
ድረስ ፡ ነውን ? እላለሁ ። አይደለም ፤ ነገር ፡
ግን ፡ እነርሱን ፡ ያስቀናቸው ፡ ዘንድ ፡ በእነርሱ ፡
፲፪፤ በደል ፡ መዳን ፡ ለአሕዛብ ፡ ሆነ ። ዳሩ ፡ ግን ፡
በደላቸው ፡ ለዓለም ፡ ባለ ፡ ጠግነት ÷ መሸነፋቸ
ውም ፡ ለአሕዛብ ፡ ባለ ፡ ጠግነት ፡ ከሆነ ÷ ይልቁ
ንስ ፡ መሙላታቸው ፡ እንዴት ፡ ይሆን ?
፲፫፡፲፬፤ ለእናንተም ፡ ለአሕዛብ ፡ እናገራለሁ ። እኔ ፡
የአሕዛብ ፡ ሐዋርያ ፡ በሆንሁ ፡ መጠን ፡ ሥጋዬ ፡
የሆኑትን ፡ አስቀንቼ ፡ ምናልባት ፡ ከእነርሱ ፡ አን
ዳንዱን ፡ አድን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አገልግሎቴን ፡ አከ
ብራለሁ ። የእነርሱ ፡ መጣል ፡ ለዓለም ፡ መታ ፲፭፤
ረቅ ፡ ከሆነ ፡ ከሙታን ፡ ከሚመጣ ፡ ሕይወት ፡
በቀር ፡ መመለሳቸው ፡ ምን ፡ ይሆን ? በኵራ ፲፮፤
ቱም ፡ ቅዱስ ፡ ከሆነ ፡ ቡሆው ፡ ደግሞ ፡ ቅዱስ ፡
ነው ፤ ሥሩም ፡ ቅዱስ ፡ ከሆነ ፡ ቅርንጫፎቹ ፡
ደግሞ ፡ ቅዱሳን ፡ ናቸው ።
ነገር ፡ ግን ፡ ከቅርንጫፎች ፡ አንዳንዱ ፡ ቢሰ ፲፯፤
በሩ ፡ አንተም ፡ የበረሀ ፡ ወይራ ፡ የሆንህ ፡ በመ
ካከላቸው ፡ ገብተህ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ የወይራ ፡
ዘይት ፡ ከሚወጣው ፡ ሥር ፡ ተካፋይ ፡ ከሆንህ ÷
በቅርንጫፎች ፡ ላይ ፡ አትመካ ፤ ብትመካባቸው ፡ ፲፰፤
ግን ፡ ሥሩ ፡ አንተን ፡ ይሸከምሃል ፡ እንጂ ፡
ሥሩን ፡ የምትሸከም ፡ አንተ ፡ አይደለህም ።
እንግዲህ ፡— እኔ ፡ እንድገባ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ተሰ ፲፱፤
በሩ ፡ ትል ፡ ይሆናል ። መልካም ፤ እነርሱ ፡ ከአ ፳፤
ለማመን ፡ የተነሣ ፡ ተሰበሩ ፡ አንተም ፡ ከእም
ነት ፡ የተነሣ ፡ ቆመሃል ። ፍራ ፡ እንጂ ፡ የትዕቢ
ትን ፡ ነገር ፡ አታስብ ። እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ፳፩፤
ተፈጠሩት ፡ ለነበሩት ፡ ቅርንጫፎች ፡ የራራላ
ቸው ፡ ካልሆነ ፡ ለአንተ ፡ ደግሞ ፡ አይራራልህ
ምና ። እንግዲህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቸርነትና ፡ ፳፪፤
ጭከና ፡ ተመልከት ፤ ጭከናው ፡ በወደቁት ፡ ላይ ፡
ነው ÷ በቸርነቱ ፡ ግን ፡ ጸንተህ ፡ ብትኖር ፡ የእግ
ዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ ነው ፤ ያለ
ዚያ ፡ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ትቈረጣለህ ። እነዚያም ፡ ፳፫፤
ደግሞ ፡ በአለማመናቸው ፡ ጸንተው ፡ ባይኖሩ ፡
በዛፉ ፡ ውስጥ ፡ ይገባሉ ፤ እግዚአብሔር ፡ መልሶ ፡
ሊያገባቸው ፡ ይችላልና ። አንተ ፡ በፍጥረቱ ፡ ፳፬፤
የበረሀ ፡ ከነበረ ፡ ወይራ ፡ ተቈርጠህ ፡ እንደ ፡ ፍጥ
ረትህ ፡ ሳትሆን ፡ በመልካም ፡ ወይራ ፡ ከገባህ ÷
ይልቁንስ ፡ እነዚያ ፡ በፍጥረታቸው ፡ ያሉት ፡
ቅርንጫፎች ፡ በራሳቸው ፡ ወይራ ፡ እንዴት ፡
አይገቡም ?
ወንድሞች ፡ ሆይ ÷ ልባሞች ፡ የሆናችሁ ፡ ፳፭፤
እንዳይመስላችሁ ፡ ይህን ፡ ምሥጢር ፡ ታውቁ ፡
ዘንድ ፡ እወዳለሁ ፤ የአሕዛብ ፡ ሙላት ፡ እስኪ
ገባ ፡ ድረስ ፡ ድንዛዜ ፡ በእስራኤል ፡ በአንዳንድ ፡
በኩል ፡ ሆነባቸው ፤ እንደዚሁም ፡ እስራኤል ፡ ፳፮፤
ሁሉ ፡ ይድናል ፤ እንዲህ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡
ተጻፈ ፡—
መድኃኒት ፡ ከጽዮን ፡ ይወጣል ፡ ከያዕቆ
ብም ፡ ኃጢአተኛነትን ፡ ያስወግዳል ።
ኃጢአታቸውንም ፡ ስወስድላቸው ፡ ከእነ ፳፯፤
ርሱ ፡ ጋር ፡ የምገባው ፡ ኪዳን ፡ ይህ ፡ ነው ።
በወንጌልስ ፡ በኩል ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ጠላቶች ፡ ፳፰፤
ናቸው ÷ በምርጫ ፡ በኩል ፡ ግን ፡ ስለ ፡ አባቶች ፡
ተወዳጆች ፡ ናቸው ፤ እግዚአብሔር ፡ በጸጋው ፡ ፳፱፤

፲። ፳ ፡ ፳፩ ፤ ኢሳ· ፷፭ ÷ ፩ ፡ ፪ ።
፲፩። ፩ ፤ ኤር· ፴፩ ÷ ፴፯ ፤ ፊልጵ· ፫ ÷ ፭ ። ፫ ፡ ፬ ፤ ፩ ነገሥ· ፲፱ ÷ ፲ ፡ ፲፰ ። ፭ ፤ ምዕ· ፱ ÷ ፳፯ ። ፮ ፤ ምዕ· ፬ ÷ ፬ ። ፯ ፤ ምዕ· ፱ ÷ ፴፩ ። ፰ ፤ ኢሳ· ፳፱ ÷ ፲ ፤ ፮ ÷ ፲ ፤ ማቴ· ፲፫ ÷ ፲፬ ። ፱ ፡ ፲ ፤ መዝ· ፷፰ ÷ ፳፪ ፡ ፳፫ ። ፲፩ ፤ የሐዋ· ፳፰ ÷ ፳፰ ። ፲፮ ፤ ዘኍል· ፲፭ ÷ ፲፰ ። ፲፯ ፤ ኤር· ፲፩ ÷ ፲፮ ። ፳፪ ፤ ዮሐ· ፲፭ ÷ ፪ ። ፳፭ ፤ ፪ ቆሮ· ፫ ÷ ፲፬ ፤ ዮሐ· ፲ ÷ ፲፮ ። ፳፮ ፤ መዝ· ፲፬ ÷ ፯ ፤ ኢሳ· ፶፱ ÷ ፳ ። ፳፯ ፤ ኢሳ· ፳፯ ÷ ፱ ፤ ፳፯ ÷ ፱ ። ፳፰ ፤ ዘዳግ· ፯ ÷ ፰ ።

፴፤ ስጦታና ፡ በመጥራቱ ፡ አይጸጸትምና ። እናን
ተም ፡ ቀድሞ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዳልታዘዛ
ችሁ ÷ አሁን ፡ ግን ፡ ከአለመታዘዛቸው ፡ የተነሣ ፡
፴፩፤ ምሕረት ፡ እንዳገኛችሁ ÷ እንዲሁ ፡ በተማራች
ሁበት ፡ ምሕረት ፡ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ ምሕረትን ፡
ያገኙ ፡ ዘንድ ፡ እነዚህ ፡ ደግሞ ፡ አሁን ፡ አልታዘ
፴፪፤ ዙም ። እግዚአብሔር ፡ ሁሉን ፡ ይምር ፡ ዘንድ ፡
ሁሉን ፡ በአለመታዘዝ ፡ ዘግቶታልና ።
፴፫፤ የእግዚአብሔር ፡ ባለ ፡ ጠግነትና ፡ ጥበብ ፡
እውቀቱም ፡ እንዴት ፡ ጥልቅ ፡ ነው ፤ ፍርዱ ፡
እንዴት ፡ የማይመረመር ፡ ነው ÷ ለመንገዱም ፡
ፍለጋ ፡ የለውም ።
፴፬፤ የጌታን ፡ ልብ ፡ ያወቀው ፡ ማን ፡ ነው ?
፴፭፤ ወይስ ፡ አማካሪው ፡ ማን ፡ ነበር ወይስ ፡
ብድራቱን ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፡ ለእርሱ ፡
አስቀድሞ ፡ የሰጠው ፡ ማን ፡ ነው ?
፴፮፤ ሁሉ ፡ ከእርሱና ፡ በእርሱ ፡ ለእርሱም ፡ ነውና ፤
ለእርሱ ፡ ለዘላለም ፡ ክብር ፡ ይሁን ፤ አሜን ።

ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

፩፤ እንግዲህ ÷ ወንድሞች ፡ ሆይ ÷ ሰውነታችሁን ፡
እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝና ፡ ሕያው ፡
ቅዱስም ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጋችሁ ፡ ታቀርቡ ፡
ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ርኅራኄ ፡ እለምናች
ኋለሁ ÷ እርሱም ፡ ለአእምሮ ፡ የሚመች ፡ አገል
፪፤ ግሎታችሁ ፡ ነው ። የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡
እርሱም ፡ በጎና ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ፍጹምም ፡
የሆነው ፡ ነገር ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፈትናችሁ ፡
ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ በልባችሁ ፡ መታደስ ፡ ተለወጡ ፡
እንጂ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ አትምሰሉ ።
፫፤ እግዚአብሔር ፡ ለእያንዳንዱ ፡ የእምነትን ፡
መጠን ፡ እንዳካፈለው ÷ እንደ ፡ ባለ ፡ አእምሮ ፡
እንዲያስብ ፡ እንጂ ፡ ማሰብ ፡ ከሚገባው ፡ አልፎ ፡
በትዕቢት ፡ እንዳያስብ ፡ በመካከላችሁ ፡ ላለው ፡
ለእያንዳንዱ ፡ በተሰጠኝ ፡ ጸጋ ፡ እናገራለሁ ።
፬፤ በአንድ ፡ አካል ፡ ብዙ ፡ ብልቶች ፡ እንዳሉን ÷
የብልቶቹም ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ አንድ ፡ እንዳይደለ ÷
፭፤ እንዲሁ ፡ ብዙዎች ፡ ስንሆን ፡ በክርስቶስ ፡ አንድ ፡
አካል ፡ ነን ÷ እርስ ፡ በርሳችንም ፡ እያንዳንዳችን ፡
፮፤ የሌላው ፡ ብልቶች ፡ ነን ። እንደ ፡ ተሰጠንም ፡
ጸጋ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስጦታ ፡ አለን ፤ ትንቢት ፡ ቢሆን ፡
እንደ ፡ እምነታችን ፡ መጠን ፡ ትንቢት ፡ እንና
፯፤ ገር ፤ አገልግሎት ፡ ቢሆን ፡ በአገልግሎታችን ፡
እንትጋ ፤ የሚያስተምርም ፡ ቢሆን ፡ በማስተ
፰፤ ማሩ ፡ ይትጋ ፤ የሚመክርም ፡ ቢሆን ፡ በመም
ከሩ ፡ ይትጋ ፤ የሚሰጥ ፡ በልግስና ፡ ይስጥ ፤
የሚገዛ ፡ በትጋት ፡ ይግዛ ፤ የሚምር ፡ በደስታ ፡
ይማር ።
ፍቅራችሁ ፡ ያለ ፡ ግብዝነት ፡ ይሁን ። ክፉ ፱፤
ውን ፡ ነገር ፡ ተጸየፉት ፤ ከበጎ ፡ ነገር ፡ ጋር ፡ ተባ
በሩ ፤ በወንድማማች ፡ መዋደድ ፡ እርስ ፡ በር ፲፤
ሳችሁ ፡ ተዋደዱ ፤ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ተከባበሩ ፤
ለሥራ ፡ ከመትጋት ፡ አትለግሙ ፤ በመንፈስ ፡ ፲፩፤
የምትቃጠሉ ፡ ሁኑ ፤ ለጌታ ፡ ተገዙ ፤ በተስፋ ፡ ፲፪፤
ደስ ፡ ይበላችሁ ፤ በመከራ ፡ ታገሡ ፤ በጸሎት ፡
ጽኑ ፤ ቅዱሳንን ፡ በሚያስፈልጋቸው ፡ እርዱ ፤ ፲፫፤
እንግዶችን ፡ ለመቀበል ፡ ትጉ ።
የሚያሳድዱአችሁን ፡ መርቁ ÷ መርቁ ፡ እንጂ ፡ ፲፬፤
አትርገሙ ። ደስ ፡ ከሚላቸው ፡ ጋር ፡ ደስ ፡ ይበ ፲፭፤
ላችሁ ÷ ከሚያለቅሱም ፡ ጋር ፡ አልቅሱ ። እርስ ፡ ፲፮፤
በርሳችሁ ፡ በአንድ ፡ አሳብ ፡ ተስማሙ ፤ የትዕ
ቢትን ፡ ነገር ፡ አታስቡ ÷ ነገር ፡ ግን ፡ የትሕት
ናን ፡ ነገር ፡ ለመሥራት ፡ ትጉ ። ልባሞች ፡ የሆ
ናችሁ ፡ አይምሰላችሁ ። ለማንም ፡ ስለ ፡ ክፉ ፡ ፲፯፤
ፈንታ ፡ ክፉን ፡ አትመልሱ ፤ በሰው ፡ ሁሉ ፡
ፊት ፡ መልካም ፡ የሆነውን ፡ አስቡ ። ቢቻላች ፲፰፤
ሁስ ፡ በእናንተ ፡ በኩል ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡
በሰላም ፡ ኑሩ ። ተወዳጆች ፡ ሆይ ÷ ራሳችሁ ፡ ፲፱፤
አትበቀሉ ÷ ለቍጣው ፡ ፈንታ ፡ ስጡ ፡ እንጂ ፤
በቀል ፡ የእኔ ፡ ነው ÷ እኔ ፡ ብድራቱን ፡ እመልሳ
ለሁ ፡ ይላል ፡ ጌታ ፡ ተብሎ ፡ ተጽፎአልና ። ጠላ ፳፤
ትህ ፡ ግን ፡ ቢራብ ፡ አብላው ፤ ቢጠማ ፡ አጠ
ጣው ፤ ይህን ፡ በማድረግህ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ የእ
ሳት ፡ ፍም ፡ ትከምራለህና ። ክፉውን ፡ በመል ፳፩፤
ካም ፡ አሸንፍ ፡ እንጂ ፡ በክፉ ፡ አትሸነፍ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ በበላይ ፡ ላሉት ፡ ባለ ፡ ሥልጣኖች ፡ ፩፤
ይገዛ ። ከእግዚአብሔር ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፡
ሥልጣን ፡ የለምና ፤ ያሉትም ፡ ባለ ፡ ሥልጣ
ኖች ፡ በእግዚአብሔር ፡ የተሾሙ ፡ ናቸው ።
ስለዚህ ፡ ባለ ፡ ሥልጣንን ፡ የሚቃወም ፡ የእግ ፪፤
ዚአብሔርን ፡ ሥርዓት ፡ ይቃወማል ፤ የሚቃ
ወሙትም ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ፍርድን ፡ ይቀበ
ላሉ ። ገዦዎች ፡ ለክፉ ፡ አድራጊዎች ፡ እንጂ ፡ ፫፤
መልካም ፡ ለሚያደርጉ ፡ የሚያስፈሩ ፡ አይደሉ
ምና ። ባለ ፡ ሥልጣንን ፡ እንዳትፈራ ፡ ትወዳለ
ህን ? መልካሙን ፡ አድርግ ፡ ከእርሱም ፡ ምስ
ጋና ፡ ይሆንልሃል ፤ ለመልካም ፡ ነገር ፡ ለአንተ ፡ ፬፤
የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ ነውና ። በከንቱ ፡

፲፩። ፴፪ ፤ ምዕ· ፫ ÷ ፱ ፤ ገላ· ፫ ÷ ፳፪ ። ፴፫ ፤ ኢዮብ ፲፩ ÷ ፯—፱ ፤ ቈላ· ፪ ÷ ፫ ። ፴፬ ፤ ኢሳ· ፵ ÷ ፲፫ ። ፴፭ ፤ ኢዮብ ፴፭ ÷ ፯ ፤ ፵፩ ÷ ፫ ። ፴፮ ፤ ፩ ዜና ፳፱ ÷ ፲፩—፲፫ ።
፲፪። ፩ ፤ ምዕ· ፮ ÷ ፲፫ ፤ ፩ ጴጥ· ፪ ÷ ፭ ። ፪ ፤ ኤፌ· ፬ ÷ ፳፫ ፤ ፭ ÷ ፲ ። ፫ ፤ ኤፌ· ፬ ÷ ፯ ። ፬ ፡ ፭ ፤ ፩ ቆሮ· ፲፪ ÷ ፲፪ ፡ ፳ ፡ ፳፯ ፤ ኤፌ· ፬ ÷ ፳፭ ። ፮—፰ ፤ ፩ ቆሮ· ፲፪ ÷ ፬ ፡ ፳፰ ፤ ኤፌ· ፬ ÷ ፲፩ ፤ ፩ ጴጥ· ፬ ÷ ፲ ፡ ፲፩ ፤ ፪ ቆሮ· ፱ ÷ ፯ ። ፱ ፤ ፩ ጢሞ· ፩ ÷ ፭ ፤ ፩ ተሰ· ፭ ÷ ፳፩ ፡ ፳፪ ። ፲ ፤ ፊልጵ· ፪ ÷ ፫ ። ፲፩ ፤ ቈላ· ፫ ÷ ፳፫ ፤ ራእ· ፫ ÷ ፲፭ ። ፲፪ ፤ ፩ ተሰ· ፭ ÷ ፲፯ ፡ ፲፯ ፤ ፊልጵ· ፬ ÷ ፮ ። ፲፫ ፤ ማቴ· ፳፭ ÷ ፴፭ ፤ ዕብ· ፲፫ ÷ ፪ ። ፲፬ ፤ ማቴ· ፭ ÷ ፵፬ ። ፲፭ ፤ ፩ ቆሮ· ፲፪ ÷ ፳፮ ። ፲፮ ፤ ፊልጵ· ፪ ÷ ፪ ፤ ማቴ· ፳ ÷ ፳፮ ፤ ምሳ· ፫ ÷ ፯ ። ፲፯ ፤ ማቴ· ፭ ÷ ፴፱ ፤ ምሳ· ፳ ÷ ፳፪ ፤ ፩ ተሰ· ፭ ÷ ፲፭ ፤ ፪ ቆሮ· ፰ ÷ ፳፩ ። ፲፰ ፤ ማር· ፱ ÷ ፶ ። ፲፱ ፤ ዘሌዋ· ፲፱ ÷ ፲፰ ፤ ዘዳግ· ፴፪ ÷ ፴፭ ። ፳ ፤ ምሳ· ፳፭ ÷ ፳፩ ፡ ፳፪ ።
፲፫። ፩ ፤ ፩ ጴጥ· ፪ ÷ ፲፫ ፤ ዮሐ· ፲፱ ÷ ፲፩ ፤ ምሳ· ፰ ÷ ፲፭ ። ፫ ፤ ፩ ጴጥ· ፪ ÷ ፲፬ ።

ግን ፡ ሰይፍ ፡ አይታጠቅምና ፡ ክፉ ፡ ብታደርግ ፡ ፍራ ። ቀጣውን ፡ ለማሰየት ፡ ክፉ ፡ አድራጊ ውን ፡ የሚበቀል ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ ነውና ። ስለዚህ ፡ ስለ ፡ ቀጣው ፡ ብቻ ፡ አይደ ለም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ሕሊና ፡ ደግሞ ፡ መገ ዛት ፡ ግድ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ደግሞ ፡ ትገብራላ ችሁና ። በዚህ ፡ ነገር ፡ የሚተጉ ፡ የእግዚአብ ሔር ፡ አገልጋዮች ፡ ናቸውና ። ለሁሉ ፡ የሚገ ባውን ፡ አስረክቡ ። ግብር ፡ ለሚገባው ፡ ግብ ርን ÷ ቀረጥ ፡ ለሚገባው ፡ ቀረጥን ÷ መፈራት ፡ ለሚገባው ፡ መፈራትን ÷ ክብር ፡ ለሚገባው ፡ ክብርን ÷ ስጡ ።

እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ከመዋደድ ፡ በቀር ፡ ለማ ንም ፡ ዕዳ ፡ አይኑርባችሁ ÷ ሌላውን ፡ የሚወድ ፡ ሕግን ፡ ፈጽሞታልና ። አታመንዝር ÷ አትግ ደል ÷ አትስረቅ ÷ በውሸት ፡ አትመስክር ÷ አት መኝ ፡ የሚለው ፡ ከሌላይቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ በዚህ ፡— በልንጀራህን ፡ እንደ ፡ ነፍስህ ፡ ውደድ ፡ በሚለው ፡ ቃል ፡ ተጠቅልሎአል ። ፍቅር ፡ ለባልንጀራው ፡ ክፉ ፡ አያደርግም ። ስለ ዚህ ፡ ፍቅር ፡ የሕግ ፡ ፍጻሜ ፡ ነው ።

ከእንቅልፍ ፡ የምትነሡበት ፡ ሰዓት ፡ አሁን ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ዘመኑን ፡ እወቁ ። ከመንገበት ፡ ጊዜ ፡ ይልቅ ፡ መዳናችን ፡ ዛሬ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ቀር በአልና ። ሌሊቱ ፡ አልፎአል ÷ ቀኑም ፡ ቀርበ አል ። እንግዲህ ፡ የጨለማውን ፡ ሥራ ፡ አው ጥተን ፡ የብርሃንን ፡ ጋሻ ፡ ጦር ፡ እንልበስ ። በቀን ፡ እንደምንሆን ፡ በአገባብ ፡ እንመላለስ ፤ በዘፈንና ፡ በስክር ፡ አይሁን ÷ በዝሙትና ፡ በመ ዳራት ፡ አይሁን ÷ በክርክርና ፡ በቅናት ፡ አይሁን ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ጌታን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ልበ ሱት ። ምኞቱንም ፡ እንዲፈጽም ፡ ለሥጋ ፡ አታ ስቡ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

በእምነት ፡ የደከመውንም ፡ ተቀበሉት ÷ በአ ሳቡም ፡ ላይ ፡ አትፍረዱ ። ሁሉን ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተፈቀደለት ፡ የሚያምን ፡ አለ ÷ ደከማው ፡ ግን ፡ አትክልት ፡ ይበላል ። የሚበላ ፡ የማይበላውን ፡ አይናቀው ፡ የማይበላውም ፡ በሚበላው ፡ አይፍረድ ÷ እግዚአብሔር ፡ ተቀብ ሎታልና ። አንተ ፡ በሌላው ፡ ሎሌ ፡ የምትፈ ርድ ፡ ግን ፡ ነህ ? እርሱ ፡ ቢቆም ፡ ወይም ፡ ቢወ ድቅ ፡ ለገዛ ፡ ጌታው ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ እግዚ አብሔር ፡ ሊያቆመው ፡ ይችላልና ፡ ይቆማል ።

ይህ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከሌላ ፡ ቀን ፡ እንዲ ሻል ፡ ያስባል ÷ ያ ፡ ግን ፡ ቀን ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያስባል ። እያንዳንዱ ፡ በገዛ ፡ አእ ምሮው ፡ አጥብቆ ፡ ይረዳ ። ቀንን ፡ የሚያከብር ፡ ለጌታ ፡ ብሎ ፡ ያከብራል ። የሚበላም ፡ እግዚአ ብሔርን ፡ ያመሰግናልና ፡ ለጌታ ፡ ብሎ ፡ ይበላል ፤ የማይበላም ፡ ለጌታ ፡ ብሎ ፡ አይበላም ፡ እግዚ አብሔርንም ፡ ያመሰግናል ። ከእኛ ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ ለራሱ ፡ የሚኖር ፡ የለምና ÷ ለራሱም ፡ የሚሞት ፡ የለም ። በሕይወት ፡ ሆነን ፡ ብንኖር ፡ ለጌታ ፡ እንኖራለንና ÷ ብንሞትም ፡ ለጌታ ፡ እን ሞታለን ። እንግዲህ ፡ በሕይወት ፡ ሆነን ፡ ብን ኖር ፡ ወይም ፡ ብንሞት ፡ የጌታ ፡ ነን ። ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ሙታንንም ፡ ሕያዋንንም ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ፡ ክርስቶስ ፡ ሞቶአልና ፡ ሕያውም ፡ ሆኖአልና ።

እንተም ፡ በወንድምህ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትፈ ርዳለህ ? ወይስ ፡ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ወንድምህን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትንቃለህ ? ሁላችን ፡ በክርስቶስ ፡ ፍርድ ፡ ወንበር ፡ ፊት ፡ እንቆማለንና ።

እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝ ÷ ይላል ፡ ጌታ ÷ ጕልበት ፡ ሁሉ ፡ ለእኔ ፡ ይንበረከክል ፡ መላስም ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግናል ፡

ተብሎ ፡ ተጽፎአልና ። እንግዲያስ ፡ እያንዳን ዳችን ፡ ስለ ፡ ራሳችን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መልስ ፡ እንሰጣለን ።

እንግዲህ ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ አንፈራረድ ። ይልቁን ፡ ግን ፡ ለወንድም ፡ እንቅ ፋትን ፡ ወይም ፡ ማሰናከያን ፡ ማንም ፡ እንዳያኖ ርበት ፡ ይህን ፡ ቍረጡ ። በራሱ ፡ ርኵስ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ሌለ ፡ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ሆኜ ፡ አውቄአለሁ ፡ ተረድቼአለሁም ። ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ርኵስ ፡ እንዲሆን ፡ ለሚቈጥር ፡ ለእርሱ ፡ ርኵስ ፡ ነው ። ወንድምህንም ፡ በመብል ፡ ምክ ንያት ፡ የምታሳዝን ፡ ከሆንህ ፡ እንግዲህ ፡ በፍ ቅር ፡ አልተመላለስህም ። ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ የሞተለትን ፡ እርሱን ፡ በመብልህ ፡ አታጥፋው ። እንግዲህ ፡ ለእናንተ ፡ ያለው ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ አይሰደብ ። የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ጽድ ቅና ፡ ሰላም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ የሆነ ፡ ደስታ ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ መብልና ፡ መጠጥ ፡ አይደለች ምና ። እንደዚህ ፡ አድርጎ ፡ ለክርስቶስ ፡ የሚ ገዛ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ያሰኛልና ÷ በሰውም ፡ ዘንድ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ። እንግዲያስ ፡ ሰላም ፡ የሚቆምበትን ፡ እርስ ፡ በርሳችንም ፡ የምንታነ ጽበትን ፡ እንከተል ። በመብል ፡ ምክንያት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ አታፍርስ ። ሁሉ ፡ ንጹሕ ፡ ነው ÷ በመጠራጠር ፡ የተበላ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ለዚያ ፡ ሰው ፡ ክፉ ፡ ነው ። ሥጋን ፡ አለመ ብላት ፡ ወይንንም ፡ አለመጠጣት ፡ ወንድምህም ፡ የሚሰናከልበትን ፡ አለማድረግ ፡ መልካም ፡ ነው ። ለአንተ ፡ ያለህ ፡ እምነት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለራስህ ፡ ይሁንልህ ። ፈተኖ ፡ መልካም ፡ እንዲ ሆን ፡ በሚቈጥረው ፡ ነገር ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ የማይ ፈርድ ፡ ብፁዕ ፡ ነው ። የሚጠራጠረው ፡ ግን ፡ ቢበላ ፡ በእምነት ፡ ስላልሆነ ፡ ተኰንኖአል ። በእ ምነትም ፡ ያልሆነ ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፭ ።

እኛም ፡ ኃይለኞች ፡ የሆንን ፡ የደካሞችን ፡ ድካም ፡ እንድንሸከም ፡ ራሳችንንም ፡ ደስ ፡ እን ዳናሰኝ ፡ ይገበናል ። እያንዳንዳችን ፡ እንድናን ጸው ፡ እርሱን ፡ ለመጥቀም ፡ በልንጀራችንን ፡ ደስ ፡ እናሰኝ ። ክርስቶስ ፡ ራሱን ፡ ደስ ፡ አላሰኘ ምና ። ነገር ፡ ግን ፡— አንተን ፡ የነቀፋበት ፡ ነቀፋ ፡ ወደቀብን ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ሆነ በት ። በመጽናትና ፡ መጻሕፍት ፡ በሚሰጡት ፡ መጽናናት ፡ ተስፋ ፡ ይሆንልን ፡ ዘንድ ፡ አስቀ ድሞ ፡ የተጻፈው ፡ ሁሉ ፡ ለትምህርታችን ፡ ተጽ ፍአልና ። በአንድ ፡ ልብ ፡ ሆናችሁ ፡ በአንድ ፡ አፍ ፡ እግዚአብሔርን ÷ እርሱም ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አባት ÷ ታከብሩ ፡ ዘንድ ÷ የትዕግሥትና ፡ የመጽናናት ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ፈቃድ ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ በአንድ ፡ አሳብ ፡ መሆንን ፡ ይስጣችሁ ።

ስለዚህ ፡ ክርስቶስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ እንደ ፡ ተቀበላችሁ ፡ እንዲሁ ፡ እርስ ፡ በርሳ ችሁ ፡ ተቀበሉት ። ለአበቶች ፡ የተሰጠውን ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ፡ ደግሞም ፡— ስለ ዚህ ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ አመሰግንሃለሁ ፡ ለስ ምህም ፡ እዘምራለሁ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ÷ አሕዛብ ፡ ስለ ፡ ምሕረቱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያክ ብሩ ፡ ዘንድ ÷ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እውነት ፡ የመገረዝ ፡ አገልጋይ ፡ ሆነ ፡ እላለሁ ።

ደግሞም ፡— አሕዛብ ፡ ሆይ ÷ ከሕዝቡ ፡ ጋር ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፡ ይላል ። ደግሞም ፡—

እናንተ ፡ አሕዛብ ፡ ሁላችሁ ÷ ጌታን ፡ አመ ስግኑ ፡ ሕዝቦቹም ፡ ሁሉ ፡ ይወድሱት ፡

ይላል ። ደግሞም ፡ ኢሳይያስ ፡—

የእሴይ ፡ ሥር ፡ አሕዛብንም ፡ ሊገዛ ፡ የሚነ ሣው ፡ ይሆናል ፤ በእርሱ ፡ አሕዛብ ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋሉ ፡

ይላል ። የተስፋ ፡ አምላክም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኃይል ፡ በተስፋ ፡ እንድትበዙ ፡ በማመናችሁ ፡ ደስታንና ፡ ሰላምን ፡ ሁሉ ፡ ይሙላባችሁ ።

እኔም ፡ ራሴ ፡ ደግሞ ÷ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ÷ በበ ጎነት ፡ ራሳችሁ ፡ እንደ ፡ ተሞላችሁ ፡ እውቀ ትም ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ሞላባችሁ ÷ እርስ ፡ በርሳ ችሁም ፡ ደግሞ ፡ ልትገሠጹ ፡ እንዲቻላችሁ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ተረድቼአለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ አሕ ዛብ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተቀድሰው ፡ የተወ ደደ ፡ መሥዋዕት ፡ ሊሆኑ ÷ ለእግዚአብሔር ፡ ወንጌል ፡ እንደ ፡ ካህን ፡ እያገለገልሁ ÷ ለአሕ ዛብ ፡ የክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ አገልጋይ ፡ እሆን ፡ ዘንድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በተሰጠኝ ፡ ጸጋ ፡ ምክ ንያት ፡ ተመልሼ ፡ ላሳስባቸው ፡ ብዬ ፡ በአንዳ ንድ ፡ በታ ፡ በድፍረት ፡ ጻፍሁላችሁ ። እንግ ዲህ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በሚሆን ፡ ነገር ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ትምክህት ፡ አለኝ ። አሕዛብ ፡ እንዲታዘዙ ፡ ክርስቶስ ፡ በቃልና ፡ በሥራ ÷ በምልክትና ፡ በድንቅ ፡ ነገር ፡ ኃይል ÷ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ኃይል ፡ በእኔ ፡ አድርጎ ፡ ከሠራው ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ልናገር ፡ አልደፍርም ፤ ስለዚህ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ጀምሬ ፡ እስከ ፡ እልዋ ሪቆን ፡ ድረስ ፡ እየዘርዉ ፡ የክርስቶስን ፡ ወንጌል ፡ ፈጽሜ ፤ ሰብኬአለሁ ። እንዲሁም ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ እንዳልሠራ ፡ የክርስቶስ ፡ ስም ፡ በተጠራበት ፡ ስፍራ ፡ ሳይሆን ፡ ወንጌልን ፡ ለመስበክ ፡ ተጣጣርሁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡—

ስለ ፡ እርሱ ፡ ያልተወራላቸውን ፡ ያያሉ ÷ ያልሰሙም ፡ ያስተውላሉ ፡

ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እንዳልመጣ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተከለከልሁ ። አሁን ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ስፍራ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ስለ ፡ ሌለኝ ÷ ከብዙ ፡ ዓመትም ፡ ጀምሬ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ልመጣ ፡ ናፍ ቆት ፡ ስላለኝ ÷ ወደ ፡ እስጳንያ ፡ በጼድሁ ፡ ጊዜ ፡ ሳልፍ ፡ እናንተን ፡ እንዳይ ፡ ÷ አስቀድሜም ፡ ዋቂት ፡ ብጠግባችሁ ፡ ወደዚያ ፡ በጉዞዬ ፡ እንድ ትረዱኝ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ። አሁን ፡ ግን ፡ ቅዱሳንን ፡ ለማገልገል ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እሄ ዳለሁ ። መቄዶንያና ፡ አካይያ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ቅዱሳን ፡ መከከል ፡ ያሉትን ፡ ድሆች ፡ ይረዱ ፡ ዘንድ ፡ ወደዋልና ። ወደዋልና ፡ የእነርሱም ፡ ባለ ፡ ዕዳዎች ፡ ናቸው ፤ አሕዛብ ፡ በእነርሱ ፡ መን ፈሳዊ ፡ ነገርን ፡ ተካፋዮች ፡ ከሆኑ ፡ በሥጋዊ ፡ ነገር ፡ ደግሞ ፡ ያገለግሉአቸው ፡ ዘንድ ፡ ይገበቸ ዋልና ። እንግዲህ ፡ ይህን ፡ ፈጽሜ ፡ ይህን ፡ ፍሬ ፡ ከተምሁላቸው ፡ በኋላ ፡ በእናንተ ፡ በኩል ፡ አልፌ ፡ ወደ ፡ እስጳንያ ፡ እሄዳለሁ ፤ ወደ ፡ እና ንተም ፡ ስመጣ ፡ በክርስቶስ ፡ በረከት ፡ ሙላት ፡ እንድመጣ ፡ አውቃለሁ ።

ወንድሞች ፡ ሆይ ÷ ስለ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ እየጸለያችሁ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ትጋደሉ ፡ ዘንድ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስና ፡ በመ ንፈስ ፡ ፍቅር ፡ እለምናችኋለሁ ፤ በእግዚአብ ሔር ፡ ፈቃድ ፡ በደስታ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ መጥቼ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ እንዳርፍ ÷ በይሁዳ ፡ ካሉት ፡ የሚሰናከልበትን ፡ አለማድረግ ፡ መልካም ፡ ነው ።

ፀ፡ ለአንተ ፡ ያለህ ፡ እምነት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለራስህ ፡ ይሁንልህ ። ፈተኖ ፡ መልካም ፡ እንዲ ሆን ፡ በሚቈጥረው ፡ ነገር ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ የማይ ፈርድ ፡ ብፁዕ ፡ ነው ። የሚጠራጠረው ፡ ግን ፡ ቢበላ ፡ በእምነት ፡ ስላልሆነ ፡ ተኰንኖአል ። በእ ምነትም ፡ ያልሆነ ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፭ ።

እኛም ፡ ኃይለኞች ፡ የሆንን ፡ የደካሞችን ፡ ድካም ፡ እንድንሸከም ፡ ራሳችንንም ፡ ደስ ፡ እን ዳናሰኝ ፡ ይገበናል ። እያንዳንዳችን ፡ እንድናን ጸው ፡ እርሱን ፡ ለመጥቀም ፡ በልንጀራችንን ፡ ደስ ፡ እናሰኝ ። ክርስቶስ ፡ ራሱን ፡ ደስ ፡ አላሰኘ ምና ። ነገር ፡ ግን ፡— አንተን ፡ የነቀፋበት ፡ ነቀፋ ፡ ወደቀብን ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ሆነ በት ። በመጽናትና ፡ መጻሕፍት ፡ በሚሰጡት ፡ መጽናናት ፡ ተስፋ ፡ ይሆንልን ፡ ዘንድ ፡ አስቀ ድሞ ፡ የተጻፈው ፡ ሁሉ ፡ ለትምህርታችን ፡ ተጽ ፍአልና ። በአንድ ፡ ልብ ፡ ሆናችሁ ፡ በአንድ ፡ አፍ ፡ እግዚአብሔርን ÷ እርሱም ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አባት ÷ ታከብሩ ፡ ዘንድ ÷ የትዕግሥትና ፡ የመጽናናት ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ፈቃድ ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ በአንድ ፡ አሳብ ፡ መሆንን ፡ ይስጣችሁ ።

ስለዚህ ፡ ክርስቶስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ እንደ ፡ ተቀበላችሁ ፡ እንዲሁ ፡ እርስ ፡ በርሳ ችሁ ፡ ተቀበሉት ። ለአበቶች ፡ የተሰጠውን ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ፡ ደግሞም ፡— ስለ ዚህ ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ አመሰግንሃለሁ ፡ ለስ ምህም ፡ እዘምራለሁ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ÷ አሕዛብ ፡ ስለ ፡ ምሕረቱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያክ ብሩ ፡ ዘንድ ÷ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እውነት ፡ የመገረዝ ፡ አገልጋይ ፡ ሆነ ፡ እላለሁ ።

ደግሞም ፡— አሕዛብ ፡ ሆይ ÷ ከሕዝቡ ፡ ጋር ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፡ ይላል ። ደግሞም ፡—

እናንተ ፡ አሕዛብ ፡ ሁላችሁ ÷ ጌታን ፡ አመ ስግኑ ፡ ሕዝቦቹም ፡ ሁሉ ፡ ይወድሱት ፡

ይላል ። ደግሞም ፡ ኢሳይያስ ፡—

የእሴይ ፡ ሥር ፡ አሕዛብንም ፡ ሊገዛ ፡ የሚነ ሣው ፡ ይሆናል ፤ በእርሱ ፡ አሕዛብ ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋሉ ፡

ይላል ። የተስፋ ፡ አምላክም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኃይል ፡ በተስፋ ፡ እንድትበዙ ፡ በማመናችሁ ፡ ደስታንና ፡ ሰላምን ፡ ሁሉ ፡ ይሙላባችሁ ።

እኔም ፡ ራሴ ፡ ደግሞ ÷ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ÷ በበ ጎነት ፡ ራሳችሁ ፡ እንደ ፡ ተሞላችሁ ፡ እውቀ ትም ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ሞላባችሁ ÷ እርስ ፡ በርሳ ችሁም ፡ ደግሞ ፡ ልትገሠጹ ፡ እንዲቻላችሁ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ተረድቼአለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ አሕ ዛብ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተቀድሰው ፡ የተወ ደደ ፡ መሥዋዕት ፡ ሊሆኑ ÷ ለእግዚአብሔር ፡ ወንጌል ፡ እንደ ፡ ካህን ፡ እያገለገልሁ ÷ ለአሕ ዛብ ፡ የክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ አገልጋይ ፡ እሆን ፡ ዘንድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በተሰጠኝ ፡ ጸጋ ፡ ምክ ንያት ፡ ተመልሼ ፡ ላሳስባቸው ፡ ብዬ ፡ በአንዳ ንድ ፡ በታ ፡ በድፍረት ፡ ጻፍሁላችሁ ። እንግ ዲህ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በሚሆን ፡ ነገር ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ትምክህት ፡ አለኝ ። አሕዛብ ፡ እንዲታዘዙ ፡ ክርስቶስ ፡ በቃልና ፡ በሥራ ÷ በምልክትና ፡ በድንቅ ፡ ነገር ፡ ኃይል ÷ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ኃይል ፡ በእኔ ፡ አድርጎ ፡ ከሠራው ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ልናገር ፡ አልደፍርም ፤ ስለዚህ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ጀምሬ ፡ እስከ ፡ እልዋ ሪቆን ፡ ድረስ ፡ እየዘርዉ ፡ የክርስቶስን ፡ ወንጌል ፡ ፈጽሜ ፤ ሰብኬአለሁ ። እንዲሁም ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ እንዳልሠራ ፡ የክርስቶስ ፡ ስም ፡ በተጠራበት ፡ ስፍራ ፡ ሳይሆን ፡ ወንጌልን ፡ ለመስበክ ፡ ተጣጣርሁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡—

ስለ ፡ እርሱ ፡ ያልተወራላቸውን ፡ ያያሉ ÷ ያልሰሙም ፡ ያስተውላሉ ፡

ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እንዳልመጣ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተከለከልሁ ። አሁን ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ስፍራ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ስለ ፡ ሌለኝ ÷ ከብዙ ፡ ዓመትም ፡ ጀምሬ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ልመጣ ፡ ናፍ ቆት ፡ ስላለኝ ÷ ወደ ፡ እስጳንያ ፡ በጼድሁ ፡ ጊዜ ፡ ሳልፍ ፡ እናንተን ፡ እንዳይ ፡ ÷ አስቀድሜም ፡ ዋቂት ፡ ብጠግባችሁ ፡ ወደዚያ ፡ በጉዞዬ ፡ እንድ ትረዱኝ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ። አሁን ፡ ግን ፡ ቅዱሳንን ፡ ለማገልገል ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እሄ ዳለሁ ። መቄዶንያና ፡ አካይያ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ቅዱሳን ፡ መከከል ፡ ያሉትን ፡ ድሆች ፡ ይረዱ ፡ ዘንድ ፡ ወደዋልና ። ወደዋልና ፡ የእነርሱም ፡ ባለ ፡ ዕዳዎች ፡ ናቸው ፤ አሕዛብ ፡ በእነርሱ ፡ መን ፈሳዊ ፡ ነገርን ፡ ተካፋዮች ፡ ከሆኑ ፡ በሥጋዊ ፡ ነገር ፡ ደግሞ ፡ ያገለግሉአቸው ፡ ዘንድ ፡ ይገበቸ ዋልና ። እንግዲህ ፡ ይህን ፡ ፈጽሜ ፡ ይህን ፡ ፍሬ ፡ ከተምሁላቸው ፡ በኋላ ፡ በእናንተ ፡ በኩል ፡ አልፌ ፡ ወደ ፡ እስጳንያ ፡ እሄዳለሁ ፤ ወደ ፡ እና ንተም ፡ ስመጣ ፡ በክርስቶስ ፡ በረከት ፡ ሙላት ፡ እንድመጣ ፡ አውቃለሁ ።

ወንድሞች ፡ ሆይ ÷ ስለ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ እየጸለያችሁ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ትጋደሉ ፡ ዘንድ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስና ፡ በመ ንፈስ ፡ ፍቅር ፡ እለምናችኋለሁ ፤ በእግዚአብ ሔር ፡ ፈቃድ ፡ በደስታ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ መጥቼ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ እንዳርፍ ÷ በይሁዳ ፡ ካሉት ፡

ፀ ። ማቴ. ፳፪ ÷ ፳፩ ። ፫ ። ማቴ. ፳፪ ÷ ፴፱ ። ፬ ። ዮሐ. ፲፫ ÷ ፴፱ ። ፱ ። ዘፀአ. ፳ ÷ ፲፫—፲፯ ፤ ዘሌዋ. ፲፱ ÷ ፲፰ ፤ ማቴ. ፲፱ ÷ ፲፰ ፤ ፲፱ ። ፲ ። ፩ ቆሮ. ፲፫ ÷ ፱—፲ ፤ ገላ. ፭ ÷ ፲፬ ። ፲፩ ። ፩ ተሰ. ፭ ÷ ፭ ። ፲፪ ። ኤፌ. ፭ ÷ ፲፩ ፤ ፮ ÷ ፲፩ ። ፲፫ ። ሉቃ. ፳፩ ÷ ፴፬ ። ፲፬ ። ም. ፰ ÷ ፲፱ ፤ ገላ. ፫ ÷ ፳፯ ።

፲፭ ። ፩ ። ፩ ቆሮ. ፰ ÷ ፲፩—፲፫ ። ፪ ፤ ቈላ. ፪ ÷ ፲፯ ። ፯ ። ፩ ቆሮ. ፲ ÷ ፴ ፤ ፩ ቆሮ. ፰ ÷ ፲፩ ። ፰ ። ፪ ተሰ. ፭ ÷ ፲ ። ፲ ። ማቴ. ፳፭ ÷ ፴፩ ፤ ፴፩ ። ፲፩ ። ኢሳ. ፵፩ ÷ ፳፫ ፤ ፊልጵ. ፪ ÷ ፲ ። ፲፫ ። ማቴ. ፯ ÷ ፭ ፤ ፲፰ ÷ ፯ ። ፲፬ ። የሐዋ. ፲ ÷ ፲፭ ፤ ቲቶ ፭ ÷ ፲፭ ። ፲፭ ። ፩ ቆሮ. ፰ ÷ ፭ ፤ ፲ ። ፲፮ ። ዮሐ. ፲፪ ÷ ፳፭ ። ፲፯ ። ቍ. ፲፱ ፤ ፲፭ ። ፲፰ ። ፩ ቆሮ. ፰ ÷ ፲፫ ።

፲፭ ። ፩ ። ፩ ተሰ. ፭ ÷ ፲፬ ። ፪ ። ፩ ቆሮ. ፲ ÷ ፳፬ ። ፫ ። ም. ፲፪ ÷ ፲፯ ። ፬ ። ማቴ. ፲፭ ÷ ፲፩ ፤ ፲፮ ÷ ፳፬ ። ፭ ። መዝ. ፷፰ ÷ ፱ ። ፮ ። ዘዳግ. ፴፪ ÷ ፵፫ ። ፯ ። መዝ. ፲፯ ÷ ፶ ። ፰ ። ኢሳ. ፲፩ ÷ ፲ ። ፱ ። ኢሳ. ፵፪ ÷ ፭ ። ፲፩ ። ም. ፭ ÷ ፲፩ ፤ የሐዋ. ፳፪ ÷ ፲፱ ። ፲፪ ። ፩ ቆሮ. ፲፬ ÷ ፲፰ ። ፲፫ ። ፩ ቆሮ. ፲፮ ÷ ፲፭ ። ፲፬ ። ፩ ቆሮ. ፲፬ ÷ ፳፪ ። ፲፭ ። ፩ ቆሮ. ፲፮ ÷ ፭ ። ፲፮ ። ፩ ቆሮ. ፲፮ ÷ ፲፱ ።

ከማይታዘዙ ፡ እድን ፡ ዘንድ ÷ ለኢየሩሳሌምም ፡ ያለኝ ፡ አገልግሎቴ ፡ ቅዱሳንን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ጸልዩ ። የሰላምም ፡ አምላክ ፡ ከሁላችሁ ፡ ጋር ፡ ይሁን ፤ አሜን ።

ምዕራፍ ፡ ፲፭ ።

፩ በክንክራአስ ፡ ባለች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገል ጋይ ፡ የምትሆን ፡ እኅታችንን ፡ ፌቤንን ፡ አደራ ፪ ብያቸኋለሁ ፤ ለቅዱሳን ፡ እንደሚገባ ፡ በጌታ ፡ ተቀበሉአት ÷ እርስዋ ፡ ለብዙዎች ፡ ለእኔም ፡ ለራሴ ፡ ደጋፊ ፡ ነበረችና ÷ ከእናንተም ፡ በምትፈልገው ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ እርዱአት ።

፫ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ አብረውኝ ፡ ለሚሠሩ ፡ ለጵርስቅላና ፡ ለአቂላ ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ፤ ፬ እነርሱም ፡ ስለ ፡ ነፍሴ ፡ ነፍሳቸውን ፡ ለሞት ፡ አቀረቡ ፡ የአሕዛብም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሁሉ ፡ የሚያመሰግኑአቸው ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ አይደለሁም ፤ ፭ በቤታቸውም ፡ ላለች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ። ከአስያ ፡ ለክርስቶስ ፡ በኵራት ፡ ለሆነው ፡ ለምወደው ፡ ለአጤኔጦን ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ። ፮ ስለ ፡ እናንተ ፡ ብዙ ፡ ለደከመች ፡ ለማርያ ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ። ፯ በሐዋርያት ፡ መካከል ፡ ስመ ፡ ጥሩዎች ፡ ለሆኑ ÷ ደግሞም ፡ ክርስቶስን ፡ በማመን ፡ ለቀደሙኝ ÷ አብረውኝም ፡ ለታሰሩ ፡ ለዘመዶቼ ፡ ለአንዲሮንቆንና ፡ ለዩልያን ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ። ፰ በጌታ ፡ ለምወደው ፡ ለጵልያጦን ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ። ፱ በክርስቶስ ፡ አብሮን ፡ ለሚሠራ ፡ ለኢራቦኖን ፡ ለምወደውም ፡ ለስንጣክን ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ። ፲ በክርስቶስ ፡ መሆኑ ፡ ተፈትኖ ፡ ለተመሰገነው ፡ ለአጤሌን ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ። ፲፩ ከአርስጣባሉ ፡ ቤተ ፡ ሰዎች ፡ ላሉት ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ። ለዘመዴ ፡ ለሄሮድዮን ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ። ከንርቀሱ ፡ ቤተ ፡ ሰዎች ፡ በጌታ ፡ ላሉት ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ። ፲፪ በጌታ ፡ ሆነው ፡ ለሚደክሙ ፡ ለጥርፊዎናና ፡ ለጢሮፊሞሳ ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ። በጌታ ፡ እጅግ ፡ ለደከመች ፡ ለተወደደች ፡ ለጠርሲዳ ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ። ፲፫ በጌታ ፡ ሆኖ ፡ ለታወቀ ፡ ለሩፎን ፡ ለእኔና ፡ ለእርሱም ፡ እናት ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ። ፲፬ ለአስቀሪጦንና ፡ ለአፍለሰንጓ ፡ ለሄሮሜንም ፡ ለጳጥሮቢም ፡ ለሄርማንም ፡ ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ ላሉ ፡ ወንድሞች ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ። ፲፭ ለፍሌጎንና ፡ ለዩልያ ፡ ለኔርያና ፡ ለእኅቱም ፡ ለአልጣጠም ፡ ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ ላሉ ፡ ቅዱሳን ፡ ሁሉ ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ። ፲፮ በተቀደሰ ፡ አሰሳም ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ሰላምታ ፡ ተሰጣጡ ። የክርስቶስ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሁሉ ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡላችኋል ።

፲፯ ነገር ፡ ግን ÷ ወንድሞች ፡ ሆይ ÷ እናንተ ፡ የተማራችሁትን ፡ ትምህርት ፡ የሚቃወሙትን ÷ መለያየትንና ፡ ማሰናከያን ፡ የሚያደርጉትን ፡ ሰዎች ፡ እንድትመለከቱ ፡ እለምናችኋለሁ ÷ ከእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ፈቀቅ ፡ በሉ ፤ ፲፰ እንዲህ ፡ ያሉት ፡ ለጌ ፡ ሆዳቸው ፡ እንጂ ፡ ለጌታችን ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አይገዙምና ÷ በመልካምና ፡ በሚያ ቈላምጥ ፡ ንግግርም ፡ ተንኰል ፡ የሌለባቸውን ፡ ሰዎች ፡ ልብ ፡ ያታልላሉ ። ፲፱ መታዘዛችሁ ፡ ለሁሉ ፡ ተወርቶአልና ፤ እንግዲህ ፡ በእናንተ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ለበጎ ፡ ነገር ፡ ጥበበኞች ፡ ለክፉም ፡ የዋሆች ፡ እንድትሆኑ ፡ እወዳለሁ ። ፳ የሰላምም ፡ አምላክ ፡ ሰይጣንን ፡ ከእግራችሁ ፡ በታች ፡ ፈጥኖ ፡ ይቀጠቅጠዋል ። የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ይሁን ።

፳፩ አብሮኝ ፡ የሚሠራ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ዘመዶቼም ፡ ሉቂዮስና ፡ ኢያሶን ፡ ሱሲጴጥሮስም ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡላችኋል ።

፳፪ ይህን ፡ መልእክት ፡ የጻፍሁ ፡ እኔ ፡ ጤርጥዮስ ፡ በጌታ ፡ ሰላምታ ፡ አቀርብላችኋለሁ ።

፳፫ የእኔና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ አስተናጋጅ ፡ ጋይዮስ ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርብላችኋል ። የከተማው ፡ መጋቢ ፡ ኤርስጦስ ፡ ወንድማችንም ፡ ቀኣስዋሮስ ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡላችኋል ። ፳፬ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ ከሁላችሁ ፡ ጋር ፡ ይሁን ፤ አሜን ።

፳፭፡፳፮ እንግዲህ ፡ እንደ ፡ ወንጌሌ ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ እንደ ፡ ተሰበከ ÷ ከዘላለም ፡ ዘመን ፡ የተሰወረው ፡ አሁን ፡ ግን ፡ የታየው ፡ በነቢያትም ፡ መጻሕፍት ፡ የዘላለም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ አዘዘ ፡ ለእምነት ፡ መታዘዝ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ለአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ የታወቀው ፡ ምሥጢር ፡ እንደ ፡ ተገለጠ ፡ መጠን ፡ ሊያበረታችሁ ፡ ለሚችለው ÷ ብቻውን ፡ ጥበብ ፡ ላለው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ድረስ ፡ ክብር ፡ ይሁን ፤ አሜን ።

፲፭ = ፫ ፤ የሐዋ. ፲፰ ÷ ፪ ። ፲፮ = ፳ ፤ ፩ ቆሮ. ፲፮ ÷ ፲፱ ። ፲፯ = ፲፮ ፤ ፩ ኢዮ. ፩ ÷ ፲፱ ። ፲፱ = ፲፮ ፤ ፩ ፊልጵ. ፫ ÷ ፲፱ ፤ ፲፱ ፡ ቈላ. ፪ ÷ ፱ ። ፲፱ ፤ ማቴ. ፲ ÷ ፲፮ ። ፳ ፤ ዘፍጥ. ፫ ÷ ፲፭ ፤ ፩ ቆሮ. ፲፮ ÷ ፳፫ ። ፳፭ ፤ የሐዋ. ፲፮ ÷ ፭ ። ፳፫ ፤ ፩ ቆሮ. ፩ ÷ ፲፬ ፤ ፪ ጢሞ. ፬ ÷ ፳ ።

መጀመሪያይቱ ፡ የሐዋርያው ፡ የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐዋርያ ፡ ሊሆን ፡ የተጠራ ፡ ጳውሎስ ፡ ፪ ወንድሙም ፡ ሶስቴንስ ÷ በቆሮንቶስ ፡ ላለች ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ÷ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ለተቀደሱት ÷ የእነርሱና ፡ የእኛ ፡ ጌታ ፡ የሆነውን ፡ የጌታችንን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ስም ፡ በየስፍራው ፡ ከሚጠሩት ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ቅዱሳን ፡ ለመሆን ፡ ለተጠሩት ፤ ፫ ከእግዚአብሔር ፡ ከአባታችን ፡ ከጌታም ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋና ፡ ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ይሁን ።

፬ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ስላመናችሁ ፡ በተሰጣችሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ምክንያት ፡ ሁል ጊዜ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ አምላክን ፡ አመሰግናለሁ ፤ ፭፡፮ ለክርስቶስ ፡ መመስከሬ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ጸና ÷ በነገር ፡ ሁሉ ፡ በቃልም ፡ ሁሉ ፡ በእውቀትም ፡ ሁሉ ፡ በእርሱ ፡ በለ ፡ ጠንቶ ፡ እንድትሆኑ ፡ ፯ ትሆኑ ፡ ተደርጋችኋልና ። እንደዚህ ፡ የጌታችንን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ መገለጥ ፡ ስትጠባበቁ ፡ አንድ ፡ የጸጋ ፡ ስጦታ ፡ እንኳ ፡ አይጎድልባችሁም ፤ ፰ እርሱም ፡ ደግሞ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ቀን ፡ ያለ ፡ ነቀፋ ፡ እንድትሆኑ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ ያጸናችኋል ። ወደ ፡ ልጁ ፡ ወደ ፡ ጌታችን ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጎብረት ፡ የጠራችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ የታመነ ፡ ነው ።

፲ ነገር ፡ ግን ÷ ወንድሞች ፡ ሆይ ÷ ሁላችሁ ፡ አንድ ፡ ንግግር ፡ እንድትናገሩ ፡ በአንድ ፡ ልብና ፡ በአንድ ፡ አሳብም ፡ የተባበራችሁ ፡ እንድትሆኑ ፡ እንጂ ፡ መለያየት ፡ በመካከላችሁ ፡ እንዳይሆን ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ እለምናችኋለሁ ። ፲፩ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ÷ በመካከላችሁ ፡ ክርክር ፡ እንዳለ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ የቀሎዔ ፡ ቤተ ፡ ሰዎች ፡ አስታውቀውኛልና ። ይህንም ፡ እላለሁ ፦ — እያንዳንዳችሁ ፡ — እኔ ፡ የጳውሎስ ፡ ነኝ ÷ እኔስ ፡ የአጵሎስ ፡ ነኝ ÷ እኔ ፡ ግን ፡ የኬፋ ፡ ነኝ ÷ እኔስ ፡ የክርስቶስ ፡ ነኝ ፡ ትላላችሁ ። ፲፫ ክርስቶስ ፡ ተከፍሎአልን ? ጳውሎስስ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ተሰቀለን ? ወይስ ፡ በጳውሎስ ፡ ስም ፡ ተጠመቃችሁን ? ፲፬፡፲፭ በስሜ ፡ እንደ ፡ ተጠመቃችሁ ፡ ማንም ፡ እንዳይል ፡ ከቀርስጶስና ፡ ከጋይዮስ ፡ በቀር ፡ ከእናንተ ፡ አንድን ፡ እንኳ ፡ ስላጠመቅሁ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰግናለሁ ። ፲፮ የእስጢፋኖስንም ፡ ቤተ ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፡ አጥምቄአለሁ ፤ ጨምሬ ፡ ሌላ ፡ አጥምቄ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አላውቅም ። ፲፯ ለማጥመቅ ፡ ክርስቶስ ፡ አላከኝምና ÷ ወንጌልን ፡ ልሰብክ ፡ እንጂ ፤ የክርስቶስ ፡ መስቀል ፡ ከንቱ ፡ እንዳይሆን ፡ በቃል ፡ ጥበብ ፡ አይደለም ።

፲፰ የመስቀሉ ፡ ቃል ፡ ለሚጠፉት ፡ ሞኝነት ÷ ለእኛ ፡ ለምንድን ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ነውና ። የጥበበኞችን ፡ ጥበብ ፡ አጠፋለሁ ፡ የአስተዋዮችንም ፡ ማስተዋል ፡ እጥላለሁ ፡ ተብሎ ፡ ተጽፎአልና ። ፲፱ ጥበበኛ ፡ የት ፡ አለ ? ጸሐፊ ፡ የት ፡ አለ ? የዚች ፡ ዓለም ፡ መርማሪ ፡ የት ፡ አለ ? እግዚአብሔር ፡ የዚችን ፡ ዓለም ፡ ጥበብ ፡ ሞኝነት ፡ እንዲሆን ፡ አላደረገምን ? ፳፩ በእግዚአብሔር ፡ ጥበብ ፡ ምክንያት ፡ ዓለም ፡ እግዚአብሔርን ፡ በጥበብዋ ፡ ስላላወቀች ÷ በስብከት ፡ ሞኝነት ፡ የሚያምኑትን ፡ ሊያድን ፡ የእግዚአብሔር ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖአልና ። ፳፪ መቼም ፡ አይሁድ ፡ ምልክትን ፡ ይለምናሉ ፡ የግሪክ ፡ ሰዎችም ፡ ጥበብን ፡ ይሻሉ ÷ እኛ ፡ ግን ፡ የተሰቀለውን ፡ ክርስቶስን ፡ እንሰብክለን ፤ ይህም ፡ ለአይሁድ ፡ ማሰናከያ ፡ ለአሕዛብም ፡ ሞኝነት ፡ ነው ÷ ለተጠሩት ፡ ግን ÷ አይሁድ ፡ ቢሆኑ ፡ የግሪክ ፡ ሰዎችም ፡ ቢሆኑ ÷ የእግዚአብሔር ፡ ኃይልና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጥበብ ፡ የሆነው ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ። ፳፭ ከሰው ፡ ይልቅ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሞኝነት ፡ ይጠበባልና ÷ የእግዚአብሔርም ፡ ድካም ፡ ከሰው ፡ ይልቅ ፡ ይበረታልና ።

፳፮ ወንድሞች ፡ ሆይ ÷ መጠራታችሁን ፡ ተመልከቱ ፤ እንደ ፡ ሰው ፡ ጥበብ ፡ ጥበበኞች ፡ የሆኑ ፡ ብዙዎች ÷ ኃይለኞች ፡ የሆኑ ፡ ብዙዎች ÷ በላባቶች ፡ የሆኑ ፡ ብዙዎች ፡ አልተጠሩም ። ፳፯ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ጥበበኞችን ፡ እንዲያሳፍር ፡ የዓለምን ፡ ሞኝ ፡ ነገር ፡ መረጠ ፤ ብርቱንም ፡ ነገር ፡ እንዲያሳፍር ፡ እግዚአብሔር ፡ የዓለምን ፡ ደካማ ፡ ነገር ፡ መረጠ ፤ ፳፰ እግዚአብሔር ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ እንዲያጠፋ ፡ የዓለምን ፡ ምናምንቴ ፡ ነገር ፡ የተናቀውንም ፡ ነገር ፡ ያልሆነውንም ፡ ነገር ፡ መረጠ ÷ ሥጋን ፡ የለበሰ ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንዳይመካ ። ፳፱፡፴ ነገር ፡ ግን ፦ — የሚመካ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ይመካ ፡

፩ = ፪ ፡ ፫ ። ሮሜ ፩ ÷ ፯ ። ፭ ፤ ፊልጵ. ፩ ÷ ፯ ። ፱ ፤ ፩ ተሰ. ፭ ÷ ፳፬ ፤ ፩ ዮሐ. ፩ ÷ ፫ ። ፲ ፤ ፊልጵ. ፪ ÷ ፪ ፡ ፫ ። ፲፪ ፤ የሐዋ. ፲፰ ÷ ፳፪ ፤ ዮሐ. ፩ ÷ ፵፪ ። ፲፫ ፤ የሐዋ. ፭ ÷ ፲፮ ። ፲፬ ፤ የሐዋ. ፲፰ ÷ ፰ ፤ ሮሜ ፲፮ ÷ ፳፫ ። ፲፰ ፤ ሮሜ ፩ ÷ ፲፮ ። ፲፱ ፤ ኢሳ ፳፱ ÷ ፲፬ ። ፳ ፤ ኢሳ ፵፬ ÷ ፳፭ ፤ ሮሜ ፩ ÷ ፳፪ ። ፳፩ ፤ ማቴ. ፲፩ ÷ ፳፭ ። ፳፪ ፤ ማቴ. ፲፮ ÷ ፩፯ ፤ ዮሐ. ፪ ÷ ፵፭ ። የሐዋ. ፲፯ ÷ ፲፰ ። ፳፫ ፤ ገላ. ፭ ÷ ፲፩ ። ፳፬ ፤ ቈላ. ፪ ÷ ፫ ። ፳፭ ፤ ዮሐ. ፯ ÷ ፵፭ ። ፳፯ ፤ ያዕ. ፪ ÷ ፭ ። ፳፰ ፤ ሮሜ ፱ ÷ ፲፯ ። ፴ ፤ ዮሐ. ፲፯ ÷ ፲፱ ፤ ፪ ቆሮ. ፭ ÷ ፳፭ ። ፴፩ ፤ ኤር. ፱ ÷ ፳፫ ፤ ፻፵፪ ።